
ትንማርቲ
በጀምስ
ሀድሌይ ቻዝ
በደምሴ ፅጌ

186

# ት ን ግ ር ት

በጄምስ ሀድሌይ ቼዝ

Addis Ababa City Government
Culture & Information Bureau
Zone 4 Public Library

ትርጉም
በደምሴ ፅጌ

Zone 4 Public Library

አዲስ አበባ
1982

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው ።
(ALL RIGHTS RESERVED)

የሽፋን ስዕል ፤ በሰዩም ታደሰ

ቦሌ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

## ማ ስ ታ ወ ሻ

የተተረጐመው፡—

BELIEVE THIS
YOU' LL BELIEVE ANYTHNG

የሚለው የጀምስ ሀድሌይ መጽሐፍ ነው

## ሌ ላ ማ ስ ታ ወ ሻ

ክፍሌ በትረ ፤ ተስፋዬ
እንዲሁም
ተወልደና ሽምሲያ
መጽሐፏ አብረን ላሣለፍናቸው ሽጋ
ቀናት ማስታወሻ ትሁን —ተቀብሉኝ

186

# አ ን ድ

ከመስታወት በተሠራው የቢሮዬ ግድግዳ ከፊት ለፊት ካለው ቢሮ ሲገባ አየሁት ። ቀጠን ብሎ ረጅም ነው ። ምናልባት እድሜው ወደ ሰላሳኛ አመቱ መጨረሻ ላይ ይሆናል ። የቀይ ዳማ ነው ። ነጭ ሙሉ ልብሱ በጥንቃቄና በፍቅር ከሰውነቱ ጋር እንዲስማማ ሆኖ የተሰፋ ነው ። የሲኒማ ተዋናይ መሆን አለበት ብዬ አሰብኩ ። የሲኒማ አዘጋጅ እንዲህ አይነቱን ሰው ቢያገኝ በቀላሉ አይለቀውም ።

ፀሐፊዬ ሱ ዳግላስ ገና ስታየው ከመቀመጫዋ ተነስታ ሞቅ ባለ ፈገግታ ተቀበለችው ። በፀሐፊዬ የማይማረኩ ወንዶች የተወሰኑ ናቸው ። ሱ ገና ሲያዩዋት የምትማርክ ውብ ልጅ ናት ።

ፈገግታዋ በሰውዬው ላይ ምንም ለውጥ አላስከተለ ። በምንጠጣው መጠጥ ውስጥ ድንገት ፣ ጥልቅ ያለችውን ዝንብ የምንመለከታትን ያህል ነው ያያት ። ደህና ያልሆነ አመለካከቱን ፣ ስታይ ፈገግታዋ ደበዘዘ ። እኔን እስኪያየኝ ድረስ ቢሮዋን በዓይኖቹ ቃኘ ። በመስታወት ግርግዳ ውስጥ ተያየን ። ፀሐፊዬን አልፎ ወደ ቢሮዬ ገባና በሩን በቀስታ ዘጋው ።

"ሀላፊው አንተ ነህ ?" ብሎ ጠየቀ ። በኢተንና በካምብሪጅ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ፣ የተማረ እንግሊዛዊ መሆኑን ወዲያው አወቅሁ ። እንግሊዝ አገር ለስድስት ወራት ስቀመጥ የቋንቋውን የተለያዩ ዘዬዎች አውቄ ስለነበረ ከየት እንደመጣ ማወቅ አልተሳነኝም ።

"ልክ ነህ" አልኩና ከመቀመጫዬ ተነስቼ በፈገግታ ተቀበልኩት ።

"ከሌይ በርደን እባላለሁ ። ምን ልርዳህ?" ብዬ ወደ ደንበኞቼ መቀመጫ አመለከትኩ ። ወንበሩን በጥርጣሬ ሲመለከት ቆይቶ ነጭ ልብሱን የማያቆሽሽበት መሆኑን ሲያረጋግጥ ተቀመጠ ።

"ገና በቅርቡ ነው መሠል ሥራ የጀመራችሁት ?" ብሎ ዙሪያውን በቅሬታ ተመለከተ ።

"እዎ ሥራ ከጀመርን ገና ስድስተኛ ቀናችን ነው ሚስተር . . . ?" በአነጋገሬ ተገረመ

ይገርማል ማን እንደሆንኩ እንኳ አታውቅም ማለት ነው ? በሚል አይነት ደልዳላ ትከሻውን ነቅነቀ ።

"ቬርኖን ዳየር እባላለሁ ። በዚህ አካባቢ የታወቅሁ ሰው መሆኔን የምታውቅ አይለስለኝም ።"

"ባለማወቄ ብዙ ተጐድቻለሁ"

"ለፓራዳይዝ ከተማ እንግዳ መሆን አለብህ"

"አልተሳሳትክም ሚስተር ዳየር ከቦስተን ነው የመጣሁት ።"

"መሥሪያ ቤትህ ከዚህ አካባቢ ሰው የቀጠረ መስሎኝ ነበር ።" አለኝ ለዚህ መልስ አልሰጠሁትም ።

"ላደርግልህ የምችለው ነገር አለ ?"

ላደርግለት የምችለው ነገር ቢኖር እንኳ በቶሎ ሊነግረኝ አልፈቀደም ።

"አንተና እሷ ብቻ ናችሁ እዚህ ያላችሁት ?"

"ያለን ክፍል ሁለታችንን ብቻ ነው እሚይዘው" አልኩት

"ሆቴሉ ሊሠጠን የቻለው ቦታ ይሄ ብቻ ነው ። ቢሆንም ለሥራችን በቂ ይመስለኛል ።"

"አይመስለኝም ። የአሜሪካን ኤክስፕሬስ አሥራ አምስት ሠራተኞች ነው ያሉት ፣"

"እነሱ እንደኛ በከተማይቱ ውስጥ ውድ በሆነው የእስፓኒሽ ቤይ ሆቴል ውስጥ አይደለም የሚሠሩት ።"

"ስለሆቴሉ ለማወቅ አልፈልግም" አለኝ ቆጣ ብሎ "እኔ እምፈልገው ብቃት ያለው የጉዞ ወኪል ድርጅት አገልግሎት እንዲሠጠኝ ነው !"

"እንዲያ ከሆነማ ሚስተር ዳየር አትክልተኛው ሥፍራ ነው የመጣኸው ። እዚህ የቢሮ ፣ ሥራ አይደለም የምንሠራው ። የተለያዩ መረጃዎችን ለመስጠት ነው የተቀመጥነው ።እኛ ይህንን ስናከናውን



እማያሚ ያለው ዋና መሥሪያ ቤታችን ፣ትኬቶችንና የጉዞ ቼኮችን አዘጋጅቶና ሌሎች ተግባሮችን አከናውኖ ለኛ ይልክልናል ። ለምሳሌ አንተ ወደ ኒው ዮርክ በአውሮፕላን ለመሄድ ትፈልግ ይሆናል ፤ እኛ በየትኛው አውሮፕላን እንደምትሄድ እንነግርሀለን ፤ ቦታ ይዘን ትኬቱን ፣እዚህ ወይም እማያሚ አውሮፕላን ማረፊያ እንዲደርስህ እናደርጋለን ።ይሄ ቢሮ ምክር ይሠጣል እና የምትፈልገው ይህን ከሆነ ከኛ ታገኘዋለህ ።"

እግሩን እያነባበረ በጥሞና አዳመጠኝ ።

"ስለ ሚስተር ሄንሪ ቪዳል የሰማህ ይመስለኛል" .

ትእቢቱ በመጠኑ እየሠለቸኝ መጣ ።

"ሚስተር ሄንሪ ቪዳል አልከኝ ? ስሙን ሰምቼው አላውቅም ቦስተንን ለቅቄ ከመምጣቴ በፊት ዝናው እዚያ የደረሰ አይመስለኝኝም ። "አልኩት "እዚህ ከመጣሁም ስሙን ያነሳብኝ ፣ ሰው ስላላጋጠመኝ ትዝ ሊለኝ አልቻለም ።"

እያፌዝኩበት ስለመሰለው ትኩር ብሎ ሲመለከተኝ ቆይቶ የማወቅ ጉጉቱን ከፊቴ ላይ ፣ ስላየ ፣

"ሚስተር ቪዳል በፍሎሪዳ ውስጥ የታወቀ ትልቅ ሰው ነው" አለኝ ።

"ከኬኔዲ ፣ ከኒክሰንና ፡ ከትሩማን የበለጠ ታዋቂ ነው በለኛ" አልኩት በርጋታ ፣ ስሙን ከዚህ በፊት አለመስማቴ የሚያስደንቅ ቻልተኝነት ነው ፡" ስለው በጉንጮቹ ላይ ሁለት ፣ ቀያይ ምልክቶች ታዩ ። አይኖቹ ብልጭ ድርግም አሉ ።

"መናቅህ ነው እንዴ?"

"ፈልጌው አይደለም ሚስተር ዳየር ላደርግልህ እምትፈልገው ነገር አለ ?" ትንሽ አቅማማና እንዲህ አለኝ ።

"የሚስተር ቪዳል የቅርብ ረዳት ነኝ ።ሚስተር ቪዳል የባንክ ሂሣቡን ከአሜሪካ ን አክስፒሬስ አውጥቶ ወደ እናንተ ድርጅት ማዛወር ይፈልጋል ። የናንተ ድርጅት ከአሜሪካው ኤክስፕሬስ የተሻለ አሠራር እንዳለው ተስፋ አደርጋለሁ"

"የምችለውን ሁሉ በደስታ ለመፈጸም ዝግጁ ነኝ" ስለው ትኩር ብሎ ተመለከተኝ ፡

"የምናዛውርላችሁ ሂሣብ ትንሽና ጣጣ ያለበት መስሎህ ይሆናል ? ሚስተር በርደን" አለኝ ምንም ቢሆን ስሜን አልነዘጋውም ። "ብዙ ሆነ ትንሽ ፡ አስቸጋሪ ሆነ ቀላል ፡ ለውጥ የሚያመጣ አይመስለኝም ሚስተር ዳየር እኛ ያለነው አገልግሎት ለመስጠት ነው"

ላልኩት ሁሉ ግድ የሌለው መሆኑን በሁኔታው አሳየኝ ።

"እንዲያ እንደሚሆን ተስፋ አለኝ ። ደህና — እየተፈተናችሁ መሆኑን አስቡ ። በሚስተር ቪዳል ድርጅት ስም የባንክ ሂሣብ ከፈቱ ሚስተር ቢዳልን በተመለከተ ማንኛውንም ጉዳይ የሚፈጸመው በኔ በኩል ነው"

"ብድሩ ምን ያህል እንደነበር ፡ፍንጭ ልትሰጠኝ ትችላለህ ?"

ከአሜሪካን ኤክስፕሬስ ጋር ያለንን የባንክ ሂሣብ ዘግቻለሁ ። ለስድስት ወራት የተዋዋልነውም ውል ተፈጽሟል ። የገንዘቡ ብዛት አንድ መቶ ሰላሳ ሺህ ነበር ።"

የሰማሁትን ስላላመንኩ በደንብ ተመለከትኩት ። መገረሜ እርካታ የሰጠው ይመስላል '

"ሂሣቡ በአመት ሁለት መቶ ሺህ ይሆናል ማለት ነው ?" ብዬ ስጠይቀው ጉልበቱን መታ መታ አደረገ ።

"አዎ ሰጥቶ መቀበል ነው ። ከዚያም በላይ ሊሆን ይችላል ።" በረጅሙ ተነፈስኩ ። ላጣው የሚገባ ገንዘብ አይደለም ።

"መጠየቂያው በየግማሽ አመቱ እንዲቀርብላችሁ ነው የምትፈልጉት ?"

"የኛ ክፍያ ደንብ እንደዚያ ነው ።"

"ዋና መሥሪያ ቤት ምን እንደሚል እንጃ ብቻ የአሜሪካን ኤክስፕሬስ በዚያ ሁኔታ ከተስማማ የኛም ድርጅት እንደነሱ ያደርግ ፡ ይሆናል ።"

"ማንኛውንም ነገር በቶሎ አዘጋጃለሁ ።" አልኩት "ብቻ አንዳንድ መሟላት የሚገባቸው ጉዳዮች . ." ብዬ ሳልጨርስ አቋረጥኩና ትክ ብዬ ተመለከትኩት ።



"እሱማ የተወቀ ነው ።" አለና ከቦርሳው ውስጥ የተጣጠፈ ወረቀት አወጣ ።

"አስፈላጊዎቹ ነገሮች በዚህ ላይ ተዘርዝረዋል ። የሚስተር ቪዳል ፡ የነገረ ፈጁና ገንዘቡ የሚቀመጥበት ባንክ አድራሻ አለበት ።" ብሎ ወረቀቱን ከጠረጴዛዩ ላይ አስቀመጠው

"ማንኛውም ነገር በስርዐት ተዘርዝሮ ታገኘዋለህ ። እግረመንገድህንም ወደ ቶኪዮ ጆሀንስበርግና ሆንግ ኮንግ የሚደረጉ የበረራ ፕሮግራሞችን ላክልኝ ። ሁለት ሁለት መቀመጫዎችንም ያዝልኝ ። ሁሉም አንደኛ ማዕረግ መሆን አለባቸው ። ለስድስት ቀናትም ምቾት ባላቸው ሆቴሎች ውስጥ አልጋ ትይዛለህ ።የዚህ ሁሉ ዋጋ ግምት እንደደረሰኝ ተጨማሪ ዝርዝሮችን እልክልሀለሁ ።"

"ከሚስተር ቪዳል ጋር የሚደረግ ማንኛውም አይነት ግንኙነት እመኖሪያ ቤቱ ድረስ በኔ አድራሻ መላክ አለበት ። ያልኩህን ሁሉ በደንብ ይዘኸዋል ?"

"አዎን" አልኩት

ከተቀመጠበት ተነሳና "በል ደህና ሁን አለኝ ።" ሊጨብጠኝ አልሞ ከረም ። ዝም ብሎ ከቢሮው ወጣና ፀሐፊዬን እንኳ ዞር ብሎ ሳያይ በሰፊው የሆቴሉ ኮሪደር ውስጥ በኩራት እየተራመደ ወደ ውጪ ወጣ ። ከአይኔ እስኪሰወር ተመለከትኩትና ሱን ወደ እኔ እንድትመጣ ጠቀስኳት ።

"ማነው ይሄ አስፈሪ ጉረኛ ?" አለችኝ ስትገባ ።

"ቬርኖን ዳየር ይባላል ። ደጋግመን ሳናየው የምንቀር አይመስለኝም" ብዬ ባጭሩ ስለማንነቱ ፡ ሳብራራላት አይኖቿ ፈጠጡ ።

"ሁለት መቶ ሺ"

"እንደዚያ ነው ያለው" የሰጠኝን ትዕዛዝ በወረቀት ላይ ጽፌ

"ሱ እስቲ ለነዚህ የጉዞ ፕሮግራሞች ግምት ሥሪ" ብዬ ሠጠኋት ።"

ጭንቅላቷን በማነቃነቅ እሽታዋን ገልፃ ወደ መቀመጫዋ ተመለሰች ።

“ስእቴን ተመለከትኩ ። ስድስት ሰዓት ከሠላሣ አምስት ደቂቃ ሆኗል ።ስልኩን አነሳሁና የአሜሪካን ኤክስፕሬስ የቀጠና ማኔጀር ለሆነው ለጆ ሀርክነስ ደወልኩለት ። ከጆ ጋር አንተ ዋውቃለን ። ምንም እንኳ በሥራ ተወዳዳሪዎች ብንሆንም በመሀላችን ጥላቻ የለም ። በፓራዳይዝ ከተማ በጓደኝነት ተስማምተን እየኖርን ልንሠራው የምንችልው በቂ ሥራ አለ ።

“ሂ ጆ በርደን ነኝ” አልኩት ስልኩን እንዳነሳ ።

“አብረን ሣንዲዊች ብንበላ ምን ይመስልሀል ?”

“እንደተሰማኝ ከሆነ ከሳንዲዊች በላይ ዋጋ ሊታወጣ ነው” አለኝ በደስታ ።

“አንተ ሌባ እንዳልከ ይሁንልህ የቻልከውን ያህል እጋብዝሀለሁ ።”

“እንዴያ ነው ልጄ በግማሽ ሰዓት ውስጥ እንገናኛለን ።”ብሎ ስልኩን ዘጋው ።

ዳየር የሰጠኝን ዝርዝር አጠናሁት ። ሄንሪ ቪዳል በፓራዳይዝ ከተማ ውስጥ የሀብታሞች ፡መኖሪያ በሆነው አካባቢ ነው የሚኖረው በፓራዳይዝ በኒው ዮርክና በማያሚ ከተሞች ውስጥ ሶስት የባንክ ደንበኞች አሉት ። ነገር ፈጁ ጂሰን ሻከርማን ነው

ዝርዝሩን ተመልከቼ ስጨርስ እፀሐፊዬ ጋ ሄዱኩና ፤

“ሮዳን ማነጋገር እፈልጋለሁ ። ዛሬ ምሳ የምበላው ከሀርክነስ ጋር ነው” የጉዞ ፕሮግራሙንና ግምቱን ከምሳ በኋላ ትሰጪኛለሽ” ስላት እሽታዋን ራሷን በመነቅነቅ ገለፀችልኝ ።

በሆቴሉ ኮሪዶር አልፌ ሮዳ ወደምትሠራበት መደብር ወረድኩ ጊዜ ለማሳለፍ ሁሌ እንደምታደርገው ብቻዋን አንድ የሴቶች መፅሔት ስታነብ አገኘኋት ።

እኔና ሮዳ ከተጋባን ሁለት አመታችን አልፏል እቦስተን ከተማ ሂልተን ሆቴል ባለው መደብር ውስጥ ትሠራ በነበረችበት ጊዜ ነው ያገኘሁአት ። ሳናስበው ነው የተጋባነው ። እኔ በምኖርበት አካባቢ ባለው አፓርተማ ውስጥ ነበር የምትኖረው ።

ከሥራ ስንወጣ እግረ መንገዴን እቤቷ አደርሳታለሁ ። ማታ ማታም አፓርታማው ውስጥ እነበረው ቡና ቤት አዘወትረን እራት



እንበላ ነበር ። ከጊዜ በኋላ ፡ አልፎ አልፎ አብረን ማደር ጀመርን ። ሮዳ ደስ የምትል ቆንጆ ነች ። የጋብቻን ነገር የጀመረችው እሷው ነች ።

“ብንጋባ በቁጠባ ለመኖር ይረዳናል ። እኔም ኪራይ ከመክፈል እድናለሁ ።” አለችኝ ፡ እኔ ከምን እንደምድን ግን አልነገረችኝም ። የብቸኝነት ኑሮ እየሰለችኝ ነበር ። ምናልባት ባገባት ቫልን እረሳ ይሆናል ብዬም አሰብኩ ።

የዛሬ አራት አመት በከህደቷ ናላዬን ያዞረችውን ልጅ ለመርሳት ከፍተኛ ፍላጐት ነበረኝ ። ስለዚህም ሮዳን አገባኋት ። ቆይቼ ነው ማንነኗቷን ያወቅሁት ። ሮዳ የቤት ሥራ የምትጠላ ፤ አልጋችንን እንኳ ማንጠፍ የሚከብዳት ሰነፍ ሴት ነች ። የቀን ሠራተኛ የግድ መቅጠር ነበረብኝ ። ከተጋባን ጀምሮ የምንመገበው በየቡና ቤቱ ነው ።

እፓራዳይዝ ከተማ እንድሠራ ስጠየቅ ሮዳም አሁን ወዳለንበት ስፓኒሽ ቤይ ሆቴል ተዛዋረችና አብረን መጣን ። የሁለታችን ደመወዝ ጥሩ ኑሮ ለመኖር አስችሎናል ። ከዚያም አልፎ ገንዘብ ማጠራቀምም ችለናል ። ብቻ ጋብቻችን ለኔ የግብረ ስጋ ግንኙነትን እንደ ልብ ከመፀፈፀም አልፎ የምመኘውን አይነት ትዳር አልሆነልኝም ።

“ሮዳ” አልኳት እምትሠራበት መደብር በር ላይ ቆም ብዬ ።

“ምሳ አብረን እንበላም ። ለሥራ ጉዳይ ቀጠሮ አለብኝ”

“እይኖቿን ከመጽሔቱ ላይ ጉትታ አስነሳቻቸው”

“እህ”

“በሥራ ምክንያት ምሳ ተጋብዠለሁ ።” አልኩኝ በትዕግስት ። ሮዳ እያነበበች ስታዳምጠኝ አንድን ነገር ደጋግሜ መናገሩን ለምጄዋለሁ ።

“እ ታዲያ ይሁና ። በአሥራ ሁለት ሰዓት እንገኛለን” ብላኝ ንባቧን ቀጠለች ።

በእሳንሳሩ ወረድኩና እቡና ቤቱ ገብቼ በምሳ ሰዓት አድርጌው የማላውቀውን ውስኪ ፡አዘዝኩ ። አስተናጋጁ ሳም ውስኪውን ሲቀዳ ።

“ሚስተር ቪዳል ስለሚባል ሰው ሰምተህ ታውቃለህ ?” ብዬ ጠየቅሁት ።

"ቪዳል !" መጠጡን እፊቴ አስቀመጠ ፡

"ስምቻለሁ ልል አልችልም ሚስተር በርደን" አለኝ ።

"በፍሎሪዳ ውስጥ ትልቅ ሰው እንደሆነ ሰምቻለሁ" ስለው ፊቱን ጨምደድ አድርጐ ፡

"ያ እንደነጋሪው ነው" አለኝ ።

ጆ ሆርከነስ አምስት ደቂቃ አርፍዶ ደረሰ ። አጠር ብሎ ደልዳላ ነው ። እድሜው ወደኔ ይጠጋል ። ብሩህ አይኖቹና ፍልቅልቅ ፈገግታ ታው ለሥራ የነቃ አእምሮ እንዳለው ያሳያሉ ።

"ያ ለኔ ነው ?" አለ ወደ ያዝኩት ብርጭቆ እያመለከት ።

"ዛሬ የከሴይን በዐል እናከብራለን ።"

ለአስተናጋጁ ምልክት ሰጠሁና ጆ አጠገቤ ሲደርስ ፈርጠም ብዬ ።

"አንድ ሰው እኔ ጋ መጥቶ ነበር" አልኩት ።

"አውቄዋለሁ እኔ ጋም ነበር ። በጣም ነው ያዘንኩልህ ከሴይ ። እኛ ጋ ያለውን ሂሣብ ለመዝጋት ማሰቡን ሲነግረኝ በደስታ ዘለልኩ ።"

ትኩር ብዬ ተመለከትኩት ።

"ጆ ልታታልለኝ አትሞክር ።"

"እርግጥ ሁለት መቶ ሽ ብር እያጡ መደሰት የማይመስል ነገር ነው ። ብቻ እኔ ፡ እንደዚያ ነኝ ። ቪዳልና ዳየር አንገቴ ላይ ደር ሰዋል ። ለአሥራ ስምንት ወራት ሲያሰለቹኝ ነው የቆዩት ። አሁን ግን በቃ ! በቃ ! ነው ።"

"ሂሳባቸው በርግጥ ሁለት መቶ ሽህ ነው ። ነው እምትለኝ?" "እንደዚያ ነው እሚመጣው ። ያውም ይሄ ያለፈው አመት ሂሳብ ነው ። በዚህ አመት ፡ ጨምሮ ሊሆን ይችላል ። ግን የወርቅ ማዕድን ያገኘህ መስሎህ ተስፋ እንዳታደርግ" አለና አርብጭቆው ውስጥ ያለውን ውስኪ አጋመሰው ።

"ቪዳል የስድስት ወር ዱቤ እንድትሰጠው ይጠይቃል ። ያም ማለት አንድ መቶ ፡ሺ የሚሆነውን የኛን ገንዘብ ለስድስት ወራት ይጠቀምበታል ማለት ነው ።ይህንን በሰባት በመቶ እሥራ ላይ ያው ለዋል ።ይሄ በስድስት ወር ውስጥ ሶስት ሺ አምስት መቶ ዶላር ፡ ያስገኝለታል ። አስበው ይሄ ገንዘብ እኛ ልናገኘው የሚገባ ነበር ። በተጨማሪም ከአሥራ አምስት ሺ ዶላር በላይ ለሚያወጣ ሥራ አምስት በመቶ ቅናሽ ይጠይቃል ። ከዚህም ፡ ሶስት ሺ ሰባት መቶ ሀምሳ ዶላር ያገኛል ። ይሄም ለኛ ሊገባ የሚገባው ገንዘብ ፡ ነው ። እና ስድስተኛው ወር ሲያልቅ አንድ መቶ ሺ ዶላር የሚያ ወጣ ሥራ አሠርቶን የከፈለን ዘጠና ሁለት ሺ ሰባት መቶ ሀምሳ ዶላር ብቻ ነው ። በዚህ ጊዜ ውስጥ እኛ ሰባት ሺ ሁለት መቶ ሀምሳ ዶላር ያወጣን ሲሆን በአመት ወደ አሥራ አምስት ሺ ዶላር አወ ጣን ማለት ነው"

በመገረም ተመለከትኩት ።

"ታዲያ ምን ይሁን ? ተስማምታችኋል ። ሂሣቡ ትንሽ አይደለም በምኑ ነው የምታማርረው ?" አለኝ ።

"አዎ በምኑ ነው እማማርረው? እነግርሀለሁ ። ሂሳቡን ፈልገነዋል። እንደምንከፍልበትም አውቀናል ። ግን ያሰብነው አምስት በመቶ ቅና ሽና ለስድስት ወራት ዱቤ ፡ ሰጥተነው ትርፍ እናገኛለን ብለን ነው ። ምንኛ ተሳስተናል ?" ስለው እጁን እትከሻዬ ላይ ጣል አደረገና

"ያዘዝነው ጥብስ እንዲበላሽ አንፈልግም ። አይደል ?" አለኝ ።

የመጠጡን ዋጋ ከፈልኩና ወደ ምግብ ቤቱገባን ። "ባንተ ። ሂሣብ ስለሆነ የምንጋበዘው ወደ ኋላ ማለት የለብህም" አለኝ ሆርከ ነስ እየተቀመጠ ፡

"ከጥብሱ ጋር የአሳ ጥብስና ሌሎች ነገሮችን አዝዣለሁ ። የምንጠ ጣውም ያስፈልገናል ።"

"ለሁለታችንም ከአዘዝነው ጥብስ በተጨማሪ የአሳ ጥብስና ቀይ የካሊፎርኒያ ወይን ጠጅ እንዲያመጣልን አስተናጋጁን አዘ ዝኩ ።

"የቦርዶን ወይን ጠጅ አይደለም ያዘዝከው" አለ ሆርከነስ ቅር እያለው ።

"ሂሳቡን ገና አላገኘሁም እና ከቪዳል ምንም ትርፍ አታገኙም ነው እምትለን ?"

“እንደዚያ አልልም ። ከውጣውረዱና ከጭቅጭቁ ጋር ሁለት በመቶ ትርፍ ቢገኝ ጥሩ ነው አልልም ።”

“ምን አይነት ውጣውረድ ?”

“ተወዳዳሪ የሌላትን ፀሐፊዬን አጥቻለሁ ። ከዳየር ጋር ሁለት

ወር እንደሠራን ሥራውን ፡ ለቃ ወጣች ። በዚያ ላይ ዳየርን ለመያዝ ፡ የምታጣወጣው ወጪ አለ ። አንድ የድብደ ጉዳይም ነበር ። ከዚህ ሁሉ በላይ ዳየር በቀላሉ የሚነካ ሰው አይደለም ። ቁርጠታም የምትለው አይነት ነው ፡”

“ጠቡ ምን አይነት ነበር ?” ስለው ሀርክነስ ፈገግ አለ ።

“አንዱ የኔ ወኪል ዳየር በጣም ሲያስቸግረው ጊዜ በቦቅስ አፍ ንጫውን አወለቀው ። ጉዳዩ እፍርድ ቤት ሳይደርስ በግልግልጨረ ስነው ። ግን አምስት ሺ ዶላርና ጥሩ ወኪላችንን አጥተናል ።”

“ዳየርን ለመያዝ ያልከውስ ምንድን ነው ?”

“ለሥራ ጉዳይ ሊያነጋግረኝ በሚፈለግበት ጊዜ እቢሮዬ አይ መጣም ። ሁሌ በጣም ውድ በሆነው ሬስቶራንት ውስጥ ነው እሚቀ ጥረኝ ። ስንጨርስ ሂሣቡን ለኔ ጥሎልኝ ነው እሚወጣው ። በግምት እሱን በመቀለብ ብቻ በአሥራ ስምንት ወራት ውስጥ ወደ አራት ሺ ዶላር ያህል ሳላወጣ አልቀረም ።”

የነገረኝን እያሠላሠልኩ ለጥቂት ደቂቃ ፀጥ ብለን ተመገብን ።

“ቪዳልስ ምን አይነት ሰው ነው ?”

“አይቼው አላውቅም ። በፓራዳይዝ ውስጥ ቆንጆ የመኖሪያ ስፍራ ፤ አንድ ትልቅ ጀልባ ፡ ሮልስ ሮይስ መኪናና ቆንጆ ሚስት እንዳ ለው አውቃለሁ ። የሚገኝባቸው ቦታዎች የተመረጡ ፡ ስለሆኑ በአ ይኔ አይቼው አላውቅም ማንኛውንም ጉዳይ የሚፈጸምለት ዳየር ነው ”

“ቪዳል ገንዘቡን እንዴት ነው የሚያገኘው ?”

ሀርክነስ የእሣ ጥቡስን ጨረሰና በረካ መንፈስ ቁና ብሎ ተቀ መጠ ።

“የሰዎችን ፍላጐት ያሟላል ”



“ምን ማለትህ ነው ?”

“ወደ ሁለት መቶ የሚሆኑ የተመረጡ ሠራተኞች አሉት። ሁሉም ከሥፍራ ስፍራ ይንቀሳቀሳሉ የጉዞው ወጪው ከፍተኛ የሆነው ለዚህ ነው ። እንደሰማሁት ከሆነ ከሠራተኞቹ ግማሾቹ በየከተማው እየዞሩ ትርፍ እቃዎች ያላቸውን ሰዎች ይፈልጋሉ ። ለምሳሌም ስኳር ቡና የቆርቆሮ እቃዎች ዘይት ጀልባዎች. . . የተገኘውን ሁሉ ይሠበስ ባሉ ። የቀሩት ሠራተኞች ደግሞ እነዚህን እቃዎች የሚፈልጉ ሰዎ ችን ይገናኛሉ ። ከዚያ ቪዳል ባለ እቃዎቹንና ፈላጊዎቹን ያገናኝና ኮሚሽኑን ይልጣል ። ጥሩ የገንዘብ ማግኛ ዘዴ ነው ። በዚህ ሥራ ላይ የሚጠበቅብህ አንዱ ምን ትርፍ ነገር እንዳለውና ሌላው ምን እንደሚፈልግ ማወቅ ብቻ ነው ። ቪዳል በዚህ ሞያ የተካነ ድርጅት ያቋቋመ ይመስላል ። ቀላል ሰው እንዳይመስልህ በተለያዩ ። አገሮች መካከልም እንዲህ አይነቱን ንግድ ያካሄዳል ።

“በጣም ደነቀኝ ።”

“ዳየር የጉዞ ፕሮግራሞችን ጠይቆኛል” ስለው ሀርክነስ እጁን አንስቶ ፡

“አትንግረኝ! ልገምት ። ቶኪዮ ፡ ጆሀንስ በርግ ፡ ሆንግ ኮንግ ልክ ነኝ ?” አለኝ ዝም ብዬ ተመለከትኩትና ፡

“ቀጥል ጨምርና ንገረኝ” አልኩት

“እንዲህ አይነቱ ሥራ ዳየር ችሎታህን ለመገመት የሚሰጥህ ነው ። እኔንም በዚህ ፈትኖኛል ፕሮግራሙን ሰሰጠው ግን ፡ ምንም አልተቀመበትም ። እርግጠኛ ሥራ መሥራት ሲፈልግ በምሳ ሰዓት ነው እሚቀጥርህ ። ከዳየር በነፃ የምታገኘው ነገር የለም ።”

“ገንዘባቸውስ ችግር የለበትም ?”

“በዚያ አትጨነቅም ። ቢዳል በወቅቱ ነው እሚከፍልህ ።”

“ከሱ ጋር ሥራ ስትጀምሩ መረጃዎችን ሠብስባችኋል ?”

“በደንብ ። ሶስቱን ባንኮችና ወኪሎቹን ሁሉ አጥንተናል ። ከፈለ ግህ ፎቶ ኮፒዎቹን ልትጥህ እችላለሁ ።

“እባክህ እንደዚያ አድርግልኝ ጆ !” እንደዚህ ስንጫወት ጥብሱ መጣ ።

"የሥራን ጉዳይ እንተውና ጥብሳችንን እንብላ" አለኝ ሀርከነስ ።

ለተወሰነ ጊዜ ዝም ብለን ከበላን በኋላ ሀርከነስ

"መቼ ነው የጐልፍ ጨዋታ የምትጋብዘኝ በርደን ብሎ ጠየቀኝ ።

"ልትሞክረኝ እምትፈልግ ከሆነ ለምን እሁድ አናደርገውም ?" ብሎ ፈገግ አለ ።

"ጥሩ ፣ እሁድ ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት ላይ እንገናኝ"

እሁድ እሁድ ሮዳ ግማሽ ቀን ሙሉ ስለምትተኛ የጠዋት ቁርሴን ለማዘጋጀት ጊዜ አገኛለሁ ። ሮዳ ምግብ ማዘጋጀት አትችልም ለመማርም ፈቃዱ የላት ። እኔ ደግሞ እሁድ እሁድ እቡና ቤቱ መብላት ስለማልፈልግ ቁርሴንና ምሳዬን እማዘጋጀው ራሴውነኝ ።"

ከሀርከነስ ጋር ቡና ከጠጣን በኋላ ስንለያይ ።

እመኪናው ውስጥ እየገባ እንዲህ አለኝ ።

"ስለ ቪዲል በተጨማሪ ለማወቅ የምትፈልገው ነገር ካለ ደውልልኝ ። በጣም ነው ያዘንኩልህ ። ከልቤ" አለኝ ።

እጥርጣሬ ውስጥ ጨምሮኝ መኪናውን አስነስቶ ጭልጥ አለ ።

* * *

እቢሮዬ እንደገባሁ እማያማሚ ላለው የድርጅታችን የክፍለሀገር ሀላፊ ለሆነው ለሀንፍሬይ ማሲንግሀም ደወልኩለትና ስለ ቪዳልሂሣብ አጫወትኩት ።

"በርደን ይህ ለብዙ ጊዜ ስጠብቀው የነበረ ሂሣብ ነው ።" አለ ። ደስ ባለው ድምፅ "አሜሪካን ኤክስፕሬስን ትቶ ወደኛ ይመጣል ብዬ አስቤውም አላውቅ ፡"

"ሀርከነስ ከሱ በመላቀቁ ደስ ብሎታል ። እስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እየገባን ሳይሆን ይቀራል ?" አልኩት ።



"ሁለት መቶ ሺ !! ከፍ ያለ ገንዘብ ይዞ እንደሚመጣ አውቄያለሁ ። ያን ለሚያህል ፣ ገንዘብ ማንኛውንም ችግር መቀበል እንችላለን"

"ትችላለህ ማለትህ ነው ?" ስለው ሳቀ

"ከስራችን አንዱ ክፍል ነው ። ግን እረዳት ያስፈልግህ ይሆናል ። የቪዳልን ሂሣብ በጥንቃቄ እንድትመለከተው ፣ እፈልጋለሁ ። እሱን ካገኘን ተጨማሪ ሠራተኛ መቅጠር እንችላለን ።"

"አገኘነው ብለህ እርግጠኛ አትሁን" ብዬ ሀርከነስ ስለሱ የነገረኝ ሁሉ አጫወትኩት ። ይሄ ትንሽ አቀዘቀዘው ።

"እሽ ጥሩ ነው ። እሲቲ አንተ የምታደርገውን እስከምናይ እንጠብቅ ። ሀርከነስ የነገረህን ሁሉ ከኛ ላይጠይቅ ይችላል ።"

"ዳየር ከዚያ የበለጠ ቅናሽ እንደሚጠይቀን አትጠራጠር ፡"

"ጣራችን አምስት በመቶ ነው ። በምንም አይነት ንቅንቅ አትበልለት"

"የመጀመሪያው እርምጃውን እጠብቃለሁ ። በመሀከሉ ስለሱ ማጥናት የሚገባን አይመስልህም ?"

"በደንብ እንጂ ግን ቪዳል ትልቅ ነው ከትልልቆቹ አንዱ ነው ። በዚህ በኩል ፣ ብዙም ችግር የሚገጥመን አይመስለኝም ። ለማንኛውም መረጃዎችን እኔ አመለክታቸዋለሁ ።

"ብድር ገማቾችን መጠየቅ ነው ። የባንኩ ሂሣብ እንኳ ይህን ያህልም የሚያስቸግር ፣ አይመስለኝም" ስለው ፀጥ አለና ።

"እስከዚህ የሚያስፈራህ ነገር አለ እንዴ ?" ብሎ ጠየቀኝ ።

"ይህን ያህልም አልጓጓሁለት ። ለምን እንደሆነ አላውቅም ። ሀርከነስም እንዳዘነልን ነው የነገረኝ ። ዳየርን አልወደድኩትም"

"ያ ማለት የምናገኘው ገንዘብ ጥሩ አይደለም ማለት አይደለም ። ለኔ ተወው" አለና ስልኩን ዘጋው

ስልኩን ስዘጋ ፀሐፊዬ ዳየር የጠየቀውን ግምት ይዛልኝ መጣች አብረን ተመለከትነው ። እንደማንኛውም ጊዜ ሥራዋ ስህተት ላገኝበት አልቻልኩም ።

ለመልካም ሥራዋ አመስግኝ ሂሣቡን ለመክፈል አስፈላጊውን ነገር ሁሉ የተዘጋጀ መሆኑን የሚገልፅ ደብዳቤ ለዳየር እንድትጽፍ ለት ነገርኳት ።

"እና በቶሎ ላኪለት ። ምን አይነት ሠራተኞች መሆናችንን እናሳየው ።"

ከሰዓት በኋላውን የተለመደ ስራችንን ስንሠራ አሣልፈነው ። ብዙ የምንሠራው ነገር ነበረን ። የእለቱን ሥራችንን ጨርሰን ፀሐፊዬ ደህና እደር ብላኝ ስትወጣ እኔም ሮዳን ይገፔ ለመውጣት በሬን ዘግቼ ወደ መደብሩ ወረድኩ ። የሆነ እቃ እየሸጠች ስለነበረ እስክትመጣ ድረስ እኮሪደሩ ውስጥ ጠበቅኳት ።

መኪና ወደ አቆምንበት ሥፍራ ስንሄድ ፡

"በእግዚአብሔር እግሬ ደነዘዘ" ብላ አቃሰተች ።

"ቀኑን ሙሉ ቁጭ ብለሽ ስለምትውይ ሊያምሽ ይገባል ። እኔ ግን ላንዲት ደቂቃ እንኳ የምቀመጥ እድል የለኝም ።"

ምሳ አብረን የማንበላ መሆኑን ስነግራት ቁጭ ብላ መፅሔት ታነብ እንደነበረ አላስታወስኳትም ማቃሰቷን ለምጀዋለሁ ። ለሱ ምክንያት አታጣም ።

እመኪናችን ውስጥ ስንገባ ።

"ዛሬ ማታ ፊልም ማየት ትፈልጊያለሽ ?" ብዬ ጠየቅኳት ።

"ምንም የሚታይ ነገር የለም ።" ብላ ጫማዋን አሽቀንጥራ ጥላ ተደላድላ ተቀመጠች ።

ሙቀቱ እያሳበደኝ ነው ። እባክህ ማቀዝቀዢያውን አስነሳው ፡"

አስነሳሁት ። በዚህ ወቅት እንደማያሚ ባይሆንም ሙቀቱ በጣም አስቸጋሪ ነው ።

አካባቢውን ለቀን ወደ ቤት ስናመራ ፡

"ስለሄንሪ ቪዳል ሰምተሽ ታውቂያለሽ ?" ብዬ ጠየቅኳት ።

"ሚስ ቪዳል ትናንት መጥታ ነበር ። ቀበቶዎችንና ሱሪዎችን ገዝታ ሄደች ።"



"ምን ትመስላለች ?" ስላት ዞር ብላ ተመለከተችኝ ።

"ለምን ለማወቅ ፈለግህ ?"

"ባሏ በዓመት ሁለት መቶ ሺ ዶላር የሚሆን የባንክ ሂሣብ ከኛ ጋር ከፍቷል" ስላት ።

"ዋው" አለች ። ብዙ ገንዘብ ሮዳን ሁሌ ያስደንቃታል ።

"ብዙ ትርፍ ታገኙበታላችሁ ማለት ነው ?"

"እሱ ነው እሚያገኘው ። አይተሽው ታውቂያለሽ ?"

"ባለቤቱ ብቻዋን ነው የመጣችው ፡"

"ምን ትመስላለች" ስላት አስነጠሳት ። ሴቶችን ስታደንቅ ሰምቻት አላውቅም ። ከሷ እኩል ውብ ሴት ይኖራል ብላ አስባም የምታውቅ አይመስለኝ ።

"እሽ አንተ ቀጠን ያሉ የቀይ ዳማ ሴቶችን አይደል የምትወደው? አለባበስ ታውቃለች ። ስለሱ እርግጠኛ ሆኜ መናገር እችላለሁ ።

"አስቸጋሪ አይደለችም ?"

"የምትለው ከገባኝ ።እርግጥ እንደሌሎቹ አስቸጋሪ ሰዎች ባትሆንም ትልቅነቷን ለማሳወቅ በመጠኑም ቢሆን ትሞክራለች ።"

"እጅ በእጅ ትከፍላለች ?"

"እንደ ተጠየቀ የሚከፈል የባንክ ሂሣብ አላት ።"

"ያለ ጭቅጭቅ ትከፍላለች ?"

"ያንን እንዴት ለማወቅ እችላለሁ ? ለማንኛውም ምን ያስጨንቀናል ? በፍጥነት ፡ ንዳ እባክህ ለመታጠብ ቸኩያለሁ ፡"

ከአንድ ሰዓት በኋላ ሮዳ ባህሩን ቁልጭ አድርጐ በሚያሳየው ሰገነት ላይ በአንድ ፡ እጅዋ ማርቲኒ በሌላው መፅሔቷን ይዛ ጋደም ብላላለች ። እኔም ከታጠብኩ በኋላ ዊስኪና ሶዳየን ቀይጬ ወደ እሷ ሄድኩ ። ለእራት ወደ ቡና ቤቱ እስክምንወርድ ድረስ ምንም እንደማ ታናግረኝ አውቃለሁ ። ስለቪዳል ድርጅትና ስለ ቬርኖን ዳየር ባወራት ደስ ይለኝ ነበር ። ግን ይሄ ጉዳይ ስሜት እንደማይሰጣት አውቃለሁ ። ከመጽሔቶቹና ከልብሶቿ ሌላ ይህን ያህልም ስሜት የሚሠጣት ነገር የለም ።

ከፊት ለፊቷ ቁጭ ብዬ ሳያት ከቫለሪ ምን ያህል የተለየች እን ደሆነች አሰብኩ ።

ለቫለሪ የማደርገው ሁሉ ስሜት ይሠጣታል ፤ ንቁና አዋቂም ነች ። በሥራ የሚያጋጥሙኝን ችግሮች ሁሉ ስነግራት ወዲያው ጠቃሚ ሀሳቦችን ታቀርብልኛለች ።

ቫለሪ (የኔ ቫል)

ከስድስት አመት በፊት እቦስተን ውስጥ ላለው የድርጅታችን ቅ/ መ/ ቤት ሀላፊ ሆኜ ስሄድ እኔ የምተካው ሮይ ካነን አውሮፕላን ማረፊያው ድረስ መጥቶ ተቀበለኝ ። እግረመንገዳችንን አውሮፕላን ማረፊያው ቡና ቤት ጐራ ብለን ስንጫወት እንዲህ አለኝ ።

"ቦስተንን በመልቀቄ ከሚሰሙኝ ነገሮች አንደኛውና ዋንኛው ተወዳዳሪ የሌላትን ፡ ፀሐፊዬን ማጣቴ ነው ። እኔ አጣኋት አንተ አገህ ሀት ። እውነቴን ነው ። ምትክ የማይገኝላት ፡ ናት ። ምንም አይነት ሥራ በየትኛውም ሰዓት ብትሠጣት የማታልጉመጉም ፤ የሠጠሃትን ሁሉ በጥራት ሠርታ የምታቀርብልህ ልጅ ነች ። . . እንዴት አድርጌ ላስ ረዳህ . . . ?

ካነን በመጀመሪያ ሲነግረኝ ባላምነውም ብዙ ሳልቆይ እያጋ ነነ እንዳላወራልኝ ተረድቻለሁ ። ቫል ፡ እሱ ያለውን ሁሉ ነበረች ። ረጅምነች ። ሽንጧ ላይ የሚደርስ ፀጉር አላት ። ትልልቅ ሰማያዊ አይኖ ቿና ውብ ከንፈሮቿ ታይተው አይጠገቡም ። የቆንጆዎች ቆንጆ ከመ ሆኗም ፡ በላይ የሥራ ቅልጥፍናና ችሎታዋ የሚታመን አይደለም ።

በጥቂት ቀናት ውስጥ ከሷ ፍቅር ያዘኝ ። ግልፅና ሰላምተኛ ብት ሆንም አንድ ነገር በችኮላ እንዳልቁርባት አስጠነቀቀኝ ። ከጠዋቱ ሶስት ተኩል እስከምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ድረስ ፡ አብረን ስን ሠራ ነው እምንውለው ፡ ብንጋባ እንኳ ይህን ያህል ሰዓት በተከታ ታይ ላያት አልችልም ። የራሷ መኪና ስላላት ከቢሮ ስንወጣ ፈገግ ብላ ሰላምታ ትሠጠኝና ትሄዳለች ። በግል ህይወቷ ውስጥ ቦታ አል ነበረኝም ። በትርፍ ጊዜዋ ምን ታደርግ እንደነበር አትናገርም ። ቀዝ ቀዝ ያለው አቀራረቧ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን እንዳልደፍራት አስገድ ዶኛል ።

በመጨረሻው ትዕግሥቴ ሲያልቅ ልቤ በፍርሀት ቢደውልም ጨከኜ እራት ጋበዝኳት ። ደንገጥ አለችና ትንሽ ቆይታ ፈገግ አለች ።



"ጥሩ ነዋ እመሠግናለሁ ።" አለችኝ ።

እባህር ዳርቻ ወዳለ አንድ ጥሩ ሬስቶራንት ይዣት ሄድኩ ። ከበ ላን በኋላም ሙዚቃው ፡ ሲጀምር ደነስን ። ቀዝቀዝ ያለው ስሜቷ ባለ መለወጡ በጥንቃቄ ነበር የያዝኳት ።

በየሣምንቱ አርብ አርብ እራት እጋብዛት ጀመር ። አንድ አርብ ቀን ሲኒማ ብጋብዛት ፡ በጨዋ ደንብ ፈቃደኛ አለመሆኗን ገለፀችልኝ

በዚያ ወቅት በሠራ አካሌ ተሠራጭታ ነበር ። ከሷ የተሻለች ሴት እንደማላገኝ አውቄዋለሁ ። እሷ ብቻ ነች ለኔ የምትሆን ። ለምንም ያህል ጊዜ ብቆይ እሷን የምትተካ ፡ ሴት የማገኝ አይመ ስለኝም ።

አበቦችና ከረሜላዎች እየገዛሁ እሰጣት ጀመር ። ለምን ብላ ስትጠይቀኝም በሥራዋ ስለምረካና ስለምትረዳኝ የምስጋና ገፀበረ ከት ነው ብዬ እንድትቀበለኝ እገፋፋት ነበር ።

አንድ አርብ ቀን በተገናኘን በሶስተኛው ወር መሆኑ ነው ። ተቃ ቅፈን በምንደንስበት ወቅት ሁሉም ነገር ከቁጥጥሬ ውጪ ወጣ ።

"ቫል" አልኳት ውብ አይኖቿን እየተመለከትኩ ። እስካሁን ሳት ረጂልኝ አትቀሪም ፡ በጣም ነው እምወድሽ ብንጋባ ምን ይመስል ሻል ? በህይወቴ ከዚህ ሌላ የምፈልገው ነገር የለኝም ። አብረን በመ ኖር ምን ያህል ደስተኞች እንደምንሆን ይታየኛል የሚሠማሽን ንገ ሪኝ ። እድሉ አለኝ?" ብዬ ጠየቅኋት ።

ውብ ፊቷን እንዳላይ ጭንቅላቷን እትከሻዬ ላይ ጣል አድርጋ ለጥቂት ደቂቃዎች ዝም ብለን ደነስን ። ቆይታ ቀና ብላ በፈገግታ ተመለከተች ። ፈገግታዋ ልቤን አሸበረው ፡

"አዎ በርደን እድሉ አለህ ። ግን በቶሎ ማግባት አልፈልግም ።" አለችኝ ። ከዳንሱ አዳራሽ ይዣት ወጣሁና በጨረቃ ብርሃን አፈካው ጨለማ ውስጥ ይዣት ገባሁ ።

"ቫል ታስቢልኛለሽ ማለት ነው ?" ላምናት አልቻልኩም ።

"በደንብ እስብልሀለሁ" አለችና ጉንጩን ሳም አደረገች ።

"ግን አታስቸኩለኝ ። ጥቂት ጊዜ እንቆይ ። እገባሀለሁ ። ቤትህንም ቀጥ አድርጌ እይዝልሀለሁ ። አሁን ግን በቶሎ ሥራዬን መልቀቅ ስለማልፈግ ታገሰኝ ።

ከደስታዬ ብዛት ያንለት ማታ እንቅልፍ አልወሰደኝም ። በማግስቱ ጠዋት የዋናው መሥሪያ ቤታችን ምክትል ሀላፊ ሊያነጋግረኝ እንደሚፈልገኝ በስልክ ጥሪ ደረሰኝ ። ለምን እንደሚፈለገኝ ባለማወቄ ገረመኝ ። ለጠዋቱ ሥራ ሀላፊነቱን ፡ ለቫል ሰጠሁና ወደ ኒው ዮርክ በረርኩ ። ቀኑ ቅዳሜ ነበር ።

ራይነር በስርዐት ተቀበሉኝ በቀጥታ ወደ ጉዳዩ ገባ ።

"በርደን አውሮፓን መመልከት የሚገባህ ጊዜ ደርሷል ። እለንደንና ፓሪስ ባሉት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶቻችን ለስድስት ለስድስት ወራት እንድትሠራ ሆኔታዎችን እያመቻቸንልህ ነው ። ፓሪስ በምትቆይበት ጊዜ ፈረንሳይኛህን ለማሻሻል እድል ይገጥመሀል ። ለንደንና ፓሪስን ፡ የሚጐበኙ ሰዎች ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ ነው ። እና አንተ ሥራህን በተሳካ ሁኔታ ለመሥራት የወቅቱን ሁኔታ ጠንቅቀህ ማወቅ ይኖርብሀል ።ባንተ ቦታ ቢል አልሰንን እየተካሁ ነው ።ሆኖም ስትመለስ ቦታህ ከአንድ ሺ አምስት መቶ ዶላር ደመወዝ ጭማሪ ጋር ክፍት ሆኖ ነው የሚጠብቅህ ።መቼ ብትሄድ ይሻልሀል ?" አለኝ ።

በጥሞና እሰብኩበት ። ከቫል መለያየቱን የምፈልገው አይደለም ። ግን ከመጋባታችን በፊት ጊዜ እንድሠጣት ጠይቃኛለች ። በሚጨምርልኝ ደመወዝ ጥሩ ኑሮ መኖር ስለምንችል የምትቃወም ፡ አይመስለኝም ። ስለዚህም አንተ ባልከኝ ቀን ለመሄድ ዝግጁ ነኝ አልኩኮት ።

"ማክሰኞ" ሲለኝ "እሺ" አልኩት

ችኮላ ነበር ። ቢሆንም ቶሎ ከሄድኩ ቶሎ መመለስ እችላለሁ ።

"በጣም ጥሩ" ደስ እንዳለው ያስታውቃል ፡

"አልሰን ሰኞ ይመጣል ። ፀሐፊህ ታለማምደዋለች ። ጥሩ ፀሐፊ ነች ። አይደል ?" ብሎ ተመለከተኝ ።

"ከማንም በላይ ነች" አልኩና ድርጅቱ በኔ ምክንያት ሊያጣት እንደሚችል ሳስበው ገረመኝ ።

ኒው ዮርክን ከመልቀቄ በፊት ወደ ቦስተን ስደውል ቫልን ቢሮውን ዘግታ ልትወጣ ፡ ስትል አገኘኋት ።

"ወደ አስር ሰዓት ላይ እመለሳለሁ ። እማጫውትሽ ነገር አለኝ ። አውሮፕላን ማፈረፊያው ፡ መጥተሽ ልትጠብቂኝ ትችያለሽ ?"



"እንዴታ ። እችላለሁ" አለች ።

ወደ ቦስተን ከመብረሬ በፊት አንድ ሰዐት ነበረኝ ። ስለዚህ ወደ ጌጣጌጥ መሸጫ ፡ መደብር ሄድኩና የቃል ኪዳን ቀለበት እንዲሁም ሁለት የጆሮ ጉትቻዎችንና አንድ አልማዝ ገዛሁ ። ሁሉንም በስጦታ ወረቀት ጠቀለልኩና በታክሲ ወደ አውሮፕላን ማረፊያው በረርኩ ።

ቫል ትጠብቀኝ ነበር ። ቦልስዋገናን ወደ አቆመችበት ቦታ ተያይዘን ስንሄድ ፡

"ምንድነው እሱ በርደን ?" ብላ ጠየቀችኝ ።

"ትልቅ ጉዳይ ነው" አልኳት ፈገግ ብዬ ወደ ፍራንክሊን የመናፈሻ ስፍራ ውስጇኝ የጠዋቱን ሥራ እንዴት አሳለፍሺው ? ያጋጠመመሽ ነገር አለ ?"

ፀጥ ያለ ስፍራ እስከምንቀመጥ ድረስ ላወራላት አለመፈለጌን ስላወቀች ። ጠዋት ፡ ያጋጣሚትን ነገሮች እያወራችልኝ ወደ መናፈሻ ሥፍራው ወሰደችኝ ። ስራ ይሄን ያህልም ፡ አልነበረም ብቻ አንዱን ሽማግሌ ቱሪስት አለምን ተዘዋውሮ እንዲጐበኝ ያግባባችው መሆኑን ነገረችኝ ። ከሰውዬው ጋር ለብዙ ጊዜ ተደራድረው ስለነበረም ተስፋ የለውም ብዬ አስቤ ነበር ።

መኪናዋን እውጪ አቁመን ሰው ያልያዘው መቀመጫ እስከ ምናገኝ ድረስ በጽጌረዳዎቹ መካከል ተንሸራሸርን ። ቦታ ስናገኝ ተቀመጥንና ራይነር ያለኝን ሁሉ አጫወትኳት ።

"ቫል ልለይሽ አልፈልግም ። ግን ለጥቂት ጊዜም ቢሆን መለያየታችን ስለጋብቻችን ፡ አንድ ውሳኔ ላይ እንድትደርሺ እድል ይሠጥሻል ። ለአንድ አመት ነው እምለይሽ ። ስመለስ ፡ ለጋብቻችን ተዘጋጅተሽ እንደምትጠብቂኝ ተስፋ አለኝ ። እርግጥ የደሞዝ ጭማሪ ባይሰጡኝ ፡ ኖሮ አላደርገውም ነበር ። አንድ ሺ አምስት መቶ ዶላር ጥሩ መቋቋሚያ ይሆነናል ። አይደል ?" ስላት ትኩር ብላ ተመለከተቺኝ ።

"ናፍቆቱን አልችለውም ።"

ስጦታውንም አበረከትኩላት ። ፈታችውና ትንሿን የወርቅ መያዣያ ስትከፍት ትንፋሿ ቁርጥ ፡ ቁርጥ አለ ። በደንነጡት አይኖቿ ተመለከተቺኝ ።

"በርደን ይህንን መቀበል አልችልም ። በፍጹም . . በጣም የሚያስር ነው ።" እባክህ ብላ መያዣያውን ልትመልስልኝ ሞከረች ። ልቀበላት አልፈለኩም ።

"ስጦታው አስደስቶኛል ። ግን በአመት ውስጥ የሚሆነው ነገር አይታወቅም ። የማፈቅርህ ይመስለኛል ። ግን እርግጠኛ መሆን አልፈልግም ። መታሠር አልፈልግም ።"

በድርጊቷ ቅር ብሰኝም አላሳወቅኋትም ።

"የምትታሰሪበት ነገር የለም ። እኔን ደስ እንዲለኝ በቀኝ እጅሽ ላይ አድርጊው ። ስለጋብቻችን ስትወስኚ ወደ ግራ እጅሽ ልታዛውሪው ትችያለሽ ። እንዲህ ብታደርጊ ምን ስህተት አለበት ?"

"በጣም ቆንጆ ቀበለት ነው" ብላ ዘለግ ላለ ጊዜ ተመለከተችው ። ከዚያ ከመያገርያው ውስጥ አወጣችና በቀኝ እጅዋ ሶስተኛ ጣት ላይ አጠለቀችው ።

"ያውልህ . . . . ደስ አለህ ?" ተቃቅፈን ተሳሳምን ።

"አሁን እራት እዘጋጅልሀለሁ ። በባልትና ሙያዬም እንደ ቢሮ ሥራዬ ጐበዝ መሆኔን እንድታውቅልኝ እፈልጋለሁ" አለችኝ ።

ወደ ከተማው ተመለስንና ለእራት መሥሪያ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ገዝታ ወደቤቷ ፣ ይዛኝ ሄደች ።

ቤቷ በደንብ የተያዘ አፓርታማ ነው ። እራቱም ተወዳዳሪ የማይገኝለት ነበር ።

ብዙ አወራን ። መሽቶብኝ ወደ ቤቴ ለመሄድ ስነሳ በማግስቱ እሁድ በመረጥነው መናፈሻ ውስጥ አብረን ልንዝናና ተስማማን ። በህይወቴ እንደዚያ ያለ ደስታ የተሞላበት የእረፍት ቀን አሳልፌ አላውቅም ።

ማክሰኞ በቦታዬ ቢል አልሰንን ተክቼ ከቫል ጋር ወደ አውሮፕላን ማረፊያው ተጓዝን ። ብዙ ከተጫወትን በኋላ ቫል ጠብቂኝ አንድ አመት ብቻ ነው እምቆየው ከዚያ በኋላ የሞቀ ፣ ትዳር እንመሠርታለን ብዬ ተሰናበትኳት ።

እንደዚያ ግን አልሆነም ። በየቀኑ እፅፍላታለሁ ። እሷ ግን ደብዳቤ መጻፍ እንደማትወድ አስጠንቅቃኝ ስለነበር ብዙም አትፅፍልኝ



ተሚልቶላት የምትፅፍልኝ ደብዳቤዎቿ ግን በናፍቆት የተሞሉና በደስታ የምትኖር መሆኗን የሚጠቁሙ ነበሩ ።

ለስድስት ወራት እለንደን ከቆየሁ በኋላ ወደ ፓሪስ ተዛወርኩ ። እቢሮዬ አጠገብ ፣ የቤት እቃው የተሟላ አፓርታማ ተከራየሁና አድራሻዬን ለቫል ጻፍኩላት ።

ላለፉት ሶስት ወራት ምንም ደብዳቤ ስላልደረሰኝ ሰግቼ ነበር ። ከሳምንት በኋላ ስልክ ልደውልላት ሳስብ አንድ ፓኬት ደረሰኝ ። በውስጡ የቃል ኪዳን ቀለበቱንና አጭር ደብዳቤ አገኘሁ ።

ውድ በርደን ፣

ቦስተንን ለመጨረሻ ጊዜ ለቅቄ መሄዴ ነው ። ልጐዳህ አልፈልግም ። ግን ሌላ ሰው ፣ ማግኘቴን እንድታውቀው እፈልጋለሁ ። አንተም ሌላ ሰው ታገኛለህ ። በጣም ነው የማዝነው ። ድንገት ሳላስበው የሆነ ነገር ነው ። ይቅርታ አድርግልኝና ልትረሳኝ ሞክር ።"

ቫል ፣

ለተወሰኑ ወራት ጤነኛ አልነበረኩም ። ስራዬን በደመነፍስ ነበር እምሠራው ። ማታ ማታ መጠጣት ቢያሰኘኝም በግድ ተቋቋምኩት ። ለተወሰነ ጊዜ እስጨናቂ የብቸኛ ኑሮ ኖርኩ ። በመጨረሻው ወደ ቦስተን ተመለስኩ ። አልሰንን ሳገኘው ቫል ለምን ሥራዋን ለቃ እንደ ሄደች ጠየቅሁት ።

"ምንም የማውቀው ነገር የለኝም" አለኝ ።

"ባወቅሁት ደስ ባለኝ ። የግሏ በሆነ ምክንያት እንደምትለቅ ነው የነገረችኝ ። ሆዱ ፣ ምን ያህል እንደማይገኝ ታውቃለህ ። ያለቺኝን ከመቀበል ሌላ ምንም ምርጫ አልነበረኝም"

እራት አመታት አለፉ ። ብስጭቱና ጭንቀቱ ግን አልለቀቀኝም ። በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለሁ ከሮዳ ጋር ተገናኘን ። በተቻለኝ መጠን ቫልን ረስቼ ደህና ኑሮ ለመኖር ሞክሪያለሁ ። ግን ሮዳን ማግባቴ መፍትሄ አልሆነልኝም ። ደስታዬን ሁሉ ያጨለመውን ደብዳቤ ካገኘሁ ስድስት አመታት አልፈዋል ። ለቫል ያለኝ ፍላጐት ግን አሁንም በውስጤ አለ ።

"በርደን!"

በድንጋጤ ባነንኩ ። ያለፈውን ሳስታውስ አጠገቤ ያለችውን ሮዳን ረስቻት ኖሯል ።

ውብ እግሮቿን ከወንበሩ ላይ አውርዳ ፣

"እርቦኛል" አለችኝ ።

"ምን ሆነኸል ? የተጨነቅህ ይመስላል ?"

"ሂደን እንብላ ። ምንም የሚያስጨንቀኝ ነገር የለም" አልኳት ።

ስለቫል ነግሬያት አላውቅም ። ከሷ በፊት ሌላ ሴት አውቅ እንደ ነበርም ጠይቃኝ አታውቅ ። ስላለፈው ለማወቅ ፍላጐቱም የላት ። ዛሬን አሸንፋ ለመኖር ነው ጥረቷ ሁሉ ።

የተለመደውን ምግብ ለመብላት ወደ ቡና ቤቱ ወረድንና በልተን ስንጨርስ እስክንተኛ ድረስ ተፋጥጠን ለማንቀላፋት ወደ መኖሪያችን ተመለስን ።



## ሁ ለ ት

በማግስቱ ጠዋት ደብዳቤዎችን ስመለከት ሀምፍሬይ ማሲንግሀም ስልክ ደወሎ ቀዝቀዝ ባለ ድምፅ ።

"ስለቪዳል አጣርቻለሁ" አለኝ ።

"ባንኮችና ጉዳይ አስፈጻሚዎቹ አስደናቂ ዘገባዎችን ነው የሰጡኝ ። ዱቤ ገማቾቹን ጠይቅ ማለትህ ልክ ነበር ። ብታምንም ባታምንም ቪዳል የራሱ የሆነ ነገር ያለው አይመስልም ። በርግጥ ምን ማለት እንደሆነ ሊገባኝ አልቻለም ። በጣም ልዩ ሁኔታ ነው ። መኖሪያ ቤቱ እቃዎቹ ከሮልስ ሮይሱ ጋር ስድስቱ መኪናዎች በሙሉ የተከራያቸው ናቸው ። በቤቱ ውስጥ ስድስት ቴሌቪዢኖችና አምስት በኤሌክትሪክ የሚሠሩ አይ ፣ ቢ ፣ ኤም የፅሕፈት መኪናዎች አሉት ፣ ሁሉንም ተከራይቷቸው ነው ። ሚስቱ የምታጌጥባቸው ጌጦች ሳይቀሩ የኪራይ ናቸው ። ከሁሉም ድርጅቶች የስድስት ወር ዱቤ እየወሰደ የክፍያው ጊዜ ሲደርስ በወቅቱ እንደሚከፍል ገማቾቹ አረጋግጠውልኛል ። ከዚህ ምን ትገምታለህ ? አለኝ ።

"ድንገት ደንበኝነታችንን ማቋረጥ ቢያስፈልግ አመቺ የሆነ ዝግጅት ማድረጉ ነው እሚታየኝ ።" አልኩት ።

"ልክ ነህ ። እኔም እንደዚያ ነው ያሰብኩት ። ሚስተር ራይነርንም አነጋግሬው ፡ነበር ። ከአሜሪካን ኤክስፕሬስ ዳይሬክተሮች አንዱን አነጋገርኩ ከጭቅጭቁና ከሚጠይቀው ከፍተኛ ቅናሽ እንፃር ከቪዳል መገላገላቸው እንዳስደሰተው ገልጾልኛል ። በገንዘቡ በኩል ፣ ግን ይህን ያህልም አስጊ ሁኔታ የለበትም ። ራይነር ሌሎች የጉዞ ወኪሎችንም አነጋግሮ ነበር ። ዳየር ወደኛ ከመምጣቱ በፊት ሁሉንም አነጋግሮ እምቢ ብለውታል ። ሁሉም ፣ ለቪዳል ስድስት ወርም ሙሉ በዱቤ አገልግሎት ሊሰጡት የሚችሉ አይደሉም ። ዳየርን አምስት በመቶ የጠየቀውን ቅናሽ እንዲያነሳ ካደረግነው እንድንገፋበት እምቢ ካለ ግን ግንኙነታችን እንዲቋረጥ ነው ራይነር የሚፈልገው"

"ዱቤውንስ ለስድስት ወር እንሰጠዋለን ?"

“ይመስለኛል ። ሌሎች ድርጅቶች ሁሉ እንደዚያ አድርገውለታል ። ዳየር በቁጥጥራችን ሥር የዋለ ይመስለኛል ። ያለው ምርጫ እኛ ባልነው መስማማት ወይም አለጉዞ ወኪል መቅረት ነው ። ያለነው የመጨረሻ እድል እኛ ብቻ የሆን ይመስለኛል ።”

“እንግዲያው ጥሩ ። ለኔ ተውልኝ” አልኩት ።

ከጠዋቱ ወደአራት ሰዓት ተኩል ገደማ ላይ ቬርኖን ዳየር ስልክ ደወለልኝ ።

“ፕሮግራማችሁ ደርሶኛል” አለ ቅር ባለው ድምፅ” ።

“ምን ማለታችሁ ነው ? ምን አይነት ጨዋታ ነው ? ዋጋችሁ ከአሜሪካን ኤክስፕሬስ ዋጋ በአስር በመቶ ይበልጣል ።”

“እነሱ ዋጋቸውን የተመኑት ከአሥራ ስምንት ወራት በፊት ነው” አልኩት ለስለስ ብዬ ።

“ከዚያ ወዲህ ዋጋዎች ጨምረዋል ። አሁንም እየጨመሩ ነው ። የላኩልህ ዋጋ በአሁኑ ወቅት ዝቅተኛ የሆነውን ነው ።”

ለጥቂት ጊዜ ዝም አለና “የባንክ ሂሣቡስ ጉዳይ ሁሉም ነገር ተሟልቷል ?” አለኝ ።

“አዎ አሁን ሂሣቡ ተከፍቷል ።”

“እንደዚያ ከሆነ እኮክ ዲ እር ሬስቶራንት ተገናኝተን ብንወያይበት ይሻላል ።” አለኝ ። ሬስቶራንቱ በፓራዳይዝ ከተማ ውስጥ በጣም ምርጥና ውዱ ነው ።

“ሚስተር ዳየር ስለግብዣው አመሰግናለሁ ።ግን ይቅርታ አድርግልኝ” አልኩት አይኔን ጨፍኜ “ምሳ እውጪ በልቼ አላውቅም በፈለግኸው ሰዓት እዚሁ ልታገኘኝ ትችላለህ”

“ለምሳ አትወጣም!” አለኝ በጩኸት “ምን ማለትህ ነው ።”

“እቢሮዬ ነው ምሳዬን እምበላው ። ሥራ ስለሚበዛብኝ እውጪ አልወጣም ።”

“ከሀርክነስ ጋር ሁሌ አብረን ነበር እምንበላው ።”

“ያ የእሱ ምርጫ ነው ። ሚስተር ዳየር መቼ ልትመጣ አስበሀል ?”



አሁንም ለጥቂት ጊዜ ዝም አለና “ከኔ ጋር ምሳ ለመብላት ፈቃዱ ሊኖርህ በተገባ ነበር” አለኝ ።

“የመፍቀድና ያለመፍቀድ ጉዳይ አይደለም ። ጊዜ የማጣት እንጂ ። ሚስተር ዳየር ፡ ምሳዬን እቢሮዬ ውስጥ ከበላሁ ብቻ ነው በቂ ጊዜ አግኝቼ የተቀላጠፈ አገልግሎት ልሠጥህ የምችለው” ስለው

“መልካም ነው እሺ” አለኝ ። የተበሳጨና የተቆጣ መሆኑ ከድምጹ ያስታውቃል ፡

“ከሰዓት በኋላ ዘጠኝ ሰዓት ላይ እመጣለሁ” ብሎ ስልኩን ዘጋው ። ቀና ብዬ ፀሐፊዬን ጠቀስኳት ።

“ዳየርን ምሳ ለመጋበዝ ከእንግዲህ ምንም ወጪ አናወጣም” አልኳት ። በጥሩ ሁኔታ እየጀመርን ነው ።

ዳየር እስከ አስር ሰዓት አልመጣም ። ሲመጣ ሌላ ባለ ጉዳይ እያነጋገርኩ ስለነበር ፡ እስከምንጨርስ ድረስ ከቢሮዬ ውጭ እየተንጐራደደ ጠበቀኝ ። አልፎ አልፎ ወደ እኔ እየተመለከተ ሰዓቱን ያያል ። ዝም አልኩት ። ባለጉዳዩ ሲወጣ ግባ ብዬ ምልክት ሠጠሁት ።

“ስላስጠበቅሁህ ይቅርታ ግን ቀጠሮአችን በዘጠኝ ሰዓት ነበር ።” እራሱን ነቅንቆና ተቀመጠ ።

“የባንኩ ሂሣብ ተከፍቷል ?” አለኝ ሀርክነስንም አነጋግረኸዋል ?”

“አነጋግሬዋለሁ ፡”

“ከሱ ጋር በተስማማንበት አይነት ከሆነ ከእናንተም ጋር እንስማማለን ፡”

ከሱ ጋር የነበረንን ስምምነት ታውቀዋለህ ?”

“አውቂዋለሁ ግን ያንን ልንቀበል አንችልም ።”

“ምን ማለትህ ነው ? ለነሱ የተስማማቸው ለናንተም መስማማት አለበት ።”

“ከነሱ ጋር የተስማማችሁት ከአሥራ ስምንት ወራት በፊት ነበር ። ሚስተር ዳየር በተቻለ መጠን ዋጋችንን ዝቅ ለማድረግ እየጣርን ነው ። የሥድስት ወራት ዱቤ ልንሰጥህ እንችላለን ። አዝናለሁ ። ቅናሽ ግን ልናደርግልህ አንችልም ።”

እንገቱን ደፋ ፡ ፊቱ ቀላ ፡ አይኖቹን አጉረጠረጠ ።

"እና ከኛ ጋር መሥራት አትፈልጉም ማለት ነው ?"

"እንደዚያ አላልኩም ሚስተር ዳየር ።"

"እንደዚያ እያልክ ነው ። ከአሜሪካን ኤክስፕሬስ ጋር በተስማማነው አይነት ካልተስማማችሁ ከኛ ጋር መሥራት አትፈልጉም ማለት ነው ።"

"እናዝናናለን" አልኩ ። ሀዘን በተቀላቀለበት ሁኔታ ። "አንተ በምትለው አይነት የሚስማማ ሌላ የጉዞ ወኪል ካገኘህ ምርጫው ያንተው ነው ሚስተር ዳየር ።"

በቁጣ ወደ ኋላው ደገፍ ብሎ ተቀመጠ ።

"የምርህን ነው? ለማትረባ ለአምስት በመቶ ቅናሽ ብለህ የሁለት መቶ ሽህ ብር ሥራ አንሠራም ነው የምትለኝ ?" አለኝ ።

"አምስት በመቶ ቅናሽ እኮ ለናንተ አስርሺ ዶላር ነው የሚያተ

ርፍላችሁ ። አዝናለሁ ሚስተር ዳየር ጉዳዩ እንደዚህ ነው ።" ከንፈሩን ነከሰና ቀዝቀዝ ብሎ "እሺ ስንት ትቀንሱልናላችሁ ። አራት በመቶ ?" ሲለኝ እያፌዘብኝ መሆኑን አወቅሁበት ።

"አዝናለሁ ግን ቅናሽ ማድረግ አንችልም" አልኩና ፈገግ አልኩ ። "ግሎባልን ወይም ፍሎሪዳ የጉዞ ወኪሎችን አነጋግረሀልሀል ?"

"ሁሉም አይረቡም" እንዳነጋገራቸው ከሁኔታው አወቅሁ ።

ሌሎችም ወኪሎች ሞልተዋል ። አሚረዳህ ከሆነ ፀሐፊዬ ዝርራቸውን እንድትሰጥህ ልጠይቃት ።"

እጆቹን እየተመለከተ ዝም ብሎ ተቀመጠና ፡

"የስድስት ወር ዱቤ ትሰጡናላችሁ ?" አለኝ

"በዚህ ተስማምተናል ።"

"ለእንዲህ አይነቱ ገቢ ምንም አይነት ቅናሽ አለመስጠታችሁ የሚያስደንቅ ነው ።"

"አዝናለሁ"



ትከሻውን ነቀነቀና ፈገግ አለ

"እሺ የባንኩን ሂሣብ ብትቀበሉን ይሻላል"

"ያ ያንተ ውሣኔ ነው ። ሚስተር ዳየር ።"

ወርቃማ የሲጋራ መያዣያውን አወጣና አንድ ሲጋራ መርጦ ለኮሰ ።

"የኔስ ኮሚሽን ?" ሲለኝ ቀናብዬ ተመለከትኩት ። "ይቅርታ . . . ያንተን ኮሚሽን ?" ስለው አይኖቱ በቁጣ ከድን ክፍት አሉ ።

"አንድ ነገር ሳትሰጡኝ ይህን ሁሉ ሂሣብ እንድንሰጣችሁ የምትጠብቁ አይመስለኝም ። ይሄ የተለመደ አሠራር ነው"

"ሚስተር ዳየር ምን ያህል እንድንሰጥህ ነው የምትፈልገው ?" ስለው ፊቱ ፈካ

"አምስት ሺ ብር ይበቃኛል ። ታዲያ እጅ በእጅ ነው የምትከፍሉኝ "

ለዚህ እፍረተ ቢስ ድፍረቱ ጥፊ ይገባዋል ፡ብዬ አሰብኩ ።

"ከዋናው መሥሪያ ቤት ጋር እነጋገርባታለሁ ።" አልኩት ። አይኖቹ ተለወጡ ።

"መቼም ይሄ በሚስጥር እንደሚያዝ ተስፋ አለኝ ።" አለኝ ፡

"የኛ ሰዎች እንደዚያ የሚያዩት አይመስለኝም ። እንዲህ አይነቱን አሠራር የሚደግፉት አይሆንም ።" አልኩና የሀዘኔታ ፈገግታየን ሰጠሁት ።

"በኔ በኩል የባንክ ሂሣብ ይዞልን የመጣ ሰው ቢከፈለው መልካም እድል ብዬ ነው እምሸኘው" ስለው በጥላቻ የተሞላ ፈገግታ አሳየኝ ።

"ሚስተር በርደን ይህንን ጉዳይ አንተ እንደምታስፈጽምልኝ ተስፋ አለኝ ። ሚስተር ቪዳል ይህንን ማወቅ አይኖርበትም ። ገባህ እኔ እኮ ከሌላው ድርጅት እናንተን መርጨ ነው የመጣሁት ።"

"ሚስተር ዳየር የድርጅታችን ምክትል ፕሬዘዳንት ጥብቅ ሰው ነው ። የሚስተር ፡ ቪዳል የቅርብ ረዳት የሱን የባንክ ሂሣብ ወደኛ

ስላዛወረ አምስት ሺ ዶላር መጠየቁን ቢሰማ ለሚስተር ቪዳል ደውሎ በአሠራሩ እሱም ይስማማ እንደ ሆነ እንደሚጠይቀው እርግጠኛ ነኝ'' ስለው የፊቱ ቀለም ተለወጠ ።

''እና ምንም አታገኝም ማለትህ ነው ?''

''አገልግሎት ። ሚስተር ዳየር ። አገልግሎታችንን ታገኛለህ'' ።

በእርግጥ እንደጠላኝ በአስተያየቱ አውቃለሁ ። በሚንቀጠቀጡት እጆቹ አንድ ፖስታ ከኪሱ አወጣና ወረወረልኝ ።

''እነዚህ መመሪያዎችህ ናቸው ። በቶሎ ሥራ ላይ አውላቸው ሚስተር በርደን መጠንቀቅ አለብህ በሥራ ላይ ወለም ዘለም አልወድም'' አለና ፈንጠር ብሎ ተነስቶ ፀሐፊዬን አልፎ ወደ ኰሪደሩ ገባ ።

ፖስታውን ከፍቼ መመሪያዎቹን አጠናኋቸው ። ጥሩ ትዕዛዝ ነው ። ለኒው ዮርክና ለቶኪዮ የአውሮፕላን በረራ ስድስት አንደኛ ማዕረግ መቀመጫዎች እንዲሁም ለአሥራ አራት ቀናት ሆቴል እንዲያዝና— መኪናና ሹፌር እንዲዘጋጅ ። ሁሉም በአንደኛ ማዕረግ እንዲሆኑ የሚል ነው ።

መመሪያዎቹን እፖስታው ውስጥ መልሼ ከተትኩና ወደ ፀሐፊዬ ሄጄ ባስቸኳይ ወደ ማያሚ እንድትልከው ሰጠኋት ።

ከዚያ ለማሲንግሀም ደወልኩና ከዳየር ጋር የተነጋገርነውን ዝርዝሬ ነገርኩት ።

በነገርኩት ሁሉ ከት ብሎ ሣቀና ''ግሩም ነው በርደን ለሚስተር ራይነር እነግረዋለሁ ። ያደረግኸው ሁሉ ትክክል ነው ። ፖስታው እንደደረሰን የቶኪዮውን ጉዞ እናዘጋጃለን ። ለሀርከነስ እንዳትነግረው ። በሚስጥር እንያዘው'' አለኝ ።

የሆነውን ሁሉ ለፀሐፊዬ ነገርኳት ። ወደ ቤታችን ስንሄድ ለሮዳም ልነግራት ፈልጌ ነበርን እግሬን እያለች ማቃሰቷን ስለጀመረች ፣ የምነግራትን ለመስማት ፈቃደኛ አትሆንም ።

ቫል ብትሆን ግን በጉጉት ነበር እምታዳምጠኝ ። ይህን ድል እንድናከብርም ትገፋፋኝ ነበር ። ሳስታውሳት የልቤ ቁስል ተቀሰቀሰ ።

* * *



የቶኪዮውን የጉዞ ፕሮግራም ፣ ትኬቶቹና ሆቴሌቹ የተያዘበትን ሰነድ የያዘው ፖስታ በጠዋት ደረሰኝ ። ወደ አራት ሰዓት ላይ ለዳየር ደወልኩለት ። ስልኩን ሲያነሳ ፣

''የቶኪዮው የጉዞ ፕሮግራም ደርሶኛል'' አልኩት ፣ በፖስታ ልላክልህ ወይስ ልከህ ታስወስደዋለህ ?''

''እራስህ እዚህ ድረስ አምጣው'' አለኝ ቆጣ ብሎ ።

''ብዙ የማዋይህ የሥራ ጉዳይ አለኝ ። ለወደፊቱ አንተ ቢሮ ድረስ እየመጣሁ ጊዜዬን በከንቱ ለባክን እልፈልግም ።'' ብሎ ስልኩን በሀይል ዘጋው ።

የጠበቅሁት ነገር ነበር ። እፀፋ መመለሱ ነው ። አሁን እኔ በተራዬ እሱ ቢሮ ሄጄ ደጅ መጥናት ኣለብኝ ። ሆኔታውን ለፀሐፊዬ አማከርኳት።

''ብዙ ሰው ካልመጣ ። ብቻዬን ልሠራው እችላለሁ ።''አለቺኝ ።

''ግን ብዙ ሰው ሊመጣ ይችላል ። ቅሬታ እንዲፈጠርብን እልፈልግም ።ሆቴሉም ይህንን ቦታ ሲሰጠን ከፍተኛ አገልግሎት እንደ ምንሰጥ ቃል አስገብቶን ነው ። ለማንኛውም ለማስንግሀም ደውዬ ልንገረው ።''

ማሲገሀም ገና ደውዬ እንደነገርኩት ሁኔታ ውን ተረዳው ።

''ቦስተን የነበረውን ቢል ኦልሶንን ታስታውሳዋለህ? ስለፍሎሪዳ አንዳንድ ነገሮችን ለማወቅ እኔ ዘንድ መጥቷል ። እሱን ወዳንተ እልከዋለሁ ። እኔ ጋ ከሚሆን አንተ ጋ ቢሠራ ይሻላል ። ከአንድ ሰዓት በኋላ ይደርስልሀል ።'' አለኝ ።

ደነገጠኩ ። ቫል ባልታወቀ ምክንያት ከቦስተን ስራዋን ለቃ ከሄደችበት ጊዜ አንስቶ አይቼው አላውቅም ። እሱን ሳስታውስ ስለ ቧ ማሰብ ጀመርኩ ። ፀሐፊዬን ጠራሁና ።

''ሌላ ጠረጴዛና ወንበር እንዲመጣልን አድርጊ ። አንቺ ካለሽበት ቦታ ወደ ግራ በኩል ፈቀቅ ብትዩ ሌላ ጠረጴዛ የሚችል ይመስለኛል ።''

ራሷን በመነቅነቅ እሺታዋን ገለፀችለኝና ወደ ስልኳ ሮጠች ።

የጉዞ ፕሮግራራሙንና ትኬቶቹን ይዤ ወደ መኪና ማቆሚያው ሥፍራ በረርኩ ። ሮዳ እንደ እንደልማዷ እሱቅ ውስጥ ተቀምጣ እመጽሔቷ ውስጥ ሰምጣለች ።

"ተጠንቀቂ የኔ ሸጋ" አልኳት "አለያ እግርሽን ታጪዋለሽ" ቀና ብላ እየተጨናበሰች ተመለከተችኝ ።

"እሀ" ምንም አላልኩ "በምሳ ሰዓት ላልመለስ እችላለሁ ። ሚስተር ሄንሪ ቪዳል ጋ ስለሄድኩ እንዳትጠብቂኝ ።"

"ብርቱ ጉዳይ ነዋ" አለችና ወደ መፅሔቷ ተመለሰች ።

ወደ እነ ሚስተር ቪዳል ሠፈር የሚያስገባው መንገድ በኤሌክትሪክ በሚሠራ መቆጣጣሪያ የተዘጋ ነው ። ማንም ሰው . . እደግመዋለሁ ማንም ሰው ማንነቱን ሳይናገርና የመጣበትን ጉዳይ ሳያሳውቅ መግባት አይፈቀድለትም ።

ዙሪያውን በዝግባ እንጨት ታጥሮ በዛፎችና በአበቦች የተመላው መንደር ከሠላሳ እስከ አርባ የሚሆኑ አስደናቂ ውብ የሀብታም ቤቶችን ይዟል ።

መኪናዬን እመግቢያው ፊት ለፊት አቆምኩና ወርቧ ሰማያዊ የደንብ ልብስ በለበሰው ዘበኛ ተፈተሸኩ ።

"ክሌይ በርደን እባላለሁ ከሚስተር ዳየር ጋር ቀጠሮ አለኝ" ስለው ። "የመንጃ ፈቃድዋን ቢያሳዩኝ ?" አለኝ

ሠጠሁት ። ለጥቂት ጊዜ ተመለከተውና መለሠልኝ ። ከዚያ ዞር ብሎ ስልኩን አነሳ ። ወዲያው መልስ አላገኘም ። ጥቂት ተነጋገረና አንድ ቁፍል ጫን ብሎ በሩን ከፈተልኝ ።

"በግራ በኩል አራተኛው በር ነው ።"

በሰፊው ጐዳና ላይ መኪናዬን አሽከረከርኳት ። ከዚያ ወደ ግራ ታጠፍኩና አንድ በር ላይ ደረስኩ ። ሌላው ዘበኛ በሩን ከፈተልኝ ።

"ሚስተር በርደን ። ወደፊት ይቀጥሉና አራት ቁጥር ማቆሚያ ላይ ያቁሙ ።" አለኝ

እንደተባልኩት መኪናዬን ወደፊት ስነዳት ባለሁለት ፎቅ ውብ ቤት ከፊቴ ድቅን አለ ።

አራት ቁጥር የመኪና ማቆሚያ ላይ አቆምኩ ። ከአንድ ጐኔ የሚስተር ቪዳል ሮልስ ሮይስ ከሌላ ጐኔ ሌላ መኪና ቆሟል ። የነሱ ነፀብራቅ የኔን መኪና ካለችበት ሁኔታ የበለጠ አሮጌ አስመሰላት ።



ነጭ ሱሪና ቀይ ጃኬት የለበሰ ጥቁር ሰው ከአትክልቱ መካከል ብቅ ብሎ ወደኔ መጣ ።

"ሚስተር በርደን ይከተሉኝ ?"

ብሎ በሚያማምሩ አበቦች መካከል እየመራ ወሰደኝ ። እበሩ አጠገብ ስንደርስ ከፈተልኝና ወደ ጐን ቆሞ "ሶስተኛው በር ነው ። ለሚስተር ዳየር መምጣትዎን እነግረዋለሁ" አለኝ ።

እክፍሉ መካከል ትልቅ ጠረጴዛ አለ ። እላዩ ላይ የተለያዩ መፅሔቶች ተበትነውበታል ። በእድሜ በመልክ በቁመትና በሰውነት ቅርፅ የሚለያዩ ስምንት ሠዎች ዙሪያውን ተቀምጠዋል ። የከተማ ሰዎች ይመስላሉ ። ሁሉም የሰነድ መያዥያ ቦርሳ ይዘዋል ። ገና ስገባ አደገኛ ተወዳዳሪ መጣብን በሚል አይነት አፍጥጠው ተመለከቱኝ ። እንዱ ጐን ስቀመጥ ነው አይኖቻቸው የለቀቁኝ ።

ፀጥ ብለን ተቀመጥን ። ከአምስት ደቂቃ በኋላ አንድ የሴት ድምፅ በማይታይ የድምፅ ማጉሊያ

"ሚስተር ሄድገር እባክዋን ቢሮ ቁጥር አምስት ይግቡ" አለ ። ሽምግል ያለ ወፍራም ሰው ተነሳና ወደ ተባለው ክፍል ተጣደፈ ።

ብዙ ደቂቃዎች አለፉ ። ሌላ ስም ተጠራ ፤ ሌላ ሰው ሮጠ ። እኔና አንድ መላጣ ሰው እስከምንቀር ድረስ በዚህ አይነት ቀጠለ ።

"የጥርስ ሀኪም እንደመጠበቅ አይነት ነው" አልኩኝ አራተኛውን ሲጋራዬን እየለኮስኩ ።

"ልክ ነህ ከዚህስ የጥርስ ሀኪሙን እመርጣለሁ" ብሎ መሐረቡን ከኪሱ አውጥቶ ያላበውን ፊቱን ጠረገ ።

ሰዓቴን ተመለከትኩ ። አንድ ሰዓት ከሥር ደቂቃ ተቀምጫለሁ ። በሚቀጥለው ጊዜ (የሚቀጥለው ጊዜ የሚባል ነገር ካለ) ሥራ ይገፍ መምጣት አለብኝ ። አልኩኝ ለራሴ ።

መላጣው ሰውዬ ተጠራ ። የእፎይታ ምልክት አሳይቶኝ ሄደ ። ከአንድ ሰዓት ተኩል በኋላ ነበር የኔ ስም የተጠራው ።

"ሚስተር በርደን እባክዎን ቁጥር አሥራ አምስት ክፍል ቢገቡ"

ሚስተር ቤርኖን ዳየርን ከትልቁ ጠረጴዛው ኋላ በሶስት ስልኮች ፣ በአንድ ቴፕ ሪኮርድር ፤ በአንድ የውስጥ መገናኛ ፣ በአበቦች ፣

በሶስት የሲጋራ መተርኮሻዎችና በብርማ የሲጋራ መያገሪያ ፓኮ ተከቦ አገኘሁት ። ደብዳቤዎቹን መጻፊያ ቦታ ማግኘቱ የሚያስገርም ነው ። እሱ ላይሆን ይችላል የሚፅፈው ። ለውዞችን እየፈለፈለ በቃል ይሆናል ፡ የሚያጽፈው ።

"ደረስክ" አለኝ እየሳቀ "የጉዞ ፕሮግራሙን ፣ የአውሮፕላን ትኬቶቹንና የሆቴል መያዣዎቹን እፊቱ አደረግሁለትና ተቀመጥኩ ።

ፕሮግራሞቹን በዝግታ ተመለከታቸው ። ስህተት እንደሚፈልግባ ቸው ያስታውቃል ። ቆየት ብሎ በድንገት ቀና አለና ።

"ለምንድነው እፓስፊክ ሆቴል የተያዙላቸው ?" ብሎ ጮኸብኝ ።

"ጥሩ የመናፈሻ ስፍራ አለው ። የጃፓንን ባህል የሚያንፀባርቅ ከመሆኑም በላይ ፀጥታም አለው ።

"በመናፈሻ ስፍራው ለመንሸራሸር ጊዜ የላቸውም ። ስለ አካ ባቢው ሁኔታስ ማይጨነቃል ? በኢምፔሪያል ሆቴል እንዲያዝላ ቸው !"

"ችግር የለውም ሚስተር ዳየር ልንለውጠው እንችላለን" ስለው አፈጠጠብኝና

"ለውጡ እስከ አስራ ሁለት ሰዓት እንዲደርሰኝ እፈልጋለሁ ።" አለኝ ።

"ይደርስሀል ። ለወደፊቱ የምትፈልገውን ሆቴል አስቀድመህ ብትነግረኝ መልካም ይሆናል"

"ጥሩ ሆቴል የትኛው እንደሆነ ለይቶ ማወቅ ያንተ ሥራ ነው"

"በኔ ግምትማ ፓስፊክ ሆቴል ነው ፡ ከሁሉም የሚሻል ።" ስለው ተናደደ ።

"ወደ ኢምፔሪያል ሆቴል ለውጠው ብዬሀለሁ" ። ብሎ የሆቴል መያገሮውን ወረወረልኝ ። ከዚያ ወደ ግርግዳው ሰዓት ተመለከተ ። ስድስት ተኩል ሆኗል ።

"እንደዚህ ረፍዷል እንዴ ?" ዝግ ብሎ ተመለከተኝና ፡ የምፀት ፈገግታ ፈገግ አለ ። "እንደገና ተመልሰህ እንድትመጣ እፈልጋለሁ ። አሁን የምሳ ቀጠሮ አለብኝ አስራ አንድ ሰዓት ላይ እዚህ እንዳገኝህ ።"



"ሚስተር ዳየር በጣም ይቅርታ አድርግልኝ አሥራ አንድ ሰዓት ላይ ሌላ ቀጠሮ አለኝ ።"

ጭንቃላቱን ወደ ጐን ዘንበል አደረገና ተመለከተኝ ።

"ይህንን የሚያክል ሂሣብ ስከፍት አገልግሎት እጠብቃለሁ ። ስለዚህ በአስራ አንድ ሰዓት እዚህ እንድትመጣ እፈልጋለሁ ።" አለኝ በቁጣ ።

"ሆኖም በጣም አዝናለሁ ። ያንያህል የሚያስቸኩል ከሆነ ከምሳ በኋላ ለምን ወደኔ ቢሮ አትመጣም ?"

ተፋጠጥን ። የሱ አይኖች በመጀመሪያ ተሠበሩ ። በቁጣ ተወጥሮ ።

"እሺ ! እሺ ! ለምሳው እንደሁ ዘግይቻለሁ ። ስለዚህ መመሪያዎ ቹን አሁን ልሰጥህ ።" አለኝ ።

ከመሳቢያው ውስጥ ወፍራም ፖስታ አወጣና ሰጠኝ ።

"ይህንን ተመልከተው ። ጥያቄ ካለህ ነገ ደውልልኝ. .ምናልባት የምትጠይቀው ነገር ሊኖር ይችላል ። ሳታነጋግረኝ ሆቴል እንዳት ይዝ ።"

"እሺ" አልኩና ተነስቼ ወደ በሩ አመራሁ ።

"ቆይ የረሳሁት ነገር አለ ።ከሚቀጥለው ማክሰኞ ጀምሮ ለአም ስት ቀናት ከቢሮህ በጭራሽ እንዳትለይ እፈልጋለሁ ።"

"ከቢሮዬ በጭራሽ እንዳልለይ?" አልኩት አይኑ አይኑን እያ የሁ ።

"እንደዚያ ነው እምልህ ። ሚስተር ቪዳል ወደ ሳን ሳልቫዶር ይሄ ዳል ። ባለቤቱም አብራው ትሄዳለች ። ሚስተር ቪዳል በስራ ተጠ ምዶ ሲውል አንተ ባለቤቱን እዚያ ሊታዩ የሚገባቸውን ነገሮች እያዟዟርክ ታሳያታለህ ።

ማንኛውም ነገር አንደኛ ማዕረግ ነው እሚያዘው ። መኪናዎ ቹና ሆቴሎቹ የአየር ማስተካከያ ያላቸው መሆን አለባቸው ።

ሚስተር ቪዳል ኢንተር ኮንቲንታል ሆቴል ነው ማረፍ የሚፈ ልገው ለነሱ አንደኛ ማዕረግ ላንተ የቁጠባ ክፍል ትይዛለህ ። መረጃ ዎቹ በሙሉ እፖስታው ውስጥ አሉልህ ።"

ይሄ ላደርገው የምፈልገው ነገር አልነበረም ። ሳን ሳልቫዶርን ስለማላውቀው በአስጐብኝነት የምሰጠው አገልግሎት የለም ። ለዚያ ውም ማስጐብኘት የኔ ሥራ አይደለም ።

"ሳን ሳልቫዶር ውስጥ ያለው ወኪላችን የሚስተር ቪዳልን ባለ ቤት በምትፈልገው አይነት ሊያስተናግዳት ይችላል ።"

"ሚስተር ቪዳል ያንን ነው እማይፈልገው !" አለና ተቆጣ ዳየር

"ሚስተር ቪዳል ባለቤቱ ከማንም ወሮበላ ጋር እንድትዞር አለመፈለጉን በጥብቅ ገልጾልኛል ።"

"የኔ ሥራ ከፍተኛ ዋጋ ያለውን የሚስተር ቪዳል የባንክ ሂሣብ መከታተል ብቻ ይመስላኛል ።" አልኩት "ምን ማድረግ እንደሚቻል አያለሁ ። እማያሚ ውስጥ የሚስተር ቪዳልን ባለቤት ሊረዳ የሚችል በደንብ የሠለጠነ አስጐብኚ አለን ።"

"ለሚስተር ቪዳል ሥራውን በደስታ ተቀብለህ እንደምትሠራው ነግሬዋለሁ ስለዚህ ፡ ብትቀበለኝ ይሻላል ።"

"እኔ ለአምስት ቀናት እሥራዬ ላይ ካልተኘሁ መመሪያዎችህን በሥራ የሚተርጉማቸው ፡ ሰው አይኖርም" አልኩት መውጫ ቀዳዳ እየፈለግሁ ።

"የሚቀጥለው ሣምንት መመሪያ እጅህ ውስጥ ነው" አለ ዳየር ትዕግስቱ እያለቀ ፡

"እስከምትመለስ ድረስ ሌላ ሥራ አይኖርም"

እጅ ሠጠሁ ።

"ምን ማድረግ እንደምችል አያለሁ" ብዬ ትቼው ወጣሁ ።

ኮካኮላ ለመጠጣትና ሰላጣ ብጤ ለመብላት እሆዋርዶ ጆንሰን ሬስቶራንት ጐራ አልኩ ። እየበላሁ የሠጠኝን መመሪያ ተመለከት ኩት ። የሚያስደንቅ የጉዞ ትዕዛዝ ነበር ።ወደ ለንደን ፓሪስና ሞስኮ ለሚጓዙ ሰዎች አንደኛ ማዕረግ ሆቴል ፡ የበረራ ትኬትና አስፈላ ጊው ሁሉ እንዲዘጋጅ ።

ሚስተር ቪዳልን ባለቤቱ ሰኞ ስለሚነሱ ሳን ሳልቫዶር አውሮ ፕላን ማረፊያ ድረስ የአየር መቆጣጠሪያ ያለው መኪና እንዲጠብቃ ቸውና ወደ ኢንተር ኮንትኔታል ሆቴል እንዲያደርሳቸው ማድረግ ።



እኔ ደግሞ በማግስቱ ማክሰኞ ወደ ዚያው ፡ሄጄ ሚስስ ቪዳልን እንዳ ስጐበኝ ፡ እሳን ሳልቫዶር በሚቆዩባቸው ጊዜያት ሁሉ ከሷ ጋር ቆይቼ ወደፓራዳይዝ ከተማ እሁድ አብረን እንድንመለስ . . .

ስጨርስ መኪናዬን አስነስቼ ወደ ቢሮዬ ከነፍኩ ። ስደርስ ቢል አልሰን ስራውን ጀምሮ ከፀሐፊዬ ጋር ብዙ ደንበኞችን ሲያስተናግዱ አገኘኋቸው ።

አልሰን ሲያየኝ ቀና ብሎ ፈገግ አለ ። እጄን በማውለብለብ ሰላ ምታ ሠጥቼው ወደ ቢሮዬ ገባሁና ለማሲንግሀም ደወልኩለት ። የተ ደረገውን የሆቴል ለውጥና ወደ ሳን ሳልቫዶር ፡ስለሚደረገው ጉዞ ነገርኩት ።

"አንተ በሌለህበት ወቅት ዳየር የማያስቸግረን ከሆነ ብትሄድ ምንም አይደል ። ላንተም ፡ለውጥ ነው ።" አለኝ ማስንግሀም ።

"ግን እዚያ ሄጄ ስለማላውቅ አስጐብኝ ልሆን አልችልም ።"

"ወደ ሳን ሳልቫዶር ቴሌክስ አድርግና የጐበኝት ፕሮግራም አዘጋጅተው እንዲጠብቁህ ፡ አድርግ ። በተጨማሪም አገሩን የሚያውቅ ሹፌር ይመዱቡልህ ። ቪዳል ይህን የሚቃወም አይመስለኝም ። የሚቃ ወም ይመስልሀል ?"

"አይመስለኝም ፡ እሺ እንዳልከኝ አደርጋለሁ ። ሆቴሌቹን እንዲ ይዙ የምትልካቸው ሰዎች ወደ እኔ እንዲመጡ ንገራቸው ። ብዙ የሚ ሠራ ነገር አለ ። ዳየርም ፕሮግራሙን ። በአስቸኳይ ነው እሚፈልገው ።"

ማሲንግሀም ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለ እንዲህ አለኝ ።

"የአሜሪካን ኤክስፕሬስ ሰዎች ለምን አስቸጋሪ ሰው ነው እንዳሉ አሁን ነው የገባኝ ፡

"ጥሩ ትዕዛዝ ነው ስታየው ይስማማሰልሀ"

"እሺ ፕሮግራሙን ነገ ጠዋት እንዲደርስህ አደርጋለሁ" ብሎ ስልኩን ዘጋው ።

ሳን ሳልኀዶር ላለው ወኪላችን ደወልኩ ። ሁሉንም እዘጋ ተው እንደሚጠብቁኝ ፡ ቃል ገቡልኝ ።

ከምሽቱ አንድ ሰዓት ከአርባ ደቂቃ ሲሆን ነው ከቢሮዬ ወጥቼ አልሰንን እንኳን ደህና መጣህ ልለው የቻልኩት ። ስጨበጠው ፈገግ ብሎ

"ክሌይ እንደገና ላይህ በመቻሌ በጣም ነው ደስ ያለኝ" አለኝ ። "ስንት ዓመት ሆነን ? ስድስት ሣይሆን ይቀራል ?"

"እንደዚያ ይሆናል ። ምን አዘጋጅተሀል ? ዛሬ ማታ የት ላድር ነው ?"

ኦልሰን ዞር ብሎ ፀሐፊዬን ተመለከተና ፡

"ያቺ አስደናቂ ልጅ በቢስካይን ጐዳና የቤት እቃው የተሟላ አፓርታማ አግኝታልኛለች" አለኝ

"ያ ማ እኔ እምኖርበት አካባቢ ነው ። ኦልሰን እጠረጴዛዬ ላይ የተባታተኑትን ወረቀቶች ላስተካክልና ወደ እኔ አፓርታማ ሄደን እራታችንን በልተን ትንሽ እንጐነጫለን ። ከባለቤቴ ከሮዳ ጋርም ላስተዋውቅህ እፈልጋለሁ ።"

"መልካም እኔም የምጨረሳቸው አንድ ሁለት ጉዳዮች አሉኝ ። ከዚያ ለመሄድ ዝግጁ ነኝ"

እንግዶች ሲኖሩን ሮዳ ንቁ ነው እምትሆነው ። ከኦልሰን ጋር በቀላሉ ተግባቡ ። በውበቷና በአለባበሷ እንደተደነቀ ይታየኛል የምን ጠጣውን ማርቲኒ እየቀየጥኩ መጥፎ ሀሳብ መጣብኝ ። በሳምንቱ መጨረሻ ላይ ሳትኳኳል ፀጉሯ ተንጨፍርሮ አሮጌ ጂንስና ሸሚዝ ለብሳ አፓርታማው ውስጥ ስትንገላወድ ቢያይ ምን ያህል በደነገጠ?

መጠጡን ስቀዳ ነው ኦልሰን ሆን ብሎ "ሥራዋን ለቃ ትታን ከሄደች ወዲህ ቫልን አይተሀት ታውቃለህ ?"ብሎ የጠየቀኝ ።

መጠጡ እጠረጴዛው ላይ ፈሰሰብኝ ። ቀና ብዬ ሳላየው "አይ ቻት አላውቅም የሰማሁትም ነገር የለ" አልኩት ።

ሮዳ ከአቾሎኒዎቹ ዘገን አደረገችና ፡

"ማነች ቫል ?" ብላ ጠየቀች በጉጉት ።

ኦልሰን ፈገግ አለ ።

"ባልሽ ስለ ቫል ዳርት አጫውቶኝ አያውቅም ማለትሽ ነው ?"

"ለኔ ምንም አይነግረኝ ።" አለችና ሮዳ ከንፈሯን እሞጥሙጣ ያቀረቡኩላትን ብርጭቆ ወሰደች ።

"ይህን ያህል ምን የተለየ ነገር አላት ?"



"የምልሽን ሁሉ ስለማትሰሚኝ ነው ምንም ነገር የማልነግርሽ መስሎ የሚታይሽ" አልኳት ሮዳን ለኦልሰን መጠጡን እየሰጠሁ

"ስለሷ አጫውቼሻለሁ እንዳትለኝ ። ምክንያቱም ምንም ነገር እንስተሀብኝ እንደማታውቅ ፡ እርግጠኛ ነኝ" አለቺን ቆጣ ብላ ።

"ባወራልሽም ምንም ስሜት አይሰጥሽም ነበር ቦስተን ውስጥ በምሠራበት ጊዜ ፀሐፊዬ ነበረች ።" አልኩኝ ነገሩን በማቃለል ። ወዲያው ቀጠል አድርጌ ። "ለቢል ጤንነት" ብዬ ብርጭቆየን አነሳሁ ።

ለጥቂት ጊዜ ዝም ብለን ጠጣን ።

"እንዴት አይነት ፀሐፊ ነበረች ?ተወዳዳሪ የሌላት ፡ስህተት የማትሠራ አስደናቂ ፡ ልጅ ነበረች በህይወቴ እንደሷ ካለ ሠራተኛ ጋር ሠርቼ አላውቅም" አለ ኦልሰን ። አባባሉ ሮዳን ሲቀፋት አየሁ ። እሷ ፊት ሌላ ሴት የሚያመሰግን ወንድ ጠላቷ ነው ።

እኔን እኔን እየተመለከተች "ወዳችሁአታል ማለት ነው ። ሥህ ተት አለመሥራቷ ሁለተኛ ጉዳይ ነው" አለች ።

"ይመስልሻል ?" ብያት ተነስቼ ወደ መስኮቱ ተጠጋሁና ። በፊት ለፊት ያለውን ቦይ ፡ ቁልቁል ተመለከትኩ ። እርግጥ ወድጃታ ለሁ ። አሁንም እወዳታለሁ ።

"በርዳን ለምን እንዳገባኝ በርግጥ አላውቅም ።" አለች ሮዳ ለኦልሰን ። በሥራዬ ደካማ እንደሆንኩ ሁሌ ይነግረኛል ። ጠዋት ማታ ይጨቀጭቀኛል ። ጐበዟንና አስደናቂዋን ፡ ቫልን አለማግባቱ የሚ ያሳዝን ነው ።"

ስላቅ የተሞላበት አነጋገሯ ኦልሰንን አስጨነቀው ።

"አንቺ ደካማ አትመስልኝም" አለ ። ኦልሰን ግራ እየተጋባ ። ልረዳው አልፈለግሁም ። ከጥቂት ደቂቃ ዝምታ በኋላ ።

"ሥህተት ላለመሥራት ማን ይጨነቃል" አለች ። ሮዳ"አስልቺ ነገር መስሎ ነው እሚታየኝ ። አንድ ሠራተኛ ቀጥረን ማሠራት ስን ችል ለምን የቤት ሥራ እንሠራለን ። በመስኮቱ መመልከትህን ስታ በቃ መጠጡን ብትቀዳልን ?" ስትለኝ ትከሻዬን ነቀነቅሁ ።

ኦልሰን እየጨነቀው "ማንኛውንም ሥራ የሚያከናውነው ማሲ ንግሀም ነው ። የኔ ሥራ አቤቱታዎችን ማዳመጥ ነበር ።" አለ ።

ዞር ብዬ ሮዳን ተመለከትኳት አባባሉ አንድ ነገር አስታወሰኝ "ሮዳ በሚመጣው ሳምንት ለስድስት ቀናት አለ ባል ልትቀሪ ነው" አልኳት ።

"ምን ማለትህ ነው ?"

ወደ ሳን ሳልቫዶር ስለሚደረገው ጉዞ ነገርኳት ። እንደከፋት ይታያል ። ከተጋባን ጀምሮ ለተወሰነ ጊዜ ስንለያይ ይሄ የመጀመሪያ ጊዜ ያችን ነው ።

"እኔስ" ጮኸች ። "ወደ መሥሪያቤት በምን ልመላለስ ነው ?"

"አውቶቡስ እንደልብ ነው ።"

"አውቶቡስ ? እንደዚያ በሚሸቱ አውቶቡሶች ማን ይሄዳል ?"

"እኔ ባደርስሽ ደስ ይለኛል" አለ አልሰን "ምንም አያስቸግረኝ" ፈገግ ብላ ተመለከተችው ።

"በርደን ለኔ አስቦልኝ አያውቅም" አመሰግናለሁ ቢል ። ቢል ብዬ ልጠራህ እችል የለ ? አንተም ሮዳ ብለህ ጥራኝ" አለችው ።

"መልካም"

ከዚህ በኋላ በኔ ላይ ስትነሳብኝ አላስደነቀኝም

"እና ከዚያች ከቪዳል ባልቴት ጋር ልትሄድ ነዋ ! በቀላሉ ወደ አልጋዋ ልትጐትትህ የምትሞክር አይነት ሴት ነች ።"

ምንም ነገር ብትናገረኝ ለሮዳ ትግስቴ አልቆ አያውቅም ነበር ። ዛሬ ግን አጥብቄ ፡ ራሴን መቆጣጠር ነበረብኝ ።

"አባክሽ ይህን የማይረባ ነገር እርሺው ። ሥራ ለመሥራት ነው እምሄደው ። የሚያስጨንቅሽ ነገር ያለ አይመስለኝም ።"

"እኔ እዚያ መደብር ውስጥ እየለፋሁ መዋሌን ስታስበው ደስ እንደሚልህ ተስፋ ፡አለኝ ።"

ለራቤ በደንብ እምትሠሪበት ቀን በመጣ አልኩና ግራ ተጋብቶና ተጨንቆ ወደ ተቀመጠው አልሰን ዞር ብዬ" የራበህ ይመስለኛል አልኩት ።"

"ይመስለኛል ። እንብላ ካልክ . . . "



"ሮዳስ ተዘጋጅተሻል ?"

"አልተዘጋጀሁም" ብላ በቁጣ ተነስታ ወደ መኝታ ክፍል ገብታ በሩን በሀይል ዘጋችው

እኔና አልሰን ተያየን ።

"ሴቶች" አልኩና ፈገግ አልኩ

"አዎ" አለኝ እሱም ። ለጥቂት ጊዜ ፀጥ ብለን ተቀምጠን ።

"ጥሩ ቤት ነው ያላችሁ ብሎ ወደ ሰገነቱ ሄደ ። ደስ እሚል እይታም አለው" አለኝ

"እውነትህን ነው ።"

ነገሩን ለመቀየር በመፈለግ ፡

"ይሄ ቪዳል የምትሉት ሰው ፡ አስገራሚ ነው እባክህ" አለኝ አልሰን ።

"አስገራሚ ልትለው ትችል ይሆን ? እርግጥ ብዙ ነገሮች አሉበት ።"

"ከአምስት አመት በፊት ብዙም ሀብት አልነበረው ። ሂልተን ሆቴል በሚሠራበት ጊዜ ደንበኛዬ ነበር ያኔ የቁጠባ ክፍሎችን ነበር የሚያዘው ።

ከኛ ጋር የባንክ ሂሣብ መክፈት ፈልጐ ነበር ። የነበረበት ዱቤ ከፍተኛ ስለነበረ ልንቀበለው አልቻልንም" ሲለኝ ቀና ብዬ ተመለከትኩት ።

"ማሲንግሀም ይህንን እንዴት አላወቀም ?"

"ጉዳዩን ወደ ኒውዮርክ ያስተላለፍኩት አይመስለኝም ። ብድር ገማቾቹን ጠየቅሁና አይሆንም ሲሉኝ ተወኩት ።"

"ታዲያ ማሲንግሀም እኮ ብድር ገማቾቹን ጠይቋል" ስለው አልሰን ሳቀብኝ ።

"እኔ የማወራልህ ከአምስት አመት በፊት የሆነውን ነው ። በአምስት አመት ውስጥ ፡ ስንት ነገር ይፈጸማል ? ያኔ ያልተቀበል ነው መሆኑን ለማሲንግሀም መንገር አስፈላጊ መስሎ ላይታያቸው ይችላል ።"

"ልክ ነህ ። እና ከቪዳል ጋር ትተዋወቃላችኋ? ። በሚቀጥለው ሣምንት እኔም እድል ገጥሞኝ ሳልተዋወቀው አልቀርም ። ለመሆኑ ምን ይመስላል ?"

"ኳስ የመሰለ ድቡልቡል ፍጡር ነው ። ድንክ ሊሆን ምንም አይቀረው ። ከአምስት ጫማ በታች ነው ። እንደአጫጭር ሰዎች ሁሉ ቁጡ ነው ። ራስ በራ ሆኖ ጺሙን ያሳድጋል ። እሳት የሆነ ሰው ነው ። የሱን አይነት ሰዎች ታውቃለህ ። ሲናገር እጆቹን ያወናጭፋል ። አይኖቹ ያፍዝ ያደንግዝ አለባቸው ። እኔ ሳውቀው በትንሽ ነገር ተነስቶ አገሩን ነው እሚበጠብጠው ። ወደ ኒውዮርክ ለመሄድ ትኬት ሲያስቆርጥ ያየኸው እንደሆነ ወደ ጨረቃ ለመጓዝ ፡ የሚጣደፍ ነው እሚማስል ህ ። ከዚያ ወዲህ ግን በጣም የተለወጠ ይመስለኛል ። በሚሊዮን የሚቆጠር ብር እንዳለው ነው እሚወራው ። ያን ያህል ሲኖርህ ደግሞ ማንነትህን ፡ ለማሳወቅ መጣር አያስፈልግህም ። ሁሉንም ነገር ለእሽከሮችህ ትተዋለህ ።"

"ምን ያህል ልክ እንደሆንክ ታውቃለህ" ብዬ ስለ ዳየር አጫወትኩት ።

ሮዳ ከመኝታ ክፍል ወጣች ። አሁንም ቅር እንዳላት ነው ።

"እንበላለን ወይስ አንበላም ?" ጠየቀች "እኔ እርቦኛል ።"

"አንቺን እኮ እየጠበቅን ነው ። የኔ ሸጋ" አልኳት ።

"መልኪም ግን በእግዚአብሔር ብላችሁ ለለውጥ ያህል ሌላ ጥሩ ቦታ ሄደን እንብላ ። እዚህ ያለው ቡና ቤት ሰልችት ብሎኛል ፡" ብላ ራመድ ራመድ እያለች ወጣች ። እኔና አልሰንም ተጠቃቀስንና ተከትለናት ወጣን ።

* * *

ሮዳ በንንግር እኔን ስታሸንፍ የምትደሰተውን ያህል ተደስታ ጨኝ አታውቅም ። ታሸንፍኛለች ። አንዳንዴ ግን ደንታ ቢስ እነጋገሯ ሲያበሳጨኝ ፡ እቃወማታለሁ ። ማንኛውንም አይነት ነቀፋ ትጠላለች ። እናም እኔን ማሸነፏ ነው ለሷ ትልቁ ድል ።

በቫል ላይ ያለኝን አመለካከት በግምት ስለደረሰችበት አጋጣሚ ፈልጋ የሷን ስም በማንሳት ልታናድደኝ ትሞክራለች ።



አልሰንን እቤቱ አድርሰን ከተመለስን በኋላ የጠጣንባቸውን ብርጭቆችና ጠርሙሶች ፡ ከጠረጴዛ ላይ ሳነሳሳ ሮዳ በአጠገቤ አለፈችና በሸሚዟ ኦቾሎኒ የያዘውን ሣህን ጐትታ ጣለችው ። ኦቾሎኒዎቹ እምንጣፍ ላይ ተበተኑ ።

እራት ስንበላም ብዙ አስቸግራኝ ስለነበር ወዲያው ተቆጣሁ ።

"ያደረግሽውን ተመልከቺ ለምን ተጠንቅቀሽ አትራመጂም ?" አልኳት ፡ ቆጣ ብዬ ።

"ምንጣፉን ታበላሺዋለሽ ።"

"ተነጫነጭ" አለቺኝ ። በድርጊቷ የተናደደች መሆኑ ይታያል ።

"ያንተ ጠንቃቃዋና እስደናቂዋ ቫል ብትሆን እንዲህ አታደርግም ነበር ። አይደል ?" ያለቺኝን ውጩ ዝም ብያት ቢሆን ኖሮ ፡ ቫልን እንሥታ ልታናድደኝ አለመቻሏን ባሳወቅኋት ነበር ። ግን አልቻልኩም ።

"እባክሽ ዝም በይ !" አልኳት በቁጣ

"ለምን የምትሄጂበትን እያየሽ አትራመጂም ?"

ፈገግ ብላ ተመለከተችኝና ወደ መኝታ ክፍሉ ገባች ።

ያለፉት አራት ቀናት በጣም አድካሚ ነበሩ ። ከመሄዴ በፊት እጠረጴዛዬ ላይ ፡ ያሉትን ወረቀቶች ፈር ማስያዝ ነበረብኝ ። በዚያ ላይ ዳየር ስለፕሮግራሙ በየሰዓቱ እየደወለ የማይረቡ ጥያቄዎችን እያነሳ እረፍት ይነሳኝ ነበር ። በዚህ ሁሉ ላይ የሮዳ ጉንተላ ሲታከልበት ከቁጥጥሬ ውጪ ወጣ ።

እመታጠቢያ ክፍል ውስጥ አንድ ነገር ትደፋና ልወለው ለመስነሳ ያዘነች በመምሰል እና በማሾፍ "እንደ እስደናቂዋ ቫል ለመሆን መጣር አለብኝ" ትላለች ።

ተጋድማ አርፍዳ የቡና ሰዓታችን ሲያልፍ ።

"ፍፁሟ ቫል አስጠብቃህ እንደማታውቅ እርግጠኛ ነኝ" ትለኛለች ።

የቫልን ስም ባነሳችብኝ ቁጥር በጣም እቆስላለሁ ። ትተወኛለች በሚል ጉንተላዎቸን ጥርሴን ነክሼ ቻልኳትቸው ።

ከሷ ተለይቼ የምቆይባቸውን አምስት ቀናት በጉጉት እጠብቅ ጀመር ።እዚያ ቆይቼ ስመለስ ቫልን ትረሳት ይሆናል ።

ሰኞ ማታ አልሰንን ራት ልንጋብዘው ይዘነው ወጣን ። ሮዳ ደስ ብሏት ነበር ። ደስ የሚል ምሽት አሳለፍን ። ግን አልሰንን አፓርተማው አድርሰን ከተመለስን በኋላ ሮዳ እወንበሩ ላይ ዘርፈጥ አለችና ሲጋራ ለኩሳ ፤

"በርደን እንጣጣ እባክህ ? በደንብ እንጠጣ" ብላ አስደነገጠችኝ ።

"ውስኪ ይሁን ?" አልኳት

"ይሁን" ።

መጠጡን አዘጋጅቼ ከፊት ለፊቷ ተቀመጥኩ ፤

"ንገረኝ በርደን ቫል ወዳጅህ ነበረች ?"

እጇ ሲንቀጠቀጥ እብርጭቆው ውስጥ የነበረው በረዶ ተፈናጥሮ እምንጣፉ ላይ ወደቀ ። ሮዳ ሳቀችብኝ ።

በረዶዎቹን ሰበሰብኩና ወደ ማድቤት ወሰድኳቸው ።

ጥቂት ቆም ብዬ ራሴን አረጋጋሁ ። ከዚያ ተመልሼ ገባሁ ። ሮዳ ትኩር ብላ ትመለከተኛለች ፤

"ወዳጅህ ነበረች ?" ደግማ ጠየቀችኝ ።

"በጭራሽ ። አዳምጪኝ ሮዳ ይሄ ነገር ስልችቶኛል ። ገባሽ ? ከዛሬ ጀምሮ ቫልን እንዳታነሺብኝ አልፈልግም ። ምን እንደፈለግሽ አልገባኝም ።ቀልድ መስሎ ታይቶሽ ይሆናል ። እኔ ግን እንደዚያ አላየውም !" አልኳት ቆጣ ብዬ ።

መጠጧን እየጠጣች በብርጭቆው ከንፈር ላይ ተመለከተችኝ ።

"ታስብላታለህ አይደል ?" አለችና ሳቀች ።

"አሁንም የምትወዳት ይመስለኛል"

"ይሄን የማይረባ ነገርሽን አቁሚ ። ድርቁናሽን ነው እምታሳይው !" ስላት ፊቷ ደም መሠለ ።

"አትክደውም አይደል ።"



"ምንም የምክደው ነገር የለም ። መጠጥሽን ጨርሺና እንተኛ ፡"

"ከጥላቢሷ የቪዳል ባለቤት ጋር አምስት ቀን ስታሳልፍ ትድን ይሆናል" አለች ጥላቻ በተመላበት ሁኔታ "በቀላሉ እንድትወዳት ልታደርግህ የምትችል ሴት ነች ፡"

መጠጡን ትቼ እመኝታ ክፍላችን ገባሁ ። በጣም ከመናደዴ የተነሳ ጥያት ባልሄድ በጥፊ ሳላጠናግራት አልቀርም ነበር ። እሷም ያበዛችው መሆኑ ተሰምቷታል ። እመታጠቢያው ክፍል እስከምገባ ድረስ አልመጣችም ። ታጥቤ ስመለስ ተኝታ አገኘሃት ።

"እየቀለድሁብህ ነበር እኮ በርደን ። ቀልድ አታውቅም እንዴ" አለችኝ ጥርጣሬ በተሞላበት አነጋገር ፤

"ጥርስሽን አላፀዳሺውም" አልኳት ቆጣ ብዬ "ቶሎ ብታፀጂው ይሻላል መተኛት እፈልጋለሁ"

"አንተም ጥርሱም ገደል ግቡ" ብላ ጀርባዋን ሰጥታኝ መብራቱን አጥፍታ ተኛች ።

# ሦ ስ ት

እሳንሳልቫዶር አውሮፕላን ማረፊያ እንደደረስኩ ሮቤርቶ ሪቬራ የተባለው ሰው ተቀበለኝ ፡ ሮበርቶ ደልዳላ ሰውነት ያለው ቀይ ሀንድ ነው ። እፊቱ ላይ ጉልቶ የሚታይ ሪዝ አለው ። እንደ አብዛኞቹ የላቲን አሜሪካ ሰዎች ጮሌ አይኖቹ በሽንግላ ፈገግታ የተሞላ ናቸው ።

"እንኳን ደህና መጡ ሲኞር ከሌይ በርደን" አለኝ የስሌን ባር ጣውን ከፍ አድርጎ እየጨበጠኝ ።

"ሁሉም ነገር ተዘጋጅቷል ። ሲኞር ቪዳልንና ባለቤታቸውን በተባለው መሠረት ፡ አግኝቻቸዋለሁ ። ምንም ችግር የለም ። በፈለጉኝ ጊዜ ያገኙኛል ። አሁን ወደ ሆቴል እንዳደርስዎ ይፈልጋሉ ?" አለኝ

"አዎ ። እሩቅ ነው እንዴ ?"

"እርቀት የለውም ።ትንሽ ቢርቅ ነው ።ቆንጆዋ መኪና ይቺ ናት ፡ የአየር መቆጣጠሪያ አላት ። በቂ ምቾትና ከፍተኛ ዋጋም አላት" ብሎ እፀሐይ ላይ ወደ ቆመችው አቧራ ፡ የነፋባት ማርቼዲስ መኪና ወሰደኝ ። የኋላውን በር ከፍቶ ባርኔጣውን ከፍ አደረገና እንድ ገባ ጋበዘኝ ።

ቀዝቀዝ አለችው መኪና ውስጥ ስገባ ደስ አለኝ ።የፀሐዩ ሙቀት በጣም ከፍተኛ ፡ነበር ።ከፊት ገብቶ ተቀመጠና ።

"ይቅር ይበሉኝ ስለ እንግሊዘኛዬ ። ሲኞር በርደን እናገራለሁ ፡ ጥሩ አሜሪካንኛ ። ግን እንግሊዘኛ በጣም ከባድ ነው ።"

"ይገባኛል አልኩት ።"

ከአውሮፕላን ማረፊያው ወጥቶ አቧራማ በሆነው መንገድ ላይ ከነፈ ። በመንገዱ ዳርዳር በጭንቅላታቸው በእጃቸውና በትከሻቸው ቀያይ ማሠሮ የተሸከሙ ገበሬዎች ይታያሉ ።

"ምንድ ነው የተሸከሙት ?" ብዬ ጠቅሁት ፡

"ውሀ ነው ሲኞር በርደን ። ውሀ ችግር ነው ። እዚህ ሁሉም ውሀ ይሸከማል ። ኑሮአችን እንደዚህ ነው ።" አንድ ቀይ ህንዳዊ ገበሬ ጥልቅ ሲልበት ከላከሱን አስጮኸው ።

"ደደቦች ናቸው ። ፀሐይ ደደብ አድርጓቸዋል ።" ብሎ በወርቅ ጥርሶች የተሞላ አፉን ከፍቶ ሳቀ ።

"ቆንጆ የጉዞ ፕሮግራም ነው ያወጣሁልዎ ። የሲኞር ቪዳል ባለቤት በጣም ደስ እንደሚላቸው ተስፋ አለኝ ።" አለኝና በሸርደዳ ዮር ብሎ ተመለከተኝ ።

"እዚህ ብዙ ድሆች ይኖራሉ ፡" ብሎ ራሱን በሀዘን ነቀነቀ ።

"ብዙ ብዙ ሀብታሞችም ። ከሀብታሞች ድሆች ይበዛሉ ። ግን ሀብታሞቹ በጣም ሀብታም ናቸው ።"

ቀይ ህንዶች በብዛት በሚታዩበት ትንሽ መንደር መሀከል አለፍን ። አብዛኞቹ የተበጣጠሰ የስሌን ባርኔጣና ነጭ ሸሚዝ እንዲሁም የተጨማደደ ሱሪዎችን ለብሰዋል ።ሴቶቹ በጥጥ ልብሳቸው ላይ የተለያየ ቀለም ያለው ጨርቅ ጣል አድርገዋል ። የመንደሩ ዋና መንገድ በፍራፍሬ ልጣጮች ፡ በሲጋራ ቁራጭና በሌላ ቆሻሻ የተሞላ ነው ። በደንብ ስመለከተው ደስታዬን ቀነሰው ።

ሳንሳልቫዶር ለመድረስ ከግማሽ ሰዓት በላይ ወሰደብን ። ሳንሳልቫዶር የኤልሳልቫዶር ዋና ከተማ ናት ። እንደሌሎች ቦታዎች ብዙ ቀይ ህንዶች ይታዩባታል ። በደንብ የለበሱና ወዛቸው ያማረ የከተማው ሀብታሞችም በብዛት ይታያሉ ።

"ቆንጆ ከተማ ነች" አለ ሮቤርቶ ። "ወደዷት ሲኞር በርደን ?"

"እንዴታ ፡"

"ሮቤርቶ ብለው ይጥሩኝ ሁሉም ሮቤርቶ ብሎ ነው እሚጠራኝ ። እዚህ የታወቅሁ አስጐብኚ ነኝ ። ብዙ ሀብታም አሜሪካኖች እኔን ይመርጣሉ ።"

"መልካም ነው ።"

"እሆቴሉ እየደረስን ነው" ብሎ አቀበት ያለውን መንገድ ይዞ ወደ ግራው ታጠፈ

"ቆንጆ ሆቴል ነው ሲኞር በርደን ። ተወዳዳሪ የለውም ። ሁሉም



በሆቴሉ ይረካሉ" ዘበኛው የመኪናውን በር ከፈተልኝና ወጣሁ ። ሌላው ሠራተኛ ሻንጣዎቼን ወደ ሆቴሉ ይዞ ገባ

"ወደ ሆቴሉ ብገባ ይሻላል ። ሮቤርቶ ያዘጋጀውን ፕሮግራም አይቼ ለሚስተር ቪዳል ማሳወቅ አለብኝ ፡" አልኩት ።

"ምንም የሚያስቸኩል ነገር የለም ሲኞር በርደን ። ሲኞር ቪዳልና ባለቤታቸው ከጓዳ ኞቻቸው ጋር ምሳ ሊበሉ ሄደዋል ።ከኔ ጋር የሚሠራው ጆስ ነው ወደ ኤል ኩኮ የወሰዳቸው ። እባህር ዳር ያለ ውብ ቦታ ነው ።

"ብዙ የቡና እርሻ ያለውን ሲኞር ጉዝማንን ሊጠይቁ ነው የሄዱት ። ሀብታም ነው ። በቶሎ የሚመለሱ አይመስለኝም ፡" አለኝ ።

ሰዓቴን ተመለከትኩ ገና እኩል ቀን ነው ።

"እሺ ሮቤርቶ" ምሳዬን እዚሁ እበላለሁ ። ወደ ስምንት ሰዓት ገደማ ብንገናኝስ" ስለው ፡

"ወደ ቤት እሄዳለሁ ማለት ነዋ" አለና በደስታ ፈነደቀ ። "ጥሩ ቤት አለኝ ። ደሀ ግን ጥሩ ። ልጆቼ አዘውትረው አያዩኝም ። ዛሬ ሲያዩኝ ተደንቀውም አያባሩ" ብሎ ባርኔጣውን ፡ አውልቆ ጨበጠውና እማርቼዲሷ ውስጥ ገባ ።

እመኝታ ክፍሌ ገብቼ ሁሉም ነገር እንደተባለው ያለ መሆኑን ካረጋገጥኩ በኋላ ገላየን ታጥቤ ልብሴን ቀያይሬ ምሳዬን ለመብላት ወደ ቡና ቤቱ ወረድኩ ። ምሳዬን ከበላሁ በኋላ ። እበረንዳው ላይ ተቀምጨ ቡና ጠጣሁ ። ከፊት ለፊቴ የመዋኛ ገንዳ ይታየኛል ። ትንንሽ ልጆች እየተንጫጩ ይዋኛሉ ። ወላጆቻቸው ከፀሐይ መጠለያ ጃንጥላው ሥር ተቀምጠው ቢራ ይጠጣሉ ።

ስምንት ሰዓት ገደማ ወደ እንግዳ ማረፊያው ስመለስ ሮቤርቶን ሲጠብቀኝ አገኘሁት

"ሲኞር በርደን ምግቡ ጥሩ አይደል ?ሁሉም ነገር ጥሩ ነው ። ክፍሉም ቆንጆ ነው" አለኝ ።

"ሁሉም ነገር ጥሩ ነው ።ፕሮግራሙን እንመልከተው?" አብረን ተመልክተነው ። እገሪቱን አለማወቁ ምንም አላስቸገረኝም ሮቤርቶም መታየት የሚገባቸውን ነገሮች ሁሉ እንዳልተወ አረጋገጠልኝ ።

Zone 4 Public Library

"ይሞቃል ከሰዓት በኋላ፣ ጠዋት መጓዝ ይሻላል ሲኞር በርደን ። ቀዝቀዝ ሲል ደግሞ ሌላ ነገር ማድረግ ይሻላል ። ከምሳ በኋላ ጋደም ብሎ ትንሽ እረፍት ማድረግ ጥሩ ነው፤" ቤሎ በንጉ አይኖቹ ተመለከተኝ ።

"ያ የሚስተር ቪዳል ባለቤት በምትፈልገው ነገር ነው የሚወሰነው ። መተኛት አትፈልግ ይሆናል፤" ስለው ዝም አለ ።

"እርሶ ያስረዳቸው ሲኞር በርደን ። ከሰዓት በኋላ በጣም ሞቃትና አድካሚ ነው"

"እስቲ እምትለውን እናያለን፤ነገ ጠዋት ልክ በሁለት ሰዓት ተኩል እዚህ እንድትገኝ ። መኪናዋም ታጥባ መወልወል ይኖርባታል ። ሮቤርቶ የምናስተናግዳቸው፤ትልልቅ ሰዎች፣ ናቸው ። መኪናዋ በዚህ ሁኔታ ለነሱ የምትሆን አይደለችም ።"

"ካሉን መኪናዎች ሁሉ የምትሻለዋ ይቺ ናት ። እጥቤ እወለውላታለሁ ።" አለ ። የባሰ ቅር አለው

"እና ነገ እንገናኝ" ብሎ ተነስቶ ወጣ ።

ሲሄድልኝ ወደ ኪዮስኩ ሄጄ የኤልሳልቫዶርን ካርታ ገዛሁ። ከዚያ ወደክፍሉ ገብቼ የመዋኛ ልብሶቼን ይዤ ወደ መዋኛ ገንዳው ሄድኩ ። አንዴ ከዋኘሁ በኋላ እጥላ ሥር ተቀምጨ ፕሮግራሙንና ካርታውን ተመለከትኩ ።ነገ የኢዝኮላን እተሳ ገሞራ ከጉበኘን በኋላ ለምሳ፣ ወደ ሆቴላችን እንመለሳመለን ከሰዓት በኋላ ምን እንደምንጎበኝ አልተጠቀሰም ። የከሰዓት በኋላ ውን ጉዳይ ከሚስስ ቪዳል ጋር መወያየት ይኖርብኛል ።

እስኪ ደከመኝ ዋኝቼ ሳበቃ ወደ አሥር ሰዓት ገደማ ወደ ክፍሌ ተመልሼ ጺሜን ተላጨሁ ። ቀለል ያለ ልብስ ለብሼ ወደ ቡና ቤቱ ወረድኩ ።

ጋዜጣ እያነበብኩ ውስኪዬን ስጠጣ ከአንድ ሰዓት በኋላ ሄንሪ ቪዳል እየተጣደፈ፣ ወደ ቡና ቤቱ ገባ ።

ሚስተር ቪዳል ምን አይነት ሰው እንደሆን ከቢል እልሰን ብሰማም ። በእርግጃ ወደኔ የሚመጣው ሰው በቀላሉ ሊገልፅ የሚቻል አይነት አይደለም ።

ኦልሰን እንዳለው ቪዳል ከአራት ጫማ በላይ ከፍ የሚል አይመስልም ። ትከሻው እንደ በቅሰኛ ትከሻ ሰፊ ነው ።



አጫጭር እግሮቹ መሬቷን በሙሉ ልብ ነው እሚረግጡ ። ዕጌረዳ የመሰለ ሸሚዝና ጥቁር ሙሉ ልብሱ ለብሷል ።

ሸበት ጣልጣል ያለበት ፀጉሩ ረጅም ነው ። እስከመሀል አናቱ መላጣ ነው ። መላጣነቱ የፊቱን ርዝመት አጉልቶ ያሳያል ። እየሸበተ ያለው ጺሙም ጥቅጥቅ ብሎ በጣም አድጓል ። ከሁሉም አሥረው የያዙኝ የሚያንፀባርቁት ትናንሽ አይኖቹ ናቸው ።ቁጡነቱን በራስ መተማመኑንና ሀይሉን ያሳያሉ ።

አጠገቤ ሲደርስ ከመቀመጫዬ ተነሳሁ ።

"ክሌይ በርደን መሆን አለብህ ? እራስህ ነህ ።" ድምፁ ከፍሉን ሞላው ። የሚያቃጭል፣ ድምፅ ነው ። አጥንት ሊሠብር በሚችል ሀይል ጨበጠኝ ።

እስተናጋጁ መጥቶ እፊቱ ቆመ ።

"ከፍራፍሬ የተሰራ ፓንች አምጣልኝ ። ልብ አርግ ጥሩ አድርግህ ሥራው ። ማታ የጠጣሁት ጥሩ አልነበረም" ብሎ ወደ እኔ ዞር አለ ።

"እል ካል ጠጥቼ አላውቅም ። በጭራሽ እልሀለሁ ሲጋራና አልኮል ጭንቅላትህን ያበላሹታል ። ሥንራህ ትወደዋለህ ? ልትወደው ይገባል ። ካልወደድከው በደንብ ልታከናውነው አትችልም፣ እምነት የሚጣልብህ እንደሆንክ ሰምቻለሁ ። ይሄ ጥሩ ነው ። የምተማመንባቸው ሰዎች እንዲኖሩኝ እሻለሁ ።" እያለ በሚያንቧርቀው ድምፁ እንደመትረየስ ተንጣጣብኝ ።

"እኔ በሥራ በምጠመድበት ጊዜ ሚስቴን እድታዝናናት የመረጠህ ዳየር ነው ። በደንብ እንደምታዝናናት እርግጠኛ ነኝ ። ምን እንደሚያጋጥማት ብነግራትም ካንተ ጋር ካልሄድኩ ብላ ድርቅ አለች ። ሴቶች እንደዚህ ናቸው ። እንዴ ድርቅ ካሉ መመለሺያ የላቸውም" ብሎ ሳቀ ።

"ሳን ሳልቫዶር ጥሩ ከተማ አይደለም ። ስርዓት የለው፣ ድርጅት የለው፣ ቀይ ህንዶች እንድ ቀን እንደሚያምፁ ይታየኛል ።

ከአውሮፕላን ማረፊያው ስትመጣ ምን አይነት ኑሮ እንደሚኖሩ አይተሀል ።"

እስተናጋጁ ባንድ ዝርግ ሳህን የተሰባበረ በረዶና የፍራፍሬ ጭማቂውን ይዞ መጥቶ እፊቱ አቀረበለት ። ቪዳል የጭማቂውን ግማሽ

ባንድ ትንፋሽ ጨለጠው ። በደንብ አልሠራውም ብሎ ወደኔ ዞር
አለ ''

''ሚስስ ቪዳል ተኝታለች ። ደክሞኛል ። ደክሞኛል ነው እም
ትለው ። አባባሏ አይገባኝም ። አሁን እኔ ድካም የሚሉ ነገር አላው
ቅም ። የቃሉን ትርጉም እንኳ አላውቅም ። ሴቶች ሁሌ ወይ ራሳ
ቸውን ያማቸዋል ወይም ይደክማቸዋል አግብተሀል እንዴ ? እንዳገባሀ
ይታየኛል ። ሀላፊነት ያለብህ ነው እምትመስለው ። ሀላፊነት ለማይሰማው
ሰው ደንታ የለኝም ። ያንተም ሚስት ደከመኝ እንደምትል እርግጠኛ
ነኝ ። ሁሉም ይደክማቸዋል ዘዴ ያሉት ይመስለኛል ።'' እንደገና
ስቆ ጭማቂውን ጠጥቶ ጨረሰ ።

ጥቂት ቆይቶ ድንገት ብድግ አለ ። ደንገጥ ብዬ አብሬው ስነሳ ።

''አትቸገር ቁጭ በል ። ነገ ምን ማድረግ እንዳለብህ አውቀኸ
ዋል ? እንዳወቅኸው እርግጠኛ ነኝ ። እንዲህ አይነቱ ከተማ ውስጥ
ብዙም የሚታይ ነገር ያለ አይመስለኝም ። ለማንኛውም ይሄ የራሷ
ጉዳይ ነው ። ጠዋት ታገኛታለህ ። እና በተቻለህ ሁሉ በደንብ አስተና
ግዳት ።'' አለና እጄን ጨፍልቆ ወጥቶ ሄደ ።

ተቀመጥኩና እብርጭቆው ውስጥ ያለውን ውስኪ ጨልጨ ሌላ
እንዲቀዳልኝ ለአስተናጋጁ ምልክት ሰጠሁት ። መጠጡ ያስፈልገ
ኛል ። አልስን ቪዳል ሀይለኛ ሰው እንደሆነ ነግሮኛል ። ግን ሀይለኛ
መባል ሲያንሰው ነው ። አንድ ምሽት ከሱ ጋር ባሳልፍ አንጐሌን
አዞሮ ፉዞ ነው እሚያደርገኝ ።

ስለሚስቱ አሰብኩና ገረመኝ ። ከሷም ጋር እንደዚሁ ይሆን፣
ከሆነ ችላው መኖሯ የሚያስደንቅ ነው ።

ደጐስጐስ ያለ አሜሪካዊ ቱሪስት ወደ ቡና ቤቱ ገብቶ ዙሪያ
ውን ቃኝቶ ሲያየኝ ወደኔ መጣ ።

''አብሬህ ብቀመጥ ቅር ይልሀል ?'' ብሎ ተቀመጠ ። ለአስተና
ጋጁ ምልክት ሰጠው ፡

''ለብቻ መጠጣት መጥፎ ልማድ እንደሆነ ሚስቴ ደጋግማ ነግ
ራኛለች'' አለና ፈገግ ብሎ ጠቀሰኝ ።

ጓደኛ በማግኘቴ ደስ አለኝ ። ከአንድ ሰዓት በላይ ለሚሆን ጊዜ
የሆነ ያልሆነውን ስናወራ ቆየንና ሰውየው ለመሄድ ተነሳ ፣



''ወይዘሮ እስካሁን ለባብሰው ሳይዘጋጁ አይቀሩም ። ሌላ ጊዜ እን
ገናኝ'' ብሎ ከቡና ቤቱ ወጣ ።

እራቴን በልቼ ምንም የምሠራው ነገር ስለሌለ መፅሐፍ ይገ
ጋደም ለማለት ወሰንኩ ። ወደ ኪዎስኩ ሄድኩና አንድ መፅሐፍ ገዛሁ ።
ዋጋውን እየከፈልሁ ሳለሁ ፣ ሄንሪ ቪዳል ከአሳንሰሩ ወጥቶ እየተንደ
ረደረ መጣ ። ከሀር የተሠራ ጥቁር ሙሉ ልብስና ነጭ ሸሚዝ ለብ
ሷል ። ደማቅ ሰማያዊ ከራባትም አስሯል ። አላየኝም ወጥቶ እደጅ
እሚጠብቀው ማርቼዲስ ውስጥ ገባ ።

ገርሞኝ ዞር ስል ሲኞር በርደን የሚል ድምፅ ሰማሁ ። ተላላኪ
ኪው ከመቀመጫው ተነስቶ ወደኔ መጣ ።

''አዎ እኔ ነኝ''

''መልእክት አለዎት ። እባክዎ አራተኛ ፎቅ ቁጥር ሰባት ክፍል
ድረስ ቢሄዱ።የሚስተር ቪዳል ባለቤት ሊያነጋግርዎ ይፈልጋሉ'' አለኝ

በመገረም ተመለከትኩት ፣

''የሚስተር ቪዳል ባለቤት ነው ያልከኝ?'' ስለው ራሱን በመ
ነቅነቅ አዎንታውን ገለፀልኝ ።

ገረመኝ ። አሳንሰሩ ውስጥ ገባሁና የቁጥር አራትን ቁልፍ ተጫ
ንኩ ። ሳጥኑ ይዞኝ ወደ ላይ ተንሳፈፈ ።ምሽቱን ካሰብኩት በተሻለ
መንገድ ላሳልፈው ይሆን ? ቪዳል ያገባትን ሴት ፣ለማየት በጣም
ጓጉቼ ነበር ።

በኮሪደሩ ውስጥ እየተራመድኩ እቁጥር ሰባት በር ላይ ስደርስ ቆም
ብዬ አመነታሁ ። ሳንኳኳ ''ግባ'' የሚል ድምጽ ሰማሁ ።

የሰማሁት ድምፅ ባማላውቀው ምክንያት ሆዴን አሸበረው ።

በሩን ከፍቼ በአበቦች ተሞልቶ ምቶቹ በአይን እሚታይ ክፍል
ውስጥ ገባሁ ። የአበቦቹ ብዛት የአበባ መሸጫ መደብር አስመስሎ
ታል ።

ረጅም ቀጠን ያለች ጥቁር ፀጉር ያላት ሴት ስስ ነጭ ቀሚስ
ለብሳ በመስኮቱ ወደ ውጩ እየተመለከተች ቆማለች ።

ለመጨረሻ ጊዜ ካየኋት ስድስት አመታት ቢያልፍም ገና
ሳያት ነው ያወቅኋት ። ልቤ በደስታ ደረቴን ረገጠው ። ከምንጊዜም

የበለጠ እራሷን ሆናለች ። ከምንጊዜውም የበለጠ አምሮባታል ፣ ግን እሷ ነች ።ፍቅሯ ለዘላለም ከኔ ጋር የሚኖረው ውዷ ነች ።

"ቫል" ብዬ ጮሁኩ በመገረም እየተመለከትኳት ።

"አንቺ ልትሆኚ አትቺይም ቫል!"

"ተገናኘን ውዱ በርደን" ብላ ወደ እኔ መጣችና እንገቴ ላይ ተጠመጠመች ።

* * *

አዲስ የወጣች ጨረቃ ደብዘዝ ያለ ውብ ብርሃኗን ወደ አል ጋው ሰዳለች ። ቫል አይኖቿን ከደን አድርጋ እጐኔ በጀርባዋ ጋደም ብላለች ። ዝም ብዬ ስመለከታት ማመን አልቻልኩም ። በህልም ውስጥ ያለሁ ነው የመሰለኝ ። ለብዙ አመታት እንዲህ አይነቱን ሁኔታ በህልሜ አይቼዋለሁ ።

ተቃቅፈን ስንሳሳም ነው ያለንበትን ቦታ ዘንግተን መጠንቀቅ የሚያስፈልገን መሆኑን የረሳነው ። ሳናውቀው ነው አልጋው ላይ ወጥ ተን የተገኘነው ።

ስመለከታት እስከ ዛሬ ተሰምቶኝ የማያውቅ ስሜት በሠራ አካሌ ተሠራጨ ፣ቅልል አለኝ ለሷ ያለኝ ። ፍቅር ምን ያህል ከፍተኛ እንደሆነም ተገነዘብኩ ።

በዚህ አይነት ከቆየን በኋላ አይኖቿን በመደፏ ጫን ጫን አደ ረገችና ፣ "ውድ በርደን አሁን ያደረግነው ምን ያህል አደገኛ እንደ ሆነ ታውቃለህ ፤ እንዲህ ማድረግ አልነበረብንም ። ባላገኝህ ይሻለኝ ነበር ። ሆነ ብዬ አውቄ ነው እንድንገናኝ ያደረግሁት ።

ምን ያህል የተቸገርኩ ይመስለሀል ? ወደ ፓራዳይዝ ከተማ መምጣ ትህን ስሰማ አላየውም ብዬ እርፌ ልቀመጥ አልቻልኩም ፤ ስንቱን አውርቼ ልጨርሰው ?" ብላ ድንገት ዞር ብላ የጠረጴዛውን ሰዓት ተመለከተች ።

"አሁን ተነሳ ። የምንጫወትባቸው አምስት ቀናት አሉን" አለች ።



"አሁን እንጫወት" አልኳት ። ባለፉት ስድስት አመታት ያጋ ጠማትን ነገሮች ለመስማት ጓጉቻለሁ ። ሰዓቱም ገና ነው ።

"አይሆንም ተነሳ" በድምጿ ውስጥ የተሳለፈልኝ ጭንቀቷ ከአልጋው ላይ ገፍትሮ አስነሳኝ ።

"ምን አይነት ሰው እንደሆነ አታውቅም የሆነውን ሁሉ ከጠረ ረጠረ ድራሽህን ነው እሚያጠፋህ ። ቂመኛና ክፉ ሰው ነው ። አንድ ነገር ለማድረግ ከወሰነ ወደ ኋላ የሚል አይነት አይደለም ። እስከመ ጨረሻው ይከታተልሀል ። እውነቴን ነው በርደን እመነኝ ።"

በድንጋጤና በመገረም ተመለከትኳት ።

"ስትወጣ ተጠንቀቅ ፣ እውጪ ማንም እንደሌለ አረጋግጠህ ውጣ" አለችኝ ።

ስሰናበታት ልስማት ጐንበስ ስል ገፋ አደረገችኝ ።

"እባክህ ቶሎ ውጣ ነገ እንነጋገራለን"

"ነገ በምን ጊዜ" አይኖቿ ላይ ያየሁት ፍርሀት እጥርጣሬ ውስጥ ጨመረኝ ።

"መቼ እንደምንጫወት አላውቅም ብቻ እንግዳ መቀበያው ጠብቀኝ ። እንደወጣ እመጣለሁ ።"

"አ ቫል እንዲህ መሆኑን ማመን አልቻልኩም እኔ.."

"እባክህ ሂድ ድንገት ቢመጣስ ?" ብላ ተንቀጠቀጠች ።

ወደ በሩ ተጠግቼ ከፈት አድርጌ ኮሪደሩን ተመለከትኩና በፍ ጥነት ወደ ኋላ ተመለከትኩ ። አንድ ወንድና ሴት ወደ እሳንሰሩ ሲያመሩ አየሁ ።

"ምንድነው ?" አለች በድንጋጤ ። ተነስታ ወደኔ እየመጣች ነበር ።

ዝም እንድትል በእጄ ምልክት ሠጠኋትና እንደገና ቀስ ብዬ ወደ ውጪ ተመለከትኩ ። የልቤ ድምታ ከኔ አልፎ ለሌላ ሰው ይሰማ ነበር ። ፍርሀቷ ተጋብቶብኛል ። ሁለቱ ሰዎች ፡ እሳንሰሩ ውስጥ ገቡ ። ወደኋላዬ ሳልመለከት ውልቅ ብዬ ወጣሁ ። በፍጥነት እየተራመ ድኩ ፣ በደረጃዎች ወረድኩና እሶስተኛው ፎቅ አለው ክፍሌ ውስጥ ገባሁ ።

ወዲያው እመታጠቢያው ክፍል ገባሁና በመስታወቱ ራሴን ተመለከትኩ ። የከንፈሯ ፡ቀለም ከንፈሮቼን አቅልቷቸዋል ። በድንጋጤ የገረጣውን ፊቴን ተመለከትኩት ። ልገልፀው የማልችለው ነገር ይታይበታል ።የወጣትነት ስሜት ነው ወይስ የሠራሁት ሀጢአት በፊቴ ላይ የሚነበበው ? ልለየው አልቻልኩም ።

ፊቴን በቀዝቃዛ ውሀ ታጥቤ ወደ መኝታ ክፍሌ ተመለስኩና ሰፊውን መስኮት ከፍቼ ፡ የምሽቱን ቀዝቃዛ አየር አስገባሁት ።

የምሽቱ አየር እርጥበት የለውም ። ሙልሙል የመሰለች ሙሉ ጨረቃ ከከተማው መብራት በላይ ደምቃ ትታያለች ። በሩቅ የዳንስ ሙዚቃና የሴት ሳቅ የሰማኛል ።

በሚንቀጠቀጡት እጆቼ ፓኬቱን ከኪሴ አውጥቼ ሲጋራ ለኮስኩና ጨረቃዋን እየተመለከትኩ ተቀመጥኩ ።

አሁን ቀዝቀዝ ብዬ ሳስበውና የቫልን ማስጠንቀቂያ ሳስታውስ እንደዚያ ማድረጌ እብደት መሆኑ ተሰማኝ ። ቫልም አብዳ ነበር ። ሁለታችንም ጥፋተኞች ነን ። እራሳችንን መቆጣጠር ተስኖን ነበር ማለት ነው ።

ያለችኝን አስታወስኩ "ምን ዓይነት ሰው እንደሆነ አታውቅም የሆነውን ሁሉ ከጠረጠረ ድራሽህን ነው እሚያጠፋው ። ቂመኛና ክፉ ሰው ነው" ከአነጋገሯ ይልቅ ፍርሀት የተመላበት ድምጿ ነበር የሠራ አካሌን በድንጋጤ ያንቀጠቀጠው ።ድሮ ሳውቃት ቫል በቀላሉ የምትፈራ ሰው አልነበረችም ። ቪዳልን እንዳየሁት ከሆነ አነጋገሯ በከንቱ እኔን ለማስፈራራት የተሰነዘረ አልነበረም ። እንዚህ እስፈሪ አይኖቹ ያደረግነውን ቢያውቁ አስከፊ የበቀል እርምጃ እንደሚወስድ በደንብ ያያሉ ።

ቆይቼ ሮዳን አስታወስኩ ። የሆነውን ሁሉ ብታውቅ ? ከቪዳል የባሰ የበቀል እርምጃ እንደምትወስድ እርግጠኛ ነኝ ። እሷን ትቼ እሌላ ሴት ጋ በመሄዶ ለዘላለሙ ይቅር አትለኝም ።

ህሊናዬ ይረበሽ ጀመር ። ነገን አሰብኩ ። አንድ ምክንያት ፈጥሬ ወይም ታመምኩ ብዬ ለሚቀጥሉት አምስት ቀናት ከቫል ጋር እንዳልቆይ ባደርግስ? መቼም ከሷ ጋር ከቆየሁ አንዱን ቀን መጋለጤ የማይቀር ነው ። ቀኑን ሙሉ ጐን ለጐን ተቀምጠን ባንድ መኪና ውስጥ ስንጓዝ ሮቤርቶ እንዳይጠረጥረን ማድረግ እችላለሁ ?



ለጥቂት ጊዜ ፀጥ ብዬ ተቀመጥኩና

ዝም ብዬ ነው በድንጋጤ ነው የሰጋሁት ። አንዴ ሆኗል እንደገናም መሆን አለበት ። እርግጥ አስገራሚ እብደት ነበር ። አልኩኝ ለራሴ አሁን ግን አልፏል ። እንዲህም እየተፀናናሁና ከአንድ ሰዓት በፊት አብረያት ቆይቼ ቀዝቀዝ ካልኩ በኋላ ሁሉ ችግሩን እንደ ማላመልጠው ይሰማኝ ነበር ። ምንም ያህል እደገኛ ቢሆን እሷ እስከፈለገችኝ ድረስ ልቋቋማት እንደማልችል ታውቆኛል ።

ስለዚህ ቁጭ አልኩበት ስለሷ ብዙ አሰብኩ ።

ቫል ቪዳልን አግብታ ? የማይታመን ነገር ነው ። እንዴት ሊገናኙ ቻሉ ? እልሰን ያለኝን አስታወስኩ ። ቪዳል አንድ ወቅት የሱ ደንበኛ ነበር ። ምናልባት ከእልሰን ጋር በምትሰራበት ጊዜ ይሆናል የተገናኙት ።

ግን ይህን መላጣ ድንክዬ ለምን አገባች ? እልሰን እንዳለኝ ቪዳል በዚያ ወቅት ሀብታም አልነበረም ስለዚህ ለገንዘቡ ብላ ልታገባው አትችልም ።ታዲያ ከኔ ይልቅ እሱን ፣ እንድትመርጥ የገፋፋት ምን ይሆን ?

በጣም የበጠበጠኝና የጐዳኝ ይሄው ነው ። ሀብታሙን ብታገባ ምንም አይደል ። ግን በዚያ ወቅት ከኔ ይልቅ እሱን በምን መረጠች ? ፣

ይህንን ሀሳብ እንደያዝኩ ተኛሁ ። ምንም ያህል እንቅልፍ አልያዘኝ ። ጠዋት አንድ ሰዓት ተኩል ላይ አስተናጋጁ ቡና ይዞልኝ ሲመጣ ተነፈስ አልኩና ። ወደ ሁለት ተኩል ገደማ ተነሳሁ ። እታች ስወርድ ተላላኪው እጅ ነሳና ፣

"ሮበርት እየጠበቀት ነው ሲኞር" አለኝ ።

"እነጋግረዋለሁ" ብዬ ጥቂት ከቆምኩ በኋላ ።

"ሚስተር ቪዳል እውስጥ ነው ያለው ?" ብዬ ጠየቅሁት ።

"ሲኞር ቪዳል በሁለት ሰዓት ነው የወጡት ? ወደ ውጪ ወጣሁና እሮቤርቶ ወደ ተቀመጠበት ሥፍራ አመራሁ ። ሲያየኝ በወርቅ ጥርሱ ፈገግ ብሎ ወደኔ መጣ ።

"እንደምን አደሩ ሲኞር በርደን ። ደስ የሚል ጠዋት ነው ። ማታ በደንብ ተኙ ?"

"አመስግናለሁ ። መኪናዋ የታለች ?" ስለው በጣቱ አመለከተኝ ሄጄ በሚገባ አየኋት በደንብ ስላሳጠባት የማታሣፍር ሆናለች ።

"ብዙ ለፋሁ" አለኝ ሮቤርቶ እያማረረ "ትልቅ መኪና ነች ።"

"ሚስስ ቪዳል ተዘጋጅታ እንደሆነ አይቼ መጣሁ" ብዬ ወደ ሆቴሉ ተመለስኩ ። አንዱን ስልክ አንስቼ ስልከኛዋን ከሰባት ቁጥር ጋር እንድታገናኘኝ ጠየቅኋት ።

"ቫል ወዲያው ስልኩን አነሳች ። ድምጿ የሠራ አካሌን አሸ በረው ።

"እንደምን አደርሽ ሚስስ ቪዳል" አልኳት ተላላኪው እንደ ሚያዳምጠኝ ስላወቅሁ

"መኪናው እየጠበቀን ነው ። እንደተነሳሽ መሄድ እንችላለን ።"

"አመስግናለሁ አሁኑኑ እመጣለሁ" አለች ። ስልኩን ዘግቼ ወደ ኪዋስኩ ሄድኩና አንድ ፓኬት ሲጋራ ገዛሁ ።

ቫል ከአስር ደቂቃ በኋላ ደረሰች ። ነጫጭ አበቦች ጣል ጣል የተደረጉበት ሰማያዊ ሸሚዝ ለብሳለች ። ፀጉሯን በነጭ ሻሽ ወደ ኋላ ሸብ አድርጋለች ። በጣም ውብ ሆና ታየችኝ ።

"እንደምን አደርክ ሚስተር በርደን ፣" አለች ፈገግ ብላ ። አይ ኖቿ እኔን እያዩም ። ፈገግታዋም ለኔ ብቻ የተሰጠ አልነበረም ።

"ዛሬ ጠዋት የት ነው እምንሄደው ?"

አንዴ ወደዚህ ብትመጪ ፕሮግራሙን ላሳይሽ እፈልጋለሁ ፣" አልኩና ብቻችንን ልንሆን የምንችልበትን ቦታ አመለከትኳት ። ተከት ላኝ መጣች ። እዚያ ሆነን ተላላኪው የምንለውን ሊሰማ አይችልም ።

ፕሮግራሙን ከኪሴ እያወጣሁ ዝቅ ባለ ድምፅ ፣

"ቫል ትንሽ ችግር አለ ። በሹፌር ነው የምንቀሳቀሰው እርግጥ የራሴ ስህተት ነው ።

አንቺ መሆንሽን አላወቅሁም ። አሁን ብናባርረው አደገኛ ነው እሚሆነው ። ሊያወራ ይችላል"

ተስፋ ስትቆርጥ ታየኝ ፣ ግን እፊቷ ላይ ምንም እንዳይታይባት ጣረች ።



"እና ምንድ ነው የምናደርገው ?" አለችኝ ።

"ሾፌሩ ከሰዓት በኋላ መሥራት አይፈልግም ። በጣም ይሞቃል ይላል ስለዚህ ከምሳ በኋላ እኔ ክፍል ልንገናኝ እንችላለን ። መነጋገር አለብን ቫል" አልኳት

ጥቂት አሰበችበትና ራሷን በመነቅነቅ መስማማቷን ገለፀች ልኝ ።

"እሺ አሁን እንውጣ ። ወዴት ነው እምንሄደው?" አለች ።

"የ ኡዛልኮ እሳተ ገሞራ የፈጠረውን ሀይቅ ለማየት ነው እምን ሄደው እሱ ይነግርሻል ። እኔ እጐኑ ነው እምቀመጠው ። ተጠንቀቂ ቫል ፣ሰውየው ጮሌ ነው ምንም የማያውቅ መስሎሽ ፣ እንዳያመልጥሽ ።

ተያይዘን ወደ ውጪ ወጣን ። ስንወጣ ሲያየን ሮቤርቶ ተንደፋ ድፎ ከመኪናዩ ውስጥ ወጣና በሮቹን ከፍቶ ባርኔጣውን አውልቆ ተቀበለን ።

"እንደምን አደሩ ሲኞራ ። መልካም ቀን ። ቆንጆ ጉዞ ነው እም ናደርገው ። በጣም በጣም ፣ አስደሳች ነው ። ታሪኩን እየሄድን እጫው ታችኋለሁ ።"

ቫል አመስግናው እመኪናዋ ውስጥ ገባች ። እኔም እሮቤርቶ ጐን ተቀመጥኩ ።

ሮቤርቶ መኪናውን እየነዳ ከለፈለፈው ውስጥ እኔና ቫል ጥቂ ቱን እንኳ የሰማነው አይለመስለኝም ። አብረን ስለምንቆይበት ከሰ ዓት በኋላ ነበር እኔ እማስበው ። ወደ እሳተ ገሞራው ያደረግነው ጉዞ አቧራ የሞላበት እረጅምና አድካሚ ነበር ። አንዳንዴማ መን ገዱ መጥፎ ከመሆኑ የተነሳ እየተንቆራሰስን ነበር እምንጓዘው ።

በመጨረሻም አገልግሎት ወደ ማይሰጠው ተራራ ሆቴል ደረስን ሆቴሉ ባዶ ቢሆንም እጠገቡ ሆነን እሳተ ገሞራው የፈጠረውን ሃይቅ በደንብ ማየት እንደምንችል ሮቢርቶ አረጋግጦልናል እውነትም ከሆቴሉ ፊት ለፊት ሆኖ ሀይቁ በደንብ ይታያል ። ሌላ ጊዜ ቢሆን ኖሮ ጠቆር ያለው አረንጓዴ ውሀና ኩባያ የመሠለው ቅርፅ ሊያስደንቀኝ በቻለ ነበር ። ግን አእምሮዬ ከሰዓት በኋላ በሚያጋጥመኝ ሁኔታ የተያዘ ስለነበር ሮቤርቶ እያደነቀ የሚያወራልኝ ነገር ሁሉ ከመስልቸትም አልፎ እረፍት ነሳኝ ። የምናየውና የሚለው ነገር ለኔም ሆነ ለቫል ስሜት እንዳልሰጠን ለማወቅ ጊዜ አልወሰደበትም ።

"ደስ አላልዎትም እንዴ?" ብሎ ጠየቀ ቫልን አትኩሮ እየተመለከተ

"ባዩት የረኩ አይመስልም ሲኞር ቪዳል?"

"በጣም አስደናቂ ነው ። ግን ሙቀቱ ከጠበቅሁት በላይ ነው ። ወደ ሆቴላችን ብንመለስ ይሻላል ።" ስትለው ትናንሽ አይኖቹ ነፍስ ዘሩ ።

"እኩለ ቀን ሲሆን በጣም ይሞቃል" ከምሳ በኋላ ትንሽ እረፍት ማድረግ ጥሩ ነው ። ማምሻውን ይቀዘቅዛል ።ሲኞራ ቪዳል ከፈለጉ ደግሞ መሸት ሲል ከተማውን እያዟዟርኩ ፣ ላሳይዎ እችላለሁ ።"

"ለዛሬው የሚበቃን ይመስለኛል ከተማዋን ነገ እናያታለን" ስትለው በደስታ ፈነደቀ ።

"በጣም ጥሩ ነው ። እቅንጀው መዋኛ ገንዳ ውስጥ እየዋኙ መዋሉ ይሻላል ። ስለዚህ እንመለስ" ብሎ ቫልን ተመለከታት ።

"አዎ እንመለስ" አለችው

ሰባት ሰዓት አካባቢ ሲሆን ከሆቴላችን ደረስን ። ቫል በጥንቃቄ ስለነዳና ሀይቁን በደንብ ስላስጎበኘት ሮቤርቶን አመሠገነችው ።

ትተነው ወደ እንግዳ መቀበያው ክፍል ገባን ።

"ሚስተር በርደን አብረን ቀለል ያለ ምሳ እንብላ?" አለች ቫል ጮክ ብላ ። ተላላኪው እንዲሰማ ። "ከዚያ ትንሽ አረፍ እላለሁ ።"

በሰዎች ወደተጣበበው ቡና ቤት ገባንና ሀምበርገር አዘዝን ። ቀና ብለን መተያየት አልቻልንም ። ሀምበርገሩም አልበላ ስላለኝ ግማሹን ተውኩት ።

ስንወጣ ቁልፍሽን አትስጪያቸው አልኳት በምልክት እሺ አለችኝ ።

"ሶስተኛ ፎቅ ክፍል 346" አልኩና ማንም ሳያየኝ የኔን ቁልፍ ሰጠኋት ። ፈገግ ብላ ወደ አሳንሰሩ አመራች ።

እንግዳ መቀበያው ውስጥ ባዶ ወንበር ፈልጌ ተቀመጥኩና ሲጋራ ለኮስኩ ። አስር ደቂቃ ያህል ከቆየሁ በኋላ ተነስቼ አሳንሰሩ ውስጥ ገባሁና ወደ ሶስተኛው ፎቅ ተንሳፈፍኩ



ቫል አልጋዬ ላይ ጋደም ብላለች በሩን በችኮላ ዘግቼ ቆለፍኩት ።

እጆቿን ዘረጋችልኝ ፤ የፊቷ ግለትና የአይኖቿ ጥሪ ሁሉን ነገር አስረሱኝ ። ዘልዬ አልጋዬ ላይ ወጣሁ ።

ዛሬ እንዳለፈው ምሽት በፍርሀት አልተጣደፍንም ። አሁን በእርጋታ ፍቅራችንን ተካፈልን ፤ ከፍቅር ሌላ ምንም ወደ ማይታይበት አለም ተቃቅፈን ጭልጥ አልን ።

* * *

የፀይዋ ጨረር በመጋረጃ በተከለለበትና የአየር ማስተካከያ ባለው ክፍል ውስጥ ቫል እጎኔ ጋደም ብላ ስድስት አመት ሙሉ ከቪዳል ጋር እንዴት እንዳሳለፈች አጫወተችኝ ።

የምትነግረኝ ሁሉ ባይገባኝም በትዕግስት እንዳዳምጣት ስትጠይቀኝ አስገረመኝ ለምን ያን ደብዳቤ እንደፃፍኩልህና ቀለበቱንም ለምን እንደመለስኩልህ ለማስረዳት ይከብደኛል ። ቢሆንም ልምከር አለችኝ ።

"ከመነሻው ለመጀመር" አለች ቫል "በመጀመሪያ የተገናኘነው ቦስተን ሂልተን ሆቴል ለሥራ ጉዳይ መጥቶ ነው ። ያን ለት ቢል አልሰን ምሳውን ሊበላ ስለሄደ ብቻዬን ነበርኩ ። ቪዳል ወደለንደን የሚበር አውሮፕላን እየፈለገ ነበር ።የጉዞውን ፕሮግራም እያጣራሁ ትኬት ሳዘጋጅለት ያለማቋረጥ ትክ ብሎ ሲመለከተኝ አሳፈረኝ ። ወቅቱ ሥራ የሚበዛበት ስለነበረ በየደቂቃው የስልክ ጥሪ ሥራዬን ያደናቅፈዋል ።ስላስጠበቅሁት ይቅርታ ስጠይቀው "ግዴለሽም አልቸኩልም" አለኝ ። ለምን እንደዚያ ተመለከተኝ በሚል ብዙ ተጨነቅሁ ያኔም ሆነ አሁን እንደማምነው ቢዳል በአእምሮዬ ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር ( HYPNOISE ) እየጣረ ነበር ። አይኖቹን እላዬ ላይ ተክሎ እንደቆመ አንድ የሆነ ሀይል እውስጤ ፣ ዘልቆ ሲያንቀጠቅጠኝ ተሰማኝ ፣" አለችና ለጥቂት ጊዜ ዝም ብላ ፣

"እማወራልህ ነገር ትርጉም አልሠጠህም?" አለችኝ "እውነቱን ነው እምነግርህ በዚያ ወቅት እንዳልኩህ ነበር የተሠማኝ ።" ትክ ብሎ እየተመለከተኝ የትኬቱን ዋጋ ከፈለና በሌላ ቀን እንደሚመመለስ ነገሮኝ ወጣ ። ከዚያንለት ወዲህ ከሀሳቤ ሊወጣ አልቻለም ።

የአእምሮዬን አንዱን ክፍል አንቆ እንደያዘው አይነት ነበር፣ የሚሠማኝ፣ "አለችና እንዴት አድርጌ ላስረዳህ በሚል አይነት እጆቿን አርገበገበች ።"

"ከዚያ አልፎ በህልሜ ጭምር እየው ጀመር ።" በምሄድባቸው ቦታዎች ሁሉ የሚከተለኝ መሠለኝ ። በምንም በምንም ያነጫንጨኝ ስለነበር አዘውትሬ እውጪ መውጣቱን ተኩውት ።

እንደዚያም አድርጌ ማለሜን ላቆመው አልቻልኩም" ብላ ከንዴን ነካ አደረገችው ።

"እስከፊው ነገር ደግሞ እንደዚያ በምሆንበት ወቅት ስላንተ አለማሰቤ ነበር ።" አንተ ከአእምሮዬ ወጥተህ እሱ የተተካ ይመስል እሱን ብቻ ማሰቤን ቀጠልኩ ።

"ያኔ የምትጽፋቸው ደብዳቤዎች አለማቋረጥ ይደርሱኝ ነበር ። ከፊሎቹን አላነበብኳቸውም ። ይሄ እንደሚጐዳህ አውቃለሁ ። ግን በዚያ ወቅት ሙሉ በሙሉ በተፅዕኖው ሥር እንዳያደርገኝ እየታገልኩት ነበር ። እርኩስ መንፈሶች ሰውን በተፅዕኗቸው ሥራ ለማዋል ጥረት፣ ያደርጋሉ ።" አለችና ትክ ብላ ተመለከተችኝ ። ቀጥላም፣

"በርደን ይህንን ታምንበታለህ?" ብላ ጠየቀችኝ ። ስለ እርኩስ መንፈሶች አስቤም አላውቅ ። ቪዳል ለኔ እብሪተኛና በራሱ የሚተማመን ቱጀር ነው ።

"እኔ እንጃ ግን ቀጥሎ ምን ሆነ?" አልኳት ።

"ከለንደን ከተመለስ በኋላ የተለያዩ ሰበቦችን እየፈጠረ ወደ ቢሮችን ይመጣ ጀመር ። እንዳላየው በሚል ከቢል ጋር ተስማምተን የምሳ ሰዓቱን ሁሉ ለውጥኩ ። ግን ምንም አልረዳኝ ።

ለሁለት አስጨናቂ ወራት በተፅዕኖው ሥር እንዳልወድቅ አበክሬ ታገልኩ ። እየቆየ ሲሄድ ግን ከአቅሜ በላይ ሆነብኝ ። በመጨረሻው ተሸነፍኩና በእጁ ገባሁ ።

"እንዳገባው አስገደደኝ ነው እምትዩኝ?" ብዬ ጠየቅኋት ። አይን አይኗን እየተመለከትኩ፣

"አላስገደደኝም" ግን በተፅዕኖ ሥር አዋለኝ ። አሜን ብዬ ካል ተቀበልኩት ምንም አይነት እረፍትና ሰላም እደማላገኝ አውቅሁት ።



በፍርሀት ከመወጠሬም በላይ በጣም አድክሞኝ ነበር ። ትግሉን ከመቀጠል አግብቼው ማረፍን ነው ቀላል ሆኖ ያገኘሁት ።"

"ግን እንዲህ ሲሆን ለምን አልነገርሽኝም ። ገስግሼ መጥቼ እረዳሽ አልነበረም?"

"ማንም ሰው ሊረዳኝ አይችልም ። እንዲህ አይነቱ ትግል ሲያጋጥምህ ወይብቻህን ትወጠዋለህ ወይም ትሸነፋለህ እንጂ ካንተ ውጪ ያለ ሰው ሊረዳህ አይችልም ። ታግዬ የወደቅሁበት የግሌ ትግል ነበር ። ገና ነገሩ ሲጀምር አንተ ጣልቃ ብትገባ፣ ሊያጠፋህ እንደሚችል ተገንዝቤዋለሁ ።የሱን ሀይል የምትቋቋምበት አቅም እንደሌለህ አውቄ አለሁ ። ያኔ እኮ አሁን የምወድህን ያህል ነበር እምወድህ ። እንድትጐዳብኝ አልፈልግም ።

አንዳንዴ ልንገረው እልና ምንም እንደማታደርግልኝ ሳውቀው እተወዋለሁ ። የኔ አንሶ ለምን ብሎ የሁለታችን ህይወት ይበላሽ? ስለዚህ ያንን ደብዳቢ ፃፍኩልህና ቀለበቱን መለስኩልህ ።"

በመደነቅ ተመለከትኳት ።አሁን ይሄን ውል የሌለው ነገር ማን ያምናል!

"አሁንም እንዳልገባህ ይታየኛል ። እየሀ ሰውዬው እርኩስ ነው፣ ሰይጣን ነው፣ በሰይጣን አታምንም ። አይደል?"

"አይኖቿ ላይ ያየሁት ፍርሀት አስደነገጠኝ ።

"ሰይጣን የሚባል ነገር ካለፈው ክፍለ ዘመን ጋር አብሮ ያለፈ ይመስለኛል በፍፁም በሰይጣን ወይም በእርኩስ መንፈስ አላምንም ። እርግጥ እንደሱ አይነት ጠንካራ ሰው እታሎ ቢወስድሽ ይገባኛል ። አረፍና ብርቱ ነው ብትይኝ እቀበልሻለሁ ። ግን አእምሮዬን በተፅዕኖው ሥር አዋለው ስለምትይው. . . ስለ መናፍስት. . . እንዲህ አይነቱን ዋጋ ቢስ ነገር በጭራሽ ልቀበል አልችልም ።" ስላት እንደዚህ እንደምትለኝ አስቀድሞ አውቄ ዋለሁ ። በሚል አይነት ራሷን ነቀነቀች ።

"እሺ እንዳልከ ከኔ እንፃር ልክ ባይሆንም በዚያ እንስማማ ። ጉዳዩ በጣም ውስብስብ ነው ። የለም በዚህ ጊዜ እናጥፋ" ብላ ፀጥ አለች ።

"አንድ ጊዜ ለምን እንዳገባኝ ጠይቄው ነበር ። የሰጠኝን መልስ ቃል በቃል ነው እማስታውሰው ።

“ብዙ ሀብት አገኛለሁ” አለኝ በሚያስፈሩ አይኖቹ ትክ ብሎ እየተመለከተ ።

“ገንዘብ ኃይል ነው ። እና እሱን እፈልጋለሁ ። እንቺም በዚህ ትረጂኛለሽ ። አጋሬ እንድትሆኚ የመረጥኩሽ ፈጣንና ብልህ አእምሮ ያለሽ ብርቱ ሠራተኛ ስለሆንሽ ነው ። በዚያ ላይ ቆንጆ ነሽ ። ገና ሳይሽ ነው ስፈልጋት የኖርኳትን ሴት ያገኘሁ መሆኑን ያወቅሁት ። በጋራ እንሠራና ከዓለምነው ግብ እንደርሳለን” አለኝ ። አለችኝ ጣራ ጣራውን እየተመለከተች ። አይኖቿ ዳምነዋል ።

“አራት አመት አብረን ስንኖር እፈለገበት ደረጃ ደረሰ ። መጠን የሌለው ገንዘብ ስላለው የፈለገውን ማድረግ ይችላል ። በዚህ ሥራው እንዲቀጥልበት የሚገፋፋው እርኩስ መንፈስ በውስጡ አለ ። እስከ ህይወቱ ፍጻሜ ገንዘብና ስልጣን ሲያካብት ነው እሚኖረው ። በተጋባን በአመቱ ነው የመጀመሪያውን ሚሊዮን ብር ያገኘው ። ይሄ ሲያረካው ቀርቶ ጥቂት ደስታ እንኳ አልሠጠውም ።”

“ገና መጀመሩ ነው” አለ “አንድ ሚሊዮን ብር ምንም አይደለች”

በዚያ ወቅት ያለ ዕረፍት ነበር የምንሠራው ። የለማቋረጥ እንጓዛለን ። ከሰዎች ጋር እንገናኛለን ። ሰዎችን እናመጣለን ። እንዲህ አይነቱን ሥራ እንዴት እጠላው ነበር መሠለህ ? ግን ለካስ እሱ እስቪንጋሊ እኔ ትሪልባይ ነበርን ። እንዲህ አድርጊ ይለኛል ። ትዕዛዙን ያለማወላወል እፈፅማለሁ ።

እንደገና ጣራ ጣራውን እየተመለከተች ፀጥ አለች ።

እና አሁንም ከስድስት አመት በኋላ ? ተጨሜነኝ ይህን አስደናቂ ታሪክ ልቀበለው አልቻልኩም ። (ትሪልባይ እና እስቪንጋሊ ምን ማለት ነው ?) መናፍስት ? ሠይጣናት ? ከምትለኝ በወቅቱ ከቢዳል ጋር ፍቅር እንደያዛትና አሁን ፍቅሯ እያለቀ መሄዱን ብትነግረኝ ይሻለኝ ነበር ። አእምሮዬን በተፅዕኖው ሥር አውሎ ወሰደኝ ከምትለኝ እንዲያ ብትለኝ ባመንኳት ፤

“አሁን ህይወቴ የራሴ ነው” አለች ፤

ይህን ያህልም አይፈልገኝ ። ትርፍ እቃ ሆኛለሁ ። በሥራ ተወጥሮ ስለሚውል እንደድሮው አዘውትሮ እንግዶችን ወደ ቤት አይጋብዝም ። አልፎ አልፎ ቢጋብዝም ማንኛውንም ነገር የማዘጋጀው



እኔ ነኝ ። እቢሮው ውስጥ ተወሽቆ ሳምንታት ያሳልፋል ። ብዙ ሠራተኞች አሉት ።

አንድ አመት ይሆነዋል ። ምን እየሠራ ፣ ምን እያቀደ እንደሆነ እንኳ ነግሮኝ አያውቅም ።ጌጡ ስለሆንኩ ብቻ እቤቱ ውስጥ ሊያየኝ ይፈልጋል ። እኔ ለሱ ጌጥ እንጂ ሌላ ምንም አይደለሁ ።

የኔን እርዳታ ባለመፈለጉ ተደስቻለሁ ። አሁን የምዝናናበት በቂ ጊዜ አለኝ ። ረጋ ብዬ ለማሰብ እድል አግኝቻለሁ ። በርደን አዘውትሬ ስለምን አስብ እንደነበር ታውቃለህ ? ስለአንተ ብቻ ነበር እማስበው ፤ ቪዳልን ካገባሁ በኋላ ላንተ ቀለበቱን በዚያ ሁኔታ መመለሴ በጣም ነው የፀፀተኝ ፤ እርግጥ በዚያ ጊዜ የአሁኗ እኔ አልነበርኩም ።

ህይወት አሰልቺ በነበረበት ወቅትና ከሀገር ሀገር በምንበርበት ጊዜ እንኳ ስላንተ አስብ ነበር ። ባለፈው ሣምንት ጋዜጣ ሳነብ የአሜሪካን የጉዞ ወኪል ድርጅት እስፓኒሽ ቤይ ሆቴል ውስጥ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንደሚከፈትና አንተ ሀላፊ ሆነህ እንደምትመጣ አወቅሁ ። ወዲያው ዳየርን ከዚህ በፊት እሠራ ለነበረበት መሥሪያ ቤት ውለታ መክፈል መፈለጌንና የባንኩ ሂሣብ ወደ እናንተ ቢዛወር የተሻለ አገልግሎት እንደምናገኝ አሳምኜ ላክሁት ።

ሄንሪ ወደ ሳንሳልቫዶር ለመጓዝ ያቀደ መሆኑን ስሰማ ይዞኝ እንዲሄድ ተማፀንኩት ። ረዘም ላለ ጊዜ አብረን ተጉዘን አናውቅም ። የአየር ለውጥ እንደሚያስፈልገኝ ካሳመንኩት በኋላ እዚህ እሱ በሥራ በሚወጠርበት ጊዜ አገሪቱን እያዘዋወረ የሚያሳየኝ አስጎብኚ እንዲዘጋጅልኝ ፣ ጠየቅሁት ። ለዳየርም አስጎብኚዬ አንተ መሆን እንዳለብህ አስጠንቅቄ ነገርኩት” ብላ እጇን መታ መታ አደረገችኝ ።

“ተቃውመህ ነበር ። አይደል ? በመጨረሻው አሸነፍኩና ይሄው አብረን ለመሆን በቃን” አለችና ጠጋ ብላ እቅፍ አደረገችኝ ።

“ስላደረስኩብህ ጉዳት በጣም ይቅርታ አድርግልኝ ። “የኔ ፍቅር እና ለምን እንዳደረግሁት ተረዳልኝ” አለችኝ ። ዝም ብዬ እቅፍ አደረግኋት ።

ቫል ጨርሼ ባልረሳሽም እንደገና አገኝሻለሁ ብዬ አስቤውም አውላቅ ። ማግባቴን ታውቂያለሽ” ስላት ራሷን በአዎንታ ነቀነቀች ።

"ስለ ባለቤትህ ዳየር ነግሮኛል ። ታስደስትሀለች ?"

"ተጋብተናል ፡"

"እኔ እውነቱን ነው የነገርኩህ በርደን ። አንተም እውነቱን ንገረኝ ። ከሷ ጋር ተደስተህ ነው እምትኖረው ?"

"አይደለም ። ግን አብረን እንኖራለን ። ያም ሆኖ የጋራ የምንለው ነገር የለም ። አይተሻታል ። እምንሠራበት ሆቴል ኪዎስክ ውስጥ ነው እምትሠራው"

"ሮዳ ? እሷ ነች እንዴ ሚስትህ ?"

"አዎ"

"ግን ደስተኛና ቆንጆ ነች ። ከተጋባችሁ ቆይቷል እንዴ ?"

"ሁለት አመት ሆኖናል ። ስህተት ነው የፈፀምነው" ስላት አይን አይኔን ተመለከተችኝ

"አትወዳትም እንዴ ?"

"አንቺን ነው እምወደው" ስላት አንገቴ ሥር ሽጉጥ አለች ።

"እንዲያ ስትለኝ መስማቱ ምን ያህል መሰለህ የሚያስደስተኝ በርደን ። ከእንግዲህ ካንተ ተለይቼ መኖር የምችል አይመስለኝም ፡"

"ማታ ስላንቺ ሳስብ ነው ያነጋሁት ፤ ከእንግዲህ ባገሽ አልፈልግም ። ምን ይሻላል ቫል ? እሺ ብሎ ይፈታሻል ?" ስላት ተሽማቀቀች ።

"አይመስለኝም ። እኔም እንዲፈታኝ አልጠይቀውም ። ባንተ ምክንያት የምተወው መሆኑን ሲያውቅ ምን እንደሚያደርግ አላውቅም"

"ግን ምን ማድረግ ይቻላል ?" አልኩኝ ትዕግስቴ አያለቀ ፥

"እንደምትወጂኝ ንገሪው ። እኔም አንቺን እንደምወድ ለሮዳ እነግራታለሁ ። ሁለቱም ሊፈቱን ይገባል ።"

ሰውዬው ምን ያህል እርኩስ እንደሆነ ነግሬሀለሁ ፤ ሰይጣን ነው ብዬሀለሁ ። አንድ ጊዜ አንድ ሰው ሊያታልለው ሞከረ ። ተደብድቦ ሽባ ሆኖ አሁን በተሽከርካሪ ወንበር ነው እሚሄደው ። እጁም ሮው ተበላሽቷል ።" ስትለኝ ትክ ብዬ ተመለከትኳት ።

"ፖሊስ ዝም አለ . . . ?"



"በጭለማ ነው ። ግን እንደመታው ይታወቃል ? በዚህ ሁኔታ ፖሊስ ምን ማድረግ ይችላል ? እኔና አንተ ፍቅረኛች መሆናችንን ቢሰማ ነፍስ ገዳዮቹን ይልቅብሀል ። አንድ ጊዜ ትዝ ይለኛል አንድ ልጃገረድ አረገዝኩልህ ትልና ልጁ፤ እንዲቀበላት ትከሰዋለች በዚህ አይነት ከሱ ገንዘብ አገኛለሁ ብላ አስባ ነበር አንድ ቀን የማታውቀው ሰው እፊቷ ላይ አሲድ ረጨባት ። አሁን አይነስውር ሆናለች ።" ይህን ስሰማ ፍርሀት ጨምድዶ ያዘኝ ።

"እንዲፈታኝ ስጠይቀው በኔና ባንተ ላይ ሊፈፅመው የሚችለውን አላውቅም ስልህ ፡እውነቴን ነው ። ሊያስገድለንም ይችላል ።"

"አላምንም "

"እየነገርኩህ" አለችና ሎኸች ። ቀና ብላ በቁጣ ተመለከተችኝ አይኖቿ ውስጥ ፡ ያለው ፍርሀት የሚያንቀጠቅጥ ነው ።

"ያስገድለናል !"

ፍርሀቷ እርግጠኛ መሆኑን ሳይ ዝም ብዬ አይን አይኗን ከመመልከት ሌላ ምንም ልል አልቻልኩም ።

"ታዲያ . . ."

"አንድ መንገድ አለ ። ሣምንቱን ሙሉ ሳስብብት ነው የቆየሁት ። ሁለታችንንም ፡ ጉዳት ላይ የማይጥል መፍትሄ አግኝቻለሁ ። እኔ ካንተ ተለይቼ መኖር እንደማልፈልግ ሁሉ አንተም ከኔ ጋር መቆየት የምትፈልግ ከሆነ ጋብቻህን እንኳ የማይነካ መፍትሄ ነው ያገኘሁት ።

"ምንድነው ?"

"የጉዞፕሮግራሞቹን እንድትከታተልለት በሚል ሰበብ እንዲቀጥርህ ላግባባው እችላለሁ ። እንደዳየር ከረዳቶቹ አንዱ ትሆናለህ ። እቤታችን ውስጥ የራስህ ቢሮ ይኖርሀል ። እሱ ለሥራ ጉዳይ ወደ ውጪ በሚወጣበት ጊዜ እንደልባችን መሆን እንችላለን ።" ብላ ይስማማሀል በሚል አይነት ተመለከተችኝ ።

"ምን ይመስለሀል ?"

የሚቻል አይመስለኝም በሚል ራሴን ነቀነቅሁ ።

"ለምን ብሎ ይህንን ይቀበላል ?"

“ሊያሳምኑት የሚችሉ ሁለት ምክንያቶች አሉ ፣ በመጀመሪያ ደረጃ ለጉዞ ወኪሎች የሚከፈለውን ገንዘብ ያድናል ። እኔም የምሠራው አገኛለሁ ። ለምን አንድ ነገር አትሠሪም እያለ ዘወትር እንደጨቀጨቀኝ ነው ። አየህ የኔ ፍቅር አብረን እንሠራለን ማለት ነው ። እኔም እንደበፊቱ ፀሐፊህ እሆናለሁ ፡” ብላ ከንዴን ጨበጥ አድርጋ በደስታ በተሞሉት አይኖቿ ተመለከተችኝ ።

“እርግጥ መጠንቀቅ ይኖርብናል ። ግን እስቲ አስቢው እሱ በወጣ ቁጥር እንደዛሬው አብረን ለመሆን የሚያጋጥመን እድል ምን ያህል ነው ?”

“““ጥርጣሬዬ ባይለቀኝም ። እንዲህ አይነቱ እቅድ ሊሠራ የሚችልበት ሁኔታም ታይቶኛል ።”

“ዳየርስ ?”

“ዳየር ስራ በጣም ነው የሚበዛበት ። የጉዞውን ጉዳይ አንተ ብትይዝለት ደስታውን አይችለውም ። እመነኝ በሱ በኩል ምንም የሚያጋጥመን ችግር አይኖርም ።”

ልቤ በመጠኑም ቢሆን መነሳሳት ጀመረ

“በደንብ ስላቀድሽው የሚሳካ ነው እሚመስለኝ ፡”

“አትጠራጠር ። አሁን ስንት ነው እሚከፍሉህ ?” የደመወዜን ልክ ነገርኳት ።”

“የዚያን እጥፍ ይከፍልሀል ።ገንዘብም ታድናለህ ፤ በሥራ ሰዓቶች ብቻ ነው የምትሠራው ፤ ወደ ቤትህ ልክ እንደወትሮህ ትገባለህ ፡” ብላ ጉንጬን በከንፈሯ ዳሰሰችው ።

“እሱም ሆነ ሮዳ ሊያውቁብን አይችሉም ።”

በየዋህነቴ አመንኳት ።

# አ ራ ት

ያለፉት አራት ቀናት ተመሳሳይ ነበሩ ። ጠዋት ጠዋት ከሮቤርቶ ጋር ለጉብኝት እንወጣለን ። እመኪናዋ ውስጥ ተለያይተን መቀመጣችን ቢያናድደንም ጐን ለጐን መቀመጡ ልክ እንደማይሆን እምንናል ። ያስለመድነውን ብንለውጥ ሮቤርቶ እንዲጠረጥረን መንገድ መክፈት ነው ።

ከተማይቱን እየተዘዋወርን ተመልክተን ። የገበያው ቦታ በቀይ ህንዶች የተሞላ ነው ። ጥራጥሬ ፣ ፍራፍሬ ፣ አታክልትና የተለያዩ ቀለም ያላቸውን የእጅ ሥራ ውጤቶቻቸውን እንዲሁም በዘይት የተጠበሱ ብስኩቶችን እጠባቡ መንገድ ዳርዳር ዘርግተው ይሸጣሉ ።

መርከቦች ከፓናማ ይዘዋቸው የሚመጡ ቱሪስቶችን የምታስተናግደውን አካጃልታ የተባለች ወደብም ጐብኝተናል ። ቱሪስቶቹ ከመርከቦቻቸው እየወረዱ በሚጠብቋቸው አውቶቡሶች ላይ ይሳፈሩና ከተማይቱን እየተዘዋወሩ ይጐበኛሉ ።

ሮቤርቶ ቡና እየታጠበ ደርቆ የሚታሸግበትን ፋብሪካ ሁሉ አስጐብኝቶናል ። ሽማግሌዎች ከሸክላ ትንንሽ አሻንጉሊቶችን የሚሰሩባትን ኢሎባስኮ የተሰኘችውን ትንሽ መንደር ሳይቀር እያዘዋወረ አሳይቶናል ።

“ይህ የሸክላ ሥራ በመሞት ላይ ያለ ጥበብ ነው ። ወጣቶቹ ለእንደዚህ ያለ ሥራ ትግስት ስለሌላቸው ትተውታል ። ሽማግሌዎቹ ሞተው ሲያልቁ እሱም ያበቃለታል” አለን ሮቤርቶ ፀፀት በተሞላበት አነጋገር ።

በየቀኑ ቀለል ያለ ምሳ ለመብላት ወደ ሆቴሉ እንመለሳለን ። ከዚያ ቫል ወደኔ ክፍል ፡ ትመጣለች ። አለፍ አለፍ ብዬ ቪዳልን ወደ አሳንሰሩ ሲገባ ወይም ሲወጣ እመለከታለሁ ። ከመጣደፉ የተነሳ ሰላሳ ስድስቱን ሰዓት ወደ ሀያ አራት ሰዓት ሊያጠቃልለው ሞክሮ የተሳካለት ይመስላል ።

ምሽቱን ብቻዬን ነው የማሳልፈው ። ቫልና ቪዳል በሥራ ምክንያት ከሚያገኟቸው ሰዎች ጋር በየማታ ክበብ ሲዞሩ ያመሻሉ ። ቫል ይሄ ሁኔታ በጣም እንደሚያስለቻት ትነግረኛለች ። አብዛኛውን ጊዜ ብቻዬን እራቴን ከበላሁ በኋላ ወጣ ብዬ በከተማው መንገዶች ላይ እንሸራሸራለሁ ። ያኔቫል ስላወጣችው እቅድ ለማሰብ ጊዜ አገኛለሁ ። ቪዳል ሊቀጥረኝ ቢስማማስ ? ለችግራችን ዘላቂና አጥጋቢ ባይሆንም ለጊዜውም ቢሆን መፍትሔ ሊሆን ይችላል ። ከምንም ይሻላል ።

ቫል በምንም አይነት መንገድ እንደማንጋለጥ እርግጠኛ ሆና ስላየሁ እኔም ላምን በት እራሴን እያዘጋጀሁ ነው ። ድርጅቱን ለቅቄ ለቪዳል ልሠራ መሆኔን ስነግረው ማሲንግ ሃም ምን ይል ይሆን ከስነምግባር ውጪ ነው ብሎ ያስብ ይሆን ? ያስቸግረኝ ይሆን ?

ቪዳል ለሶስት ዓመት በኮንትራት እንዲቀጥረኝ ልታግባባው እንደምትችል ቫል ነግራኛለች ። እንደዚያ ልታደርግ ከቻለች ስለሚሲንግ ሃም የሚያስጨንቀኝ ነገር አይኖርም ።

ሮዳስ ምን ትል ይሆን ? እሷን ተጨማሪ ገንዘብ በመስጠትና እኔ ላመላልሳት ስለማልችል ወደ ሥራ የምትሔድበት አንድ መኪና በመግዛት እክሳታለሁ ። እሷ ይሄን ያህልም ግድ የሚኖራት አይመስለኝም ።

ሁሉንም ነገር በትእግሥት እንድይዘው ቫል አስጠንቅቃኛለች ። ስለዚህ ጉዳይ አልጋችን ላይ ጐን ለጐን ጋደም ብለን ስንጫወት ።

"እኔም ቪዳልን በጥንቃቄ ነው እምይዘው ። ሥራ ሳይበዛበትና በደህና ሁኔታ ላይ ሆኖ ሳገኘው ብቻ ነው እማነጋግረው ። ጉብኝቱን ጨርሰን እንደተመለስን ከዚህ ሌላ ምንም ሥራ አይኖረኝም ። ብላኛለች ።

በቢዳል ተጽዕኖ ሥር ስለመሆኗ አዘውትሬ ባስብም ከዚያንለት ወዲህ እንስቼባት ፣ አላውቅም ። እሷም አለማመኔን የተቀበለችው ይመስላል ። መናፍስቱና ሰይጣናቱ አእምሮዋ ፣ ሲረበሽ የፈጠራቸው መሆን አለባቸው ። አሁን ግን ሁሉም ለቅቀዋታል ። ብዬ ደመደምኩ ።

ግን ቆይቶ አንድ በጣም ሊያስደንቀኝ የቻለ ነገር ተፈፀመ ። ምናልባትም አጋናው ሊሆን ይችላል ግን . . .

እሳን ሳልቫዶር ውስጥ የመጨረሻችን የሆነውን ሞቅ ያለ ፍቅር ተለዋውጠን አልጋው ፣ ጎይ ጐን ለጐን ጋደም ብለናል ። ሙሉ በሙሉ



ዘና ብዬ ነበር የተኛሁት ። አልፎ ፣ አልፎ ነገ ሳንሳልቫዶርን ለቅቀን ስለመሔዳችን አስባለሁ ። ያለፉት ቀናት ለኔ እንደ ህልም ነበሩ ። ሳንሳልቫዶርን ይህን ያህልም ባልደሰትባት አራት የማይረሱ ድንቅ ፣ ቀናትን ያሳለፍኩባት ከተማ በመሆኗ ሳመልከባት እኖራለሁ ። ነገ ወደ ግድ የለሺ ሮዳ ፣ እመለሳለሁ ። አፓርታማችን እንዴት ሆኖ ይጠብቀኝ ይሆን ? የጽዳት ሠራተኛዋ ቅዳሜና እሁድ ስለማትሰራ ቤታችንን በነዚህ ቀናት እኔው ነበርኩ የማፀዳው ። እተመሰቃቀለ ሁኔታ ውስጥ እንደምገባ እርግጠኛ ነኝ ። ግን እዚህ ያገኘሁት ደስታ ያንን እንዳስበው ብዙም ጊዜ አልሰጠኝ ።

እንዲህ በሀሳብ ወደኋላና ወደፊት ስንሸራሸር ድንገት ሳላስበው ና ሳልጠነቀቅ የቫል ጣቶች ክንዴን ጥርቅም አድርገው ያዙኝ ። ጥፍሮቿ እስጋዬ ውስጥ ተሰኩ ። በድንጋጤ ። "ቫል ምንድ ነው ?" ብዬ ጮሁኩ ።

ክንዴን መንጭቄ ትክ ብዬ ተመለከትኳት ። በአይኖቿ ውስጥ ያየሁት ድንጋጤ ፍርሃት ለቀቀብኝ ። ገርጥታለች ። ከንፈሮቿ ይንቀጠቀጣሉ ። የሠራ አካሏ በፍርሃት ይርዳል ።

ከአልጋው ላይ እየተንደፋደፈች ዘላ ወረደችና ልብሷን ማጠላለቅ ጀመረች ።

"እዚህ ነው ያለው ! ብላ ትንፋሿ ቁርጥ አለ ። ተመልሶ መጥቷል ! ፣ ሁሌም ቢሆን ተመልሶ ሲመጣ ይታወቀኛል ! እንደዚህ የሚያመኝ እቅርቤ በሚሆንበት ጊዜ ነው" ሸሚዟን ለብሳ ፣ ነጠላ ጫማዋን ሰከታ ወደመስተዋቱ ሮጠች ። "እዚህ ሊሆን አይችልም !" አልኳት !

ግን ጭንቀቷ ወደ እኔም ተጋባ ። ልብሶቼን መለባበስ ጀመርኩ ።

"ገና አሥር ሰዓት አልሆነም ። ከምሽቱ ሁለት ሰዓት በፊት እንደማይመለስ ሮቤርቶ ነግሮኛል ።

"ተመልሷል !" ማበጠሪያውን አንስታ ፀጉሯን አበጠረችና ትንሽ ፀጥ አለች ። ከዚያ ጐኗን በእጇቿ ደግፋ አጎነበሰች ።" በእግዚአብሔር በጣም ነው እሚያመኝ" አለች እያቃሰተች ።

ልብሴን ለብሼ ተነሳሁ ።

"ዝም ብለሽ አትበጂ !" ብዬ ጮሁኩባት ። ፍርሀት ስለለቀቀችብኝ ተናድጃለሁ ።

"እዚህ ሊሆን አይችልም! ተቀምጪ ። በድንጋጤ ሰውነትሽ ተሳስሯል !"

"እየነገርኩህ እዚህ ነው ያለው !" ብላ አቃሰተች ።

"እታች ውረድና ለባብሼ እክፍሌ እስከምገባ ድረስ በጨዋታ ያዘው ። ቶሎ በል !" ድንጋጤው እምይዘውን አሳጣኝ ። ልቤ እየዘለለ ከክፍሉ ወጣሁና ወደ አሳንሰሩ ሮጬ ቁልፉን ተጭኜ እስኪመጣልኝ እየጠበቅሁ አሰብኩበት ።

"ሆን ብላ የሌለ ነገር ፈጥራ ነው እምታስጨንቀኝ" አልኩኝ ለራሴ "ቪዳል የሸንኮራ አገዳ እርሻ ያለውን ወዳጁን ለመጠየቅ ወደ ሳንታ ሮዛ መሄዱን ሮቤርቶ ነግሮኛል ። እንዲያውም እያዘነ ነው ያጫወተኝ ።

"በጣም ረጅምና አድካሚ ጉዞ ነው ። ሲኞር በርዶን ። ምስኪን ጆስ የምሳ ሰዓት እንቅልፉን ሊያጣ ነው ። ከምሽቱ ሁለት ሰዓት በፊት ሊመለሱ አይችሉም " ነው ያለኝ ።

ወደታች ይዞኝ የወረደው አሳንሰር በር ተከፍቶ ወደ እንግዳ መቀበያው ክፍል ስገባ ሄንሪ ቪዳልን አየሁት ። እንግዳ ተቀባዩ ጠረጴዛ አጠገብ ቆሞ ወፍራም ፖስታ እየተቀበለ ነበር ።

ገና ሳየው ነዘረኝ ። አለሁበት ድርቅ ብዬ ቀረሁ ። መጥፎ ስሜት ቀስ በቀስ በሆዴ ውስጥ ሲሰራጭ ተሰማኝ ።

መምጣቴን ያወቀ ይመስል በድንገት ዞር አለና በአጭር እግሮቹ እየዘለለ ወደኔ መጣ ። በሚያስፈሩ ትንንሽ አይኖቹ ትክ ብሎ እየተመለከተ ።

"ጉብኝታችሁ እንዴት ነበር ?" ብሎ አምቧረቀብኝ

"ይሄን ያህልም እንደማይሆን እርግጠኛ ነኝ ። ካልመጣሁ ብላ ሙዝዝ ስትል አስጠንቅቄያት ነበር ። ሴቶች ሙዝዝ ካሉ አይመለሱም ። ከሰዓት በኋላ አልወጣችሁም እንዴ? ሙቀቱ ከበዳት ? ስትዝለፈለፍ ይታየኛል ። እኔን ያን ያህል ሞቆኝ አያውቅም ። እንዴት ይስማማኝ መሰለህ ። እየዋኘች መዝናናት ስትችል ። ይሄኔ እክፍሏ ውስጥ ተኝታ ይሆናል ። ምንም የምትሠራው ነገር የለ" አለና ፖስታውን ከፍቶ ይመለከት ጀመር ። የሆነ ነገር እንስቼ ላናግረው ብሞክርም አልቻልኩም ። አእምሮዬ በድንጋጤ ታውሯል ።



"ነገ እንሄዳለን" አለና ትናንሽ አይኖቹ አንዴ እኔን አንዴ ፖስታውን ተመለከቱ ።

"እኔና ባለቤቴ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ከአርባ አምስት ገደማ ተዘጋጅቶ እንወጣለን ። ማንኛውንም ነገር ላንተ ትቻለሁ ። ሚስተር ክሌይ በርደን ። የሠራተኞቹን ጉርሻ ፣ የእቃዎቹን - - -በዝርዝር እንድነግርህ አያስፈልግም ። ቀና ብሎ ተመለከተኝ ። "ለመልካም አገልግሎትህ ይቼን ሁለት መቶ ብር ተቀበለኝ ። ባለቤቴ በደንብ እንዳስተናገድካት ነግራኛለች ። በጣም አመሰግናለሁ ። "ብሎ አልፎኝ አሳንሰሩ ውስጥ ገባ ።

ቫል እስካሁን ወደ ክፍላቸው ተመልሳለች ። ይታወቅባት ይሆን ? አይመስለኝም ። እንደ እድል ነው ያመለጥነው ። በጣም ጠባብ እድል

እመዋኛው ገንዳ አካባቢ ጥቂት ሰዎች አሉ ። ህፃናት እየተንቦጫረቁ ይዋኛሉ ። ደረጃውን ወርጄ ከመዋኛ ሥፍራው ራቅ ብዬ አንዱ ጥላ ሥር ተቀመጥሁ ።

ህሊናዬ በፍርሃት ተበጥብጧል ። ቪዳል ተመልሶ መምጣቱን ቫል እንዴት ልታውቅ ቻለች ? አንድ ነገር ከመሆኑ በፊት የማወቅ ሀይል ይኖራት ይሆን ? ጉንጪ ጉንጯን በእጆቿ እየጨመቀች ስትጨነቅ ፊቷ እንዴት ተጨማዶ እንደነበር እስታወስኩ ። እቅርቤ ሲሆን ነው እንደዚህ የሚያመኝ "ያለችውም ትዝ አለኝ ። የሆነ መንፈስ አድሮብናል ። (MEDIUMS) ስለሚሉ ሰዎች በየጋዜጣው ላይ ባነብም ። እንዲህ አይነቶቹ አታላዮችና ቀውሶች መሆን ፣ አለባቸው ብዬ ደምድሜ ነበር ። ቫል ግን ቀውስ እንዳልሆነች እርግጠኛ ነኝ ።

"ማደር ? (መያዝ?) "

እትምህርት ቤት ሳለሁ መጽሐፍ ቅዱስ አጥንቼ ነበር ። ስይጣን ስላደረባቸው ሰዎች ያነበብኩት ትዝ አለኝ ። ቪዳል ሰይጣን መሆኑን ነግራኛለች ። ያ ፎኝን ቃል ቢቃል ፣ እስታወስኩ ።

"እርኩስ መንፈሶች ሰዎችን በተጽዕኗቸው ሥር ለማዋል ይጥራሉ ። እሱ እርኩስ መንፈስ ነው ! ሰይጣን ነው !"

ስለዚህ ጉዳይ አሁን እንደገና ጠይቄያት የምትሠጠኝን መልስ ሳላሾፍ ለማዳመጥ ጓጓሁ ። ግን ወደ ፓራዳይዝ ከተማ ከመመለሳችን በፊት ላናግራት አልችልም ።

ሌላ ሀሳብ በድ፣ ፡፡ ሰፌን አደረቀው ።

"ቪዳል በኔና በሷ መካከል ስላለው ግንኙነት ይጠራጠር ይሆን?" የቪዳልን ሾፌር ጆስን አገኘው ይሆናል ብዬ ተነሳሁና በሆቴሉ ጓሮ ዞሬ ታክሲዎች ወደሚቆሙበት ቦታ ሄድኩ ። አላገኘሁትም ። ወደ ሆቴሉ ተመልሼ ልገባ ስል ። ሮቤርቶን እጥላው ሥር ተቀምጦ ከሆቴሉ ተላላኪ ጋር ሲያወራ አየሁት ። ወደ እነሱ ስሄድ አየኝና ብድግ ብሎ መጣ ።

"የመጨረሻ ቀናችን ነው ሲኞር በርደን ። በጣም የሚያሳዝን ነው ። ሲኞሪና ቀዝቀዝ ሲል በመኪና እንዳንሸራሽራቸው ይፈልጉ ይሆናል?"

"አይመስለኝም" አልኩት ጉርሻ ፍለጋ መሆኑን ሳላውቅሁ ። እንደ ዚያ በማለቱ አስገርሞኝ ነበር ።

"ሚስተር ቪዳል በድንገት ስለተመለሱ የምትወጣ አይመስለ ኝም" ስለው ደስ አለው ።

"ለጆስ ጥሩ አጋጣሚ ነበር ። እስከ ሳንታ ሮዛ ድረስ መንዳት አልነበረበትም ። በሙቀቱ ምክንያት የሲኞር ቪዳል ጓደኛ እግማሽ መንገድ ድረስ መጥተው ነው የተቀበሏቸው ።"

"እንዲያ ነዋ" እፎይ ብዬ ተንፈስ አልኩ ። ቢዳል በኛ ላይ ምንም ጥርጣሬ የለውም ማለት ነው ። የተመለሰው እኛን እጅ ከፍንጅ ለመያዝ አልነበረም ።

"መኪናዋን ነገ ጠዋት በአንድ ሰዓት ተኩል ይዘህ መምጣት ትችላለህ?"

"አዎ ሲኞር በርደን ይተማመኑብኝ" አለና ቀጥሎ የምለውን በጉጉት ጠበቀ ።

"ሲኞሪና እማይፈልጉኝ ከሆነ ልሂዳ?"

"እስቲ ላረጋግጥ" ብዬ ወደ እንግዳ መቀበያቸው ክፍል ሄጄ ስልክ ደወልኩ ። ቫል ነበረች ያነሳችው ።

"በርደን ነኝ" አልኳት "ሮቤርቶ ለመጨረሻ ጊዜ በመኪናዋ ለመንሸራሸር ትፈልጊ እንደ ሆነ ማወቅ ይሻል ።"

"እስቲ ባለቤቴን ልጠይቅ ?" አለችኝ ። ድምጿ የተረጋጋ ይመስ



ላል ። ከጥቂት ዝምታ በኋላ "ግድየለም ። አልፈልግም በለው ። በኋላ ለመዋኘት ፈልገናል" ብላ ስልኩን ዘጋች ።

መሄድ የሚችል መሆኑን ስነግረው ሮቤርቶ በደስታ ከነፈ ። የምሠራው አልነበረኝም ። ብዋኝ ደስ ይለኝ ነበር ። ግን ቫልና ቪዳል ለመዋኘት ስለሚመጡ ተውኩት ።

ወደ ከተማይቱ ወርጄ ሙቀቱ እያቃጠለኝ ሱቆቹን እየተዘዋወ ርኩ ስመለከት ድንገት አንድ ነገር ትዝ አለኝ ። ለሮዳ ስጦታ መግዛት ነበረብኝ ። የምሰጣትን ሁሉ በደስታ ስለማትቀበለኝ ለሷ ስጦታ መግ ዛት ቀላል ነገር አይደለም ። ስለዚህም ብዙ ሳማርጥ ቆየሁ ። በመጨ ረሻው ከዘንዶ ቆዳ የተሠራ ቀበቶ ገዛሁላት ።

ወደ ሆቴሉ ተመለስኩና እቡና ቤቱ ገባሁ ። ጂን በቶኒክ አዝዤ እበረንዳው ላይ ተቀመጥኩ ።

ትደላድዬ ከተቀመጥሁ በኋላ ወደ መዋኛ ሥፍራው ተመለከትኩ ። ቫልና ቢዳል ከአንድ ዛፍ ጥላ ሥር ተቀምጠዋል ። ቪዳል የወይን ጠጅ ቀለም ያለው የዋና ልብስ ለብሷል ።

ጥቅጥቅ ያለው ሰውነቱ በከርዳዳ ጥቁር ፀጉር ተሸፍኗል ። ትክ ብዬ ስመለከተው አረመኔያዊ ሀይሉና ጥንካሬው ታየኝ ። እጫጭር እግሮቹና ጣንቃ የመሠለው ደረቱ ከሰው ይልቅ ዝንጀሮ አስመስሎታል ።

ድንገት ዞር አለና ተመለከተኝ ። አንድ ሰው ትክ ብሎ የሚመለ ከተው መሆኑ የተሰማው ይመስላል ። ከዚያ ለቫል አንድ ነገር ነገራት ። ወደኔ ዞር ብላ ፈገግ አለችና በጭንቅላቷ ምልክት ሰጠችኝ ። እሱም እጁን አንስቶ እንድቀላቀላቸው ጠቀሰኝ ።

* * *

ከሳን ሳልቫዶር ተነስቶ በጓቲማላ በኩል ወደ ማያሚ የሚበረው አውሮፕላን ሞልቶ ነበር ። አውሮፕላን ማረፊያው የደረስነው ከበረራው ሰዓት ሀያ ደቂቃ ቀድመን ስለነበር ቪዳል የመብረሪያችን ሰዓት ሲደርስ ጥራኝ ብሎ ቫልን ይዞ የክብር እንግዶች ወደሚያርፉ በት ክፍል ሄደ ።

እኔና ሮቤርቶ ጓዛችንን አዘጋጀን ። ከዚያ ስለጉዛችን ከአንድ ሆስቴስ ጋር ተነጋግሬ ሳበቃ ለሮቤርቶ ጉርሻ ሰጠሁት ። ያን ያህልም

ምስጋና የሚገባው ባይሆንም ስለሰጠን አገልግሎትም በደንብ አመሰገንኩት ።

የመጨረሻው ተሳፋሪ ፍተሻውን አልፎ ወደ አውሮፕላኑ ሲያመራ እንግዳ ማረፊያው ክፍል ገብቼ ጠራኋቸው ።

አውሮፕላኑ ውስጥ የአንደኛ ማእረግ ቦታቸውን መያዛቸውንና በሆስቴሷ ተገቢው እንክብካቤ እየተደረገላቸው መሆኑን ካረጋገጥኩ በኋላ ወደ መቀመጫዬ ሄድኩ ።

ከአንድ ሳምንት በኋላ ከቪዳል ረዳቶች አንዱ እሆናለሁ ብዬ አስብና እጠራጠራለሁ ።

ቫል ቪዳልን እመቺ በሆነ ጊዜ ስታገኘው ነገሩን እንደምታነሳለት ቃል ገብታልኝ ነበር ። ታዲያ በጣም ያስገረመኝ አመቺ ሆኖ ያገኘቺው ሳናስበው ከሄደበት በድንገት የተመለሰበትን ቀን ነበር ። ስንለያይ በፍርሃት ተሸብራ ነበር ግን ወዲያው ተረጋግታ ቪዳልን እንዲቀጥረኝ ልታግባባው መቻሏ በጣም ነው ያስደነቀኝ ።

እመቀኛው ስፍራ አብሬያቸው እንድቀመጥ ሲጠራኝ ቫል የእራት ልብስ እቀይራለሁ ብላ ሁለታችንን ትታን እንደሄደች ።

"ባለቤቴ ከረዳቶቼ አንዱ እንድትሆን ማሰቧ ብልህነት ነው" ። አለኝ ።

"ዳየር ሊያስብበት የሚገባ ጉዳይ ነበር ። ብዙ ገንዘብ ያድንልኛል ።" አለና ፍጥጥ ብሎ ተመለከተኝ "በርደን ሳንቲሞችን ካዳንክ ብሮቹ ራሳቸውን ይጠብቃሉ ። (ሚስተር ብሎ እንዳልጠራኝ አስተዋልኩ) ለወኪሎች የሚከፈል ኮሚሽን ከፍተኛ እንደሆነ ሊነግረኝ ይገባ ነበር ። ባለቤቴ ጠይቃህ ለኔ ለመሥራት ፈቃደኛ እንደሆንክ ነግራኛለች ። እኔም ይስማማኛል ። ለዝግጅት አንድ ሣምንት እሰጥሀለሁ ። የነገ ሣምንት ዳየርን እነጋግረው ። ባለቤቴም ካንተ ጋር ለመሥራት ትፈልጋለች ። ሥራውን ታውቀዋለች ። ጊዜም ያሳልፍላታል ። ሁሉም ሰው መሥራት አለበት ። በሙያህ ብቁ መሆንክን ነግራኛለች ። እንደሆንክም ተስፋ አደርጋሁ ። ዝርክርክነት አልወድም ። ነገ ፊ ጄን ጂስን ሻካርማንን እነጋግረው ። ኮንትራቱን እሱ ይጨርስልሀል ። መመሪያዎችን ከባለቤቴ ታገኛለህ ። ጥያቄ ካለህም እሷን ጠይቃት" ብሎ ተነሳ ። "ነቅተህና ጠንክረህ ከሠራህ ከኛ ጋር በመሆንህ ትደሰታለህ" ብሎኝ ወደ ሆቴሉ ተጣደፈ ።



ወደ ኋላ ደገፍ ብዬ ከአውሮፕላኑ መቀመጫ ጋር ወገቤን በቀበቶ አሠርኩ ። ተሳካ ። ከአንድ ሣምንት በኋላ እንደገና ከቫል ጋር ልሠራ ነው ። ጊዜውን ለስድስት አመት ወደ ኋላ እንደመመለስ ያህል ነው ። ትልቁ ምኞቴ ከሷ ጋር ለመሆን ነበር ።

"እሱ በማይኖርበት ጊዜ ሁሉ እንደዚህ አብረን መሆን እንችላለን" ብላ ቃል ገብታልኛለች ። እነዚያ ለሷ ስል የምኖርባቸው ቀናት ናቸው ።

በሚመጣው ሳምንት ስለምፈጽማቸው ነገሮች ሁሉ አሰብኩ ። ስለ ሮዳም አሰብኩ ። እቪዳል ጋ ስሠራ ከእድገትና ከገንዘብ ሌላ ምንም እንደማላገኝ እሷን ማሳመን ይኖርብኛል ። ሊኖራት የሚችለውን ቅንጣት ጥርጣሬ ሁሉ ደብዛውን ማጥፋት አለብኝ ።

ቫልም እሷ እምትሠራበት ሱቅ እንዳትሄድ ማስጠንቀቅ አለብኝ ። አልስን ካያት አደገኛ ነው እሚሆነው ። ማንነቷን ለሮዳ ይነግርና የአደጋውን ቀፎ ይከፍተዋል ።

እማያሚ አውሮፕላን ማረፊያ ደርሰን ከአውሮፕላኑ እንደወረድን ቪዳል "ጓዞችንን ተቆጣጠር" ብሎኝ ቫልን ይዞ ወደ ሚጠብቃቸው ሮልስ ሮይስ መኪና ገሰገሰ ። ከአንዳንድ ውጣ ውረድ በኋላ እቃዎችን በኩሌ አሸከሜ ስወጣ ቬሮኖን ዳየርን እንግዳ መሸኛው ክፍል ውስጥ አገኘሁት ። ሲያየኝ የስላቅ ፈገግታ እየሠጠኝ ፣

"እና ከኛ ጋር ተቀላቀልክ? አንተ ምስኪን ግራ የተጋባህ ሰው" አለኝ ።

"ቪዳል ነው የነገረኝ ። ወደ ባርነት ቤታችን እንኳን በደህና መጣህ ። የሚስተር ቪዳል ባለቤት እየተንቀሳቀሰች መሆኗን ሰምቻለሁ ። ሚስተር ቪዳል ለሷ መክፈሉን አቁሞ ላንተ ይከፈልሃል ። በኔና ባንተ መካከል ይቅርና አንዳንዴ በጣም አስቸጋሪ ትሆናለች ፤ ደግሜ እነግርሀለሁ ። አስቸጋሪ ትሆናለች ። አሥፈሪ የምትሆንበትም ወቅት አለ ።" ብሎ ፈገግ አለ ።

"ብስጭት መሆን አለበት ። ከሚስተር ቪዳል ጋር መኖር ቀላል አይመስለኝም ።" ሲለኝ ግጨው ግጨው አለኝ ። ግን እራሴን ተቆጣጠርኩ ።

"ጓዞችንን ይገኛለሁ" አልኩት ።

"ለኔ ተውልኝ፣ እየቀፈፈኝ የሱ ኩሊ የምሆንበት ቀን ዛሬ ብቻ በመሆኑ እምላክን እመሰግነዋለሁ። በሚመጣው ሰኞ እንገናኝ" ብሎ ሻንጣዎቹን በኩሊ አሸክሞ እውጪ ወደሚጠብቀው ቮልስዋገን መኪና ሄደ።

* * *

ቤታችንን እንደጠበቅሁት ተመሰቃቅሎ ነው ያገኘሁት። ሮዳም እልነበረች። ሳሎኑና የመኝታ ክፍሉ ምስቅልቅላቸው ወጥቷል። የፖት ኳኳልባቸው ነገሮች፣ የሲጋራ ቁራጮች፣ በየቦታው ተበታትነው ወድቀዋል። እልጋው አልተነጠፈም። የከንፈር ቀለሟን እምንጣፍ ላይ ጥላ እረጋግጠዋለች። የመታጠቢያው ክፍል ነገር አይወራ፤ ልብሶች በየቦታው ወድቀዋል። ይህን ሁሉ ለማጽዳት ከሁለት ሰዓት በላይ ፈጀብኝ። አፀዳድቼ ስጨርስ የምሳ ሰዓት ስለ ደረሰ ማርቲኒ ቀዳሁና ወደ። ወጥ ቤቱ ገባሁ። እንደጠበቅሁት ሰሞኑን ምንም ነገር አልገዛች ከጥቂት ሠርዲኖች በስተቀር ምንም የሚበላ ነገር የለ።

ወዴት ሄዳ ይሆን? እሁድ እሁድ ከቤት ወጥተን አናውቅም። እሷም እቤት ውስጥ ከወዲያ ወዲህ ስትልና እሰገነቱ ላይ ፀሐይ እየሞቀች ማሳለፉን ነበር እምትመርጠው ። አውሮፕላን ላይ አንድ ሲኒ ቡና ብቻ ስለነበር የቀመስኩት ራበኝ። ወደ ቡና ቤቱ ለመሄድ ስነሳ እሮዳ ከተፍ አለች።

"አ ሂሎ" አለችና ጉንጩን ሳም አደረገችኝ፣

"መቼ እንደምትመጣ በውል አላወቅሁም ጥሩ ጉዞ ነበር።?

እንደወትሮዋ ባትኳኳልም የሚያምርባትን ልብስ ለብሳ ነው የወጣችው።

"የት ነበርሽ ?"

ብቻዬን መቀመጡ ስላስጠላኝ ወደ ከበበ ሄድኩኝ። የሚበላ ነገር አለ እንዴ? ብላ ጠየቀችኝ "እንደሌለ ታውቂያለሽ፣ ይልቅ ወደ ቡና ቤቱ እንሂድ።"

"ምን መከራ ነው!? አሁንም ወደዚያ! ስትመጣ የሚቀመስ ነገር ይዘህ ትመጣለህ ብዬ ነበር።"



"ምንም አላመጣሁ። ብቻ አንድ ነገር ይሻር ልሻለሁ።" አል ኩና ቀበቶውን ሰጣኋት። ወዲያው ጉድለት አገኘችበት።

"ልኬ አይደለም። ደግሞስ ከምን ጋር ልታጠቀው ነው?"

"ያ የራሽሽ ችግር ነው። ነይ እንሂድ እርቦኛል፣"

ወደ ቡና ቤቱ ወረድንና ጥብስ አዘዝን።

"ከቪዳል ባልቴት ጋር እንዴት አሳለፍክ" አለችና የስላቅ ፈገግታ ሰጠችኝ።

"ተማረክህላት እንዴ?"

ዳቦውን አንስቼ ቅቤ ቀባ ቀባ እያደረግሁ፣

"ቅር ሳሰኝሽ በጣም አዝናለሁ፤ አንቺ እንደምታስቢው በሁለታችን መሀል የተፈጸመ ነገር የለም።"

"እሽ ሌላው ቢቀር አስቀያሚ አለመሆኗን እመን።"

"አስቀያሚ አለመሆኗን አምናለሁ።"

ትንኮሳዋ ሊያናድደኝ ባለመቻሉ ስትበሳጭ ታየኝ። "ወደ አልጋዋ ልትጐትትህ አልሞከረችም ነው እምትለኝ?"

"ይህንን የማይረባ ጨዋታ ብንተወውስ የኔ ሸጋ።" አልኳት ዝግ ብዬ።

"የሚጫወትሽ ቁም ነገር አለኝ ግን በጀመርኩት እቀጥላለሁ የምትይ ከሆን እስክትጨርሺ ልጠብቅሽ" እንዲህ ካላልኳት የምታቋርጠኝ አልመሰለኝም። ልክ ነበርኩ። ወዲያው በቁጣ ጋለች። እንደ ልጅ ሲቆጥሯት። አትወድም።

"እና ምንድነው ቁም ነገሩ?"

"ስለ ሚስስ ቪዳል ተናግረሽ እንደጨረሽ እርግጠኛ ነሽ?"

"ተወው እባክህ በርደን አትንቋሸሽብኝ! ይልቅ ቁም ነገር ያልከውን ንገረኝ፣"

"ሥራ ልለውጥ ነው። ቪዳል ከረዳቶቹ አንዱ እንድሆን ጠይቆኝ ተስማምቻለሁ፣" ስላት አይኖቿ ፈጠጡ።

"ከአሜሪካን የጉዞ ወኪል ድርጅት እለቃለሁ ነው እምትለኝ ።"

"ልክ ነሽ"

"ግን ለምን ?"

"የሚከፈለኝ ደመወዝ አሁን ከማገኘው እጥፍ ነው ። ስራውም በጣም ጥሩ ነው ። እና ላጣው የሚገባ እድል አይደለም ።"

"ነው እንዴ?" አስተናጋጅዋ ምግቡን ስታቀርብልን ዝም ብላ ተቀመጠች ።

"ጡረታህስ? አሁን አለህበት መሥሪያ ቤት ብዙ አመት ነው የሠራኸው ። ያበድክ ይመስለኛል ፡ በርደን ። ሚስተር ቪዳል አንድ ነገር ቢሆንስ? ከዚያ ምን ትሆናለህ ?"

"እስቤበት የማላውቀውን ጉዳይ ነው ያነሳችው ። ግን ለቪዳል ልሠራ የፈለግሁበትን እውነተኛ ምኝንያት ልንግራት አልችልም ።

"ምንም የሚያጋጥመው ነገር የለም ። የጡረታውንም ጉዳይ እስ ቦበታል ።"

ከጥብሱ ጎረስ ጎረስ አደረገች ።

"የምታደርገውን የምታውቅ ይመስለኛል ? ለመሆኑ የት ሆነህ ነው እምትሠራው ?

"ከቤቱ አቅራቢያ ቢሮዎች አሉት ።"

"ሄይ እኔስ?" ብላ የያዘችውን ቢላና ሹካ አስቀመጠችና አፈጠጠችብኝ ።

"ወደ ሥራዬ በምን ልመላለስ ነው?"

"ከማገኘው ተጨማሪ ደሞዝ መኪና ልገዛልሽ እችላለሁ" ስላት አይኖቿ በሩ ።

"እውነትህን ነው ? ታዲያ የማይረባ መኪና እንዳትገዛልኝ አውስቲን ወይም ቶዮታ ነው እምፈልገው"

"የፈለግሽውን አይነት ነው አምገዛልሽ?"

"ተስማማና" አለች ። ደስ እንዳላት ከሁኔታዋ ይታወቃል ። ስለ መኪናዋ ስታስብ ሌላ ተቃውሞ ልታነሳ አልቻለችም ። እሷን ማሸነፍ



ይህን ያህል ቀላል ነበር ። ሆኖም ማታ ቴሌቪዢን ተመልከተን ልንተኛ ስንል ድንገት ፡

"ባልቴቷን እንደልብህ ታያታለህ?" አለችኝ ።

"ማንን?"

"ሚስስ ቪዳልን"

"አይመስለኝም ፡ እንደሰማሁት ከሆነ አብዛኛውን ጊዜ ከሚስተር ቪዳል ጋር አብራ ነው የምትጓዘው ።"

"እ" አለችና ዝም አለች በዚህ አይነት መቀጠሉዋ ዋጋ እንደ ሌለው ሲሰማት ።

"ናፍቀኸኛል እኮ ና እንተኛ ብላ ወደ መኝታ ክፍላችን ይዛኝ ገባች ። ከሷ ጋር ፍቅር በምንለዋወጥበት ጊዜ ሁሉ ገላዬ እንጂ ልቤ ከቫል ጋር ነበር ። ሮዳ ሁኔታዬን ስላወቀች ፣

"ምን ሆነሀል ? እንደወትሮህ አይደለህም" አለችኝ ።

"አዝናለሁ በሀሳብ ተጠምጄ ነው" ስላት ጀርባዋን ሰጥታኝ ተኛች ። ረዘም ላለ ጊዜ ስለቫል አሰብኩ ። ከእኩለ ሌሊት በኋላ ነበር እንቅልፍ የወሰደኝ ።

* * *

ሳምንቱን በመጣደፍ አሳለፍኩ ። አልሰን መምጣቱ ብዙ ጠቀመኝ ። ማሲንግሀምንም አግኝቼ ቪዳል ስለሠጠኝ ሥራ አጫወትኩት ። አልተቃወመኝም ።

"ያ ያንተ ምርጫ ነው በርደን" አለ ሚስንግሀም

"ስናጣህ በጣም ነው እምናዝነው ። የምትወስደው እርምጃ ትክክል መሆኑን እምነህበታል? ቪዳል መጨበጫ የሌለው ሰው ነው ።"

"እኔ እንደዚያ አልልም ። ብዙ አስቤበታለሁ ። ለውጥ ያስፈልገኛል ። አሁን ከምሠራው ሥራም ለየት ያለ ይሆንልኛል ። ክፍያውም ጥሩ ነው ።"

"በጄ ። ሞክረው ። ሥራውን ጀምረውና ካልወደድከው ወደ እኛ ተመለስ ፣ ላንተ የሚሆን ቦታ አናጣም ።" አለኝ ።

ያሄ ከጠበቅሁት በላይ ነበር ።

እቪዳል ነገሬፌጅ ጂሰን ሻከርማን ጋ ሄድኩ ። ኮንትራቱን አዘጋጅቶ ነው የጠበቀኝ ። ቀላል ውል ነበር ። እኔ ሥራውን ለመልቀቅ ወይም እነሱ ሊያባርሩኝ ከፈለጉ ከስድስት ወር በፊት ማሳወቅ ይኖርብናል ። ኮንትራቱ ለሶስት አመት ሆኖ በያመቱ የደመወዝ ጭማሪ ይኖረኛል ። ፈረምኩ ፤ ፈረመበት ።

ሮዳም የገዛሁላትን አውስቲን ወደደቻት ። በሥራ ብጠመድም ቀኑ አላልቅ እያለኝ ተቸገርኩ ። ከቫል ጋር የምገናኝበትን ወቅት በጉጉት እየጠበቅሁ ነው ።

ቅዳሜ ጠዋት እጠረጴዛዬ ላይ ያሉትን ወረቀቶች ሳስተካክል ዳየር መጣ ።

"ለሰኞ እየተዘጋጀህ ነው እንዴ?" ጠየቀኝ ።

"ሥራውን ሁሉ ላንተ እየተውኩ ነው ። በጣም ብዙ ሥራ ነው እሚጠብቅህ ። በሳምንቱ መጨረሻ ቪዳል ወደ ውጪ ይሄዳል ። ብዙ የራስ ምታት መድሐኒት ማምጣት ይኖርብሀል ።" ብሎ ከፖስታ ውስጥ አረንጓዴ ካርድ አወጣና ፤

"ይሄ ማለፊያህ ነው ። እመግቢያው ላይ ስትደርስ ለዘበኛው ታሳየዋለህ ። እንዳትጥለው" ብሎ ቢሮዬን ቃኘት ቃኘት አደረገና እጠረጴዛዬ ጠርዝ ላይ አረፍ አለ ።

"ይህንን ሥራ ለምን እንደምትለቅ አልገባኝም ። እዚህ ሀላፊው አንተ ነህ ። በተወሰነ ሰዓት ነው የምትሠራው" ብሎ ትከሻውን ነቀነቀ ።

"ራስህን እየቀበርክ ነው ። ከቪዳል ጋር አንድ ሁለት ሳምንት እንደሠራህ ይህኛውን ሥራህን ታመሠግናለህ ።" በትካዜ ተመለከተኝ ።

"ሚስስ ቪዳልን በጥንቃቄ ያዛት ። እውነቱን ነው እምልህ ። በሁለታችን መካከል ይቅርና በጣም ግራ የምታጋባ ሴት ነች ። አንድ ቀን ደህና የሆነች እንደሆን ሌላ ቀን ተለውጣ ነው እምታገኛት ።

ከሁለት ወራት በፊት ምን አይነት ነገር የገጠመኝ መሰለህ? እኔና እሷ ትልቅ የራት ግብዣ ለማዘጋጀት እቅድ ስናወጣ ከምንጠራቸው እንግዳዎች የአንዱን ስም ሁለታችንም ማስታወስ ያቅተናል ።



ተስፋ ቆርጠን ልንተወው ስንል ስሙ ድንገት ትዝ አለኝና ጣቴን እንደዚህ አጮህኩ" ብሎ ጣቱን እያጮኸ አሳየኝ ።

"ብታምንም ባታምንም ድምፁን ስትሰማ ፍዝዝ አለችና ድርቅ ብላ ተቀመጠች ። አይኖቿ ባዶ ሆኑ ፤ ነሆለለች ፤ እንዲህ ሆና ሳያት እንዴት ደነገጥኩ መሠለህ? የማታ ክበብ ውስጥ በዚህ አይነት ሁኔታ ሰዎችን ሲያዝናኑበት አይቻለሁ ። ስለዚህ እፊቷ ጣቴን እንደገና ሁለት ጊዜ ሳጮህ ነቃች ። የሆነውን ሁሉ የምታስታውስ አትመስልም ።" ብሎ ወርቃማውን የሲጋራ መያዥያ አውጥቶ ጋበዘኝ ።

"ግራ ያጋባል አይደል?"

የተሰማኝ ስሜት በፊቴ ላይ እንዳይታይ ሲጋራውን አልተቀበልኩም ።

"እና አልነገረኝም እንዳትል" አለኝ ፤ "ባርያህ ልታደርጋት እስካልፈለግህ ድረስ እሷ ፊት ጣትህን ማጮህ የለብህም ። በተለይ ቪዳል ባለበት እንደዚያ ማድረግ አደገኛ ነው እሚሆነው ።"

"ይቅርታ አድርግልኝ" አልኩት በንቀት "ዝግጅት እያደረግሁ ነው ።" ብዬ አንድ መሳቢያ ከፍቼ እውስጡ ያሉትን ነገሮች ማውጣት ጀመርኩ ።

"በወሬ ስራ ላስፈታህ አይገባም" ብሎ ከጠረጴዛው ላይ ተነሳ ።

"መልካም ቅዳሜና እሁድ ይሁንልህ" ብሎ ወደበሩ ተራመደ ከዚያ ቆም አለና

"አ አንድ ነገር ረስቼ ። ቪዳል በሳምንት ሰባት ቀናት ነው እሚሠራው ። በሳምንቱ መጨረሻ ላይ እረፍት መጠበቅ የለብህም ። እኔም አርፌ አላውቅ ።" እንደዚያ ብሎኝ ደስ እያለው ጥሎኝ ወጣ ።

እልሰን ወደ ቢሮዬ ስለገባ ስለ ቫል ዳየር የነገረኝን ላስብበት አልቻልኩም ። እስከ ስድስት ሰዓት ሁላችንም በሥራ ተወጥረን ቆየን ። የመጨረሻ ቀኔ ስለሆነ ፀሐፊዬንና እልሰንን ከእኔና ከሮዳ ጋር ምሳ እንዲበሉ ጋበዝኳቸው ። ምሳውን በልተን ስንለያይ ሮዳ እቃ ለመግዛት መፈለጓን ነገረችኝ ። አሁን የራሷ መኪና ስላላት ትቻት ወደ አፓርታማው ተመለስኩ ።

እሰገነቱ ላይ ቁጭ ብዬ ዳየር ስለ ቫል ያጫወተችኝን አስታወስኩ ። እሷ ያለችኝም ትዝ አለኝ ። በርግጥ ቪዳል የሰውን አእምሮ በተጽዕኖው

ሥር የማጥል ሀይል አለው? ካለውስ ቫል በተጽዕኖው ሥር ነች ማለት ነው? ከሆነችሽ ወዳጆች መሆናችንን በቀላሉ ሊያውቅ አይችልም?

ስለአደገኛነቱ ያጫወተኝንና ፍርሀቴን ሳስታውስ እሰገነቱ ላይ ተረጋግቼ ልቀመጥ አልቻልኩም ። ከዚህ አስጨናቂ ሀሳብ ለመላቀቅ አንድ ነገር ማድረግ አለብኝ ።

ልብሴን ለውጬ ወደ ጐልፍ ክበብ አመራሁ ። ጆ ሀርክነስን የሚያጫውተው ሰው ሲፈልግ አገኘሁት ። ገና ሲያየኝ ፊቱ ፈካ ።

"ዛሬ መሸነፍህ ነው" አለኝ "በደንብ ነው የተዘጋጀሁት ።"

ቫልን እያሰብሁ ሀሳቤን ሰብስቤ ልጫወት አልቻልኩም ። በሀይወቱ ተጫውቼው የማላውቀው አይነት መጥፎ የጐልፍ ጨዋታ ተጫወትኩ ።

ተያይዘን ወደ ቡና ቤቱ ስንሄድ ሀርክነስ "አንድ የሚያስጨንቅህ ነገር እንዳለ ይታየኛል ። ምንድነው? ዳየር እየረበሸህ ነው እንዴ?" ብሎ ጠየቀኝ ። ውሎ አድሮ መስማቱ የማይቀር መሆኑን ስላወቅሁ ከነገ ጀምሮ ለቪዳል የምሠራ መሆኑን ነገርኩት ። ዜናው አስደነገጠው ።

"ጥሩ ነገር ነው ብለህ ነው በርደን? በእርግጥ የሚያገባኝ ነገር የለም ግን በኔ በኩል ሥራ እንኳ ባጣ ከቪዳል ጋር የምሠራ አይመስለኝም ።"

"ተንኰለኛ ሊሆን ይችላል ግን የሚከፍለኝ ደሞዝ ጥሩ ነው ። ለውጥም ፈልጌያለሁ ።"

"ለስንት ጊዜ አብረኸው ልትሠራ? በዚህ አይነት ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆይ አይመስለኝም ። የገነባው ሁሉ ከአሁኑ መሸተት ጀምሯል ። እውነቱን ነው ከሱ ከተላቀቅን በኋላ ነው ጥሩ እንቅልፍ ያገኘሁት ። በቅርቡ በአስደናቂ ሁኔታ እንደሚወድቅ ነው የሚሰማኝ ።" ሲለኝ ትክ ብዬ ተመለከትኩት ።

"እንደሱ ሊሰማህ ይችላል ግን ምን ተጨባጭ ማስረጃ አለህ?"

"ምንም ተጨባጭ ነገር የለኝ ። ሰዎች ግን እንደዚያ ያወራሉ ። ካለ እሳት ጭስ ይኖራል? " ሌላ ሰው በአቅራቢያችን አለመኖሩን ለማረጋገጥ ገልመጥ ብሎ ተመለከተና ቀጠለ ፣



"አንድ በርግጥ የማውቀው ነገር አለ ። ዱቤ ከሚሰጡት ድርጅት አንዱ አሁን የተፈራረሙት ውል ሲያልቅ የስድስት ወር መሆኑ ቀርቶ የአንድ ወር ዱቤ ብቻ ሲሰጠው ወስኗል ይሄ በሌሎቹ ድርጅቶች ሲሰማ ሁሉም እንደዚያ ማድረጋቸው የማይቀር ነው ። በርደን የናንተስ ድርጅት ይህንን ሲሰማ ዝም የሚል ይመስልሀል? ቪዳል እንዲህ አይነት ነገር የሚያጋጥመው መሆኑን ከጠረጠረ የጉዞውን ጉዳይ የሚያስፈጽምለት እንዳተ አይነት የሰለጠነ ሰው መቀጠሩ ብልህነት ነው ። ቢያንስ ለወኪሎቹ የሚከፍለውን ገንዘብ ያድናል ።"

ፍዝዝ ብዬ ተመለከትኩት ። ሀሳቡን ባልቀበለውም እንደዚህ ታይቶኝ አያውቅም ነበር ። ቪዳል በርግጥ ይህንን ጠርጥሮ ከሆነ የቀጠረኝ የሚያስገርም ነው ።

"ያም ቢሆን ቢወድቅም እኔን የሚያስጋኝ ነገር የለም ። ማሲን ግሀም ሥራ እንደሚሰጠኝ ቃል ገብቶልኛል ። ጥቂት ገንዘብ እስካገኝ ቪዳል እንደሚቆይም ተስፋ አለኝ ።" ስለው ፣

"እኔም ተስፋ አደርጋለሁ" አለኝ በስጋት እየተመለከተ ።

"አሁን ብሄድ ይሻለኛል ። አሊያ ባለቤቴ ቆዳዬን ነው እምትገፈው በሚቀጥለው ሳምንት እንገናኝ ።"

ከሄደ በኋላ ያለኝን ሁሉ አሰብኩበት ። ማስንግሀም ብድር ገጣቸችን ጠይቆ ቪዳል የራሱ የሆነ ነገር እንዳሌለው አጣርቶአል ። ያሉት እቃዎች ሁሉ የኪራይ ናቸው ። ያኔ ያልኩት ትዝ አለኝ ።

ማስንግሀም መልሶ እንደሚቀበለኝ ባያረጋግጥልኝ ኖሮ በስጋሁ ነበር ። አሁን ግን ግድ የለኝም ። ዳቦዬን እምገምጥበት ሁኔታ ላይ ነው ያለሁት ።

ከጐልፉ ክበብ ወጥቼ ወደ ከተማ ወርጄ ለሳምንቱ መጨረሻ የሚሆን አስቤዛ ገዛሁ ። የህዝብ ቤተ መጻሕፍቱም ከመንገድ ባሻገር ስለሆነ አስቤዛውን እመኪናዬ ውስጥ ወርውሬ ወደዚያ አመራሁ ።

ደርበብ ያለች ትልቅ ሴት በፈገግታ ተቀበለችኝ ።

"ሚስተር በርደን መሆን አለብህ" አለችኝ ። "ወደኛ የምትመጣበትን ቀን በጉጉት ነበር እምጠብቀው ።"

ደነቀኝ ።

"ስሜን በምን አወቅሽው?" ብዬ ስጠይቃት ሳቀች ።

“ወደ ከተማችን የሚመጡትን አዳዲስ ሰዎች ማወቅ አለብኝ ። የአሜሪካን የጉዞ ወኪል ድርጅት ውስጥ አይደል የምትሠራው? ቢሯችሁም እስፓኒሽ ቤይ ሆቴል ውስጥ ነው ። ምን ልርዳህ? ሚስተር በርደን”

በስነ አእምሮ ጥበብ አእምሮን በተፅዕኖ ሥር ስለማዋል የተጻፈ ነገር እንዳለ ጠየቅኋት ።

“በዚያ ላይ ብቻ የተሠራ ነገር የለንም ። በስንክሳሩ (ኢንሳይክሎፖዲያ) ውስጥ ጥቂት ተጽፎ ታገኛለህ ላምጣልህ?” አለችኝ ።

ብዙም ባይሆን ከስንክሳሩ ውስጥ ጥሩ መረጃ አገኘሁ ። ሴቶች ከወንዶች ይልቅ በቀላሉ በተፅዕኖ ሥር ሊውሉ እንደሚችሉ ፤ በተጽዕኖ ሥር የዋሉ ሰዎች የማይፈልጉትን ነገር እንዲያደርጉ ማስገደድ አለመቻሉን ፤ ራሳቸውን እንዲጐዱ ሊታዘዙ አለመቻላቸውን ፣ የሚጠሉትን ምግብ እንኳ እንዲበሉ ማድረግ እንደማይቻል ፤ ግን በተፅዕኖ ሥር ያዋላቸው ሰው የበሬ ስጋን የአሣ ስጋ ነው ብሎ ሊያሣምናቸው እንደሚችል ፤ የተለመደና መጥፎ ያልሆነ ነገር ከሆነ ግን በትዕዛዝ ሊፈጽሙት እንደሚችሉና ከተጽዕኖው ሲላቀቁ ያደረጉትን ለማስታወስ እንደማይችሉ ፤ እንዲህ አይነቱ ነገር ባለሙያ ባልሆነ ሰው ከተደረገ አደገኛ ሊሆን እንደሚችል ተገነዘብኩ ።

የተዘረዘረው ትክክል ከሆነ አእምሮው በተጽዕኖ ሥር የዋለው ሰው በደህና ቀን ሊያደርገው የማይፈልገውን ነገር እንዲያደርግ ማስገደድ አለመቻሉን ማወቁ ለኔ አንድ ተስፋ ነበር ። እንደጽሑፉ ከሆነ ቪዳል እኔና ቫል ወዳጆች መሆናችንን እንድትናዘዝ ሊያስገድዳት አይችልም ማለት ነው ።

በመጠኑም ቢሆን ተጽናንቼ ስለጉዳዩ እያሰብኩ ወደ ቤቴ ሄድኩ ። ምግብ ሳዘጋጅ ሮዳ መጣች ።

“እራት እየደረሰ ነው” አልኳት “የፈለግሽውን ሁሉ አገኘሽ?”

“አላገኘሁም ። ማርቲኒ ቅዳልኝ የኔ ሸጋ እግሬን እየቆረጠመኝ ነው ።”

እግሯ ደህና የሆነበት ቀን ትዝ አይለኝም ።

“ምን ነበር ለመግዛት የፈለግሽው?”

“በተለይ የምፈልገው ነገር አልነበረኝም ። አንድ ነገር ባገኝ



ብዬ ነበር ግን ሁሉም ነገር ውድ ነው ። ያም ሆኖ ባልቴቷ የባሏን ብር በየቦታው ከመርጨት አልተቆጠበችም” ስትለኝ ተሸማቀቅሁ ።

“ሮዳ ሚስስ ቪዳልን ሁሌም ባልቴት እያልሽ መጥራት ይኖርብሻል እንዴ?”

“ለምን አልላትም? ቅር ይልሃል ?”

“ቅር አይለኝም” አልኩና መጠጡን ቀዳሁላት “ካስደሰተሽ እንደፈለግሽ ጥሪያት”

“አመሰግናለሁ ። እንዳሻኝ እጠራታለሁ ። ኤልዛቤት አርደን መደብር ውስጥ እቃውን ሁሉ እያግበሰበሰች ስትገዛ አየኋት ። ሰላም እንዳትለኝ ኮርታ የሽርደዳ ፈገግታዋን ወረወረችልኝ ።

“እንዴት አይነት መጥፎ አጋጣሚ ነው?” ስላት አይኗ ተጉረጠረጠ ።

“እታፌዝብኝ ሚስትህ መሆኔን ታውቃለች እንዴ?” ዝም ብያት ወደ ሰገነቱ ወጣሁና እራት የምንበላበትን ጠረጴዛ ማዘጋጀት ጀመርኩ።

“ሚስቱ መሆንሽን በምን ልታውቅ ትችላለች?”

“አንተ ነግረሀት ይሆናል? ደንበኛዬ ነች እኮ ነግረሀታል?”

“አልነገርኳትም ። ለመብላት ተዘጋጅተሻል?”

“ያንተ ሚስት መሆኔን ብታውቅ ታነጋግረኝ ነበር”

“ልታነጋግሪያት ከኝኝሽ ሳገኛት ሚስቴ መሆንሽን እነግራታለሁ።”

“ሳገኛት፣ ታገኛታለህና ምን ማለትህ ነው?”

“ብዙ ጊዜ እንደማትኖር ነግሬሻለሁ” ስላት የምፀት ፈገግታ ወረወረችልኝ ።

“እንዴት አይነት መጥፎ አጋጣሚ ነው?” አለችና ከት ብላ ሳቀች ።

*   *   *

እሳሎን ውስጥ ያለው ስልክ ሲያንቃጭል ከእንቅልፌ ቀሰቀሰኝ። ምንም ያህል የተኛሁ አልመሰለኝም ። ቴሌቪዢን ስንመለከት አምሽተን እኩለ ሌሊት ላይ ነው የተኛነው ።

ድብት እድርጎኝ እየተራገምኩ አልጋችን አጠገብ ያለውን መብራት አበራሁ ።

ሮዳም ተነስታ ቁጭ አለች ። ፊቷ በባዝሊን ተለብጦ ፀጉሯ ተንጨፍሮ ሳያት ሰይጣን መሰለችኝ ።

"ምንድነው እሱ?" አጉረጠረጠች "መብራቱን አጥፋው ።"

"ስልኩ ነው" አልኳት ነጠላ ጫማዬን ለማግኘት እየዳሰስኩ ።

"ገደል ይግባ የተሳሳተ ቁጥር መሆን አለበት ። ዝም በለውና ያንቃጭል"

ለአሜሪካን የጉዞ ወኪል ብዙ አመት ስሠራ ለምጀው መሆን አለበት ስልክ እየጮኸ ዝም ማለት አልችልም ። ወደ ሣሎኑ ተንገዳገድኩና አነሳሁት ።

"በርደን አንተ ነህ?"

ብደነግጥም የቪዳልን ድምጽ ወዲያው ለየሁት ።

"አዎ ። ሚስተር ቪዳል ነህ እንዴ?"

"አዎ እኔ ነኝ በርደን ነገ ጠዋት . . . ዛሬ ጠዋት ልክ በሶስት ሰዓት ተኩል እሳንሳልቫዶሮ መገኘት አለብኝ ። ስለዚህ ጉዞውን አዘጋጅተህ ጥራኝ" አለና ስልኩን ዘጋው ።

ረዘም ላለ ጊዜ በእጄ ላይ ያለውን መነጋገሪያ ተመለከትኩት ። ከዚያ ቀስ ብዬ አስቀመጥኩትና ሰዓቴን ተመለከትኩ ። ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ከሩብ ነው ።

ከዚህ በፊት ወደ ሳንሳልቫዶር የተደረገውን ጉዞ ሳዘጋጅ ያየሁት ፕሮግራም ትዝ አለኝ ። ዛሬ ጥዋት በሶስት ሰዓት ተኩል እዚያ ሊያደርሰው የሚችል አውሮፕላን የለም ።

በመጀመሪያ ለአሜሪካን የጉዞ ወኪል የምሽት አገልግሎት ደውዬ ሳገናኘው እስቤ ነበር ። ትዝ ሲለኝ ዛሬ ለካ ሰኞ ጠዋት ነው ። ከዛሬ ጀምሮ የቀጠረኝ ስለሆነ ጉዳዩን ማስፈጸም የኔው ሀላፊነት ኖሯል ።



እስፓኒሽ ቤይ ሆቴል የነበረኝን ቢሮ ለቅቄ ከመውጣቴ በፊት የመረጃ መጻሕፍቶቼንና ቻርቶቼን ይገፎ ነው የመጣሁት ። ካለነሱ መረጃ እንደሌለው ቱሪስት የምጨብጠው ነው እማጣው ።

ቪዳል እሳን ሳልቫዶር በሶስት ተኩል መገኘት እንዳለበት ነው የነገረኝ ። በዚያ ሰዓት ሊያደርሰው የሚችል አውሮፕላን እለመኖሩንና የአየር ታክስ ይፈልግ እንደሆነ ደውዬ ልጠይቀው አልፈለግሁም ። እንደሀብቱ የአየር ታክስ ቢከራይ ምንም ሊጐዳው አይችልም ።

ስለዚህ የፍሎሪዳን የአየር ታክስ አገልግሎት የማታ ክፍል ሀላፊ የሆነውን ሮጀር ኤቨርትን በስልክ አነጋገርኩት ።

"ምንም ችግር የለውም ሚስተር በርደን" አለኝ ። ታክሲው በአሥራ ሁለት ከአርባ አምስት ነው የሚበረው ። ያንተ ሰው ትኬቱን አውሮፕላን ማረፊያው ሲመጣ ሊያገኝ ይችላል ። ይስማማል?"

"ጥሩ ነው ለወጥ ካለ እደውልልሀለሁ ። ዋጋው ስንት ነው?"

"ከነመመለሻው ነው?"

"ላይሆን ይችላል ። ለመሄድና ለመመለሺያ የሚከፈለውን ለይተህ ንገረኝ?"

"መሄጃያው ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አምስት ዶላር ነው ። መመለሺያው አንድ ሺ ሶስት መቶ ዶላር ነው ።"

"ከግማሽ ሰዓት በፊት ካልደወልኩልህ የመሄጃውን ገንዘብ ብቻ ያዝልኝ"

"እሺ የመንገደኛውን ስም ትሰጠኛ?"

"ሚስተር ሄንሪ ቪዳል ከፓራዳይዝ"

"እስቲ ድገምልኝ" አለኝ ጮክ ብዬ ደገምኩለት ።

"ይሄ እጅ በእጅ የሚከፈል ነው ሚስተር በርደን ዱቤ እንስጥም ።"

"ሚስተር ቪዳል የአንድ ወር ዱቤ ይፈልጋል ። እንደዚያ ነው የሚከፈለው ።"

"እጅ በእጅ ካልከፈሉ መጓዝ አይቻልም ሚስተር በርደን ። መመሪያ ተሰጥቶኛል ።"

"በአሁኑ ሰዓት ገንዘብ ማግኘት ያስቸግር ይሆናል" አልኩት ማላብ እየጀመረኝ ። ባንኮቹ . . ."

"መመሪያ ነው ሚስተር በርደን ። ባልኩህ ትስማማለህ ወይስ ይሠረዝ?"

ሮዳ በበሩ ብቅ ስትል እደውልልሃለሁ ብዬ ስልኩን ዘጋሁት ።

"ምንድነው እሱ?" ብላ ጮኸች "ስለ እግዚአብሔር ብለህ እንተኛ ከጥቂት ሰዓት በኋላ ሥራ እሄዳለሁ እኮ"

"ሂጂና ተኚ አታስቸግሪኝ" ብዬ ተቆጣሁና ለሚስተር ቪዳል ደወልኩለት ።

"የሚስተር ቪዳል መኖሪያ ቤት ነው" አለኝ አንድ በጉራ የተነፋ ድምፅ ።

"ሚስተር በርደን ነኝ ። ከሚስተር ቪዳል ጋር አገናኘኝ" ጥቂት ቆይቶ ቪዳል ስልኩን አነሳ ።

"ጨረስክ በርደን?" አለኝ በተሰላቸ ድምፅ ።

"ሚስተር ቪዳል በሶስት ተኩል እሳንሳልቫዶር የሚያደርስህ አውሮፕላን የለም በአሥራ ሁለት ከሩብ የሚነሳ የአየር ታክሲ ይገኛልሀለሁ ። ስለዚህ ልክ በአሥራ ሁለት ከሩብ አውሮፕላን ማረፊያው እንድትገኝ ። ትኬቱንም እዚያው ታገኘዋለህ ። አውሮፕላኑ አድርሶህ እዚያው እንዲጠብቅህ ትፈልጋለህ? ካልፈለግህ በሌላ አውሮፕላን ቦታ እይዝልሃለሁ ።"

"ያንን ሳንሳልቫዶር እንደደረስኩ እኔው እፈጽመዋለሁ ። ታክሲው እዚያ እንዲቆየኝ አልፈልግም ።"

"መልካም ። አንድ የቀረ ነገር አለ ሚስተር ቪዳል ። ዋጋው ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አምስት ብር ሆኖ እጅ በእጅ ነው እሚከፈለው ።" የመጨረሻውን ቃል ጫን ብዬ ነው የተናገርኩት ።

"በኔ የባንክ ሂሳብ እንዲይዙት ንገራቸው" አለና ስልኩን ዘጋው ።

"እየተራገምኩ እንደገና ደወልኩለት ። ስልኩ አጠገቡ መሆን አለበት ። ምክንያቱም ወዲያው አነሳው ።

"አሁን ደግሞ ምንድ ነው ። ?



"በርደን ነኝ ሚስተር ቪዳል ከፍሎሪዳ የአየር ታክሲ አገልግሎት ጋር የባንክ ሂሳብ ስለሌለህ ገንዘቡን እጅ በእጅ ነው የሚፈልጉት ።

"ምንድነው እሚፈልጉት !?" ጮኸ፤ መነጋገሪያውን ሊያስጥለኝ ነበር ።

"ሀላፊው በምንም አይነት እንደማይችል ነው የነገረኝ ሚስተር ቪዳል ።" አልኩት ። "አዝናለሁ አውሮፕላኑ ከመነሳቱ በፊት የትኬቱ ዋጋ መከፈል አለበት ።"

"በኔ ላይ ማንም እንደዚያ ሊያደርግ አይችልም" ! ብሎ ሲጮህ የደም ስሮቹ ተበጣጥሰው ሊወድቁ የተቃረበ ይመስል ነበር ።

"በደንብ አድምጠኝ ክሌይ በርደን የቀጠርኩህ ባለቤቴ በሞያው ብቁ መሆንህን ስለነገረችኝ ነው ። ስለዚህ ብቃት ይኑርህ ። ያን የማይረባ ሰው የአንድ ወር ዱቤ እንዲሰጠኝ፣ ንገረው ። አለያ ሥራህን ታጣዋለህ በለው" ብሎ ስልኩን እጀርዬ ላይ ደረገመው ።

ቁና ቁና እየተነፈስኩ ቁጭ አልኩ ። ከዚያ ራሴን አበረታቼ ተነሳሁና ለአየር ፣ ታክሲው አገልግሎት ደወልኩ ። ኤቨርት ስልኩን አነሳ ።" ክሌይ በርደን ነኝ" አልኩኝ፣ ድምጼን አጣፍጬ ።

"ሚስተር ቪዳል ባንክ ከመከፈቱ በፊት ያን ያህል ገንዘብ ሊያገኝ አልቻለም ። ይሄንን እንደውለታ ልትፈጽሙልን አትችሉም ። ጥሩ መሆናችሁን ካወቀ ከናንተ ጋር ብዙ ሥራ ሊሠራ ይችላል ፣"

"ካልከፈሉ መጓዝ አይችሉም ። የተሰጠኝ መመሪያ ይሄ ነው ። ሚስተር በርደን በጣም አዝናለሁ ።"

"ሚስተር ቪዳል ተንኮለኛ ሰው ነው ሚስተር ኤቨርት ። ይህን ጉዳይ ወደ ባላዮችህ ሊያደርሰው ይችላል ።" ስለው አጉተመተመና ፣

"ያ ድውይ ከሥራው አስወጣዋለሁ ብሎ ዛተ እንዴ ?"

"አዎ ፣ እንደዚያ ያሰበ ይመስለኛል"

"እውነትህን ነው? ከኔ አንድ መልእክት ልታስተላልፍለት ትችላለህ? ገደል ግባ ብሎሀል በለው ልድገመው እንዴ ሚስተር በርደን?"

"አያስፈልግም ። አመሰግናለሁ ሚስተር ኤቨርት ፣ በግልጽ ነው የነገርከኝ ። ካልከፈሉ መጓዝ አይቻልም ።"

"እንደዚያ ነው ። ልሠርዘው እንዴ?"

"እንደገና እደውላለሁ" አልኩት እየሰጋሁ ወደ ቪዳል ቤት ደወልኩ ። ሲጠብቀኝ የቆየ ይመስል ቪዳል ስልኩን አነሳው ።

"እሺ በርደን ጨረስከው እንዴ?" እምቧረቀብኝ ።

"አዝናለሁ ሚስተር ቪዳል ። ኤቨርት ያለውን በትክክል ብደግምልህ ይሻል ይመስለኛል ። ካልከፈሉ መጓዝ አይቻልም ነው ያለው ። እናም ካልፈለገ ገደል ግባ በለው ብሎኛል ።" አዲሱ ስራዬ ገደል ገባ ምንም ማድረግ አልችል ። ቫልን እማገኝበት ሌላ ዘዴ እፈጥራለሁ ። ይሄው ከአሁኑ አንገሸገሸኝ ።

"በርግጥ እንደዚያ ነው ያለው?" ቀዝቀዝ ባለ ድምጽ ጠየቀኝ ።

"የራሱ ቃላት ናቸው ።"

"ገደል ግባ ብሎ?"

"አዎ" እንዲህ ስለው ቪዳል ከት ብሎ ሳቀ ። ገረመኝ ።

"ድፍረትህ ከገመትኩት በላይ ነው በርደን ። ሁሌም እንዲህ እውነቱን ንገረኝ ። ያዘዝኳቸውን ሁሉ አሜን አሜን ብለው ከሚቀበሉት ሠራተኞቼ የተሻልክ ሆነህ ነው ያገኘሁህ ። ለኤቨርት አውሮፕላን ማረፊያ ድረስ በአሥራ ሁለት ከሩብ እንደምገኝና የትኬቱንም ዋጋ እንደምከፍለው ንገረው" በኩሉ ስልኩን ዘጋው ።



# አ ም ስ ት

እቪዳል መኖሪያ ቤት ጠዋት ሁለት ሰዐት ከሀምሳ ደቂቃ ላይ ደረስኩ ። እንቅልፍ ሳልጠግብ ያደርኩ ከመሆኑም ሌላ ቫልን እንደገና የማገኝበት ቀን በመሆኑ ጭንቅ ጭንቅ ይለኝ ነበር ። እንደደረስኩ መኪናዬን አቁሜ ወደ ዳየር ቢሮ ሂድኩ ፡ ከቪዳል ረዳቶች አንዱ እንደመሆኔ መጠን ለአስተናጋጁ መምጣቴን መንገር አላስፈለገኝም ። የዳየርን ቢሮ በር ከፍቼ ገባሁ ።

ያልተከፈቱ ፖስታዎችን እፊቱ ከምሮ ቡና ይጠጣል ።

"ሄሎ" አለ ሲያየኝ "ማታ የሆነውን ሰምቻለሁ ። ቪዳል በሚያደርገው ነገር መደናገጥ የለብህም ። እንደነገርኩህ እሱ የተወሰነ ሰዐት የለውም ። ሥራውን ለመጀመር የቸኮልክ ይመስለኛል ?"

"የት ነው እምሆነው?"

"አሳይሀለሁ ፡" አለና ቡናውን ጨርሶ ከቢሮው ይዞኝ ወጣ ። "እመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ነው እምትሠራው ። ሚስስ ቪዳል እዚህ መሥራት አትፈልግም ። ላንተ የተለየ ነገር እንደተደረገልህ ቁጠረው ። ቢሮህን ለማዘጋጀት አንድ ሳምንት ፈጅቶብኛል" እየተናገረ በተለያዩ ዛፎች መካከል በሚያልፈው መንገድ እየመራ ወደቤታቸው ይዞኝ ሄደ ።

"ሚስስ ቪዳል ምርጥ ነገሮችን ትወዳለች ። እቢሮህ ውስጥ የምታገኛቸው ነገሮች ሁሉ ውብና በጥንቃቄ የመተረጡ ናቸው ። ምቾትም አላቸው" ።

ወደ ቤቱ ውስጥ ገባንና አሮጌ የጥንት መሣሪያዎች በብዛት በሚታዩበት አዳራሽ ውስጥ አልፈን አንድ በር ላይ ደረስን ። ከፈተና ወደ ጐን ቆሞ አልፌው እንድገባ ምልክት ሰጠኝ ።

"እንደቤትህ ቁጠረው ፡ ትልቁ ጠረጴዛ ያንተ ነው ። አይ ቢ ኤም ያለበት ጠረጴዛ የሚስስ ቪዳል ነው ። የሥራውን ፕሮግራም ጠረጴዛው ላይ ታገኝዋለህ ። ተመልከተው ። አሁን እኔ ወደ ጉጀዬ ልብረር " ብሎኝ ሄደ ።

እበሩ ላይ ቆሜ በፅሐይ ብርሃን የደመቀውን ትልቅ ክፍል ተመለከትኩት ። ምቾት እንዳለው ያስታውቃል ። ትላልቆቹ መስኮቶች የመኖኛ ሥፍራውን ያሳያሉ ። ጠረጴዛዬ የቢሊያርድ ፣ መጫወቻ ያክላል ። አራት ስልኮች ፣ አንድ የውስጥ መገናኛ ፣ እና የቴሌክስ ማስተላለፊያ አሉበት ። አንድ ግሩንዲንግ ቴፕ ሪኮርደር እጠረጴዛዬ አጠገብ አለችው ትንሽ ጠረጴዛ ላይ ተቀምጧል ። ክፍሉን ተመለከትኩና ተቀመጥኩ ። ከፊት ለፊቴ አነስ ያለ ጠረጴዛ ላይ አንድ አይ ቢ ኤም የጽሕፈት መኪና ሁለት ስልኮች አንድ ግሩንዲንግ ቴፕ ሪኮርደር ብዙ እርሳሶችና ብእሮች ተቀምጠዋል ። ክፍሉ የአየር መቆጣጠሪያም አለው ።

በርግጥም እስከ ዛሬ እንዲህ ምቾት ባለው ቢሮ ውስጥ ሰርቼ አላውቅም ።

በፖስታ ማስቀመጫው ውስጥ ከአሥራ ሁለት በላይ የሚሆኑ ወፍራም ፖስታዎች አሉ ። ሶስት ሰዓት ሆነ ። ቫል መቼ ይሆን የምትመጣው? ዳየር ሥራ ይበዛብሃል ያለኝን አስታወስኩና አንዱን ፖስታ አንስቼ ከፈትኩት ። ሚስተር ዊሊያም ጃክሰንና ባለቤቱ ለሁለት ሳምንት ወደ ራንጉን ስለሚጓዙ አንደኛ ማዕረግ ሆቴል እንዲያዝላቸው ቪዛም እንዲዘጋጅላቸው የሚል ትእዛዝ ነበር ።

ምን አይነት ሥራ ውስጥ እንደገባሁ አሁን ታወቀኝ ። ይሄ የጉዞ ትዕዛዝ አሜሪካን የጉዞ ወኪል ውስጥ ሆኜ ቢደርሰኝ ኖሮ ወደ ማሲንግሀም እልከውና የቪዛውንም ሆነ ማንኛውንም ጉዳይ እሱ ያስፈጽመው ነበር ። ለዚህ ሥራ እሱ ብዙ ረዳቶች አሉት ። እኔ ብቻዬን ነኝ ። የበርማ ኤምባሲ ተወካይ ጽሕፈት ቤት እማያሚ ነው ያለው ። እዚያ ደርሶ ለመመለስ አንድ ሰዐት ይፈጃል ። በዚያ ላይ ጉዳዩ ባስቸኳይ አይፈፀምም ። ቪዛዎቹን ከአራት ሰዓት በፊት ይገባ መመለስ አልችልም ። ግማሽ ቀን እዚያ አለቀ ማለት ነው ። ይሄ ደግሞ እሚሆን አይደለም ።

የውስጥ መገናኛውን ስመለከት የዳየርን ስም አገኘሁና ቁልፍን ተጫንኩ ።

"በርደን ነኝ ። ወደ ማያሚ በፍጥነት የሚሄድ ተላላኪ እፈልጋለሁ ። ልታዝልኝ ትችላለህ ።" አልኩት ።

"ያ የኔ ሥራ አይደለም ። ሉቃስን ጠይቀው ። እንዲህ አይነቱ ጉዳይ እሱን ነው እሚመለከተው አዝናለሁ" ብሎ ዘጋው ።



የበርናርድ ሉቃስን ቁጥር ፈልጌ ቁልፉን ተጫንኩና ችግሬን ዘረዘሬ ነገርኩት ።

"ምንም ሰው የለን" አለኝ ። ከድምፁ የማይተባበረኝ መሆኑን አወቅሁ ።

"ስለዚህ ጉዳይ የማውቀው ነገር የለኝም ። እንዲህ አይነቱን ነገር የሚያስፈጽምልን የአሜሪካን የጉዞ ወኪል ነበር ። ለምን እነሱን አትጠይቃቸውም?" "ከነሱ ጋር ያለን ግንኙነት ተቋርጧል" አልኩት ብስጭቴን እንዳያውቅ ተጠንቅቄ ።

"የጉዞን ጉዳይ በተመለከተ እኔ ነኝ የማስፈጽመው ። ስለዚህ ተላላኪ ያስፈልገኛል" ።

"እንደዚያ ከሆነ ሚስተር ቪዳልን ማነጋገር ይኖርብሀል ። ተጨማሪ ሰው ለማስቀጠር ሥልጣን የለኝም ።" ብሎኝ ዘጋው ።

ይሄ ቫል ልታስፈጽመው የሚገባ ጉዳይ ነው አልኩ ለራሴ ። ፕሮግራሙን እንደገና ተመለከትኩት ። ጃክሰንና ባለቤቱ ከነገ ወዲያ መሄድ አለባቸው ። ቪዛቸውን ለማዘጋጀት ጊዜ አለ ማለት ነው ። የአውሮፕላን ትኬትም እቆርጥላቸዋለሁ ፤ መኪናና ሆቴልም ላዘጋጅላቸው እችላለሁ ። ይሄ ሁሉ በስልክና በቴሌክስ ሊፈጸም የሚችል ነው ።

ወረቀቱን እፖስታው ውስጥ መልሼ ሌላ ከፈትኩ ። ለሚስተር ፖሰን ፣ ለሚስተር ማክፌድ ፤ ለሚስተር ሀምሊተን ፤ ለሚስተር ፍሬምሊን ወደ ቶኪዮ ጉዞ እንዲዘጋጅ በተጨማሪም ሚስተር ጂሰንን የፈንጣጣ ክትባት እንዲወስዱ ማስታወስ ፣ ለሚስተር ማክፌድ ቪዛ እንዲወጣ የሚል ትዕዛዝ ነው በዝርዝር የሠፈረው ። ሁሉንም ረገምኳቸው ። በሶስት ቀናት ውስጥ መጓዝ ይኖርባቸዋል ። ለጃፓን አየር መንገድ ደወልኩና ቦታ ያዝኩላቸው ። ለፓስፊክ ሆቴልም በቴሌክስ አልጋ እንዲያዝላቸው መልክት አስተላለፍኩ ።

የከፈትኩት ፖስታ ሁሉ ራስ የሚበጠብጥ ትዕዛዝ ነው ይዞልኝ ብቅ የሚለው ። ዳየር በርግጥ ሥራውን ሁሉ ወዝፎልኛል ። ቫል አሁንም አልመጣች ። በፍጥነት ብሰራም አለፀሐፊ ብቻዬን እንዴት አድርጌ ልገፋው?

ቫል የት ገባች? የስራው ብዛት እናዶ እስጋት ላይ ጣለኝ ። ሰዐቴን ተመለከትኩ ። አምስት ሰዐት ከአስር ሆኗል ። የሠራሁትን ሥራ በፅሑፍ አሰፈርኩ ። እፖስታ ውስጥ አሥራ አራት ትዕዛዛትን ነው

ያገኘሁት ። እምስቱ አጣዳፊ ሲሆኑ የቀሩት ነገ ሊፈፀሙ የሚችሉ ናቸው ።

ከአሁን አሁን ቫል ትመጣለች በሚል አምስቱን ትዕዛዞች ተጋ ተርኩአቸው ። በሥራ ተወጥሬ ዳየር እስከሚደውልልኝ ድረስ ሰዐቱ ሰባት መድረሱ አልታወቀኝም ። "ረስቼው ሳልነግርህ ከኔ ቢሮ በስተ ጀርባ ምግብ ቤት አለ ። ደህና ምግብ ይሠራሉ ። ዋጋቸውም ርካሽ ነው" አለኝ ።

"ሳንድዊች ሊልኩልኝ ይችላሉ?"

"አዎ በደንብ ። ለካ እቢሮህ ምሳ የምትበላ ሰው መሆንክን ረስቼዋለሁ ።" ማሾፉ ይታወቅበታል ።

"በአረንጓዴው ስልክ 23 ቁጥር ብትደውል የፈለግኸውን ይል ኩልሀል ።"

"ሚስስ ቪዳልን አይተሀታል?"

"በድንገት ወደ ፓልም የባህር ዳርቻ ሄዳለች። ብቅ አላለችም እንዴ?" ሲለኝ በረጂሙ ተነፈስኩ ።

"አላለችም ።"

"ዛሬ ደህና አትመስልም ። አንተ ሥራ የምትጀምርበት ቀን ~ሆኑን እረስታው ይሆናል ። ተላላኪውን አገኘህ?"

"አላገኘሁም ።"

"መጥፎ አጋጣሚ ነው ። እንዴት እያደረግህ ነው? ሥራው ለብ ቻህ እንደሚበዛብህ ይታየኛል ።"

"እያጠናቀቅሁት ነው" ብዬ ዘጋሁበት ።

በድንገት ወደ ፓልም የባህር ዳርቻ!! ለማመን የሚያስቸግር ነበር ። ለአንድ ሣምንት አልተለያየንም ። ረስታ ሊሆን አይችልም ። እንደ ኔው ሰዐቱንና ቀኑን እየቆጠረች እንደሰነበተች እርግጠኛ ነኝ ። እተሽ ከርካሪ ወንበሬ ላይ እንደተቀመጥኩ ወደ መስኮቱ ዞርኩ ። ከአስር ሰዓት በፊት ቪዛዎቹን ማውጣት አለብኝ ። ሄጄ እንዳላስጨርሰው ጊዜው አይበቃኝም ። የማደርገው ጠፍቶኝ ስጨነቅ የበፊቷ ፀሐፊዬ ትዝ አለችኝ ። ለምን አልጠይቃትም? ማሲንግሀም የሰማ እንደሆን ግን እች ግር ላይ ልትወድቅ ትችላለች ። ለማንኛውም ብጠይቃት ጉዳት የለ



በትም ። እልኩ ለራሴ ። አልሰን ወደ ምሣ ስለሚሄድ ብቻዋን ነው እም ትሆነው ። ደወልኩላት ።

"ሄሎ በርደን ፣ ስላንተ እያሰብኩ ነበር ። አዲሱ ሥራ እንዴት ይዞ ሀል?"

"ሱ ፣ እማጥ ውስጥ ገብቼልሻለሁ ። እረዳት የለኝም ። ለራንጉን ሁለት ቪዛዎችን ከአሥር ሰዐት በፊት እፈልጋለሁ ። ብትረጂኝ ህይወ ቴን ነው እምታተርፊው ።"

"ፓስፖርቶቹ አሉህ?"

"አዎ"

"ጃክ ወደ ማያሚ ቪዛ ለማውጣት ይሄዳል ። ከመሄዱ በፊት ወዳንተ እልከዋለሁ ። ከግማሽ ሰዓት በኋላ ይደርሳል ።" አለችኝ ።

"ግሩም ነው በጣም አመሰግናለሁ ።"

"ክሌይ ለጃክ ምናምን ስጠው ። ወሬው የተሠማ እንደሁ . . . "

"ግድየለሽም እስጠዋለሁ ። በርግጥ ህይወቴን ነው ያዳንሽው ።"

"በል ቻዎ" ብላ ስልኩን ዘጋች ።

እጠረጴዛዬ ላይ የተበታተኑትን ወረቀቶች እየተመለከትኩ ተቀ መጥኩ ። እራሴው መተየብ ይኖብርኛል ብዬ ወሰንኩ ። ወረቀቶቼን ስሰበስብ በሩ በሀይል ተበረገደና ቫል ገባች ።

ገና ሳያት ልቤ ዘለለ ። ከመቼውም የበለጠ ደምቃ ታየችኝ ። በትከሻዋ ትልቅ የፕላስቲክ ቦርሳ አንግታለች ። በሩን ዘግታ ወደኔ መጣች ።

"ፍቅርዬ የት ገባች ብለህ ተጨንቀህ እንዴ?" ቀስ ብዬ ከተቀ መጥኩበት ተነሳሁ ።

"ዳየር ነግሮኛል" አልኳት ዝቅ ባለ ድምፅ

"መሄድ ነበረብኝ ። ኢታ እየሸጡ ነው ። ምን የመሰለ ቆንጆ ቀሚስ በርካሽ ዋጋ ገዛሁ ። አሳይሀለሁ ።" ጠጋ ብዬ ተጠመጠምኩባት ።

"ተው በርደን እዚህ አይሆንም" አለች እንድርቃት እየገፋችኝ ። በሹክሹክታ ነበር የምትናገረው ። "አደገኛ ነው ። አንዱ ድንገት ሊገባ ይችላል ።"

ራሴን ተቆጣጠርኩና ለቀቅኋት ። ቁጭትና ተስፋ መ    በሠራ አካሌ ተሠራጨ ።

"ልብሱን ተይው ቫል" አልኳት ሎክ ብዬ "ዳየር ለኛ የከመረልንን ሥራ አይተሽዋል ?" ስላት ቆጣ አለች ።

"ምን ማለትህ ነው?"

"አጣዳፊ የሆነ መእት ሥራ አለ ። እየጠበቅሁሽ ነበር ።" ብዬ ፕሮግራሞቹን አንስቼ እጠረጴዛዋ ላይ መልሼ ወረወርኳቸው ።

"አሁን ሥራ መጀመር አለብሽ ። ከእያንዳንዱ አራት ካርቦን ኮፒ ልትሠሪልኝ ትችያለሽ፣ አንቺ እነሱን ስትሠሪ እኔ የትኬቶቹን ጉዳይ አስፈጽማለሁ ።"

"ግን በርደን" አለችኝ ውብ አይኖቿ በድንጋጤ ተሞልተው ።

"የተጨነቅህ ይመስላል ። ይህን ያህል የሚያስጨንቅህ ምንድ ነው?"

ጥርሴን ነከስኩ ።

ቫል ባስቸኳይ ሥራ ካልጀመርሽ ስድስቱም ሰዎች ሊጓዙ አይችሉም ። እኛ ሥራችንን ከመጀመራችን ድከመት ሊያይብን ነው ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ አንቺው ገምቺው ።"

በርደን "እየጮኸክብኝ ነው እኮ"

"አዝናለሁ ። ጠዋት በጣም ተረብሼ ነበር ። የቀድሞዋን ፀሐፊዬን ሳይቀር እርዳታ ጠይቂያለሁ ። ቫል ስራውን መሥራት አለብን።"

"ግን እንደዚህ ለብሼ ልሠራ አልችልም ። መለወጥ አለብኝ ።" የለበስኩት ልብስ እንደልቤ ለመቀመጥ አይመቸኝም ። በዚያ ላይ ገና ምሳ አልበላሁም ። አንተስ በልተሀል እንዴ?"

አልፈያት ሄድኩና እሷ ወንበር ላይ ተቀምጬ የጽሕፈት መኪናውን አስተካከልኩ ።

"አሁን ምንም አልቀምስ ። አንቺ ልብስሽን እስከምትለውጪ ሥራውን እጀምራለሁ ። በፍጥነት ጨርሰሽ ነይ አትቺይም?" ስላት ትከሻየን ነካ አደረገችኝ ።

"እንደተናደድክብኝ ይታየኛል ።"

"በቶሎ ለመድረስ ሞክሪ!" ብዬ እፅሕፈት መኪናው ውስጥ ወረቀት አስገብቼ መጻፍ ጀመርኩ ።



ዘለግ ላለ ጊዜ ተመለከተችኝና ቦርሳዋን አንስታ ወጣች ።

የውስጥ መገናኛው ተንጫረረ ። እየተራገምኩ ተነሳሁና ቁልፉን ተጫንኩት ።

"ሚስተር በርደን የጥበቃ ጓዱ ነኝ ። በሞተር ሳይክል የመጣ ጃክ ነኝ የሚል መልዕክተኛ ይፈልግዎታል ።"

"ወደኔ ላከው" ብዬ ወደ ፅሕፈት መኪናዬ ሄድኩ ።
ከአንድ አምስት ደቂቃ በኋላ አንድ ልጅ ጃካን እስከትላ ገባች ። ገና ሲገባ ምኞት ብቻ የሆነውን ቢሮዬን ተመለከተና አይኖቹ ፈጠጡ ።

"እነዚህን ከቪዛዎቹ ጋር በፍጥነት ይዘህልኝ ድረስ ጃክ በጣም አጣዳፊ ጉዳይ ነው"

"ሚስስ ሀርክነስ ነግራኛለች" ብሎ ጠቀሰኝ ።

ቆማ ወደ ምትጠብቀው ልጅ ስሸኘው አሥር ዶላር አስጨበጥኩት ።

ከሄደ በኋላ አንዱን ፕሮግራም ጨርሼ ሌላውን ስጀምር ቫል መጣች ። ጠቆር ያለ ቀሚስና ነጭ ሸሚዝ ለብሳለች በጣም አምሮባታል ።

"ሳንድዊችና ማርቲኒ አዝዣለሁ አሁን ሥራየን ለመጀመር ዝግጁ ነኝ" አለች ።

"መልካም እኔ የጉዞ ፕሮግራሞቹን አዘጋጃለሁ" ብዬ ቦታዋን ለቀቅሁላት ።

"ንዴትህ በረደልህ አይደል የኔ ሸጋ?"

"እንዴታ"

ተቀመጠች ።

"እንደገና አብረን የምንሠራበትን ወቅት በጉጉት ነበር የጠበቅሁት ። ቢሮህን ወደድከው?" አለችኝ ።

ጊዜ እያባከንኩ መሆኑ ስለተሰማኝ እወንበሬ ላይ ተቀምጬ ስልኩን አያነሳሁ ።

"ዳየር አጣዳፊ ሥራ ቶሎ ባይተውልን ኖሮ ቆንጆ ነበር" አልኳት ።

ወጺያው በሩ ተንኳኳና ዩኒፎርም የለበሰ ልጅ ሳንድዊቹንና ኮክቴሉን ተሽከርካሪ ጠረጴዛ ላይ አድርጎ እየገፋ ገባ ።

"እሽ ፈርዳይ" አለች ቫል "አስቀምጠውና ውጣ ። ራሳችንን እና ስተናግዳለን ።"

ሲወጣ ተነሳችና መጠጡን ቀዳች ። እኔ ከፖን አም አየር መንገድ ጋር እየተነጋገርኩ ነበር ።

"እርቦኛል እንብላ በርደን" አለችና በንፁህ ነጭ ጨርቅ የተሸፈነውን ሳንድዊች ገለጠች ።

"እየሠራን እንብላ" አልኳት ።

"እየበላሁ መጻፍ አልችልም ። ሁሉንም ነገር አጨማልቀዋለሁ ። አንተም በስልክ እየተነጋገርክ መብላት አትችልም ። እባክህ አታስቸግረኝ ክሌይ ናና ብላ ።"

ተሸነፍኩ ። ሰዎቹ በወቅቱ ሊጓዙ ካልቻሉ መጥፎ ሁኔታ ሊፈጠር ነው ። ቫልም እኔ ወደ ቤቴ ከመሄዴ በፊት ልናከናውነው የሚገባንን ሥራ ልክ ካላወቀች የባሰ መጥፎ ነገር ሊሆን ነው ።

ወደ ተሽከርካሪው ጠረጴዛ ሄድኩና የቀዳችልኝን ማርቲኒ ተቀበልኳት ።

"ለጤንነታችን የኔ ፍቅር" ብላ ፈገግ አለች ። "ደስ ይላል አይደል?"

ማርቲኒውን ባንድ ትንፋሽ ሳጋምሰው ተሻለኝ ። የረሀብ ስሜትም ተሰማኝ ። ሳንዲዊቾችንን እያነሳን በላን ።

"አቤት ይህንን አጋጣሚ ስጠብቅ ሳምንቱ እንዴት ረዘመብኝ መሠለህ ። አንተስ አልረዘመብህም?"

"መርዘም ብቻ" አልኩና ፀጥ አልኩ ። ከዚያ

"ቫል እረዳት ያስፈልገናል ። የቪዛዎቹንና ሌሎች ጉዳዮችን የሚያስፈጽምልን ተላላኪ ያስፈልገናል ። ሉቃስን ጠይቄው ሚስተር ቪዳልን እንጋግረው ብሎኛል ። አንቺ ልትጨርሺው አትችይም?"

"ሰውየው የሚከፈለው ከሆነ ሄንሪ ደስ አይለውም ።"

"በነፃ የሚሠራ ሰው የምታገኚ አይመስለኝም" ንዴቴ እንደገና ተመለሰ ። ለሷ ችግሩ ምንም አልመሰላት ።



"ለመተባበር ፈቃደኛ አይሆንም እንጂ ሉቃስን ላነጋግረው እችላለሁ ።" አለችኝ ።

"እይው ቫል አንቺ ልትጨርሺው ካልቻልሽ ሥራውን ልንሠራው አንችልም ። ነገሩ ግልፅ ይመስለኛል ።"

"በየቀኑ ቪዛ ስናወጣ አንኖርም ።"

"ሌሎች ሥራዎች ሊኖሩ ይችላሉ ። ከውጪ አንድ ሰው ያስፈልገናል ።"

"ፍቅርዬ መብላቱን ተውከው እኮ" ስትለኝ ማርቲኒዬን ጨረስኩት ።

"በቃኝ "አልኩና ወደ ጠረጴዛዬ ተመለስኩ ።

"በርደን"

ስልኩን እያነሳሁ ምንድ ነው አልኳት ።

"ይህን ያህል አትጨነቅ ። እንወጣዋለን" ዝግ ባለ ድምጽ "ቫል ካንቺ ጋር እንድሆን በርግጥ የምትፈልጊ ከሆነ መወጣት ብቻ ሳይሆን ተላላኪም ማግኘት አለብን" አልኳት

ከዚያ ወደ ሰሜን ምስራቅ አየር መንገድ ደወልኩና ቦታ እንዲይዙልኝ ጠየቅሁ ።

"ሳንድ ዊች ጨምሬ ብበላ ስግብግብ ነች ትለኛለህ ? በጣም ጥሩ ነው አይደለም እንዴ?" አለችና ማርቲኒ ቀዳች

"እባክህ ትንሽ ብላ ምንም አልቀመስም እኮ"

በጣም ስለበሸቅሁ ላናግራት ቀርቶ ቀና ብዬ ላያት አልቻልኩም። ፀጥ ብዬ ስሠራ ፣ የአውሮፕላን ትኬቶቹን ጉዳይ የሚያስፈጽመው ሠራተኛ ደወለልኝ ። ስልኩን በእጄ እንደያዝኩ አዲሱን ሥራዬን የጀመርኩበት ሁኔታ ትዝ አለኝ ። "መጥፎ አጀማመር ነው ፣" አልኩኝ ለራሴ ። በዚህ አይነት እዘልቀው ይሆን ? ቫል ለጥቂት ጊዜ እቅፍ አድርጌ እንድስማት ብትፈቅድልኝ ኖሮ እንዲህ የምጨብጠውን እስከ ማጣ ድረስ አልናደድም ነበር ።

በዚያ ላይ ሆን ብላ ችግሩን አቃልላ ማየቷ የባሰ አበሳጨኝ ። ይህ አጋጣሚ የቀድሞውን ሥራዬንና ጉበዟን ፀሐፊዬን እንዳስታውስ አደረገኝ ።

ተነጋግሬ ጨርሼ ስልኩን ስዘጋ ቫል ገና እየበላች ነበር። ሰተለ ያዩ አየር መንገዶች መደወል አለብኝ።

"ስለ እግዚአብሔር ብለሽ ቫል ስራሽን ጀምሪ! እስቲ ሰዓቱን ተመልከችው፣ ዘጠኝ ሊሆን ነው እኮ?"

አይኖቿን አፍጥጣ ሌላ ሳንድዊች አነሳች።

"በርንደን ምንድ ነው እንደዚህ የሚያንጫንጭህ፣ እባክህ አት ጨህብኝ። ደስ አይለኝም!!"

"አዝናለሁ ። ለመጮህ ፈልጌ አይደለም። ይሄን ሥራ መጨረስ አለብን።"

ከፓን አም አየር መንገድ ሲደወልልኝ የተጓዦቹን ስምና የሚጓዙበትን ቀን ሰጠሁ። ቫል ሳንድዊቾቹን ጨረሰችና እጅዋን አባብሳ ማርቲኒዋን ይዛ ወደ ጠረጴዛዋ ሄደችና መጻፍ ጀመረች።

እያዘገመችና እየለቀመች ስትተይብ ይሰማል። ከዚህ በፊት ሳውቃት እንደሷ በፍጥነት የሚጽፍ አልነበረም። የጽሕፈት መኪናውን እንደመትረየስ ነበር የምትንጣጣው። እያረፈች ታፕ ታፕ ስታደርግ ንዴቴ ጨመረ ። በዚህ አይነት ፕሮግራሞቹን ጽፋ ለመጨረስ ሳምንት ሊወስድባት ነው። እኔ እንኳ ብዙ ልምድ የሌለኝ ከአሁን ፍጥነቷ አራት እጅ የበለጠ ፈጥኜ ልተይብ እችላለሁ። ለአየር መንገዶቹ እየደወልኩ ሳዳምጣት ምን አይነት ጣጣ ነው አለችና የጸፈችው ን ተመለከተች። ከዚያ ወረቀቶቹን ከጽሕፈት መኪናው ውስጥ ላጥ አድርጋ አውጥታ ጨባብጣ እቆሻሻ መጣያ ቅርጫቱ ውስጥ ወረወረችውና ቀና ብላ ተመለከተችኝ።

"አፍጥጠህ አትመልከተኝ። ተረጋግቼ እንዳልሠራ እያደረግኸኝ ነው" አለችኝ ቆጣ ብላ

"ለስድስት አመታት የጽሕፈት መኪና በእጇ ነክቼ አላውቅም ከኔ ምን ትጠብቃለህ?"

"ሥራ እንለዋወጥ" አልኳት አላስችል ቢለኝ።

"አንቺ ከአየር መንገዶች ጋር እየተነጋገርሽ ቦታ ያዥ። እኔ ልጻፍ"

"ሞቻለሏ" አይኖቿ ተጉረጠረጡ። "አንተም ሥራህን ሥራ እኔም የራሴን እሠራለሁ"



እንደዚህ ተፋጠን ሳለን በሩ በዝግታ ተከፈተና አንድ ሰው ገባ። ሳየው ደነገጥሁ ማለቱ ብቻ በቂ አይሆንም። ከፊልም ውስጥ የወጣ የከተማ ወሮበላ ነው፣ እሚመስል። የለበሰው ሙሉ ልብስ ግራጫ ሆኖ ጥቁር መስመሮች አሉበት። ሸሚዙ ጥቁር ሆኖ ነጭ ከራባት፣ ሸብ ተደርጎበታል። ባርኔጣውም ነጭ ነው። ጋዜጦች በወንጀለኞች ላይ ለማሳቅ የሚያወጧቸውን የፈገግ ስእሎች ይመስላል።

ይሄ ግን የቀልድ ሰው አልነበረም። ገና ሳየው ነው ልቤ በፍርሀት ፍጥነቱን የጨመረው። እንደ እባብ አይን እግንባሩ ላይ የተለጠፉት አይኖቹ፤ ከንፈር የሌለበት የሚመስለው ጠባቡ አፉ! እንደ መርዛም እባብ አደገኛ መሆኑን ነው የጠቆሙኝ።

ትናንሽ አይኖቹ በንቀት ተመለከቱኝ። ከዚያ በኩራት ዞር ሲል ቫልን አያት ወደ ጠረጴዛዋ ተጠጋና አንድ ፖስታ እፊቷ አስቀመጠላት።

"ሚስተር ቪዳል ባስቸኳይ እንዲፈጸም ብለዋል።" አለ በጐርናና ድምፁ ።

ከዚያ ዞር ብሎ ልክ እንደ እባብ ድምፅ ሳያሰማ ከክፍሉ ውስጥ ሹልክ ብሎ ወጣ ።

ቫልን ተመለከትኳት። ፊቷ አዲስ እንደወረደ በረዶ ነጭ ሆኗል። ፍዝዝ ብዬ ስመለከታት የውስጥ መገናኛ መሣሪያው ጩኸት አስበረገገኝ። ቁልፉን ተጫንኩ።

"በርደን" አለኝ ዳየር ነው።

"አንድ ትእዛዝ ልኬልሀለሁ ። ባለፈው ሳምንት ልስጥህ ይገባኝ ነበር። ረስቼው ነው። በጣም አዝናለሁ ሚስተር ዌርንስታይን ዛሬ ገብቶ እስፓኒሽ ቤይ ሆቴል ውስጥ አልጋ መያዙን ሰምቻለሁ። ሚስተር ቪዳል አሳ ለማጥመድ ጀልባውን ሊያውሰው ቃል ገብቶለታል። ስለዚህ ጀልባዋንና ሠራተኛዋን አዘጋጅለት ። ትእዛዙን በዝርዝር ተጽፎ ታገኘዋለሁ።" ሲለኝ የውስጥ መገናኛውን ተስፋ በቆረጠ አይን ተመለከትኩ። ቅድም ያየሁት ሰውዬ ከአእምሮዬ አልወጣ ብሎ እየረበሸኝ ነበር።

ቫል ድንገት ተነስታ ወደኔ መጣችና፣

"ዳየር" አለች በቁጣ "አንተ ራስህ ፈጽመው። ገባህ! እኛ በጣም ሥራ ይበዛብናል። እንደረሳኸው አንተው ራስህ ፈጽመው" አለችና

ዘጋችበት ። ተያየን ፤ ጉንጮችዋ ቀልተዋል ! አይኖችዋ በቁጣ ይንቦ
ቦጋሉ ።

"የቅድሙ ሰውዬ ማን ነው?" አልኳት ስር በሩን እየተመለ
ትኩ ።

"ጉሊዮ ጌስቲ ነው ። የባሌ ቀኝ እጅ ። እንደዚያ ተብለው አይ
ደል የሚጠሩት ? አሲዱን እልጅቷ ፊት ላይ የረጨው ሰው ነው ።
ባሌ አንድ ምልክት ቢሠጠው ሁለታችንንም ሊገለን የሚችል ሰው
ነው" ስትለኝ ።

አፌ ደረቀ ። አንድ ነገር ልናገር ስሞክር እንደበቴ ከዳኝ ።

"ቪዳል ነፍስ ገዳዮች አሉት ስትለኝ አላመንኳትም ነበር ። አሁን
ግን አመንኳት ። ማየት ማመን አይደል ? ፍርሀት በጀርባዬ ሲገባ ተ
ማኝ ።

ወደ ጠረጴዛዋ ተመለሰችና ጌስቲ ያመጣውን ፖስታ ከፍታ ደብ
ዳቤውን ማንበብ ጀመረች ። ቀና ብላ ስታየኝ ቁና ቁና ተነፈሰች ።

"ቪዳል ከነገ ወዲያ ወደ ሊቢያ ይጓዛል ። ከአራት ቀናት በኋላ
ነው እሚመለሰው ። ለጉዞው የሚያስፈልገውን ሁሉ ማዘጋጀት አለ
ብን" ብላ በከንፈሮቿ ፈገግ አለች ።

"ከሞላ ጎደል ለአንድ ስምንት ብቻችንን ልንሆን ነው ፍቅርዬ
እስቲ አስበው ? ሳምንቱን ሙሉ?"

"ጌስቲን ሳይ የተሰማኝ ፍርሀት ወሬውን ስሰማ ሊሰማኝ የሚ
ገባውን ደስታ በጣም ፣ ቀንሶታል አሁኑኑ የአውሮፕላኑን ጉዳይ እጨር
ስለታለሁ" ብዬ ስልኩን አነሳሁ ።

* * *

የአሜሪካን የጉዞ ወኪል ተላላኪ ጃክ ወደ ቢሮዬ ገብቶ ፈገግ
አለና እየጠቀሰ ቪዛዎቹን ሰጠኝ ።

"ይሄው ሚስተር በርደን" ብሎ አይኖቹ እቫል ላይ ሲያርፉ
ከንፈሮቹ ድምጽ ሳያወጡ እንደሚያፏጩ ሁሉ አሞጠሞጡ ። "ሁሉ
ንም ነገር እንዳዘዙኝ አከናውናለሁ ።"



"አመሰግናለሁ ጃክ ህይወቴን ነው ያተረፍከው ።" ቫል የቪዳልን
የሊቢያ የጉዞ ፕሮግራም ተይባ እስከምትጨርሰው በትእግሥት እየጠ
በቅሁ ነበር ።

ለሚስተር ጃክሰንና ለባለቤቱ ቪዛዎቹን የሚያደርስልኝ ሰው
የለም ። እፖላስ ሆቴል ውስጥ ነው ያረፉት ። ጃክ በዚያው ስለሚያ
ልፍ ሊያደርስልኝ ይችላል ። ስፈራ ስቸር ጠየቅሁት ። እያቅማማ
ሰዓቱን ተመለከተና ፣

"በጣም ረፍዶብኛል ። ሚስተር አልሰን ከሰማ አገር ይቃጠላል"

ቪዛውንና የጉዞ ፕሮግራሙን እፖስታ ውስጥ ከተትኩና አም
ስት ዶላር ከኪሴ አውጥቼ አሳየሁት ። ፈገግ ብሎ መስማማቱን ገለ
ፀልኝ ፣

"እሺ ሚስተር በርደን ያዘዙኝን ሁሉ እፈጽማለሁ ። አልሰን ቢቆ
ጣም የምመልስለት አንድ ሳበብ አላጣም ።" ብሎ ፖስታውን ከነብሩ
ተቀበለኝ ። ሲወጣ ወደ ቫል ዞር ብዬ ተመለከትኩ ።

"ይሄ ጉዳይ ከኪሴ አስራ አምስት ዶላር አስወጥቶኛል ተላላኪ
ለምን እንደሚያስፈልገን ይታይሻል ?"

"አታናግረኝ ። ሥራ ላይ ነኝ" አለች በቁጣ ። "ምን ጣጣ ነው
እንደገና አሳሳትከኝ !"

"እዝናለሁ" አልኳት ያላዘንኩ መሆኔን በሚያሳውቅ ድምጽ ።

ወደ ቴሌክስ ማስተላለፊያው ሄጄ ወደ ኒውዮርከ መልክት ሳስ
ተላልፍ ከስልኮቼ አንዱ አንቃጨለ ።

"እባክሽ አንሺልኝ ?" አልኩ ቀና ብዬ ሳልመለከታት ። እያጉ
ተመተመች ሄዳ ስልኩን አነሳችና በሰለቸ ድምጽ "ሄሎ አዎን እዚህ
ነው ያለው ማለበል? አ" ብላ ዝም አለች "አንድ ጊዜ ይቆዩኝ ።
ለአንተ ነው" አለች እያንሾካሾከች "ሚስትህ ናት"

ተያየን ። ያልጠበቅሁት ነገር ነበር ። እጄን አላበኝ ። ሮዳ ስልኩን
ያነሳችው ቫል መሆኗን አውቃ ይሆን ? መነጋገሪያውን አነሳሁ ።

"ሮዳ?"

"እኔ ነኝ ከዳቦውና ከቅቤው ጋር ሁለት ፓኮ ሲጋራ ይዘህልኝ
ልትመጣ ትችላለህ? እኔ ወጥቼ መግዛት አልቻልኩም ።" ስትለኝ
እጠረጴዛዬ ላይ የተዝረከረኩትን ወረቀቶችና ሰዓቴን ተመለከትኩ ።

''አዝናለሁ የኔ ወለላ የምችል አይመስለኝም ። ብዙ ሥራ ስላለ ብኝ በጊዜ አልወጣም ። እስከ ሶስት ተኩል ድረስ ሳላመሽ የምቀር አይመስለኝም ።''

''ሶስት ተኩል?'' አለች በጩኸት ''ምን አይነት ሥራ ነው እሱ?!''

''በጣም ሥራ የሚበዛበት ቀን ነው'' አልኳት በዝግታ ።

''የመጀመሪያ ቀን . . . ታውቂው የለ የኔ ወለላ መሥራት አለ ብኝ ። ጠረጴዛዬ በሥራ ፡ እንደተሞላ ነው ።''

''ሳትበላ ቁጭ ብላ እስከ ሶስት ተኩል ትጠብቀኛለች ብለ፣ አስበህ እንደሆን ተሳስተሃል!'' ብላ ተንጣጣች ።

''እሺ . . . እሺ አትጠብቂኝ ባሰኘሽ ጊዜ ብይ'' ብዬ ስልኩን ዘጋ ሁት ።

''ድምጼን ለየችው እንዴ?'' አለች ቫል ።

''እኔ እንጃ ። አሁን ለየች አልለየች ደንታ የለኝም ! ሥራችንን እን ሥራ ፡''

ከምሽቱ አንድ ሰዓት ላይ ቫል የሊቢያውን የጉዞ ፕሮግራም ጽፋ ጨረሰችና ።

''ተመስገን ነው ። ሁለተኛውን ጨረስኩ ። አሁን ተነስቼ መሮጥ አለብኝ ። አለዚያ አረፍዳለሁ'' አለች ። ካርቦኖቹን ስታነሳሳ ትኩር ብዬ ተመለከትኩት ።

''መሄድሽ ነው እንዴ ?''

''መሄድ አለብኝ ።''

''አምስት ፕሮግራም ይቀርኛል እኮ ቫል''

''መቆየት አለበት'' አለች በተሰላቸ አነጋገር ፣

''ከዌርንስታይንቤ ጋር የእራት ግብዣ ቀጠሮ አለኝ ። ቢዳል ነው ቀጠሮውን የያዘው ። ልቀር አልችልም''

''እሺ'' መከራከር አልቻልኩም ''መሄድ ካለብሽ መሄድ አለብሽ ነው ።''



''አትናደድ ፍቅርዬ ነገ በደንብ እሠራለሁ ።''

''ተስፋ አደርጋለሁ'' አልኳት

በፍጥነት ወደኔ መጣችና ጉንጮቼን ሳም ሳም አድርጋ ወጥታ ሔደች ።

ፀጉሬን በጣቶቼ ፎከት ፎከት አደረግሁ

ቀድሞውኑ ይህንን መገመት ነበረብኝ ። እቪዳል ቤት ውስጥ እንዴት አድርገን ፍቅር ፣ መለዋወጥ እንችላለን ? እበፊቱ መሥሪያ ቤቴ ብሆን ለማንኛውም ነገር ያመቸን ነበር ።

ከብስጭቴ የተነሳ ጠረጴዛውን በቡጢ ደሰቅሁት ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ቀዝቀዝ አልኩና ቫል የጻፋቻውን ፕሮግራም ተመለከትኩ ። ስህተት በስህተት ነው ። ''ምን አስጨነቀኝ አልኩ?'' ለራሴ የሚስቱን ሥራ ካልወደደው ራሱ ይንገራት ። ፕሮግራሙን ትኬቱንና ሆቴሉ የተያዘበትን ሰነድ አንድ ፖስታ ውስጥ ከትቼ እሳን ሳልቫዶር የሚገኘውን የኢንተር ኮንትኔንታል ሆቴልን አድራሻ ጻፍኩበት ። ከዚያ ቫል ትታው የሄደችውን ፕሮግራም ተየብኩ ።

በመኪናዬ ወደ ማያሚ አውሮፕላን ማረፊያ ከነፍኩ ። ፖስታውን ለቪዳል ልኬ ወደ ቤቴ ስመለስ ከምሽቱ ስድስት ሰዓት ሆኗል ። ሮዳ ቴሌቪዥን ትመለከት ነበር ።

''እምሽተህል'' ብላ ጮኸችብኝ አይኗን ከቴሌቪዥኑ ላይ ሳታነሳ ።

''አሁን ምንም አትናገረኝ ። ደስ የሚል ነገር እያየሁ ነው ።''

ወደ ማድቤት ገብቼ ተንጐዳጐድኩ ። የሚቀመስ ነገር የለም ።

''ምንም ነገር አልገዛሽ እንዴ?'' ጮክ ብዬ ጠየቅኋት ።

''እረስቼዋለሁ እባክህ ። አታቋርጠኝ'' አለችኝ ። ቢዛ ያለ ውስኪ ከሶዳ ጋር ቀዳሁና በቆርቆሮ የታሸገውን አደንጓሬ ከፍቼ ሞቅ እንኳ ሳላደርገው ተጋተርኩት ። የቴሌቪዥኑ ፕሮግራም ሲያበቃ እራት ቢጤዬን በልቼ ጨረስኩ ።

ሮዳ ወደ ማድቤቱ መጣች ። ወገቧን ይዛ እበሩ ላይ ሳያት ችግር እንዳለ ተሰማኝ ።

''እና ባልቴቷ ስልክህን ታነሳልህ ጀመራ !?''

የጠበቅሁት ነገር ነበር ። የሮዳን ችሎታ ዝቅ አድርጌ ገምቼው አላውቅም ። "በእጋጣሚ እቢሮዬ መጥታ ነው ያነሳችው ።" አልኩኝ ብርጭቆዬን እያነሳሁ ። "በቴሌክስ መልክት እያስተላለፍኩ ነበር ።"

"ሚስስ ቪዳል ባጋጣሚ እቢሮዬ መጥታ ነው!" አለች ሮዳ በማሾፍ ያልኳትን እየደገመች ።

"ማንን ለማታለል ነው ? እመንዝራዋ ወደ ውጪ ሄዳለች አላልከኝም ነበር?" ።

ንዴቴን እፍኜ ያዝኩና ብርጭቆየን አስቀመጥኩ ።

"ብዙ ልቅ አትሁኚ ሮዳ! ሚስስ ቪዳል ብዙ ጊዜ አትኖርም እንጂ አሁን የለችም አላልኩሽም ። ቢሮዬ ተስማምቶኝ እንደሁ ብላ ለማየት ነበር የመጣችው"

"ልቅ ብለህ አትስደበኝ!" ብላ ጮኸች ። "ልቅ አፍ መባል የሚገባት ያንተ ባልቴት ነች ። እመንዝራ ባትሆንም መስላ ነው እምትታየኝ ።"

"እንዳልሽ ይሁንልሽ ስለደከመኝ መተኛቴ ነው" ብዬ አልፌያት ልሄድ ስል መንገዱን ዘጋችብኝ ።

"ደክሞሀል!" ጮኸች "እስካሁን ስትሠራ ለምን አይደክምህ፣ ይህን ያህል ህፃን ልጅ መሰልኩህ እንዴ፣ ከሷ ጋር ስትዳራ ይሆናል የደከመህ"

ብዙ ውስኪ መጠጣት አልነበረብኝም ። አድርጌ የማላውቀውን ነገር አደረግሁ ። በጥፊ ሳጮላት እየተንደረደረች ወደ ሣሎኑ ሄደችና አዙሯት እወለሉ ላይ ተቀመጠች ። እዚያው እንዳለች አፏን ከፍታ አይኖቿ ደም ለብሰው ተመለከተችኝ ።

አልፌያት ሄድኩና እመኝታ ክፍሉ ገባሁ ። በንዴትና በፀፀት እየተንቀጠቀጥኩ ነበር ። አይኖቼን በእጆቼ ከድኜ አልጋው ላይ ተቀመጥኩ ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሳግ እየተናነቃት መጣችና አልጋው ጠርዝ ላይ ቁጭ ብላ ልብሶቿን ማወላለቅ ጀመረች ።

ንዴቴ ስላልበረደልኝ ስታለቅስ ሳያት ምንም አልተሰማኝ ። በዚያ ላይ እኔና ቫል ከቪዳል ቤት ውጪ የምንገናኝበትን መንገድ እያሰብኩ ስለነበር ለሮዳ የምጨነቅበት ጊዜ አልነበረኝም ።



ቆየት ብላ እንባ እየተናነቃት ።

"እንደዚያ ማለት አልነበረብኝም በርደን ። ልትመታኝ ይገባል ። ጥፋተኛ ነኝ" አለችኝ ። እንዲህ ስትለኝ እቅፍ አድርጌ ይቅርታ ልጠይቃት በተገባ ነበር ። ግን አላደረግሁትም ። በዚያ ፋንታ ፣

"በቃ እንርሳው" አልኩና ተነስቼ ልብሴን ማወላለቅ ጀመርኩ ።

"በጣም ነው የጐዳኸኝ ። የምሬን ነው ። በጣም ጐድተኸኛል ።"

"አንቺስ የጐዳሽኝ አይመስለሽም?" ብዬ ፒጃማዬን ይዤ ወደ መታጠቢያ ክፍሉ አመራሁ ።

"ለማንኛውም እርሸው ።"

ቆይቶ በጭለማው ውስጥ ጐን ለጐን እንደተኛን ልታቅፈኝ ሞከረች ። እጅዋን ገፋ አደረግሁና

"እባክሽ ተይኝ" አልኳት "አንቺን ባይደክምሽም እኔን በጣም ደክሞኛል"

ጭካኔ የተሞላበት አባባል ነበር ። ግን ገና በንዴት እየፈላሁ ስለ ነበር ብትጐዳ ባትጐዳ ደንታ አልነበረኝም ።

ያን ለት ማታ ብዙም እንቅልፍ አልያዘኝ ።

በማግስቱ ስለሚጠብቀኝ ሥራ ፣ ቫል ሥራዋን በደንብ ለመሥራት ስላለመቻሏ ፣ በተለይም ደግሞ አብረን እየዋልን ልነካት ስላለመቻሌ ሁሉ ሳወጣና ሳወርድ ነው የነጋልኝ ።

ሮዳ ወዲያው ነው እንቅልፍ የያዛት ። ስታንኮራፋብኝ ተናድጄ ከአንድም ሁለት ሶስቴ ልቀሰቅሳት ቃጥቶኝ ነበር ። ግን አላደረግሁትም

ከጠዋቱ አሥራ ሁለት ሰዐት ተኩል ሲሆን እንዳልቀሰቅሳት። ተጠንቅቄ ከአልጋው ወረድኩ ። ጺሜን ተላጭቼ ከታጠብኩ በኋላ ልብሶቼን ለባበስኩ ።

ሮዳ አልነቃችም ። ቢጣቴ እየተራመድሁ ወደማድቤቱ ገባሁና ቡና አፈላሁ ። የሚቀመስ ነገር የለም ። ዞር ስል እጠረጴዛው ላይ የሲጋራ ፓኬት አየሁ ። "ሲጋራውን እንደ ምግቡ አልረሳችውም አይደል?" አልኩና ራሴን ነቀነቅሁ ።

ስኒውን ከማጠቢያው ውስጥ ጨምሬ ላጥብ ስዘጋጅ ሮዳ አዝናና ተጐማቁላ ብቅ አለች ።

''ለምን በጠዋት ተነሳህ?'' ብላ ጠየቀችኝ ።

''ወደ ቢሮዬ መሄዴ ነው ። ብዙ የምሠራው ሥራ አለኝ ። ዳቦና ክሬሙን ዛሬ እንኳ እስታውሰሽ ለመግዛት ሞክሪ እስቲ ። የማመሽ ከሆነ እደውልልሻለሁ ።''

''አ በርደን ይህንን ስራ ባትይዘው ይሻለኝ ነበር ። እውነቴን ነው ። ልክ እንዳልሆነ እርግጠኛ ነኝ ።''

''ልክ እኮ ነች ።'' አልኩኝ ለራሴ ''ግን እንዴ ገብቼበታለሁ'' ነገሩን ለመለወጥ ።

''መኪናሽን ወደሻታል አይደል? ማታ እንገናኝ'' ብዬ ትቻት ወጣሁ ።

* * *

ቫል እስከ አራት ከሩብ ወደ ቢሮ አልመጣችም ። ገብታ በሩን ስትዘጋ የጥፋተኝነት ምልክት አይኖቿ ላይ ይታይ ነበር ።

''ስለዘገየሁ በጣም አዝናለሁ ፍቅርዬ ብላ በፍጥነት እወንበሯ ላይ ተቀመጠች ። በጣም አስጠሊ ምሽት ነበር ያሳለፍኩት ። ጠዋት እንቅልፍ ይዞኝ ጭልጥ አለ''

ከአንድ ሰዐት ተኩል ጀምሬ ብዙ ሥራ አከናውኛለሁ ። ሶስት ትዕዛዞችንና የቀሩትን ፕሮግራሞች ጽፌ ከመጨረሴም ሌላ ከአየር መንገዶችም ጋር በስልክ እየተነጋገርሁ ቦታዎችን ያዝኩ ። አሁን የቀረኝ አራት ቪዛዎችን ማውጣት ነው ።

''ቫል የቪዛው ችግር አሁንም ተመልሶ መጣብን ። አባክሽ ለሉቃስ ደውይለትና ተላላኪ ይመድብልን'' ስላት አይኖቿ ፈጠጡ ።

''እንደዚያ ለማድረግ ምንም ስልጣን የለኝ'' አለችኝ ''እሺ እንግዲያው ያለምንም ስልጣን አንድ ተላላኪ እናገኛለን'' አልኩና ከዚያ በፊት ወደ እማውቀው የሠራተኛ አስቀጣሪ ድርጅት ደውዬ ባስቸኳይ አንድ ተላላኪ እንደምፈልግ ነገርኳቸው ።

ከአንድ ሰዓት በኋላ በአረፍት ላይ ያለ አንድ ተማሪ ለመቀጠር፡ ፈቃደኛ መሆኑን ገለፀልኝ ። ደመወዙ በሳምንት ስልሳ ዶላር ነው ። ይህን እንደሰማሁ ።



ወደ ቴሌክስ መኪናው ሄጄ ለቪዳል መልእክት አስተላለፍኩ። ''በሳምንት ስልሳ ዶላር የሚከፈለው አንድ ተላላኪ ለመቅጠር ስለ ፈለግሁ መስማማት አለመስማማትህን ግለጽልኝ ።

በርደን''

እኔ ይህንን ሳደርግ ቫል ዝም ብላ ትመለከተኝ ነበር ። ''እሺ ይሄ በዚህ አለቀ'' አልኳት ፣ ወደ ወንበሬ እየተመለስኩ ። ባልሽ ካልተስማማ እከፍለዋለሁ''

''ደስ የሚለው አይመስለኝም''

''ምንም ማድረግ አልችልም ። ንገሪኝ ቫል በሱ ወጪ የሚጓዙት ሰዎች ሁሉ ምንድናቸው ?''

''ገሚሶቹ ለሱ የሚሠሩ ሰዎች ናቸው ? ገሚሶቹ ጉቦ የሚሰጣቸው ናቸው ። ገንዘብ መስጠት ስለሚፈራ የነፃ ጉብኝት ያዘጋጅላቸዋል ። ?''

ለምን ድነው ጉቦ የሚሰጣቸው ?''

''መረጃ ለማግኘት ነዋ ። ሌሎች በሚሠጡት መረጃ ነው የሚኖረው ።''

''የሚያገኘው የዱቤ አገልግሎት በየቦታው ከስድስት ወር ወደ አንድ ወር ዝቅ እያለ መሆኑን ሰምተሻል እንዴ? ያጋጠመው ችግር አለ?'' ስላት ሽምቅቅ አለች ።

''ችግር?''

''እንደሚወድቅ ነው እሚወራው ? ከወሬም በላይ የሆነ ይመስለኛል ። በርግጥ የሚወድቅ ይመስላል ቫል ?'' ስላት በምላሷ ከንፈሯን አረጠበችና ፣

''በሚሊዮን የሚቆጠር ብር ነው ያለው'' አለችኝ ፡

''ታዲያ ያ ምንድነው ? ከሱ በፊት ብዙ ሚሊዮን ብር የነበራቸው ሰዎች ወድቀዋል ። ግን ላንቺ የነገረሽ ነገር አለ ? እይው ቫል ለማወቅ ጉጉት አድሮብኝ አይደለም የምጠይቅሽ ። ላንቺ እየሰብኩ ነው ። እንደተወራው ቢወድቅ ምን ትሆኛለሽ ?''

''ሰይጣን የራሱን ሰዎች ይጠብቃልቸዋል ።'' በዚህ ላይ እንዳ

ለን የውስጥ መገናኛው ድምጽ አሰማ ። ቁልፉን ስሜነው ዳየር ባስ ቸኳይ መከናወን ያለባቸውን ሶስት ትእዛዞች የላከልኝ መሆኑን ነገረኝ ። ያለኝን ስለሰማች መልክቱን አልደገምሁለትም ።

"ሥራችንን እንቀጥል ።" ብዬ አንዱን ፖስታ አነሳሁ ።

እሷም እያዘገመች መጻፉን ቀጠለች ። ዳየር የላከልኝን ትእዛዝ ደርሶ እየተመለከትኩ ታፕ ታፕ የሚለውን የጽሕፈት መኪና ድምጽ ስሰማ ንዴቴን መቆጣጠር አቃተኝ ።

"ቫል በዚህ አይነት መቀጠል አንችልም ። ፈጣን ጸሐፊ ማግኘት አለብኝ ። ችግሩ ይታይሻል አይደል ? ጨርሰሽ ስለረሳሽው በዚህ አይነት መቀጠል አንችልም ። ላስቀይምሽ አስቤ አይደለም የምናገረው ።" እያልኩ ስናገራት ፊቷ በድንጋጤ ተጨማደደ ። ከዚያ እጽሕፈት መኪናው ላይ በግንባሯ ደፋ ብላ በሳግ ተርገፈገፈች ።

በድንጋጤ ተነስቼ ወደ እሷ ሄድኩ ። በእቅፌ ውስጥ አድርጊ ላባብላት ከቃጣኝ በኋላ ተውኩት ።

"ቫል ይቅር በይኝ" ቁጣዬና ብስጭቴ ሁሉ ወደ ቁጭትና ወደ ሀዘን ተለወጠ ። ላስቀይምሽ ፈልጌ አይደለም ። ፍቅርዬ አትበሳጪ ። ቀና በይና እንነጋገርበት ። አንድ መፍትሔ ማግኘት አለብን ። ተነሺ ፍቅርዬ ተስፋ አትቁረጪ ።"

ቀና ብላ ተቀመጠች ። "በፊቷ ላይ ያየሁት ፍርሀት አስደነገጠኝ፣"

"ምን እየሆነ እንደሁ አይታይህም እንዴ?" አለችና በመዳፏ አይኖቿን ጫን ጫን አደረገቻቸው ።

"በርግጥ ሥራውን የረሳሁት ይመስልሀል? በፊትህ የሚደረገው ትንንቅ እንዴት አይታይህም?" ስትለኝ ትክ ብዬ ተመለከትኳት ።

"ትንንቅ ?! ይቅርታሽን ግን የምትይው ሁሉ ሊገባኝ አልቻለም" ስላት ተስፋ በቆረጠ አይነት ጭኗን መታ መታ አደረገች ።

"ስንቴ ላስረዳህ? አንተ አይገባህም" ብላ አፍጥጣ ተመለከተች ኝና አቀረቀረች ።

"እየቀጣኝ ነው ። ገና ልጽፍ ጣቶቼን እጽሕፈት መኪናው ላይ ሳሳርፍ ተጽዕኖ ያሳድርብኛል ። ስህተት እንድሠራ ያደርገኛል ። ገና ቁልፎቹን ስነካ ጣቶቼ ውሀ ይሆናሉ ። ትንንቅ ነው በርዳን ዛሬ



ጠዋት ተኝቼ እንዳረፍድ ያደረገኝ እሱ ነው ። ትላንትናም ወደ ፓልም የባህር ዳርቻ ሄጄ የማልፈልገውን ልብስ እንድገዛ ያደረገኝ እሱ ነው። በራሴ ላይ የነበረኝን መተማመን ሁሉ ሆን ብሎ የደመሠሠው እሱ ነው ። እየቀጣኝ ነው!"

ትሪልባይና እስቬንጋሊ ፣ ስይጣናትና እርኩስ መናፍስት... ሁሉም እንደገና ተመለሱ ። የማደርገው ጠፍቶኝ ዝም ብዬ ተመለከትኳት ። የምትለኝ ሁሉ እንዲገባኝ እየጣርኩ ነው ።

"ግን ለምን ቫል? ለምንድነው ሊቀጣሽ የሚመክረው?" ስላት በንዴት እጆቿን ጨብጣ ፣ እየተወራጨች ።

"ከመጀመሪያው ምሽት በኋላ ከሱ ጋር ነጠላ ተጋፈን አናውቅም ። አ በርደን! ከሱ ጋር ?!በምንም አይነት! በምንም! አይነት ስለሱ መናገር አልችለም" አለችና አይኖቿን በመዳፏ ሸፈነች ።

የቴሌክስ መኪናው መንቀሳቀስ ጀመረ ። እዚያው እንደቆምኩ ኮር ብዬ ተመለከትኩት እሷም ፣ ሲ.ቃ እየተናነቃት ዝም አለች ።

"እሱ ነው" ከአይኖቿ የሚወጣው ፍርሀት አንቀጠቀጠኝ ። የቴሌክስ መኪናው መጻፉን አቆመ ።

"ሂድና ተመልከተው ።"

ልቤ እየዘለለ ወደ ተሌክስ መኪናው ሄድኩና ወረቀቱን በጥሼ ተመለከትኩት ። ሳነበው እጄም ወረቀቱም ይንቀጠቀጡ ነበር ።

"በማይረባ ነገር አታስቸግረኝ ። የፈለግኸውን ሰው መቅጠር ትችላላህ ። ሚስስ ቪዳልም ፣ ረዳት ጸሐፊ ከፈለገች ቅጠርላት ።"

ሄንሪ ቫዳል ።

መልእክቱን ዝም ብዬ ለቫል ሰጠኋት ። አንብባው ስትጨርስ ተያየን ።

"እየኸው አይደል" አለችኝ እየተንቀጠቀጠች "እንደተሳካለት አውቋል ። አሁን ፣ አመንከኝ ? አሁንም እያበድኩ ይመስልሀል?አሁንም በሱ ተጽእኖ ሥር አይደለችም ብለህ ነው እም ታምነው? ሙሉ በሙሉ በሱ ፈቃድ የምንቀሳቀስ መሆኔን አታምንም ።?"

"ልረዳሽ የምችልበት አንድ መንገድ መኖር አለበት ቫል ፣"

"ግን አሁንም አላመንከኝም ። አይደል ?"

"አሁን አምኛለሁ ። ሌላ ሊሆን አይችልም ። ቫል በተጽናው ሥር አውሎሻል ። ግን እንዴት ነው ልረዳሽ የምችለው ?ስላት በድካም የዛለ ጭንቅላቷን ነቀነቀች

"ምንም ልታደርግልኝ አትችልም ። ማንም ሊረዳኝ አይችልም ። እቋቋመዋለሁ ፣ ብዬ አስቤ ነበር ፣ ግን አልቻልኩም" አለችና ዞር ብላ በከፊል ለራሷ እንዲህ አለች ።

"በህይወት እስካለሁ ድረስ ፣ በህይወት እስካለ ፣ ድረስ ፤ ባሪያው ሆኘ ነው እምኖረው ።" ትንሽ ቆይቶ ዳየር እሷ ፊት በምንም አይነት ጣትህን እንዳታጮህ ያለኝ ትዝ አለኝ ፣ የሚያስከትለውን ችግር ሳላስበው እጄን አንስቼ ።

"ቫል ተመልከቺኝ" አልኩና ጣቴን ፣ አጮሁኩ ።



## ስድስት

የጠረጴዛዬ ሰዓት ሰባት ከሩብ ይላል ። ከቫል ጋር በዚያ ሁኔታ ስጨነቅ ቆይቼ ሁለት ሰዐት ማለፉ አልታወቀኝም ። ድንጋጤው ስላ ልለቀቀኝ ሥራ መሥራት አልቻልኩም ። እፊቴ የተከመሩትን ትዕዛዞች አፍጥጬ መመልከት ብቻ ሆነ ።

ምንድ ነው ያደረግሁት? እያልኩ ራሴን ደጋግሜ ጠየቅሁ ። ጣቴን በማጮህ ምን አይነት ሰይጣን ነው የቀሰቀስኩት? ዳየር ያስጠነቀቀኝ ቢሆንም እንዲህ አይነቱ አስፈሪ ሁኔታ ይፈጠራል ብዬ አላሰብኩም ። ገና ጣቴን እፊቷ ሳጮህ በቅፅበት ንሁልል ብላ ፉዞ ሆነች። እፊቷ ላይ የሚፍለቀለቀው ስሜት ሁሉ ጥፍት ብሎ አመድ መሰለች። አይኖቿ መመልከታቸውን አቆሙ ።

ከዚያ እፊት ለፊቷ ያለውን ግርግዳ እየተመለከተች "እገልህለሁ ! ብላ ጮኸች ።

"አንተ ካልሞትክ ነፃ አልወጣም ! ሞትህ ብቻ ነው የመዳን ተስፋዬ"

አለሁበት ቦታ ደረቅሁ ። ስመለከታት ቀስ ብላ ተነሳች ።

ከፊት ለፊቷ አንድ ሰው የምታይ ይመስላል ። "እዚህ ቆመህ ሳቅ ብኝ" አለች "በደንብ ሳቅ አንተ ሰይጣን አበላሽተኸኛል ! ጉድተኸኛል! አሁን እኔ በተራዬ አጠፋሀለሁ" አለችና ጥፍሮቿን አሹላ ፣ ጥርሶቿን እግጥጣ ፣ ተንደርድራ ከግርግዳው ጋር ተጋጨች ። ከዚያ መለስ ብላ ደም በለበሱት አይኖቿ አፈጠጠችበትና እንደገና ተጠግታ በሁለቱም እጆቿ ግርግዳውን ደበደበች ።

ቆይታ ከአቅሟ በላይ የሆነ ሰው አንቆ የያዛት ይመስል "ልቀቀኝ!" ብላ ጮኸች ።

"እገልሀለሁ! እገልሀለሁ!"

አስፈሪና አስጨናቂ ሁኔታ ነበር ። እቆምኩበት ሥፍራ ደርቄ ቀረሁ ። ከዚያ አንድ ነገር ያነቃት ይመስል ጉሮሮዋን ለማስለቀቅ

እየሞከረች እሪ ብላ ጮሃ ተንበረከከች ። ፊቷን አጨማዶ የያዘው ፍርሀት ቀስቀሰኝና እንደምንም ብዬ እጆቿን ጥርቅም አድርጌ ያዝኳቸው ።

"ቫል!"

በሚያስደንቅ ሀይል አንድ እጇን አስለቅቃ በጥፊ ደረገመችብኝ። ለጥቂት ጊዜ አይኖቼ ብርሃን አጡ ። ለቅቂያት ወደ ኋላዬ ስንገዳገድ ተነስታ ቆመችና የሆነ ሰው እንዳይመታት የምትከላከል ይመስል እጆቿን አወናጭፋ በጀርባዋ ተዘረጋች ። ስትወድቅ የጠረጴዛው እግር ማጅራቷን ሲመታት አይኖቿ ተስለምልመው ፀጥ አለች ።

በድንጋጤ ተሸብሬ ልቤ እየዘለለ ተንደርድሬ ሄጄ አጠገቧ ተንበረከክሁ ። ስትተነፍስ ጡቶቿ ወደ ላይና ወደታች ቢሉም ሙሉ በሙሉ አእምሮዋን ስታለች ።

እየተርበተበትኩ ሄጄ በውስጥ መገናኛው ዳየርን ጠራሁት ።

"ማን ነህ አንተ?" አለኝ በስለቸ ፣ አነጋገር "ምሳ ልበላ መሄዴ ነው"

"በርደን ነኝ ። እርዳታ እፈልጋለሁ" ብዬ ጮሀኩበት "ሚስስ ቪዳል አደጋ አጋጥሟታል ። ባስቸኳይ ዶክተር ይዘህልኝ ና" ስለው ደንገጥ ብሎ ።

"ተጐድታለች እንዴ?" አለኝ ።

"አዎ ተጐድታለች ። አንድ ሰው ላልክኝ ። ዶክተሩንም ባስቸኳይ ይዘህ ድረስ ።"

"ደረስኩ" አለኝ በተጣደፈ ድምፅ ። መገናኛውን ዘግቼ ዞር ስል ቫል አቃሰተች ። ተንደርድሬ ስሄድ አኖቿን ከፈተች ።

"አቤት እራሴን ። ምንድነው የሆንኩት ?"

"ወድቀሽ ነው" አልኳት "እዚያው ሁኚ እርዳታ ጠይቄልሻለሁ።"

"እንደተንጋለለች እጄን እስኪያመኝ ድረስ ጥብቅ አድርጋ ያዘች ።"

"እዚህ ነበር አይደል? አየኸው አይደል!" ብላ ተንቀጠቀጠች ።

"ሲገለኝ ነበር በርደን ። እባክህ ብቻዬን ጥለኸኝ አትሂድ ።"



"የትም አልሄድ ። ዶክተሩ እየመጣ ነው ። ዝምበይ" ስላት

አንድ ነገር አለችና በረጅሙ ተነፈሰች ። ከዚያ አይኖቿ ተከደኑ እንደገና እራሷን ሳተች ። ቆይቶ በሩ ተከፈተና በመካከለኛ እድሜ ውስጥ ያለች አንድ ሴት ገባች ። ነጭ ፀጉርና አትኩረው የሚመለከቱ አይኖች አሏት ። ቫልን ትክ ብላ ስትመለከታት ገለል አልኩላት ። አጠገቧ ተንበረከከችና የቀኝ አይኗን ከፈት አድርጋ አየች ። የልብ ትርታዋን አዳመጠች ።

"ሚስስ ክሌመንስ እባላለሁ ። የሚስተር ቪዳል ሠራተኛ ነኝ" አለችኝ ።

"ትተኸን ብትወጣ የተሻለ ይሆናል ። ሚስተር በርደን"

"ጠረጴዛው ጭንቅላቷን መትቷታል" አልኳት ወደበሩ እያመራሁ ።

"የምረዳሽ ነገር የለም?"

"ሀኪሙ እየመጣ ነው ። እስከሚያያት ድረስ እዚሁ ብትቆይ ይሻላል ።"

በሚንቀጠቀጡት እግሮቼ ከክፍሉ ወጥቼ በኮሪደሩ ውስጥ አልፌ ደረጃውን ወረድኩና አትክልቶቹ መሀል ገባሁ ።"

"በርደን"

በድንጋጤ ዞር አልኩ ። ዳየር በፍጥነት ወደ እኔ እየመጣ ነበር ።

"ምንድነው የተፈጠረው?"

ሲለኝ የሆነውን መደበቅ አልቻልኩም ።

"ፍዝዝ አለችና ወደቀች ፤ ጠረጴዛው እራሷን መትቷታል" ስለው አይን አይኔን ተመለከተኝ ።

"በጣም ደንግጠሀል ። አሁን የሚያስፈልግህ አንድ ነገር መጠጣት ነው ። ና ወደ እኔ ቢሮ እንሂድ" ብሎ እጄን ይዞ እየመራ ወደ ቢሮው ወሰደኝ ። ልንገባ ስንል የመኪና ድምፅ ሰምቼ ዞር ስል ።

"ዶክተር ፎንታን ነው" አለኝ ዳየር "እሱ ሊረዳት ይችላል"

አቢሮው እንደገባን ውስኪ ቀድቶ ሰጠኝ ።

“እስቲ አረፍ በል ። ጣዕረሞት ያየህ ነው እምትመስለው” አለኝ ዳየር ። ትኩር ብዬ ተመለከትኩት ። እንደወትሮው አያሾፈብኝ አይደ ለም ። ከልቡ ነው የሚናገረው ።

ቁጭ ብዬ የቀዳልኝን ውስኪ ጨለጥኩና ብርጭቆውን አስቀመ ጥኩ ።

“አንተ ነህ እንዴ የቀሰቀስክባት?” ብሎ ጣቶቹን አጮኸ ። በአዎንታ ራሴን ነቀነቅሁ ።

ሳላስበው የሆነውን ሁሉ ዘክዝኬ ልነግረው ነበር ።

“ልክ እኔ እንደሆንኩት ነው ። የሆነውን ሁሉ ለቪዳል መንገር ይኖርብሀል” ሲለኝ ተሽማቀቅሁ ።

“ዶክተሩ ቢነግረው አይሻልም? ምን ያህል እንደተጐዳች የሚ ያውቀው እሱ ነው”

“ይሻል ነበር ግን ቢዳል የሆነውን ሁሉ በመጀመሪያ ካንተ መስማት መፈለጉ አይቀርም ። እስቲ ከውስኪው ድገም ።”

“አመሰግናለሁ በቃኝ ።”

“አንድ ጠጣ ። ድንጋጤውን ገና አልለቀቀህም እኮ” አለና ለሁለ ታችንም ቀዳ ።

“እና በርደን አደጋው የደረሰባት ጣትህን በማጮኸ መሆኑን በምንም አይነት ለቪዳል እንዳትነግረው ። ደስ አይለውም ። ዝም ብላ ራሷን ስታ መውደቋን ብቻ ንገረው”

“እውነትህን ነው ። አልኩት ዳየርን በልቤ እያመሰገንሁ ።

“ግራ የሚያጋባ ነው ። አይደል? ምን ይመስልሀል? ስታያት አእ ምሮዋ በሆነ ሀይል ተፅዕኖ ሥራ የዋለ አልመሠለህም? አንዳንዴ ስለ ቪዳል ሳስብ እገረማለሁ ። የሰውን አእምሮ በተጽዕኖ ሥር የማዋል ሀይል ሊኖረው ይችላል? ፍጥጥ ብሎ ሲመለከተኝ በአየር ላይ የተንሳፈፈ ኩ ነው እሚመስለኝ ። ግራ የሚገባ ሁኔታ ነው ። አእምሮዋን በተጽ ዕኖው ሥር ያዋለው ይመስልሀል?” ሲለኝ መልስ አልሰጠሁትም ግን

“ለምን እንደዚያ ያደርጋል ።” ብዬ ጠየቅሁት ።

“ሳያት ሁኔታዋ ብዙ ጊዜ ያሳስበኛል ። ዶክተር ራፓች የተባ ለው ጓደኛዬ ያጫወተኝ ትዝ ይለኛል ። እንደ እሱ አባባል ፍልቅል ቅና ውብ ሴቶች አብዛኛውን ጊዜ አይነጥላ ይኖርባቸዋል ። ዶክተሩ



የስነአእምሮ ሊቅ ስለሆነ እርግጠኛ ሳይሆን እንዲህ አይነቱ ነገር ከዎንም ተነስቶ የሚናገር ሰው አይደለም” ሲለኝ ትክ ብዬ ተመለከትኩት።

“እና ስለሚስስ ቪዳል እጫወትኸዋል ማለት ነው?” ስለው ደነገጠ ።

“ምን ማለትህ ነው? የማወቅ ጉጉት አለኝ እንጂ አሉባልታ የማወራ ሰው አይደለሁም ። ዶክተሩ የሰውን አእምሮ በተጽዕኖ ሥር የማዋል ችሎታ ስላለው አንድ ሰውም አጫውቶኛል ። የሰውየው ሚስት አይነ ጥላ ነበረባት ፤ ታዲያ ሊገናኛት በፈለገ ቁጥር አእምሮዋን በተጽዕኖ ሥር ማዋል ነበረበት ።

ለብዙ ጊዜ በዚህ አይነት ተሳክቶለት አብረው ከኖሩ በኋላ ሴትዮዋ አበደች ። አሁን የምነግርህ ግምቴን ነው ። ሚስተር ቪዳል እቫል ላይ እንደዚያ አይነት ተጽዕኖ የሚያደርግባት ነው እሚመስለኝ” ሲለኝ በፍርሀት ተጨበጥኩ ። እውን በቫል ላይ እንደህ አይነት ነገር እየተፈፀመባት ይሆን?

“ነጠላ ተጋፈን አናውቅም” ያለችኝ ትዝ አለኝ ።

“አሁንም አልተሻለህ?” አለኝ ዳየር በሀዘኔታ እየተመለከተ ለምን ወደ ቤትህ አትሄድም ። በጣም እንደተነካህ ይገባኛል ።”

ከውስኪው ጠጣሁለት ።

“በጣም ነው የተሰማኝ ። ጠረጴዛው እራሷን ሲገጫት ሞተች ብዬ ነበር ።”

“እቤትህ ሂድ ።”

“የለም አልሄድም ። ወደ ቢሮዬ እመለሳለሁ ። ብዙ የምሠራው ሥራ አለኝ ።”

“ያን የውሸት ዶክተር ለቪዳል እንዲደውልለት ንገረው ።”

ዶክተር ፎንታን ከቤት ወጥቶ ደረጃዎቹን ሲወርድ አገኘሁት ። ረጂም ነው ። ትንንሽ አይኖችና ሹል አፍንጫ አለው ። እራሴን አስ ተዋወቅሁትና ፤

“እንዴት ነች ዶክተር?” ብዬ ጠየቅሁት ።

“ጠረጴዛው አቁስሏታል ። ግን ይህን ያህል የሚያሰጋ አይደለም። ትንሽ ቀን መተኛት ይኖርባታል” አለኝ ።

"ሚስተር ቪዳል የሆነውን መስማት አለበት" ስለው ፈገግ አለ ። ከዚያ ቀና ብሎ ተመለከተኝና "ነግሬዋለሁ ።" አለኝ እመኪናው ውስጥ እየገባ ።

እቢሮዬ ገብቼ በሩን ዘጋሁ ። እእምሮዬ እንደተረበሸ ነው ። እወንበሬ ላይ ስቀመጥ ስልኩ አንቃጨለ ። ቪዳል መሆኑ ስለተሰማኝ ስልኩን ማንሳት ፈራሁ ። ልቤ በሀይል ደወለ ። ደጋግሞ ሲያንቃጭልብኝ አነሳሁት ።

"በርደን ነህ?" ድምፁን ስሰማ የባሰ ደነገጥኩ ።

"እዎ ሚስተር ቪዳል"

"ምንድነው የሆነው? ያ ጅል ዶክተር ሚስስ ቪዳል ራሷን ስታ ስትወድቅ ተጐድታ ለች ነው እሚለኝ ። እንደዚያ ስትሆን አይቼ አላውቅም ። አንተ እዚያው ነበርክ ። ምን ሆና ነው ራሷን የሳተችው?" ሲለኝ የደረቀውን ከንፈሬን አራስኩ ።

"እኔ እንጃ ሚስተር ቪዳል በቴሌክስ መልዕክት እያስተላለፍኩ ነበር ። ሚስስ ቪዳል ስትነሳ ሰማሁ ። ጥቂት ቆይታ ወደቀች ።

"እራሷን የሳተች ይመስልሃል?"

"ይመስለኛል" ስለው ፀጥ አለና ከት ብሎ ሳቀ ።

"ሴቶች!. . ." ብሎ እንደገና ፀጥ አለ ።

"ሥራውን እንዴት ይዛዋለች?"

"ደህና ይዛለች ሚስተር ቪዳል"

"በርደን ከዚህ ቀደም ያልኩህን አስታውስ ። ሁሌ እውነቱን ንገረኝ" ብሎ ሲጮህ ኩምሽሽ አልኩ ።

"ጥያቄዬን እደግመዋለሁ ። ባለቤቴ ሥራዋን እንዴት ይዛዋለች?" ደህና ይዛለች ። ብዬ ልመልስለት ስዘጋጅ በስህተት የተሞላው ሥራዋ ከአንድ ሰዐት በኋላ የሚደርሰው መሆኑን ሳስታውስ መዋሸቱ እንደማያዋጣኝ ተገነዘብኩ ።

"እርግጥ ለብዙ ጊዜ ሩምምድ አላደረገችም ። ስድስት አመት ሙሉ የተወችውን ሥራ ባንዴ!" ንግግሬን አቋርጦ "በብቃት ትሠራዊለች?" አለኝ ።



"በብቃት መሥራት ከእኔ እንጂ ከሷ አይጠበቅም ሚስተር ቪዳል" ስለው ሳቀ ።

"ብልህ ሰው ነህ ። ዶክተሩ ለጥቂት ቀናት መተኛት ይኖርባታል ነው ያለኝ ። በርደን አንድ ፀሐፊ ቅጠር ። ባለቤቴም ስለሚሰለቻት በሥራው የምትገፋበት አይመስለኝም ። ሴቶችን እውቃቸዋለሁ ። ስለ ሥራ ማውራት እንጂ በተግባር መፈፀም አይሆንላቸውም ። የሆነ ያልሆነ ሰበብ እየፈጠሩ እራሳቸውን ይስታሉ ።" ሲለኝ በጣም ስለጠላሁት የተናገረው እቢሮዬ ውስጥ ቢሆን ሳልደበድበው አልቀርም ነበር ።

"ጥሩ ፀሐፊ ፈልጌ እቀጥራለሁ" አልኩት ።

"የተሟላ አገልግሎት ነው እምፈልገው በርደን ። እና ያንን ለማሟላት ጥረት አድርግ ።" ብሎ ስልኩን ዘጋው ።

መነጋገሪያውን እያስቀመጥኩ እጠረጴዛዬ ላይ አፍጥጠው የሚጠብቁኝን ሥራዎች ተመለከትኩ ። አሁን ስለሆነውም ሆነ ዳየር ስለነገረኝ ነገር ለማሰብ ጊዜ የለኝም ። ትእዛዞቹ መፈጸም ይኖርባቸዋል ።

ወደ ሠራተኛ አስቀጣሪ ድርጅት ደወልኩና በኮንትራት የምትሠራ ብቃት ያላት ፀሐፊ እንደምፈልግ ነገርኳቸው ።

"በጣም በአስቸኳይ ነው እምፈልገው ። ስለዚህ አሁኑኑ ወደ እኔ እንድትመጣ ብዬ የሄንሪ ቪዳልን ስም ሳነሳባት የምታነጋግረኝ ሴት ደንገጥ ብላ በግማሽ ሰዐት ውስጥ ምርጥ ፀሐፊ እንደምትልክልኝ አረጋገጠችልኝ ።

"ኮኒ ሀገንን እልክልሀለሁ ። ምርጥ ፀሐፊ ነች ። ለምን ያህል ጊዜ ነው እምትፈልጓት ?"

"ለአንድ ወይም ለሁለት ሳምንት ሊሆን ይችላል ። እርግጠኛ አይደለሁም"

"እሺ ሚስተር በርደን አሁኑኑ እልክታለሁ ።"

"ተላላኪው መጥቷል እንዴ?" ረስቼው ነበር ።

"አልመጣም ።"

"ይመጣል ። ምሳህን በልተህ ሂድ ስላልኩት ነው የዘገየው ።

እንዲህ ባለችኝ ከአሥር ደቂቃ በኋላ ልጁ መጣ ። ሬይ ፓርተር ይባላል ። ፀጉሩ እንደቁመቱ ረጂም ነው ። ስራውን በቅልጥፍና ለመሥራት የተዘጋጀ ይመስላል ። ጭምት ልጅ ነው ።

ቪዛ እንዴት ማውጣት እንደሚችል ካስረዳሁት በኋላ ፓስፖርቶቹን ሰጥቼ ላክሁት ።

ከዚያ ትዕዛዞቹን መፈጸም ጀመርኩ ። ስልክ ስደውል ፣ ቴሌክስ ሳደርግና የመረጃ መጻሕፍቶቼን ስመለከት ስለቫል ለማሰብ ጊዜ አላገኘሁም ።

ኮኒ ሀገንም ቆይታ ደረሰችልኝ ። አስራ ስምንት ወይም ሀያ አመት ቢሆናት ነው ። ወፍራም ሴቶች በሚበዙበት አገር በውፍረት ከእሷ የምትመስተካከል ሴትእይቼ አላውቅም ። ክብ ፊቷ ቅልጥፍናዋን፡ ተጫዋችነቷንና ደግነቷን አጉልቶ ያሳያል ። ገና ሳያት ወደድኳት ። እንደ ወፍራም ሴቶች ሁሉ ጥብቅ ያለ ሱሪና ትላልቅ ጡቶቿን ሸፈን ያደረገ ሸሚዝ ለብሳለች ።

ሶስት ፕሮግራሞችን እንድትተይብልኝ ሰጠኋት ። አጫጭር ወፍራም ጣቶቿ እጽሕፈት መኪናው ላይ ሲያርፉ የሚያስፈልገኝን እረዳት ያገኘሁ መሆኑ ታወቀኝ ።

ሶስቱ ፕሮግራሞች በአሥራ አምስት ደቂቃ ውስጥ ተሠርተው አለቁ ። ያለምንም ስህተት ነው የተሠሩት ። ደስ እያለኝ ተጨማሪ ሥራዎችን ሰጠኋት ።

እስከ አሥር ሰዓት ከአርባ አምስት በሥራ ተጠምደን ቆየን ። ፓርተርም ቪዛዎቹን ይዞልኝ መጣ ። ነገ ይሄን ያህል ሥራ እንደማይበዛበት አረጋጌጨለት አራቱን ፕሮግራሞች በየሆቴሉ እንዲያደርስልኝ ሀጠሁት ።

"ሥራ ካለ ይስጡኝ ሚስተር በርደን" አለ ፈገግ ብሎ "ለሚከፈለኝ ዋጋ ተመጣጣኝ ሥራ መስራት ነው እምፈልገው ።"

ሲወጣ ኮኒ ቦርሳዋን ከፈተችና የወረቀት ክረጢት አወጣች ።

"ሚስተር በርደን ትንሽ ትቀምሳለህ?" ብላ ጠየቀችኝ "እኔ ከራት በፊት መክሰስ ቢጤ ለምጃለሁ ።"

ግድየለም አመሰግናለሁ ። ሥራችንን እየጨረስን ነው ።" ብዬ ጠረጴዛዬን ባዶ ሆኖ ሳየው ማመን አቃተኝ ።



ኮኒ ማንዲዊቿን ገመጥ አድርጋ እርካታዋን ጭንቅላቷን በመነቅነቅ አሳየችኝ ።

"ለሚስተር ቪዳል በመስራቴ በጣም ነው ደስ ያለኝ ። በዚያ ላይ የቢሮው ምቾት ለወንድ ጓደኛዬ ስንቱን አወራለት ይሆን? ታውቃለህ ሚስተር በርደን ለሚስተር ቪዳል መሥራት ለኔ ትልቅ ክብር ነው ።" እንዲያ ስትለኝ ልወጥውጥ አልኩ ። እስከ አሁን በሥራ ተወጥሮ ስለነበር ቫልንና ቪዳልን እረስቻቸው ነበር ።

"እሺ ሥራችንን እንጨርስ" አልኩኝ "እየመሸ ነው ።"

አሥራ አንድ ከአሥር ላይ የመጨረሻውን ፕሮግራም ሠራሁ ። ኮኒም አይ ቢ ኤሟን ሸፍና ተነሳች ።

"ነገ በስንት ልምጣ?"

"በሶስት ድረሺያ"

"እደርሳለሁ ደህና እደር" ብላኝ በግዴለሽ አረማመዷ ገልበጥ ገልበጥ እያለች ወጣች ።

ወደ ቤቴ ለመሄድ የሚያጣድፈኝ ነገር አልነበረም ። ሮዳንም እንደማሽ አስጠንቅቄያታለሁ ። እቤት ሄጄ እሷ ባለችበት ዛሬ ስላጋጠሙኝ ነገሮች በጥሞና ማሰብ አልችልም ።

ስለዚህ ዝም ብዬ ተቀመጥኩ ። በመጀመሪያ ዳየር የነገረኝን ነገር አሰብኩበት ። ቪዳል ቫልን በተፅዕኖ ሥር አውሎ እየተጠቀመባት ይሆን? ሊሆን መቻሉን ሳስበው በንዴት ተቃጠልኩ ። ሰው ይህን ያህል መጥፎ ሊሆን ይችላል?! የነገረችኝ ትዝ አለኝ ።

እርኩስ መንፈስ ነው ። ሰይጣን ነው ። ይህን ሰይጣናዊ ተግባር በርግጥ እየፈጸመው ከሆነ እንዴት አድርጌ ነው ልረዳት የምችለው? ነገሩን በዝርዝር ልንገራትና ላስጠንቅቃት? ደጋግሜ ካሰብኩበት በኋላ መፍትሄ ሳላገኝ ለሷ መንገሩ የባሰ ሊጎዳት እንደሚችል ታየኝ ። በራሷ እንደማታዝና ሙሉ በሙሉ በተጽዕኖው ሥር መሆኗን ነግራኝ የለ? የሚሆነው ሁሉ በግልጽ ስለታየኝ የነገረችኝ ከልቧ እንደሆን ተገዝነ ብኩ ።

"ምንም ልታደርግልኝ አትችልም" ነው ያለችኝ ።

"ማንም ሊረዳኝ አይችል ።"

እንዲህ አይነቱን ሽንፈት ልቀበለው አልፈለግሁም ። በሆነው መንገድ ልረዳት ወሰኛለሁ ። እርግጥ እቪዳል ውስጥ ካለው ሀይል ጋር መጋፈጡ ለኔ አደገኛ ሊሆን ይችላል ። ሳለላወቅ ጣቴን አጮሄ ያደረስኩትን አይነት ጉዳምት ላስከትል እችላለሁ ።

ስለዚህ አልኩ ለራሴ በመጀመሪያ በስነአእምሮ ሰውን በተጽዕኖ ሥር ስለማዋል በይበልጥ ማወቅ አለብኝ ። በዚህ ሞያ የተካነ ሰው ማነጋገር አለብኝ ። ግን የማውቀው ማን አለ? የዳየር ጓደኛ ዶክተር ራፓች አለ ። በሱ ላይ አቅማማሁ ። ዶክተሮች ስለታካሚዎቻቸው ማውራት የለባቸውም ። ግን ይሄ ዶክተር ለዳየር ሚስቱ ንበተጽዕኖ ሥር ስላዋላት ሰው አውርቶታል ። ስለዚህ ጉዳይ የጠየቅሁት መሆኑን ለዳየር እንዲነግረው አልፈልግም ። ዶክተሩ ስም ጠቅሶ እንዳልነገረው እርግጠኛ ነኝ ። በዘዴ ከቀረብኩት ችግር ላይ ገጥመኝ ይችላል ። የስልክ ማውጫውን እያገላበጥሁ ስመለከት ።

ዶክተር ሁጐ ራፓች የነርቭ ሀኪም 1141 ደቡብ ጐዳና ፓልም የባህር ዳርቻ ። የሚል አድራሻ አገኘሁና ደወልኩለት ።

"ዶክተር ራፓች ነኝ'' ረጋ ያለ ወፍራም የአዛውንት ድምፅ መልስ ሰጠኝ ።

"ጆርጅ ፌሎስ እባላለሁ ። ዶክተር ።'' አልኩት እበሬቱ መሥሪያ ቤት ሳለሁ አውቀው የነበረ የአንድ ሰው ስም ተጠቅሜ ።

"የሰውን አእምሮ በተፅዕኖ ሥር ስለማዋል አንዳንድ ነገሮችን ልጠይቆዋዎ እፈልግአለሁ ። ቀጠሮ ይዘን መነጋገር እንችላለን?'' ስለው ፀጥ አለ ።

"ሚስተር ፌሎስ ሰው ነው ወደ እኔ የላከህ?''

"አንድ ግብዣ ላይ ነው ስምዎን የሰማሁት ። ዶክተር ። እርስዎ አንዳንድ በሽተኞችን ለመርዳት አእምሯቸውን በተፅዕኖ ሥር ያውሉ እንደነበር አንዱ ሲያወራ ሰማሁ ።''

"እማውቀው ሰው ነው?'' አሉኝ ረጋ ባለና በተጠነቀቀ ድምፅ ።

"ስሙን አላስታውሰውም ዶክተር ። አጭር ወፍራም መላጣ ነው ። እንደሚያውቁት እግብዣ ላይ የተለያዩ ሰዎች ይነሳሉ ። '' ብዬ ሳቅ አልኩ ።

"ግን ለምንድነው ለማወቅ የፈለግሽው?'' የተለመደ አይነት ምክንያት ሰጠሁት ።



"አንድ ልቦለድ እየጻፍኩ ነው ። እና በዚህ ጉዳይ ላይ የምጽፈው ትክክል እንዲሆን እሻለሁ ። ሊያነጋግሩኝ ከተስማሙ የደንቡን እከፍላለሁ ።''

"ሚስተር ፌሎስ ስራ በጣም ነው እሚበዛብኝ'' ብሎ ለጥቂት ጊዜ ዝም አለ'' ሆኖም በሶስት ሰዐት ላይ እሚመችህ ከሆነ ላነዳጋግሀር እችላለሁ ።

"ከምሽቱ ሶስት ሰዐት?''

"አዎ''

"መልካም ነው ዶክተር እመጣለሁ ።'' ሁለታችንም ስልኩን ዘጋን ። ተመልሼ እሀሳቤ ውስጥ ገባሁ ።

ስለዚህ ጉዳይ ስንጫወት ቫል ትሪልባይንና እስቬንጋሊን ደጋግማ አንስታብኛለች ።

ትሪልባይ ማን ነበረች? እስቬንጋሌስ ማን ነበር? ትሪልባይ የተሰኘ ክላሲካክ የልቦለድ ድርሰት አልነበረም እንዴ? ስለመኖሩ የሰማሁ ይመስለኛል ግን አላነበብኩትም ፡ ይህን መጽሐፍ ባገኝ አንድ ፍንጭ ይሰጠኝ ይሆን ።

እህዝብ ቤተመጻሕፍት ውስጥ አገኘው ይሆናል ። ቤተመጻሕፍቱ በመንገድ ላይ ነው ። ከምሽቱ አንድ ሰዐት ላይ ነው እሚዘጋው ። ብዙ ጊዜ አለኝ ። መጽሐፉን አሁኑኑ ሄጄ ማግኘት አለብኝ ብዬ ወሰንኩ ። ልነሳ ስል ሚስስ ክሌመንስ ገባች ።

"አለህ እንዴ ሚስተር በርደን? የሄድክ መስሎኝ ፈርቼ ነበር ። ሚስስ ቪዳል ጥሪልኝ ብላለች ።'' አለችኝ በመጠራቴ አለመደሰቷን በአይኖቿ እየነገረችኝ ።

"ሚስተር ቪዳል ወደ ሊብያ ስለሚያደርገው ጉዞ እያሰበች ነው ። ለጉዞው የሚያስፈልጉት ነገሮች ሁሉ መዘጋጀታቸውን አንተ ካላረጋገጥክላት አርፌ አልተኛም ብላለች ።''

ልቤ ዘለል ዘለል አለ ። ልታየኝ ስለፈለገች ሰበብ መፍጠሯ ነው እንጂ የጉዞው ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ማለቁን ታውቃለች ።

መሳቢያውን ከፍቼ አንድ ፕሮግራም አወጣሁና "ሚስስ ቪዳል እየሠራችው የነበረ አንድ ትንሽ ጉዳይ አለ ። ከገባሁ አይቀር እሱንም እስፈጽሜ ብወጣ ይሻላል '' አልኩአት ።

“እሺ እንሂድ” ብላ ወጣች ።

በኮሪዶሩ ውስጥ ስናልፍ “እባክህ ለረጅም ጊዜ አትቆይ ። እረፍት ማድረግ አለባት ።” አለችኝ ።

“ጥቂት ደቂቃዎች ይበቁኛል ።”

እበሩ ላይ ስንደርስ አመነታች ፤ ከዚያ ቀስ ብላ አንኳኳችና ከፍታ ወደ ጐን ቆም ብላ አሳለፈችኝ ።

“ሚስተር በርደን መጥቷል” ብላ በሩን ዘግታ ሄደች ።

ቫል እትልቅ ጥንድ አልጋ ላይ ተኝታለች ። መስኮቶቹ ተጋርደ ዋል ። ቀዝቀዝ ያለው ክፍል ምቾት ብቻ በሆኑ የቤት እቃዎች ተሞ ልቷል ።

አመድ ለብሳ ሳያት ደነገጥኩ ። ፍርሀትና ጭንቀት በአይኖቿ ውስጥ ነግሠዋል ።

አጠገቧ ስደርስ እጇቿን ዘረጋችልኝ ። እቅፍ አድርጌ እደረቱ ላይ ልጥፍ ባደርጋት ደስ ባለኝ ። እጇቿ ድርቅ ብለው ቀዝቅዘዋል ።

“እንዴት ነሽ ፍቅርዬ” ብዬ ጠየቅኋት ድምጼን ዝቅ አድርጌ ።

“በመምጣትህ ደስ ነው ያለኝ ።” አለችና አልጋው ላይ እንድቀ መጥ በእጇ ምልክት ሰጠችኝ ። እጇን አልለቀቀችም ።

“ምንድነው የሆንኩት? ቁጭ ብዬ ሥስራ እንደነበር አስታውሳ ለሁ ። ከዚያ እዚህ አልጋ ላይ መሆኔን ነው ያወቅሁት ። ምንድነው የሆንኩት ?”

ዳየር አልዋሸኝም ማለት ነው? ንሁልል ብላ ስትነቃ ምንም እንደማታስታውስ ነግሮኛል ። የሆነውን ሁሉ ልንገራት? ብዬ አሰብ ኩና በፍርሀት አመድ ለብሳ ስትንቀጠቀጥ ሳያት አለመናገሩን መረጥኩ።

“ምን እንደሆንሽ እኔ እንጃ ቫል ። ወደ አንቺ እየተመለከትኩ አልነበረም ። ስትወድቂ ነው የሰማሁት ። ራስሽን ስተሽ ሳይሆን አይቀ ርም ።”

“ሊሆን አይችልም” ብላ እጇን ጠበቅ አድርጋ ያዘች ።

“ከዚህ በፊትም እንደዚሀ ሆኛለሁ ። እሳሎኑ ውስጥ ቁጭ ብዬ ስነሳ ነበር ። ከዚያ የሆነውን ሳላውቅ ራሴን አልጋ ላይ አገኘሁት”



ብላ ተሸማቀቀች ። “በኋላ ጊዜውን ስመለከት የአንድ ሰዐት ልዩነት አገኘሁ ። አንድ ሰዐት የት እንደነበርኩ ፤ ምን እንደሆንኩ አላውቅም ነበር ማለት ነው ። እንዲህ አይነቱ ሁኔታ ሲያጋጥመኝ የዛሬው ስምን ተኛው መሆኑን ነው ።” አይኖቿን ከብለል ከብለል እያደረገች ተመለ ከተችኝ ።

“እሱ ነው እንዲህ የሚያደርገኝ አውቃለሁ እሱ ነው”

እኔም እንዲህ የሚያደርጋት እሱ እንደሆነ አምኛለሁ ። የነገረ ችኝን ሁሉ አመንኩበት ። ሁሉም ነገር በጭንቀት የፈጠረችው አልነ በረም ። በሰውየው ተፅዕኖ ሥር መሆኗን አረጋግጫለሁ ።

“ልረዳሽ የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ” አልኳት “ቫል ከእንግ ዲህ ብቻሽን አይደለሽም ። እኔ አለሁልሽ ” ስላት ተስፋ በቆረጠ አይነት እራሷን በእጅዋ ደገፍ አደረገች ።

“ምንም የምታደርገው ነገር አይኖርም ። አሸንፎኛል”

“ላደርገው የምችለው አንድ ነገር ይኖራል ። እናም አደርገዋለሁ” ስላት ቀና ብላ ተመለከተችኝ ። ሁኔታዋ ልቤን አኮማተረው ።

“የኔን ነገር ተወው በርደን ። እንዴት እየሠራህ ነው? በኔ ምትክ ፀሐፊ አገኘህ?

“እምትተይብልኝ ልጅ አግኝቻለሁ ። የግድ ረዳት ማግኘት ነበረ ብኝ ። አንቺ አጠገብ ለመቆየት ያለኝ እድል እንዲያ ማድረግ ብቻ ነው ።”

“እንደ በፊቷ እኔ ቀልጣፋ ነች” አለችና ሳግ ተናነቃት ።

“እኔ ከእንግዲህ በደንብ ልሠራ አልችልም ። ምንም ነገር ልሠራ አልችልም! አበላሽቶኛል!”

ኮቴ ሰማሁና ፈጠን ብዬ ከአልጋው ላይ ተነስቼ ቆምኩ ። በሩ ተንኳኩቶ ሚስስ ክለመንስ ገባች ።

“ሚስስ ቪዳል መድሐኒታቸውን የሚውጡበት ጊዜ ደርሷል ሚስተር በርደን ።”

“እሺ እየወጣሁ ነው” ብዬ ወደ ቫል ዞር አልኩና ።

“ሚስስ ቫል ምንም የሚያሳስብ ጉዳይ የለም ሁሉንም እኔ እፈጽ ማለሁ” አልኳት ።

“እመሰግናለሁ ።”

በኮሪደሩ ውስጥ አልፌ ደረጃውን ስወርድ እቫል ላይ ያየሁት ጭንቀት እረፍት ነሳኝ ።

“እመኚኝ እመኚኝ” አልኩ ለራሴ ። ቫል የኔ ፍቅር በምንም በምንም ብዬ እረዳሻለሁ ።”

እሕዝብ ቤተመጻሕፍቱ ለመድረስ አምስት ደቂቃ ብቻ ወሰደብኝ ። አሥራ ሁለት ተኩል ሆኗል ። ስገባ አቃቤ መጻሕፍቷ በፈገግታ ተቀበለችኝ ።

“ሄሎ ሚስተር በርደን አሁንም አእምሮን በተጽዕኖ ሥር ስለማዋል ለማወቅ እየጓጓህ ነው ።”

“ጥሩ የማስታወስ ችሎታ አለሽ” አልኳት ። እፊቷ እየቆምኩ ።

“ምንም አልል አረፍ ። በላ”

እየተቀመጥሁ የመጻሕፍት ቤቱን ቃኘሁ ። እማንበቢያው ጠረጴዛ ላይ ጥቂት ተማሪዎች አሉ ።

“ትሪልባይ የሚባል መጽሐፍ ያለ ይመስለኛል ። ልክነኝ ክላሲክ ስነጽሑፍ ነው” ስላት ራሷን ነቀነቀች ።

“በዚያ ስም የሚጠሩ ሁለት መጻሕፍት አሉ ። አንደኛው በ1833 በቻርለስ ኖድለር የተጻፈ ነው ። ሌላው በ1885 በጆርጅ ዱ ሞርዬ የተፃፈ ነው ። ላንተ የሚሆንህ የሞርዬ መጽሐፍ ይመስለኛል ። በእንደዚህ አይነቱ ጉዳይ ላይ ነው የሚያተኩረው” በመገረም ትክ ብዬ ተመለከትኳት ።

“የሚያስደንቅ የማስታወስ ችሎታ ነው ያለሽ” ስላት ሳቀች ።

“ይሄን ያህል የሚያስደንቅ አይደለም ። ከሁለት ሳምንት በፊት መጽሐፉን ተጠይቄ ነበር ። በዚያ ምክንያት ተመልክቼዋለሁ ። ለዚህ ነው በቀላሉ ላስታውሰው የቻልኩት ።”

“አንድ ኮፒ ይኖራችሁአል?”

“በጭራሽ ። ሚስተር በርደን ። እንደ ቻርለስ ዲክንስና እስኮትን የመሳሰሉ ክላሲኮች አሉን ። ዱ ሞርዬ ግን የለንም ። በአሁኑ ጊዜ የሚፈለገው የለም ።



“ያም ሆኖ በሁለት ሳምንት ውስጥ ሁለት ጊዜ ተጠይቋል ።”

“እውነት ነው ። ያጋጣሚ ጉዳይ ነው ። ወደ እንግሊዝ አገር ካልላኩ እዚህ አንድ ኮፒ እንኳ የማገኝ አይመስለኝም” ስትለኝ ተስፋ ቆረጥኩ ።

“መጽሐፉን አንብበሽዋል?”

“አብዛኞቹን የእንግሊዝ ክላሲክ ስለነጽሑፎች አንብቤያቸዋለሁ ። ሚስተር በርደን ።”

“እንግዲያው እመጽሐፍ ውስጥ እስቬንጋሊ የተሰኘ ገፀ ባህሪይ እንዳለ ትዝ ይልሻል ማለት ነው?”

“እንዴታ! በደንብ ትዝ ይለኛል ። በታሪኩ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ነው ያለው ። እንዲያውም መጽሐፉ በጣም ተደናቂ ሆኖ የነበረው በዚህ ገፀ ባህርይ ምክንያት ነው ቢባል ከእውነት የራቀ አይሆንም ።”

“እንዴት? ታሪኩን ልትነግሪኝ ትችያለሽ?

“ባጭሩ እንደዚህ ነው ። የሀንጋሪው ሙዚቀኛ እስቬንጋሊ ትሪልባይ የተባለች ልጅ ያገኛል ። ተሪልባይ የሰውነት ቅርጿ እንከን የማይወጣላት ውብ ልጅ ነበረች ። ከእስቬንጋሊ ጋር ሲገናኙ ሥራ ለመያዝ ጥረት እያደረገች ነበር ። እስቬንጋሊ አእምሮዋ ን በተፅዕኖው ሥር ያውልና ዘፈን ያስተምራታል ። በዚያ ወቅት ጥሩ ድምፅም ሆነ ችሎታው አልነበራትም ። ግን በሱ ሀይል ተፅዕኖ ባንድ ጊዜ ታዋቂ ዘፋኝ ለመሆን በቃች ።

“የዘመኑ ታላላቅ ሰዎች እሷ ስትዘፍን ለማዳመጥ ይጐርፉ ጀመር ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሀብታም ሆነች ።

በዚህ አይነት ቆይተው አንድ ምሽት እለንደን ከተማ ውስጥ ታላላቅ ሰዎች በተገኙበት ስትዘፍን ከመድረኩ አጠገብ እነበረው መቀመጫ ላይ ቁጭ ብሎ ያዳምጥ የነበረው እስቬንጋሊ በልብ ድካም ይሞታል ። በዚህ አይነት ከሱ ተፅዕኖ ሥር ስትላቀቅ ። ያ ተወዳጁ ድምፅ ይጠፋና መዝፈን ያቅታታል ። በመጨረሻውም በችግር ትሞታለች ። ታሪኩ እንግዲህ ባጭሩ ይሄነው ሚስተር በርደን”አለችኝ ፈገግ ብላ ።

“እርግጥ በ׳ ፦ የተጋነነ ታሪክ ነው ። ብቻ በጊዜው በጣም ተወ

ዳጅ ነበር ። አሁን ትዕግሥቱን አግኝተህ ልታነበው የምትችል አይመስለኝም ። ጊዜው ያለፈበት ይመስለኛል ።”

የነገረችኝን ሁሉ በከፍተኛ ጉጉት ነው ያዳመጥኳት ።

“መጽሐፉን ከኔ ሌላ የጠየቀው ሰው ማን እንደሆን ብጠይቅ ያስቀይም ይሆን ።?”

“ልነግርህ አልችልም ። ከዚህ በፊት አይቻት አላውቅም ። በደ ንብ የለበሰች ቆንጆ ሴት ነች የቀይ ዳማ ሆና ትልልቅ ሰማያዊ አይኖች አሏት ። ሳያት አሳስባኝ ነበር ። የተጨነቀች ነው እምትመስለው ።”

“ሻል!”

“በጣም አመሰግናለሁ” አልኩና ተነሳሁ ።” ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው ።”

ወደ መኪናዬ ስመለስ ሰዐቴን ተመለከትኩ ። አሥራ ሁለት ከአርባ አምስት ሆኗል ። ወደ ቤት ገብቼ እንደገና ወደ ፓልም የባህር ዳርቻ መመለሱ ድካም ነው ትርፉ ። ብዙ የማሰላስለውም ጉዳይ አለኝ ። እመኪናዬ ውስጥ ገብቼ አራቅቢያዬ ወደ አለው ሆዋርድ ጆንሰን ሬስቶራንት አመራሁ ።

ከሚንጫጩት ቱሪስቶች ራቅ ያለ ጠረጴዛ አገኘሁ ። ሳንድዊች አዘዝኩና እስኪመጣልኝ ድረስ ተነስቼ ለሮዳ ስልክ ደወልኩ ። ስልኩን ስታነሳ ፣

“የኔ ሸጋ በሥራ ምክንያት አመሻለሁ” አልኳት ።

“እስከ እራት አልመጣም እራትሽን ብይ አትጠብቂኝ ።”

“በየቀኑ እንደዚሁ ሊሆን ነው ማለት ነው” ብላ ጠየቀችኝ በንዴት ፣

“አይመስለኝም ። አንቺስ እንዴት ነሽ?”

“ያው ነኝ ። አሁንም እንደተናደድክብኝ ነው?”

“እርሸው ብየሽ ነበር እኮ ። እኔ እረስቼዋለሁ ።” አልኳት ልቤ ከሷ ጋር አልነበረም ።

“መቼም እኔ ይቅርታ ጠይቁአለሁ ። አንተም ይቅርታ ልትጠይቀኝ የሚገባ ይመስለኛል ። የመታኸኝ እስካሁን ያመኛል ።”



“ይቅርታ እጠይቃለሁ” ስላት ዝም አለችና ፤

“እንግዲህ ወደ ቡና ቤቱ እወርድና እበላለሁ ። እርቦኛል ” አለችኝ ።

“እዎ ብይ ። በኋላ እንገናኛለን የኔ ወለላ” ብዬ ስልኩን ዘጋሁት ።

“ምን አይነት ንግግር ነው?” አልኩኝ ወደ ጠረጴዛው ስመለስ።

ሳንድዊች ቀርቦልኝ ነበር ። እየበላሁ ለዶክተር ራፓች የምለውን አሠላስልኩ ።

* * *

ምዕራብ ፓልም የባህር ዳርቻ የሚገኘው ትናንሽ አሮጌ ቤቶች በብዛት ከሚታዩበት የከተማዋ ክፍል ወጣ ብሎ ነው ። መንገዱ ጠባብ ሆኖ ግራና ቀኙ ከጣውላ በተሠሩ ቤቶች የተሞላ ነው ። እቤቶቹ ፊት ለፊት በበሰበሰ የእንጨት አጥር የተከበቡ የአትክልት ስፍራዎች አሉ ።

ፓርቶሪካውያን ፣ እስፓኒያርዶችና ጥቂት ጥቋቁር ሰዎች በየበረንዳው ላይና በየቤቶቹ ፊት ለፊት እያወሩ ካርታ ይጫወታሉ ። ግማሾቹም እያንጎላጁ ተቀምጠዋል ፤ አንዳንዶቹ ሴቶች ህፃን ልጅ ታቅፈዋል ።

የቤት ቁጥር 1141ን እየፈለግሁ በመኪናዬ ሳልፍ በቁጣ ፣ በጉጉትና በግዴለሽነት የሚመለከቱ አይኖች አከታትለው አረፉብኝ ።

የምፈልገውን ቤት እመንገዱ መጨረሻ ላይ አገኘሁት ። ረዘም ላለ ጊዜ እመኪናዬ ውስጥ ቆየሁ ። ቁጥሩ የተለጠፈበት ቤት የነርቭ ሀኪም የሆኑት የዶክተር ሁጐ ራፓች ነው ብዬ ማመን አቃተኝ ። ቤቱ አውሎ ነፋስ እንዳያጠቃው በዛፉ ሽቦዎች ታሽጓል ። ከሸክላ በተሠራ ግንብ ላይ አንድ የውሀ ማጠራቀሚያ አለ ። ከዚያ ወደ ቤት የሚገባው ቧንቧ ውሀ ያንጠባጥባል ። ወደ ቤቱ የሚወስደው መንገድ በቁጥቋጦ የተሸፈነ ሲሆን የፍራፍሬ ልጣጮችና ቁርጥራጭ ወረቀቶች ተጥለውበታል ። በመስኮቱ ላይ ያሉት የመረብ መጋረጃዎች ቆሽሸዋል ። ከእንጨት የተሠራው የፀሐይ መከለከያ ከአንድ ጐን ወልቆ አዘንብሏል ። አሁን ይሄ በርግጥ የዶክተር ራፓች መኖሪያ ነው?

ከመኪናው ውስጥ ወጣሁና የእንጨት በሩን ገፋ አድርጌ ገባሁ ። ሶስት ደረጃዎችን ወጥቼ እበረንዳው ላይ ደረስኩ ። የበረንዳው ጣውላ ገና ስረግጠው ተንጫጫ ።

ማንኳኪያም የኤሌክትሪክ መጥሪያም የለው ። በእጄ በሩን አንኳኳሁ ። እሙክቀቱ ውስጥ ቆሜ ስጠብቅ ትክሻዬን ከበደኝና ዞር ስል ከፊት ለፊት ካሉት ቤቶች በረንዳ ላይ የተቀመጡ ወጣቶች መካከለኛ እድሜ ያላቸውና ሽማግሌ ጥቋቁር ሰዎች ሀውልት ይመስል ፀጥ ብለው ይመለከቱኛል ።

በሩ ሲከፈት አንድ ሰው ብቅ አለ ። ቀጠን ያለ ረጂም ነጭ ፀጉር ያለው አዛውንት ነው ። ነጭ ቆዳው ተሸብሽቧል ። በግምት ሰማንያ አምስት ወይም ሰማንያ ስድስት ይሆነዋል ። ዝም ብዬ ስመለከተው ጠልቀው የሚያዩት የጥቁር አይኖቹ ሀይል ተሰማኝ ።

"ሚስተር ፊሎውስ?" ሲለኝ ዝግ ባለው ወፍራም ድምፁ ሰየሁት ።

"ልክ ነው" አልኩ "ዶክተር ራፓች ኖት?"

"አዎ ። ግባ ። እዚያ ያሉት ልጆቼ በመገረም እየተመለከቱህ ነው። እያዩ ከመደነቅ ሌላ ምንም የሌላቸው ሰዎች ናቸው ።"

እየመራ አቧራ ወደ ሞላበት ክፍል አስገባኝ ። ከሱ መቀመጫ በስተጀርባ ባለው የመጽሐፍ መደርደሪያ ላይ ብዙ መጻሕፍት ተደር ድረዋል ። ከጠረጴዛው ፊት ለፊት ሁለት መቀመጫዎች አሉ ።

"በሽተኞችን የምመረምርበት ክፍል ይሄ ነው ሚስተር ፊሎውስ" አለኝ ለመቀመጥ ወደ ጠረጴዛው ኋላ እየዞረ ።

"እዚህኛው ላይ ተቀመጥ ። ደረቁ መቀመጫ የታካሚዎቼ ነው።" ብሎ ተቀመጠ ። ሰማያዊ ደም ስሮች የሚንሸራሸሩበትን እጁን እጠረጴዛው ላይ ጣል አድርጎ ይመለከተኝ ጀመር ።

በመጠኑ ግራ ተጋብቼ ስቀመጥበት ወንበሩ እየተንሳጠጠ ይዞኝ ሰመጠ ። አሁን ይሄ ግማሽ ነጭ ግማሽ ጥቁር የሆነ ደሀ ሽማግሌ በርግጥ የሀብታሙ የዳየር ጓደኛ ሊሆን ይችላል? የነርቭ ሀኪምስ ሊሆን ይችላል ?

"ግራ እንደተጋባህ ይታየኛል ሚስተር ፊሎውስ ለምን እንደሆን ይገባኛል ። ምክንያቱን ስንገርህ?" አለኝ ።

"በእንዲህ አይነት ሁኔታ ካልኖርኩ ልጆቼ ወደ እኔ አይመጡም ።"

ልጆቼ የሚላቸው በአካባቢው የሚኖሩ ችግረኛ ሰዎችን ነው ። ወደ እኔ በመምጣት የረዱኝ ነው እሚመስላቸው ። እነሱም የኔን እርዳታ ስለሚፈልጉ ሁኔታው ለሁለታችንም ይስማማል ። ለአንድ ጊዜ ምርመራ ሀያ አምስት ሳንቲም ብቻ ነው እማስከፍለው" ብሎ ትላልቅ ቢጫ ጥርሶቹን እያሳየኝ ፈገግ አለ ።

ደንበኛ አገልግሎት መስጠት ካቋረጥሁ ቆይቻለሁ ። አንድ ጊዜ የራሴ ክሊኒክ ነበረኝ ። አሁን አርጅቻለሁ ፤ አሁን ለሚያስፈልገኝ ነገር የሚሆን በቂ ገንዘብ አለኝ ። እዚህ አካባቢ የምኖረው የኔን እርዳታ የሚሹ ወገኖቼን ለመርዳት ነው ። ሙሉ በሙሉ የራሴን ጥቅም የረሳሁ እንዳይመስልህ ። በሰማይ ቤት የማገኘውን እያሰብኩ ነው ።" ሲለኝ ዘና አልኩ ።

"ሊደነቁ ይገባዎታል ዶክተር" አልኩት ።

"እርስዎን በማግኘቴ እድለኛ ነኝ ።"

"መደነቅ አልፈልግም" ብሎ እጅ ላይ ያሠራትን ተራ ሰዐት ተመለከተ ።

"ሀያ ደቂቃ ብቻ ነው እምሰጥህ ሚስተር ፊሎውስ ምን ልርዳህ?"

እሬስቶራንቱ ውስጥ ሆኜ አንድ ታሪክ አዘጋጅቻለሁ ። እንደሚ ቀበለውም እርግጠኛ ነበርኩ ።

"በስልክ እንዳነጋገርኩዎት ረጂም ልብወለድ ድርሰት ለመጻፍ ታሪኩን እያዋቀርኩ ነው ። ሁኔታው እንደዚህ ነው ። አንድ ሰው (ዶክስ ብለን) እንጥራው — የሰውን አእምሮ በተዕፅኖ ሥር የማዋል ሀይል አለው ። እማታ ክበብ ውስጥ ነው እሚሠራው ። አንድ ሴት ልጅ ፣ ሜሪ ብለን እንጥራት - ወደ ማታ ክበብ ከጓደኞቿ ጋር ትመጣለች ። በጓደኞቿ ገፋፊነት ሰውየው በተፅዕኖው ስር እንዲያውላት ትፈቅድለታለች ። ከዚያ ሰውየው እያዘዛት የተለመዱ ነገሮችን ትፈጽማለች ።

"ዶክስ ሴሰኛ ነው ። ልጅቷን ይወዳታል ። ስለዚህም ሊያገኛት ቆርጦ ይነሳል ። ዶክተር ፣ ዝርዝሩን በማውራት ላደክምዎት አልፈልግም ፣ እና ዶክስ ሜሪ የምትኖርበትን ቦታ ፈልጐ ያገኝና ማታ የመኝታ ክፍሏን መስኮት ሠብሮ ይገባል ። ሜሪ በተፅዕኖው ሥር ስለሆነች ያዘዛትን እንድታደርግ ጣቱን ማጩህ ብቻ ይበቃው ነበር ። ስለዚህ ጣቱን ያጮህና ንሁልል ስትልለት ይገናኛታል ። በማግስቱ ጠዋት ስትነሳ ምን እንደተደረገች ልታውቅ አትችልም ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ዶክስ ባሰኘው ጊዜ እሷ ጋ ይሄዳል ። ዶክተር አሁን ማወቅ የምፈል

ገው እንዲህ አይነቱን ነገር በእርግጥ ማድረግ መቻል አለመቻሉን ነው ።'' ስለው የደከሙ ጥቋቁር አይኖቹ ተመለከቱኝ ።

''እምትፈቅድልኝ ከሆነ ሚስተር ፊሎውስ የታሪክህ መዋቅር አዲስ አይደለም ። እንዲህ አይነቱ ነገር በአሥራ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ፈረንሳይ ውስጥ ተፈፅሟል ።'' ሲለኝ በድንጋጤ ደረቅሁ።

''እና ሊፈጸም ይቻላል ማለት ነው?''

''አዎ ሊሆምን ይችላል '' በቀላሉ ልቀበለው የምችል አባባል አልነበረም ።

''ግን ዶክተር ለኔ እንደሚገባኝ ከሆነና ካነበብኩትም አዕምሮው በተፅዕኖ ሥር የዋለን ሰው የ ማይፈልገውን ነገር እንዲፈጸም ማስገደድ እንደማይቻል ነው የተረዳሁት ። እና እኔ እምለው እውነት ከሆነ አንድን ሴት በዚህ አይነት አስገድዶ መገናኘት አይቻልም ማለት ነው ።''

''በአብዛኛው አንተ እንደምትለው ነው ። ግን ሁሉም ሰው አንድ አይደለም ። ሁኔታው የሚወሰነው በተፅዕኖ አድራጊው ሀይልና በተደራጊው አቅም ነው ። ጠንካራ ሰው አለ ፤ ጠንካራ ያልሆነ አለ ። ራስጥቲን እንደዚያ አይነት ሀይል እንደነበረው ይነገራል ። እኔም የማውቃቸው አንዳንድ ሰዎች ነበሩ ።''

ሁኔታው ደስ ስላላለኝ ንግግራችንን ባጭሩ መቅጨት ፈለግሁ ።

''ሌላ ጥያቄ ዶክተር ። ልጅቷ ከተማውን ለቃ ብትሄድ እዚያም በዶክስ ተፅዕኖ ሥር ልትሆን ትችላለች? እርቀት ልዩነት አያመጣም?''

''ያ በሱ ሀይል ነው እሚወሰነው ። በጣም ሀይለኛ ከሆነ አገሩን እንኳ ለቃ ብትሄድም ከተፅዕኖው ነፃ ልትሆን አትችልም ።''

''ይሄ በሳይንስ የተረጋገጠ ነው?'' ስለው እንደመሰልቸት ብሎ፣

''ሚስተር ፌሎውስ የምሰጥህ መአረጃዎች ሁሉ በሳይንስ የተረጋገጡ ናቸው ። ለምሳሌ እኔ ከዚህ ክፍለ ሀገር ለቀው እሌላ ክፍለ ሀገር የሚኖሩ ታካሚዎች አሉኝ ። አሁን ድረስ በአእምሮ እንገናኛለን ። አንድ ችግር ሲያጋጥማቸው በደብዳቤ ወይም በስልክ ያሳውቁኛል ። ከዚያ አእምሯቸውን በተፅዕኖ ሥር አውልና ከችግራቸው አላቅቃቸዋለሁ ።''

እስካሁን የነገረኝ ሁሉ ቫል ካለችኝ ጋር ይመሳሰላል ። የምጨብጠውን እያጣሁ ሄድኩ ።



''እንደዚያ ከሆነ ሜሪ ከዶክስ ተፅዕኖ በምን አይነት መንገድ መላቀቅ ትችላለች? እኔ በማዋቅረው ታሪክ ውስጥ ከተፅዕኖው መላቀቂያ የግድ አስፈላጊ ነው ።''

''እንደ እውነቱ ከሆነ ሚስተር ፊሎውስ ያ የሚቻል አይመስለኝም ። በፈጠርከው ሁኔታ ውስጥ ተጣብቀሀል ማለት ነው ። አየህ ይሄ የሚያሳየው በሙያው ያልተካነ ሰው የሰውን አእምሮ በተፅዕኖው ሥር ለማዋል ሲሞክር አደገኛ መሆኑን ነው ። ዶክስ እራሱ ካልለቀቃት ወይም ካልሞተ በታሪክህ ውስጥ የፈጠርካት ሴት ለዘላለሙ በሱ ተፅዕኖ ሥር መኖሯ ነው ።''

''ለምሳሌ እርስዎን የመሰለ ዶክተር ጋ ብትሄድስ? እሱ የዶክስን ሀይል ተቋቁሞ ነፃ ሊያወጣት አይችልም?'' አልኩኝ ተስፋ በቆረጠ አነጋገር ።

በአሉታ ራሱን ነቀነቀ ።

''የሚቻል አይመስለኝም ። ዶክተሩም መሞከር የለበትም ። እኔም ብሆን አልሞክረውም።ታሪክህን ተአማኒ ለማድረግ ዶክስ ከፍተኛ ሀይል እንዳለው ነው የገመትነው ። ስለዚህ ሁለቱ ሰዎች በሲትየዋ አእምሮ ውስጥ የሚያደርጉት ግጭት ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስባት ይችላል ።'' ሲለኝ መሀረቤን አውጥቼ በላብ የተጠመቀውን እጄን ጠረግሁ ።

''እና ዶክሰን እንለዲቃት ማግባባት ብቻ ነው ማለት ነው መፍትሄው ።''

''ወይም ጊዜውን ጠብቆ የሚመጣ የልብ ድካም ። አንድ ትሪል ባይ የሚባል ክላሲክ. . .''

''አውቀዋለሁ እስቬንጋሊ በልብ ድካም ሲሞት ትሪልባይ መዝፈን አቃታት . . .''

''ልክ ነህ ሚስተር ፊሎውስ''

''ግን እኔ በመጽሐፌ ውስጥ እንዲህ አይነቱን መፍትሄ ልጠቀምበት አልፈልግም ።'' ስለው የደከመውን ትከሻውን ነቅንቅ አደረገና ሰዐቱን ተመለከተ ።

''እንዲለቃት ማግባባት ካልተቻለ መሞት አለበት ማለት ነው ። አደጋ ሊያጋጥመው ይችላል ። ከዶክስ ለመላቀቅ አንድ ነገር መፍጠር

እንደምትችል እርግጠኛ ነኝ ሚስተር ፊሎውስ ። ለዚህ የኔ እርዳታ የሚያስፈልግህ አይመስለኝም ” ብሎ ፈገግ አለ ።

“የምትጽፈው አስጨናቂ ታሪክ ከሆነ ሴትየዋ ገድላው ልትገላገል ትችላለች ። አትችልም? እንዴ?”



## ሰባት

“እሺ ዶክተር ራጋኘ ሀምሳ ዶላር ከፍየዎት ተጨባብጠን በመገረም ከሚመለከቱኝ ልጆችዎ አይን ርቂ የሄድኩ ቢሆንም ውይይታችንን እንደቀጠልን አድርገን እንቁጠረው ። መኪናዬን ያቆምኩት ፀጥ ባለው የባህር ዳርቻ ነው ። ከዘንባባ ዛፎች በስተቀር የሚያዳምጠን የለም ።

“በመጀመሪያ ውድ ጊዜዎትን ለኔ በመሰዋትዎ ላመሰግንዎ ይገባኛል ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ያንተን ታሪክ ከማዳመጥ የተሻለ ሥራ እሠራበት ነበር የሚል ስሜት እንደማያድርብዎ እርግጠኛ ነኝ ። ታካሚዎችዎን ሀያ አምስት ሳንቲም ብቻ እንደማያስከፍሉ ነግረውኛል ። መልካም ። የኔ ሀምሳ ዶ/ር ብዙ ታካሚዎችን ይወክላል ። ለከፈልኩት ገንዘብ ተገቢውን አገልግሎት የሰጡኝ መሆኑን ላረጋግጥልው እወዳለሁ ።

“እርግጠኛ ሆኜ ልቀበለው ያልቻልኩትን ነገር አረጋግጠውልኛል ። አንድ መፍትሄ ብቻ እንዳለ እርስዎም ቫልም ተናግራችኋል ።

እሷ “በህይወት እስካለሁ ድረስ ፤ በህይወት እስካለ ድረስ ባሪያው ሆኜ ነው እምኖረው” ነው ያለችው ።

“እርስዎ ደግሞ ዶክተር ያንኑ ነገር በሌላ ቃል ሲናገሩ ።

“ዶክስ እራሱ ካልኩቀታት ወይም ካልሞተ በታሪክህ ውስጥ የፈጠርካት ሴት ለዘለዓለም በተፅዕኖው ሥር መኖሯ ነው” ነው ያሉኝ ።

“እና እኔ አሁን ያመንኩት ቫል ነፃ ልትወጣ የምትችለው ቪዳል ሲሞት ብቻ መሆኑን ነው ። እንደዚህ ቀላልና የተወሳሰበ ጉዳይ ነው ። የተወሳሰበ የሚያደርገው የቪዳል ሁኔታ ነው ። ሲያዩት ለብዙ አመታት የሚኖር ሰው ነው እሚመስል ። የማያጨስ ፡ የማይጠጣ ፡ ጉልበቱ ገና ያልተነካ ጎልማሳ ነው ። እራሱን በደንብ ነው እሚጠብቀው ።”

“ሆኖም ቫል ከተፅዕኖው ሥር ነፃ እንድትወጣ ከሱ መሞት ሌላ መፍትሄ የለም ።”

ዶክተር እርስዎም "የምትጽፈው አስጨናቂ ታሪክ ከሆነ ገድላውል ትገላገል ትችላለች ። አትችልም እንዴ?" ብለውኛል ።

ሞቃቱ ነፋስ በመኪናዋ መስኮት ቢገባም ሰውነቴን አላሞቀውም ።

"ጠቃሚ ሀሣብ ነው የለገሱኝ ዶክተር ። ግን ትክክል አይደለም። ጠቃሚ ነው ያልኩት እኔ ግድያን እንደመፍትሄ አስቤው ስለማላውቅ ነው ። ከተፅዕኖው ለመላቀቅ ቫል ቪዳልን መግደል አለባት ያሉት ልክ አለመሆኑን ላሳይዎት እችላለሁ ። ቫል ለኔ ከህይወት ሁሉ በላይ መሆኗን ልነግርዎት የሚገባ ይመስለኛል ።

ይሄ የተጋነነ ይመስላል ። አይደል? ግን እውነት ነው ። የዛሬ ስድስት አመት ካየኋት ጀምሮ የቫል ፍቅር ከልቤ ወጥቶ አያውቅም ። መግደል ማለት አደጋ ላይ መውደቅ ማለት ነው ። ላቆመው እምችል እስከሆነ ድረስ ቫል ላደጋ ስትጋለጥ ዝም ብዬ አላይም ። ያም ሆኖ የሰጡኝ ሀሳብ ጠቃሚ ነው ። ሀላፊነቱን እኔ ልወስድ እችላለሁ ። አንተስ ቪዳልን መግደል የምትችል ይመስልሀል? ብለው ይጠይቁኝ ይሆናል ለዚህ ጥያቄ መልስ ከመስጠቴ በፊት እስኪ ስለቪዳል ጥቂት እንነጋገር ። እኔ በሰይጣን አላምንም ። ግን ቫል እንደምትለው ሰይጣን ካለ ቪዳል ሰይጣን ሊሆን ይችላል ። አንድን ሴት በተፅዕኖው ሥር አውሎ የሚገናኝ ፣ በራሷ እንዳትተማመን አድርጎ ዋጋ ቢስ የሚያደርግ ሰው ሰይጣን መሆን አለበት ። እንዲህ አይነቶቹን ሰዎች መቅጣት የፓሊስና የፍርድ ቤቶች ፋንታ ነው ይሉኝ ይሆናል ። ግን ስንነጋገር ይህንን ሀሳብ አላቀረቡልኝም ። ይህንን ጉዳይ ለፓሊስ ባቀርብ በቪዳል ሀብት ቀንቼና ተመቅኝቼ የፈጠርኩት እብደት ነው ብለው እንደሚቆጥሩት ሁለታችንም እናውቃለን ።

"የመጀመሪያውን ጥያቄዬን አልመለስክልኝም ይሉኝ ይሆናል ። ቪዳልን መግደል የምችል መስሎ ሊሰማኝ ይችላል ። እውነቱን ለመናገር እዘንባባዎቹ ዛፎች ስር እመኪናዬ ውስጥ ቁጭ ብዬ በኤሌክትሪክ መብራት ደምቃ የምትታየውን የፓራዳይዝ ከተማ ስመለከት ቪዳልን መግደሉ አላስፈራኝም ። ሀሳቡ ሀሳብ ብቻ ሆኖ እስከ ቀረ ድረስ አያስፈራኝም ። እንዲያውም አሁን ያለው ትክክለኛ መፍትሄ እሱን መግደሉ ብቻ መሆኑን አምኜ በታለሁ ። እሱን በመግደል እኔና ቫል የዛሬ ስድስት አመት ጀምረነው በእሱ ምክንያት የተቋረጠውን ፍቅራችንን እንቀጥለዋለን። ተጋብተን ለዘላለሙ በደስታ እንኖራለን ። ሮዳም እንኳ የምትስማማበት ይመስለኛል ። ሮዳ ልትፈታኝ ከተስማማችና



ቪዳል ከሞተ ለስድስት አመታት የኖርኩበት የህልም ዓለም ዕውን ይሆናል ማለት ነው ።

"ግን ቪዳልን በመግደልህ ዘላለም ስትፀፀት ትኖራለህ ነው እሚሉኝ ። ልክ ሊሆኑ ይችላሉ ። ምናልባት ያደረግሁት ትክክል መሆኑን እራሴን ላሳምነው እችል ይሆናል ። እርስዎ ግን አሁንም ያንኑ ጥያቄ እያነሱብኝ ነው ። በርግጥ ቪዳልን መግደል ትችላለህ? እንደዚህ መጠየቅዎ ተገቢ ነበር ። ህይወት በማጥፋት ምንም የማይጨነቁ ሰዎች አሉ። አባቴ እንደዚያ ነበርወደ ገጠር እየመጣ ሲያርስ አንድም ቀን እትከሻው ላይ የሞተ እንስሳ ጣል ሳያደርግ ተመልሶ አያውቅም ። ሚዳቋ ፣ ጥንቸል ፣ ተኩላ ፣ ጅግራ ፤ ቆቅና ዳክየ ሳይቀረው እያደነ ያመጣ ነበር ። ተኩሶ አይስትም ። እኔንም ተኩስ ሊያስተምረኝ ደጋግሞ ሞክሯል ። ግን አልተሳካለትም ። እኔ እንኳን ጥንቸል ዝንብ መግደል እፈራለሁ ። እራሴ ልገል ቀርቶ የሞተ ነገር ሳይ ሆዴ ይገላበጣል ። በዚህ ከአባቴ ጋር ደጋግመን እንጣላ ነበር ። ወደ ጥያቄዎ ልመለስና ቪዳልን መግደል የምትችል ይመስልሀል? ላሉኝ መልሴ እኔ እንጃ ነው ። በሀሳቤ ልገለው እችላለሁ ። እኔና ቫል ሳንጠረጠር እንዴት ልንገድለው እንደምንችል እቅድ ላወጣ እችላለሁ ። ገድየው ነፃ እማወጣት ከሆነ አይፀጽተኝም ልል እችላለሁ ። ግን ያሰብኩትን ሁሉ በተግባር እምፈጽምበት ወቅት ሲመጣ እማደርገው ለመሆኔ እርግጠኛ አይደለሁም ። እኔ እንጃ አድፍጬ ልገለው የምችል አይመስለኝም ። ብቻ እንደሁኔታው ነው እሚወሰነው ።

እንዳደርገው የሚያስገድደኝ ነገር ከመጣ አደርገው ይሆናል ።

በንፋሱ ተገፍቶ በመኪናዬ መስኮት የገባው ዝናብ እጄ ላይ ሲያርፍ በሀሳብ አንቀላፍቶ የነበረውን እእምሮዬን ቀሰቀሰው ። ነፋሱ በዘንባባዎቹ ላይ እያፋጨ ያልፏል ። ባህሩም መናወጥ ጀምሯል ። ጥቁር ዳመና ጨረቃዋን ጋረዳት ። ብልጭታው ሰማዩን ሰንጠቀና ነጐድጓዱ አስገመገመ ። ከዚያ አካባቢውን ሁሉ እፍኖ የሚያስጨንቅ ሀይለኛ ዝናብ ዘነበ ።

የመኪናዋን መስኮት በፍጥነት ዘግቼ የመስታወት መጥረጊያውን አስነሳሁ ። ሞተሩን ቀሰቀስኩና የአየር መቆጣጠሪያውን አንቀሳቀስኩ ። ለተወሰነ ጊዜ ማለቂያ ከሌለው ሀሳቤ ተላቀቅሁ ። ጊዜ አለኝ ። ቪዳል ከስድስት ቀናት በፊት አይመለስም ።

ወደ ቤቴ አመራሁ ።

* * *

ለሚቀጥሉት ሁለት ቀናት ያለማቋረጥ ዘነበ ።

ሮዳ እቤት በምትውልበት ጊዜ ወይ መጽሔት ታነባለች ወይም ትልቅ መነፅሯን አድርጋ እሰገነቱ ላይ ጋደም ብላ ታንቀላፋለች ። የአየር መቆጣጠሪያ አገልግሎቱ ከዌስት እንዲስ የተነሳ አውሎ ነፋስ ወደዚህ እየገሰገሰ እንደሆነ መግለፁን አወራችልኝ ። ለሰሞኑ መጥፎ የአየር ሁኔታም ምክንያት እሱ ነው ። እርግጥ አውሎ ነፋሱ በኛ አቅጣጫ እየመጣ መሆኑን ለማረጋገጥ ጊዜ ይወስዳል ።

አእምሮዬ በሌሎች ጉዳያት ስለ ተወጠረ ስለ አውሎ ነፋሱ ለማሰብ አልቻልኩም ።

በነዚያ ሁለት ቀናት ውስጥ ስለ ቫል የሰማሁት ነገር የለም ። ዳየርን መጠየቅ አስፈራኝ ። ሚስስ ክሌመንስን ፈልጐ ስለባል መጠየቁ ደግሞ የባሰ አስፈራኝ ። በቀን ሁለት ጊዜ የሚመላለሰውን ዶክተር ፎንቴንን እንኳ ተነስቼ በመስኮቱ በኩል መመልከቱን ጠላሁ ። በቀን ሁለቴ መመላለሱ ቫል በጠና መታመሟን ነው እሚያረጋግጠው ። ስለሁኔታው ለመጠየቅ ድፍረት ማጣቴ አስጨነቀኝ ። ካንድም ሁለት ሶስቴ አይኔን ጨፍኜ ገብቼ ላያት ቃጥቶኝ ነበር ግን እጉል ድፍረት መሆኑ ስለተሰማኝ ጥርሴን ነክሼ ተውኩት ።

ማታ እጐኔ የተኛችው ሮዳ እንቅልፍ ሲወስዳት ስለቫል አሰብኩ። ውሽንፍሩ መስኮቱን ሲያንገጫግጨው እያዳመጥኩ ክራሴ ጋር ስሟገት የግድያውን መፍትሔነት ለመቀበል እየተቃረብኩ መጣሁ ።

"ምናልባት እሱን ለመግደል ወኔው ላይኖርህ ይችላል" አልኩት ለራሴ ፣ ግን ወኔውንስ ብታገኘው በምን አይነት መንገድ ልትፈጽመው ነው፣ ይህንን ሳትወስን አመቺ ሁኔታ ቢያጋጥምህ ምን አይነት ሞኝነት ነው እሚሆነው?

ቪዳል ችግር እንደሚፈጥርብኝ ነው የሚታየኝ ። ከኔ ሶስት እጅ የበለጠ ጠንካራ ነው ። ከኔ የበለጠ ቀልጣፋና ፈጣን እንደሆነም እርግጠኛ ነኝ ። እሱን ለመግደል ቀላሉና አስተማማኙ መንገድ በጥይት መምታት ነው ። ግን ስለመሣሪያ የማውቀው ነገር የለም ። ያም ሆኖ ሌላ የተሻለ ምርጫ አልነበረኝም ። መተኮስ ባልችልም አጠገቡ ከሆንኩ አልስተውም ስለዚህ የምገለው ከሆነ በጥይት መሆን አለበት ብዬ ወሰንኩ ።

ሽጉጡስ ከየት ይመጣል? መጠንቀቅ አለብኝ ። ድርጊቱን ከፈፀምኩ በኋላ በኔ ሽጉጥ መሞቱ መታወቅ የለበትም ። ለዚህ መፍትሄው



በብድር የያዙትን መሣሪያ ከሚሸጡ ሰዎች ላይ መግዛት ነው ። እንዳነበብኩት ከሆነ ከእንዲህ አይነት ሰዎች ያለምንም ጥያቄ መሣሪያውን መግዛት ይቻላል ። እምዕራብ የባህር ዳርቻ አካባቢ እንዲህ አይነቱን መደብር አላጣም ።

ከመሥሪያ ቤት ወጥቼ ለአንድ ሁለት ሰዐት ብዘዋወር ገዝቼ እንደምመለስ እርግጠኛ ነኝ ።

ስነቃ ፀሐይዋ ጨረሯን በሰፊው ዘርግታለች ። ነፋሱም እያፋጨ በከፍተኛ ፍጥነት ይከንፋል ። ቁርስ ስንበላ ሮዳ ስለአየር ጠባዩ አወራችኝ ።

"አውሎ ነፋሱ በኛ አቅጣጫ የመጣ ይመስለኛል ። ስለዚሁ ጉዳይ ከደንበኛዬ ጋር ስንጫወት ወደዚህ ከመጣ በጣም አስከፊ ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል ነው የነገረኝ ። የዛሬ ሶስት አመት በአውሎ ነፋሱ ምክንያት የደረሰው አደጋ በጣም ከፍተኛ ነበር ። አሥር ሰዎች ህይወታቸውን አጥተዋል ። እስቲ አስበው" አለችኝ ፍርሀት እየተሰማት ።

ቡናዬን ስጨርስ ፣

"ገና እዚህ አልደረሰም ። አይደል?" ብዬ ተነሳሁ "መሄድ አለብኝ"

"እንደ ቀልድ አትየው በርደን" አይኖቿ በስጋት ተከበዋል ። ሮዳ ነገሮችን አጋነና ማውራት ትወዳለች ። እንደ አውሎ ንፋስ የመሳሰሉ አደገኛ ነገሮችንማ ስታገኝ ደስ ነው እሚላት ።

"አውሎ ነፋሱ በሚያስነሳው ማዕበል ከሌላው አካባቢ ተነጥለን ልንቀር እንችላለን ። ምግብ እንኳ የማናገኝበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል ። የምትለውን ሙሉ በሙሉ አላዳመጥኳትም" በኋላ እንገናኝ ወለላዬ እማመሽ ከሆነ እደውላለሁ"

"በዚያ በማይረባ ሥራ ተወጥረህ ስለ እኔ ማሰቡን ትተኸዋል ።" አለች በድንገት ተቆጥታ ። "እኔ ብጨነቅ ላንተ ምንህም አይደል?"

"እኔም የራሴ ችግሮች አሉኝ ሮዳ" ብዬ ቦርሳዬን አንስቼ ትቻት ወጣሁ ።

እቪዳል ግቢ ገብቼ መኪናዬን ሳቆም ዳየር በጃንር መኪናው ደረሰብኝ ።

"እንዴትነህ? ሚስተር በርደን ለሁለት ቀናት ተያይተን አናው

ቅም ። ማቪስ እስካሁን ፓስታዎቹን ለይታ ሳትጨርስ አትቀርም ። ደብዳቤ መጥቶልህ እንደሁ ማየት ትፈልጋለህ?''

"እዎ ስለእውሎ ነፋሱ የሚወራው ምንድነው? ባልቤቷ እየተ ጨነቀች ነው ።''

"ላለፉት ሶስት አመታት ወደኛ መጥቶ አያውቅም ነበር ። አሁን ሊጎበኘን ያሰበ ይመስላል'' ብሎ እየመራ ወደ ቢሮው ወሰደኝ ።

"እርግጥ አንዳንዴ እዚህ ከመድረሱ በፊት ጉልበቱን እዚያው ጨርሶ የሚከስምበት ወቅትም አለ ።''

እወንበሩ ላይ ተቀመጠና እፊቱ ያሉትን ፓስታችች አገላብጦ ሶስቱን ለኔ ሰጠኝ ።

"እነሱ ያንተ ናቸው ። ብዙም እንደማያስቸግሩህ ተስፋ አለኝ'' ብሎ ፈገግ አለ ።

"አዲሷ ፀሐፊህ እንዴት ነች?''

"ማሩም ነች ። እንዲያ ስትለኝ አንድ ነገር አስታወስኩ ። በግዜያዊነት ነው የቀጠርኳት ። ሚስስ ቪዳል እንዴት ነች ?'' ብዬ አይኑን እንዳላይ አንድን ፓስታ ከፈትኩ ። እፌ ደርቆ ልቤ ወደላይ ወደላይ እያለ ነበር ።

"በርደን ፀሐፊህ ጥሩ ከሆነች በቋሚነት እንድትቀጥራት ነው እምመክርህ ። ሚስስ ቪዳል ከእንግዲህ ሥራ ልትሠራ የምትችል አይመስለኝም ።''

ሲለኝ ቀና ብዬ ተመለከትኩት ።

"እስከዚህ ተጎድታለች እንዴ?''

"ምስጢር ነው ። ይህንን ለማንም መንገር የለብህም ። ግራ በሚያጋባ ሁኔታ ላይ ነው ያለችው ። አሁንም ድንዝዝ ብላ የሚሆነውን ሁሉ የምትለይ አትመስልም ። ንሁልል ብላ ጅል መስላለች ።'' ብሎ ብርማውን የሲጋራ መያዥያ አውጥቶ አንድ ሲጋራ ለኩሶ ለኔም ጋበዘኝ ።

"ለማመን ባይፈልግም ዶክተር ፎንቴን ራሱ ግራ ተጋብቷል ። እርግጥ አእምሮዋ በተፅዕኖ ሥር ሊውል እንደሚችል እያወቅም ።



እኔም አልነግረው ። ዛሬ ከሰዐት በኋላ ሌላ ባለሙያ አምጥቶ ሊያስመረምራት ነው ።

"አይተሀታል እንዴ?'' ብዬ በችኮላ ጠየቅሁት ።

"አላየኋትም ። ሚስስ ክሌመንስ አብዛኛውን ጊዜ ከእሷ ጋር ነች ። እሷ እንደነገረችኝ ሚስስ ቪዳል በግማሽ ነው እራሷን እምታውቀው ። አትናገር አትበላ ምናለፋህ በጠቅላላው ፋዞ ሆናለች ። እንደ ሚስስ ክሌመንስ አባባል ምንም ነገር የምትፈልግ አትመስልም ።''

"አበላሸቶኛል!''

"ለምን ጓደኛህ ዶክተር ራፓች እንዲያያት አታደርግም ?''

"ምንም ዋጋ የለው ። ያ ሽማግሌ እኮ አብቅቷል ። ልጆቹ የሚላቸውን ጥቁሮች ከመርዳት አልፎ ሌላ ሰው ሊረዳ የሚችልበት አቅም የለውም ።

"ጓደኛው መስለኸኝ ነበር ።''

"እንዴ ለተቸገሩ ሰዎች እርዳታ ስንሰበስብ ነው ያገኘሁት ። ስላስደነቀኝ ገንዘብ ሰጠሁት ። መጥፎ ሰው አይደለም ።''

"ስለጣት ማገጫሁ ጉዳይ ለዶክተር ፎንቴን ልትነግረው አይገባም?''

"እንደዚያ ባደርግ ራሴን ለአደጋ አጋልጬ መስጠቴ ነው ። በምንም አይነት እንደዚያ አላደርግም ። አንተ ከፈለግህ ንገረው ። በነገራችን ላይ አንተንህ አይደል ይህንን ነገር የቀሰቀስከው?'' ሲለኝ ተሸማቀቅሁ ።

"ምን ለማለት ፈልገህ ነው?''

"አትናደድ'' ብሎ ፈገግ አለ "ጣትህን ስታጮህ ተነስታ እንደ ወደቀችና ጠረጴዛው ማጅራቷን እንደመታት አልነገርከኝም እንዴ?'' ሲለኝ ቀዝቀዝ አልኩ ።

"ግን ከዚያ በኋላ የተሻላት መስሎኝ ነበር''

"የተሻላት ይመስልሀል? ባለሙያው ከመረመራት በኋላ አንድ ነገር እናውቅ ይሆናል ።

"በጠና መታመሟን ቪዳል ሰምቷል እንዴ?''

"እስካሁን አልሰማም ። ግን መስማቱ አይቀርም ። ዶክተር ፎንቴን ዛሬ ይደውልለታል ።"

"ውጤቱን እንድትነግረኝ" አልኩት ወደ በሩ እያመራሁ "ሀላፊነት ስለሚሰማኝ እየተጨነቅሁ ነው"

"እኔ አንተን ብሆን አልጨነቅም ። አንተ ባታደርገው ሌላ ሰው ሊያደርገው ይችል ነበር ። ሰዎች ሁሌም በአንድ አጋጣሚ ጣታቸውን ያጮሀሉ ። አያጮሁም እንዴ?"

ወደ ቢሮዬ ስገባ ኮኒን እየተየበች አገኘኋት ። ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ተቀምጬ አዲስ የደረሱንን ትዕዛዞች ተመለከትኩ ። ዳየር ያወራልኝ ነገር በጣም አሳሰቦኛል ። በዚህ ስሜት ተነሳስቼ የመጣው ቢመጣ ቫልን ሳላያት አልውልም ብዬ ወሰንኩ ።

ለኮኒ ሥራ ሰጠሁና ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ እንደምመለስ ነግሬያት ከቢሮዬ ወጣሁ ። በረጅሙ ኮሪደር ውስጥ ወደ ቫል መኝታ ክፍል የሚወስደውን አቅጣጫ ተመለከትኩ ። ከዚያ በፍጥነት ወደ በሩ ሄጄ ቆም ብዬ አዳመጥኩ ። ምንም አይሰማ ። ቀስ ብዬ አንኳኳሁ ። ምንም መልስ የለ ። ልቤ ታምቡር እየመታ በሩን በዝግታ ከፍቼ ወደ ውስጥ ተመለከትኩ ። ቫል ብቻዋን እትልቁ አልጋ ላይ ተኝታለች።

"ቫል?"

በሩን ገርበብ አድርጌ ወደ አልጋው ሄጄ ስመለከታት ደነገጥኩ ። ክስት ብላ ገርጥታለች ። ባዶ አይኖቿ አንድ ቦታ ተተክለው ሳይ አስፈሩኝ ።

"ቫል"

ስጠራት አልተንቀሳቀሰችም ። አይኖቿም እንደደረቁ ናቸው ።

እክፍሉ ውስጥ የምቆይበት እያንዳንዱ ደቂቃ አደገኛ መሆኑን አውቅአለሁ ። አንድ ሰው ቢመጣ እዚህ ለመሆኔ ምን ምክንያት ልሰጥ ነው ። ጣቴን በማጮኽ እንደዚህ ካደረግኋት ዳየር እንደነገረኝ እንደገና እፊቷ ባጮህባት ላነቃት አልችልም? በማላውቀው ነገር ላይ ደፍሬ ሙከራ ማድረግ ይኖርብኛል?"

"ቫል!"

ምንም መልስ የለ? ክንዷን ነካ አደረግሁት ። ምንም አልተሰማት ። መሞከር አለብኝ ። እያመነታሁ እጄን አነሳሁና ጣቴን ሁለቴ አጮሁክ ።



ወዲያው ተለወጠች ። በሀይል ተርገፈገፈች ። አይኖቿ ነፍስ ዘሩ ። ወደ ላይ ትክ ብላ ተመለከተችኝ ።

"አይዞሽ ፍቅርዬ እኔ ነኝ ። በርደን ነኝ?" እጆቿን አንስታ እየተከላከለች ወደ ኋላዋ አፈገፈገች ።

"ቫል እኔ ነኝ ። በርደን ነኝ"

"በርደን አይደለህም ።" አለች ዝቅ ባለ ድምፅ ።

"ከአጠገቤ ዞር በል ። ማ እንደሆንክ አውቄያለሁ ። አንተ ሰይጣን! ከአጠገቤ ዞር በል!"

በድምጿና በአይኖቿ ውስጥ ያየሁት ፍርሀት ወደ በሩ አሥሮጠኝ ።

"ውጣ!" አለች ጮክ ብላ "ውጣ!"

በድንጋጤ እየተንቀጠቀጥኩ ቀስ ብዬ ዘግቼ ወጣሁ ። ከበሩ አለፍ ስል ለተወሰነ ጊዜ እግርግዳው ላይ ደገፍ ብዬ ቆምኩ ። ተለያየን! ቪዳልን መስዬ ነው የታየኋት ።

እየተንገዳገድኩ በኮሪደሩ ውስጥ አልፌ ደረጃዎቹን ወርጄ ወደ መኪናዬ ሄድኩ ።

እመኪናዬ ውስጥ ከገባሁ በኋላ ራሴን ለማረጋጋት እየሞከርኩ ላንድ አምስት ደቂቃ ያህል ዝም ብዬ ከተቀመጥኩ በኋላ የመኪናዬን ሞተር አስነሳሁ ።

"እገለዋለሁ!'"

ግን በመጀመሪያ መሳሪያ መግዛት አለብኝ!

* * *

መኪናዬን ራቅ ወዳለ ስፍራ አቁሜ አሮጌዎቹ የእንጨት ቤቶች ወደሚገኙበት አቅጣጫ አመራሁ ። ወደ መንደሩ እየገባሁ ስሄድ በቁጣ የሚመለከቱኝ አይኖች እየበዙ ሄዱ ። ለነሱ ግድ አልነበረኝም ። እቃ ይዘው ገንዘብ የሚያበድሩ ሰዎችን መደብር እየፈለግሁ በጠባቡ መንገድ ገሰገስኩ ።

ወደ ደቡብ የባህር ዳርቻ መጠምዘዣ ላይ አንድ መደብር አገኘሁ ። ተጋጣሚ በሮቹን ከፍቼ በሰው ጠረን ወደታፈገው ክፍል ገባሁ ።

ከባንኮኒው ፊት ለፊት የተቆጣጠሩ እቃዎች የያዙ ብዙ ሰዎች ቆመዋል ። ሁለት ጥቁር ሰራተኞች እየተቆጡ ሊያስተናግዳቸው ይሞክራሉ ። የሰዎቹ አይኖች በችግርና በተስፋ መቁረጥ የጨለሙ ናቸው ።

እየተጠራጠርኩ ቆሜ ስመለከት አንድ ጥቁር እጅ ሲወዛወዝ አየሁ ። ባለ እጁ ወደ እኔ ና ነው እሚለኝ ። ከባንኮኒው ርቂ ወደ ሰውየው አመራሁ ።

ጥቁር ኮትና ግራጫ ሸሚዝ የለበሰ ጥቁር ሽማግሌ በፈገግታ ተቀበለኝ ። ግንባሩ ፈጠጥ ያለ ነው ። ከርዳዳ ፀጉሩ ሙሉ በሙሉ ሸብቷል ። ረጃጅም ነጭ ቅንድቦቹ አይኖቹን እጥልተዋቸዋል ።

"አቤት ጌታዬ" አለኝ "ምን ልርዳዎት?" ተጠጋሁት ።

"መሣሪያ ለመግዛት እፈልጋለሁ" አልኩት ። ምን ሊያደርገኝ ይችላል ፖሊስ ይጠራል? እምቢ ይለኛል? ለሁሉም ግድ አልነበረኝም።

"አቤት ጌታዬ" ከሁኔታው ያልተለመደ ነገር እንዳልጠየቅሁት ተረዳሁ ። የአበባ መያገርያ ወይም የጠረጴዛ ሰዐት የጠየቅሁትን ያህል ነው የተሰማው ።

"መሣሪያ? ለአደን የሚሆን ነው? ላስመርጥዎት እችላለሁ ።በቅርቡ የመጣ አንድ 22 ቁጥር ጠመንጃ አለን ። ይፈልጉት ይሆን ጌታዬ"

"ሽጉጥ ነው እምፈልገው ።" ስለመሣሪያ ጥቂት እውቀት ቢኖረኝ አልኩ ፣ ለራሴ "ጠመንጃ አይደለም የምፈልገው" ስለው እፀሀይ ላይ የከረመ አጥንት የመሰለ ጥርሱን እያሳየ ፈገግ አለ ።

"አዎ ብዙ ሰዎች ሽጉጥ መግዛት ይፈልጋሉ ። የአዲሱ ኑሯችን ውጤት ነው ። እራሳችንን መጠበቅ ይኖርብናል ። ጌታዬ በጣም ጥሩ መሣሪያ ላቀርብልዎት እችላለሁ" ብሎ በጥቋቁር አይኖቹ ከላይ እስከታች ተመለከተኝ ።

"ዋጋው ትንሽ ወደድ ይላል ግን ሽጉጡ ተራ ነገር አይደለም ። ፓሊስያ 38 አውቶማቲክ ነው፣ ቆንጆ መሣሪያ ነው ።"

"ምንም የምለው ነገር አልነበረኝም ። የምፈልገው ቪዳልን ሊገድል የሚችል ሽጉጥ ነው ። ይህንን ደግሞ ልነግረው አልችልም ።



"ዋጋው ስንት ይሆናል?"

"አንድ መቶ ሰላሳ ዶላር ነው ። ይስማማዎታል? ጥቁር አይኖቹ ትክ ብለው ተመለከቱኝ" ቆንጆ መሣሪያ ነው"

"አሳየኝ"

ሄዶ የተወሰነ ደቂቃዎች ቆይቶ ሽጉጡን ይዞ መጣ ።

ሽጉጡን ትኩር ብዬ ተመለከትኩት ። አይኖቼ አጭሩን አፈሙዝና ምላጩን ሲመለከቱ፡ አንድ ነገር በሠራ አካሌ ሲሰራጭ ተሰማኝ ።

"በዚህ አካባቢ ነው እሚኖሩት ጌታዬ?" አለኝ ጥቁሩ ሽማግሌ ።

"የሚያሳዝን መንደር ሆኗል ። ከሰላሳ ዓመት በፊት እንዴት ደስ የሚል ሥፍራ እንደነበር አስታውሳለሁ ። አሁን ግን ሁኔታው ሁሉ ተለውጧል ። ሰዎች ስለሚፈሩ ሽጉጥ ፍለጋ ወደ እኔ ይመጣሉ ። እራሳቸውን መጠበቅ አለባቸው ። እና እንዲህ አይነቱ ሽጉጥ ካለ. . ." ብሎ አንስቶ እመዳፉ ላይ ገልበጥ ገልበጥ አደረገው ።

"በሰላም ተኝተው ማደር ይችላሉ ። በር ቢንኳኳ ፣ መስኮት ቢሰበር ፣ አልጋዎ አካባቢ ጥላ ቢያዩ ፣ እንዲህ አይነት ሽጉጥ ካልዎት የሚፈሩት ነገር አይኖርም ።

"ስለመሣሪያ የማውቀው ነገር የለም" አልኩት "እባክህ እንዴት እንደሚተኮስ አሳየኝ ።?

ከአሥር ደቂቃ በኋላ በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ የጐረሰ ሽጉጥ እደረት ኪሴ እድርጌ ወደ ውጪ ወጣሁ ።

እቪዳል መኖሪያ ቤት አራት ከአርባ አምስት ላይ ደረስኩ ። መኪናዬን ሳቆም ዶክተር ፎንቴን ከአንድ አጭር ወፍራም ሰውዬ ጋር ከቤት ወጥተው ደረጃውን ሲወርዱ አየሁ ። ባለሙያው መሆን አለበት ። ያወሩ ነበር ። ፎንቴን ጉንበስ ብሎ በስጋት አጭሩ ሰውየ የሚለውን ያዳምጣል ። ተያይዘው እፎንቴን መኪና ውስጥ ገብተው ሄዱ ።

ከዚያ ዳየር ብቅ አለ ። ሲያየኝ ደረጃውን ወርዶ ወደ እኔ መጣ ።

"የት ነበርክ"

"እውጪ የምጽፈው ጉዳይ ነበረኝ ። ምን ወሬ አለ?"

"ሁለቱም ግራ ተጋብተዋል ። የነርቭ መታወክ ነው ብለዋል የውሽት ዶክተሮች ። ለማንኛውም ፎንቴን ቪዳልን አነጋግሮታል ። ተመልሶ እየመጣ ነው"

ድንገት የወረደው ውሽንፍር የቀላቀለ ዝናብ በችኮላ ወደ ቤት እንድንገባ አስገደደን ። ዝናቡ ሲንገርቀገርቅ ዝም ብለን ቆምን ።

"አበቃልን!" አለ ዳየር የቀረልን አይመስለኝም ። ከግማሽ ሰዐት በፊት ስለ አውሎ ንፋሱ ደንታ አልነበረኝም ።

"የነርቭ መታወክ?" ስለው ትክሻውን ነቀነቀ ።

"ለሁሉም ይሄ መልስ ሊሆን ይችላል ። አይመስልህም?" አለ ዝናብ ያረገዘውን ሰማይ እየተመለከተ ።

"ከ1928 ወዲህ ታይቶ የማይታወቅ አውሎ ነፋስ ነው አሉ ። የሚነፍሰው ። ሠራተኞቼ ምን እያደረጉ እንደሆን ማየት አለብኝ ።"

ቻዎ ብሎኝ በዝናብ ውስጥ እየሮጠ ወደ ቢሮው ሄደ ።

እኔም በዝግታ እርምጃ ደረጃዎቹን ወጥቼ ወደ ቢሮዬ ገባሁ ።

ኮኒ የተጋመሰ ሀምበርገር በአንድ እጅዋ ይዛ በስልክ እየተነጋገረች ነበር ።

"ልክ ነው" አለች "እሺ ቪዛዎቹን አዘጋጃለሁ ።" ብላ ዘጋ ችው ።

"አንድ ፕሮግራም አዘጋጅቼ ጨርሻሪሁ ሚስተር በርደን" አለች በደስታ ፈግጋ ።

"ቪዛዎቹን እንዲያወጣ ፓርተርን ልኬዋለሁ ። ሚስተር ሲ ሜየርና ባለቤታቸው ናቸው የሚጓዙት ።"

ስለምን እንደምታወራ አልገባኝም ። እንዲገባኝም አልፈልግሁ ። ብቻ ገብቶኛል በሚል ራሴን ነቀነቅሁ ።

"ጥሩ ሠርተሻል" አልኳት ። ሌላ ምን አለ?"

"አንድ ፕሮግራም አለ . . ." ስትለኝ በግማሽ ነበር እማዳምጣት።

"ተመልሶ መቼ ይመጣ ይሆን? ማወቅ አለብኝ" የውስጥ መገ ናኛውን ቁልፍ ተጭኜ መልስ ሲሰጠኝ ።



"በርደን ነኝ" አልኩት ለዳየር ሚስተር ቪዳል መቼ ነበር ይመለ ሳል ያልከኝ የአውሮፕላን ትኬት ልያዝለት እንዴ?"

"ተሳፍሮ ወደዚህ እየመጣ ነው ። ነገ ጠዋት አሥራ ሁለት ሰዐት ላይ ይደርሳል ። ለሹፌሩ ንገሬዋሪሁ ። አንተ የምታደርገው ነገር የለም የውስጥ መገናኛውን ጉንበስ ብዬ ስዘጋው ሽጉጡ ከደረት ኪሴ ሸርተት ብሎ እጄን ነካው ።

* * *

"ይቅርታ ሚስተር በርደን የአየር መቆጣጠሪያ አገልግሎት የሚ ያስተላልፈውን መልዕክት ማዳመጥ ፈልጌ ነበር" አለች ኮኒ ። በሀ ሳብ ርቄ ስለነበር በውል አላዳመጥኳትም ።

"ምን ነበር ያልሽኝ?" ስላት ትንሽ ሬድዮ አንስታ አሳየችኝ ። "የአየር መቆጣጠሪያ"

"አ እሱን ነው . . . አዳምጪ ።

በመስኮቱ በኩል ወደውጪ ተመለከትኩ ። ዝናቡ አካባቢውን ሁሉ ጋርዶ በሀይል ይወርዳል ።

ሔርሜስ የተሰኘው አውሎ ነፋስ ከምዕራብ ኢንዲስ ተነስቶ በሰ ዐት ሀያ ማይልስ እየተጓዘ ወደ ፍሎሪዳ በመገስገስ ላይ መሆኑን ትንሿ ሬድዮ ተናገረች ። አቅጣጫውን ካልለወጠ (የሚለውጥ ግን አይመስልም) ። በሁለት ቀናት ውስጥ ምዕራብ ኬይ ይደርሳል በማግ ስቱም ማያሚን ይመታታል ።

"ይህ የአውሎ ነፋስ ማስጠንቀቂያ ነው" አለ ድምፁ "በየሰዐቱ ሁኔታው ስለሚገልጽ እንድታዳምጡ ።"

ኮኒ ሬድዮኗን ዘግታ የወረቀት ከረጢቷን ከቦርሳዋ ውስጥ ስታ ወጣ ።

"ማስጠንቀቂያው ለምን አስፈለገ?" ብዬ ጠየቅኋት ።

"እንዲህ አይነቱ አውሎ ነፋስ ሲመጣ ሁላችንም ዝግጅት ማድ ረግ አለብን ። ሀብታሞቹ በጊዜው ወደ ሌላ ቦታ ይሄዳሉ ። እንደኔና እንዳንተ አይነቱ ደግሞ እዚሁ ቁጭ ብለን እንጠብቃለን ና እንደበደ

ባለን ። የሚያስደንቅ ነገር ነው ። እዚህ ከተማ ውስጥ አውሎ ነፋሱ ሁለት ጊዜ አጋጥሞኛል ። በህይወት ኖሬ ለማውራት መብቃቴ የሚያስገርም ነው'' ብላ ወደ ወረቀት ክረጢቷ ውስጥ ተመለከተች ።

''ሚስተር በርደን ትንሽ ባለ ቸኮሌት ብስኩት ትቀምሳለህ?''

''አሁን አልፈልግም አመሰግናለሁ ።''

የውስጥ መገናኛው ጢዝ የሚል ድምፅ አሰማ ። ቁልፉን ተጫንኩ ።

''እንዴ ወደ ቢሮዬ ብቅ ብትል'' አለ ዳየር ።

''ጃንጥላ ፈልገህ ይዘህ ና ። በሀይል እየዘነበ ነው ።''

''እመጣለሁ ። ዝናቡንም እያየሁት ነው''

ወደዳየር ቢሮ ስሮጥ ዝናቡ አበሰበሰኝ ። የስልክ መነጋገሪያ እጀሮው ላይ ለጥፎ ቁጭ ብሏል ።

''ሀሪ ሰዎቹን ይዘህ ሥራ ። በጣውላ ዙሪያውን ምቱት ። ጀልባዋን አንተ ተጠባበቅ ። እሺ! ምን አልክ? ማን ያውቃል ቪዳልን ታውቀዋለህ እዚሁ እቆያለሁ ይል ይሆናል ይደውልልኝ'' ብሎ ስልኩን ዘጋው ።

ወደ ተቀመጠበት እየተጠጋሁ እጃኬቴ ላይ ያለውን ዝናብ አራገፍኩ ።

ሐርሚስ ሀይለኛ ነው እሉ ዘንድሮ ። ከነገ ጀምሮ ቢሮ ዝግ ነው ። ሠራተኞች በሙሉ ወይ ወደ ደላስ ይሄዳሉ ። ቪዳል እዚያ ሌላ ጽ/ቤት አለው ። ወይም በየቤታቸው ይቆያሉ ። አንተስ በርደን እዚሁ ትቆያለህ ወይስ ትሄዳለህ?'' ሲለኝ አጠረጴዛው ላይ መርከዝ አልኩ ።

''እኔ እንደ እናንተ አይደለሁም ። ምንድነው ይሄን ያህል መሸበር?'' ስለው ሳቀብኝ ።

''እንደኛው ነህ ሚስተር በርደን ። አውሎ ነፋሱ አጋጥሞህ ስለማያውቅ ነው ። ቀላል ነገር እንዳይመስልህ ። እዚህ የቀረነው የሚያስነሳውን ማዕበል በጭንቀት ነው እምናሳልፈው ። የሀብታሞች ስደት ተጀምሯል ። መሄድ የሚችል ሁሉ ይሄዳል ። ፓራዳይዝ ከተማና ማያሚ ባዷቸውን ሆነው ጭር ነው እሚሉት ። ቪዳል እዚሁ እቆያለሁ ካለ ሚስስ ክሌመንስና የወጥ ቤት ሠራተኞችም አይሄዱም ። እኔም አልሄድ። እንዲህ አይነቱን ችግር ከዚህ በፊትም እዚሁ ሆኘ አሳልፌዋለሁ ።



በጣም የሚቀፍ ነው ። በቆርቆሮ የታሸገ ምግብ ነው እምትበላው ። የኤሌክትሪክ መብራት አይኖርም ። በዚያ ላይ የማዕበሉ ድምፅ እረፍት ይነሳሀል ። አንተ ወደ ቤትህ ብትሄድ ይሻላል ። እዚህ ምን ታደርጋለህ ? ሥራ እንደሁ አይኖርም ።

"ሚስስ ቪዳል እንዴት ልትሆን ነው?'' ስለው እኔ እንጃ በሚል አይነት ትከሻውን ነቀነቀ ።

"የሷን ጉዳይ ቪዳል ነው እሚወስነው ። ከዚህ መንቀሳቀስ የለባትም ካለ እኔም እዚሁ እቆያለሁ ማለት ነው ። ነገ ሲመጣ ወደዳላስ ትሂድ እንደሚል ተስፋ አለኝ ። ሚስተር በርደን አውሎ ነፋስ እንደቆመ ሠራተኞቹን በሙሉ ስለምጠራ የት እንደምትቆይ ማወቅ እፈልጋለሁ ። የቤትህ አድራሻ አለኝ ። አይደል?'' ሲለኝ አላመነታሁም ።

"ከዚህ አልሄድም'' አልኩት ችግር ከመጣ የምረዳው ነገር ይኖራል ። ግን ቪዳል ወደዳላስ ከሄደ እኔም ወደ ቤቴ እሄዳለሁ'' ስለው በመገረም ተመለከተኝ ።

"ደስ እንዳለህ ። የምትሠራው ሥራ የለም ። ግን እዚሁ እቆያለሁ ካልክ ጓደኛ አገኘሁ ማለት ነው ። ነገ ስትመጣ ለመኝታ የሚሆን ነገር ይዘህ ና ። ከነገ በኋላ መንቀሳቀስ የሚቻል አይመስለኝም ።'' የነጐድጓድ ግምግምታ መስኮቶቹን እንገጫገጫቸው ።

"እየተጠናከረ ነው'' ብሎ ስልኩን አነሳና ወደ እኔ እየተመለከተ "ሚስስ ክሌመንስን አነጋግራት ። የማረፊያ ክፍል ታዘጋጅልሀለች'' አለኝ ።

ዶፍ እየወረደ ስለነበረ ከአስተናጋጅዋ ጃንጥላ ተውሼ ነው ወደ ቢሮዬ የተመለስኩት ። ለኮኒም ከነገ ጀምሮ ቢሮ እንደሚዘጋና አውሎ ነፋሱ ሲያቆም እንደምጠራት ነገርኳት ። ከዚያ በውስጥ መገናኛው ሚስስ ክሌመንስን አነጋገርኩ ።

"ሚስተር ዳየር አውሎ ነፋስ እስከሚያልፍ ድረስ እዚሁ አንድ ክፍል ይሰጥሀል ብሎኝ ነበር ። ሊዘጋጅልኝ ይችላል?''

"ይቻላል ። ሚስተር በርደን ። ቢሮ ቁጥር ሁለት ካንተ ቢሮ ቀጥሎ አለው ውስጥ ማረፍ ትችላለህ'' ቫል ካለችበት ሰላሳ ያርድ ብቻ ነው እምርቀው ማለት ነው ።

የምንሠራው ብዙም ሥራ የለ ። ዝናቡ ጋብ ሲል ወደ ዘጠኝ ሰዐት ላይ ኮኒን ወደ ቤቷ ሰደድኳት ።

ስትሄድልኝ እወንበሬ ላይ ደገፍ ብዬ ተቀምጬ ሲጋራ ለኮስኩ ። እና ቪዳል ነገ መመለሱ ነው ማለት ነው ። ቫልም የነርቭ መታወክ ደርሶባታል ነው የተባለው ።

ለቫልና ለቪዳል ቅርብ ሆኜ እዚህ ቤት ውስጥ የተለያዩ ምሽቶችን ላሳልፍ ነው ።

ሽጉጤን ከደረት ኪሴ አውጥቼ ተመለከትኩት ። ጥቁሩ ሽማግሌ እንዴት እንደማጐርሰውና በመጠበቂያው እንዴት እንደምጠቀም አስረድቶኛል ። አሁን አልጐረሰም ። በኪሴ ስድስት ካርታዎችን ይገኛሉ ። ሽጉጡን ወደ መስኮቱ አነጣጥሬ ምላጩን ሳብኩ ። ቀጭ የሚል ድምፅ አሰማ ። አመቺ ሁኔታ ሲያጋጥመኝ እተኩስበት ይሆናል? ሽጉጡን እቦርሳዬ ውስጥ ከትቼ ሌላ ሲጋራ ለኮስኩ ። ያለምንም ችግር ቪዳልን ለመግደል የሚቻልበትን ሁኔታ እማሰላስልበት ወቅት ነው ። እኔም ሆንኩ ቫል መጠርጠር የለብንም ። ፀጥ ባለው ክፍል ውስጥ ይህንን ሳወጣና ሳወርድ ሁለት ሰዐት አሳለፍኩ ። ግን ድርጊቱን ያለምንም ችግር የምፈፅምበት ሁኔታ ሊታየኝ አልቻለም ። ሆኖም አንድ ጥሩ አጋጣሚ ይከሰታል በሚል ራሴን ለማፅናናት ሞከርኩ ። ሽጉጥ አለኝ፣ አጋጣሚው ሲመጣ እጠቀምበታለሁ ። ብዙ አስቤ እዚህ ደረጃ ላይ ነው የደረስኩት ። ደስ የማይል የተሽመደመደ ሙከራ ነበር ።

በመጨረሻም ማስቤን አቁሜ ከቢሮዬ ወጣሁ ። ነፋሱ በዘንባባ ዛፎች መካከል እያፏጨ ያልፋል ፤ በመኪናዬ ወደ ቤት ስሄድ መንገዱ ተጨናንቋል ። መኪናዎቹ ሁሉ ከተማውን ለቀው ለመውጣት የሚጣደፉ ይመስላሉ ። እንደሠርዲን የተጠቀጠቁ አውቶሞቢሎች በብዛት ይታያሉ ። ዳየር እንዳለው ስደቱ ተጀምሯል ።

ሱቆች በብዛት በሚገኙባቸው መንገዶች ላይ ሰዎች በኤሌክትሪክ የሚሠሩ ማስታወቂያዎችንና የመደብር ስሞችን ያወላልቃሉ ። መስኮቶቹን በጣውላ ያሽጋሉ ። የቤት እቃዎች የሚጭኑ ካሚዮኖች መንገድ ስለዘጉብኝ ወደ ጐን ታጥፌ በሌላ አቅጣጫ ወደ ቤት በሚያደርሰኝ መንገድ ከነፍኩ ።

የመኖሪያ ቤቶች በብዛት በሚገኙበት አካባቢዎች ሰዎች እጣራው ላይ ወጥተው የጭስ ማውጫዎችን ይደፍናሉ ። አንዳንዶቹ መስኮቶችን ያሽጋሉ ።

ነፋሱ ሀይለኛ ከመሆኑም የተነሳ መኪናየን ቀጥ ብዬ በአንድ መስመር ልነዳት አልቻልኩም ። አንዳንዴ ሀይለኛው ነፋስ ወደ ጐን ይገፈትራታል ።



የጋራ ወደ ሆነው የመኪና ማቆሚያ ሥፍራ በደህና መድረሴ እድለኛ ነኝ ። በሩን ቆልፌ ስሄድ ከባድ ዝናብ ወረደ ።

በአሳንሰሩ ወጥቼ ወደ አፓርተማ ስገባ ሮዳ እመስኮቱ ጋ ወደ ውጪ ትመለከት ነበር ።

"እውሎ ነፋሱ እየመጣ ነው" እልኳት ቦርሳዬን እጠረጴዛዬ መሳቢያ ውስጥ እያስገባሁ ።

"ከተማይቱን ለመልቀቅ የሚደረገውን ዝግጅት አየሽ?" ስላት ወደ እኔ ዞር አላለችም ። መልስም አልሰጠችኝ ። ዝም ብዬ ተመለከትኳትና ወደ መኝታ ክፍሌ ገባሁ ።

አንድ ትልቅ ሻንጣ አልጋው ላይ አለ ። ከፍቼ ሳይ በሮዳ ልብሶች ሞተልቷል ። እቃዋን እሻንጣ ውስጥ በደንብ መክተት አይሆንላትም ። በተንቀሳቀስን ቁጥር እኔው ነበርኩ የማዘጋጅላት ። ወደ ሳሎን ተመለስኩ ።

"ሻንጣው ምንድነው ወለላዬ?" ብዬ ጠየቅኋት በጥርጣሬ ።

"እውሎ ነፋስ እስኪያበቃ እሆቴሉ ውስጥ ነው እምቆየው" አለችኝ ቀዝቀዝ ባለ ድምፅ ።

"ዳፊን (አሊቃዋ ነች) ስራ እንደሚበዛብን ነግራኛለች ። እየተመላለሱ መሥራት አደገኛ ነው ብላኛለች ። ማወቅ የምትፈልግ ከሆነ እዚያው እየገባሁ ነው ።"

ኮስተር ብላ ስትናገር ጥርጣሬየን አባሰችው ።

"የሆንሽው ነገር አለ እንዴ ወለላዬ?" ስላት ዞር አለች ። ፊቷ ቀልቷል ፤ አይኖቿ ይንቦገቦጋሉ ።"

"አንተ አስመሳይ! የማላይህ ነገር አለኝ!" ብላ ጮኸችና ወደ ጠረጴዛው ሮጣ አንድ መጽሔት ይዛ መጣች ። ገልብጣ እንዲያዘችው የቫልን ፎቶ ግራፍ አየሁ ። ምንም ያልተሰማኝ መስዬ ለመታየት ሞከርኩ ።

"ታዲያ ይሄ ምን ያልተለመደ ነገር አለበት?"

"ልታታልለኝ አትሞክር አንተ ውሻ!" ሮዳ ጮኸች ።

"ለቢል ኦልሰን ሳሳየው ማንነቷን ነግሮኛል ። ያንተ ውቧ ቀልጣፋ ሠራተኛህ ቫል ዳርት አይደለችም? ለስድስት አመታት ስታታ

ስትላት የኖርክው አመንዝራ አይደለችም? አብረሀት ሽርሽር የሄድ ከው ሲሰኛ አይደለችም !!

"አንተና ያንተ ርካሽ አልማዝና የጆሮ ጉትቻ" ብላ አንድ ነገር ወረወረችብኝ ። እፊቴ ላይ አርፎ አመሬት ወደቀ ።

ለቫል ያሠራሁትን የቃል ማሠሪያ ቀለበት አመያገርያው ውስጥ አድርጌ ከጻፈችልኝ ደብዳቤ ጋር ሸሚዜን አማስቀምጥበት መሳቢያ ውስጥ አኑሬው ነበር ።

የወርቅ መያገርያውን አንስቼ እኪሴ ከተትኩት ። ነጐድጓዱ ሲያስገመግም መስኮቶቹ ተንገጫገጩ ።

"ስለሷ እወሩቱን ስነግርህ መታኸኝ አይደል? አንተ አስቀያሚ ዲቃላ አንተ አንተ. . .ብላ" ጥፍሮቿን አሹላ መጣችብኝ ። እጅዋን ይዤ ቀስ ብዬ ገፋ አድርጌ እወንበሩ ላይ አስቀመጥኳት ።

"እሺ ሮዳ ረጋ በይና እንነጋገርበት ። ስም ማንሳቱንና መጮሁን ተይው ። አልኳት ዝግ ብዬ "እንድንፋታ እፈልጋለሁ" ለመነሳት እየታገለች ነበር ግን ያልኳትን ስትሰማ ተዝለፍልፋችና ትክ ብላ ተመለከተችኝ ።

"ምንድነው . . . እምትፈልገው?"

"ፍቺ ፣ ሮዳ የሰለጠን ሰዎች እንሁን ። እንዳልተስማማን ታውቂዋ ለሽ ። መጋባት አልነበረብንም ። አንቺ ገና ወጣት ነሽ ። ከኔ የተሻለ አስደስቶ የሚያኖርሽ ባል ልታገኚ ትችያለሽ" ስላት ቁና ቁና ተነፈ ሰች ።

"እኔን አባረህ ያቺን ልክስክስ ልታገባ አቅደሀል እንዴ?"

"ምንም እቅድ የለኝ ሮዳ ። ነፃ መሆን ነው እምፈልገው ። አን ቺም ነፃ መሆን ያለብሽ ይመስለኛል ።"

"ነፃ እንድሆን ትፈልጋለህ?" ብላ ከንፈሮቿ በአሽሙር ተጣ መሙ ። እንዴት ታስብልኛለህ ። እና እኔን ፈተህ ከዚያች ምናምንቴ ጋር እንደልብህ ለመሆን ፈልገህላ?"

"በመግባባት ልንነጋገርበት አንችልም እንዴ? ሮዳ እንፋታ የም ልሽ እኮ ለሁለታችንም አስቢ ነው ። እርግጥ አሁን ስለተናደድሽ እም ልሽ ሊታይሽ አይችልም ። አውሎ ነፋሱ ሲያቆምና ቀዝቀዝ ስትይ



በደንብ አስቢበት ። ለሁለታችንም የሚጠቅም መሆኑን እንደምትገነ ዘቢው እርግጠኛ ነኝ"

"እንደዚያ ነው! እንዴት ጥሩ ነገር አሰብክልኝ? ልንገርህ አንተ ሌሰኛ ። ምንም ላስብበት አልፈልግም ። አስቤበት አብቅቻለሁ" ብላ ተነስታ ወደ መኝታ ክፍሉ ተንደረደረች ።

ስለቀፈፈኝ ዝም ብዬ ወደ መስኮቱ ሄድኩና ማዕበሉን እመለከት ጀመር ።

ሻንጣዋን አንጠልጥላ ብቅ አለች ። የዝናብ ልብስና ዝናብ የማያ ስገባ የፕላስቲክ ባርኔጣ አድርጋለች ። ሻንጣዋን እጠረጴዛዬ ላይ ስታ ደርገው ገና ወጣትና ቆንጆ ሆና ታየችኝ ።

"አንተ የምታስብበት አንድ ነገር ልሰጥህ ነው ። አውሎ ነፋሱ በሚያቆምበት ጊዜ ሚስትህ እንደሆንኩ ተመልሼ እመጣለሁ ። እስከ ዚያ አንተ ሥራውን የምትለቅ መሆኑን ለቪዳል እንድትነግረው ። ወደ ሚስተር ማሲንግሀምም ሄደህ ወደ ድሮው ሥራህ መመለስ የም ትፈልግ መሆኑን ግለፅለት ። እንደዚያ ካደረግህ ላጠፋኸው ጥፋት ሁሉ ይቅር እልሀለሁ። ከእንግዲህ ወዲህ አመንዝራዋን ሳይሆን እኔን ነው ተደስቼ እንድኖር ማድረግ ያለብህ ። እንፋታ በምትለው ነገር አልስ ማማም ። ለእኔ ትዳሬ ተስማምቶኛል ። ያልኩህን ሁሉ ይዘኸዋል?"

"አዝናለሁ ሮዳ ነፃ መውጣት ነው እምፈልገው ። እናም እወጣ ለሁ ። ከእንግዲህ ካንቺ ጋር መኖር አልፈልግም ። የማትፈችኝ ከሆነ ሁለታችንም በመረጥነው መንገድ እንጓዝ ።" አልኳት ዝግ ብዬ ።

"እንዴት ተሳስተሀል? ለምን እንዲህ እንዳልኩህ ልንገርህ? ያል ኩህን ሁሉ ካልፈጸምክ አሁን የምትሠራውን ሥራና ከባልቴቷ ጋር ያለህን ግንኙነት ካላቋረጥክ ለዚያ የገንዘብ ስልቻ እጽፍና የም ትሠራውን ሁሉ እገልጽለታለሁ ። በፎቶግራፍ አይቼዋለሁ ። ቀላል ሰው አይመስለኝም ። ከሚስቱ ጋር ምን እያደረግህ እንደሆን ሲያ ውቅ ሁለታችሁንም አስሮ ነው እሚገርፋችሁ ። ስለዚህ ተጠንቀቅ በኋላ እየተነፋረቅህ ወደ እኔ ብትመጣ የምጨነቅልህ እእንዳይመስልህ" ብላ ሻንጣዋን አንጠልጥላ ወጣች ። የበሩ ድምጽና የነጐድጓዱ ድምፅ ባንድ ላይ ቤቱን አናጉት ።

# ስ ም ን ት

ከጠዋቱ በአሥራ ሁለት ሰዐት እንዲቀሰቅሰኝ የሞላሁት የጠረ ጴዛ ሰዐት በደወሉ አስበርግጎ አስነሳኝ ። በጊዜ ነው የተኛሁት ። አእምሮዬም ውል በሌላቸው ሀሳቦች ስለተወጠረ እንቅልፍ እንዲወስ ደኝ ኪኒን ውጬ ነበር ።

የዋጥኩት ኪኒን ወደ እንቅልፍ አለም ይዞኝ ጭልጥ ከማለቱ በፊት መጪውን ጊዜ በፍርሀት አሰብኩት ። እሮዳ ለቪዳል ከመጻፍ ወደ ኋላ እንደማትል እርግጠኛ ነኝ ። ቪዳል የኔና የሷን ፍቅረኛነት ቢያውቅ ያለማወላወል እንደሚገለን ቫል እርግጠኛ ሆና ነው የነገረ ችኝ ። ማስጠንቀቂያዋ ዝም ብሎ የተነገረ እንዳልሆነ ይሰማኛል ። ጉዳዩን ለቪዳል ብትገልጽለት እምገደል መሆኑን ለሮዳ መንገሩ ዋጋ የለውም ። እንዳትናገር ፈጥሬና አጋንኜ ያወራሁላት ነው እሚመስ ላት ። በምንም አይነት አታምንም ። መደብደቤን ታምን ይሆናል ። መገደሌን ግን በፍፁም አታምንም ።

"መገደል?"

ቃሉ አዞሮ መለሰኝ ። ቪዳልን ከገደልኩት ችግሮቼ ሁሉ ይወገ ዳሉ ። ቫል ነፃ ትሆናለች ፤ ሮዳም ማስፈራሪያዋን ታጣለች ። አልፈታም ብትለኝ እንኳ እኔና ቫል ወደ ሌላ ቦታ ሄደን እንኖራለን ።

ቫል ወደድሮዋ እሷነቷ ከተመለሰች ሁለታችንም ሥራ እንይ ዛለን ። ወደ ካናዳ ወይም ወደ እንግሊዝ አገር ጠፍተን መሄድ እንች ላለን ። ከተሰጠን ስልጠናና ከልምዳችን አንፃር በጉዞ ወኪል ድርጅ ቶች ውስጥ ጥሩ ሥራ እንደምናገኝ እርግጠኛ ነኝ ። ማን ያውቃል ገንዘብ አጠራቅመን የራሳችንን የጉዞ ወኪል ድርጅት እናቋቁም ይሆናል ።

የእንቅልፉ ኪኒን እየተጫጫነኝ ሲሄድ ሁሉም ነገር ብሩህ ሆኖ ታየኝ ። መጪው ዘመን ከዚህ በፊት እንዳሰብኩት ጨለማ ላይሆን ይችላል ። በከፊል እንቅልፍ ውስጥ ተኝቼ ሳስበው ቪዳልን ያለምንም ችግር ልገለው እንደምችል ታየኝ ።

እየተፍጨረጨርኩ ተነስቼ የሰዐቱን ደወል ዘጋሁት ። የፀሐይዋ ጨረር መስኮቶቹ ላይ ባለው የብርሃን መከላከያ ውስጥ አልፎ ከቤት ገብቷል ። እሊጋው ጠርዝ ላይ ቁጭ ብዬ ፀጉሬን በጣቶቼ ሰቅሰቅ ሰቅሰቅ አደረግሁ ። እራስ ምታቱ ግንባሬን አጨማደደው ። የክፍሉ ፀጥታ አስገረመኝ ። ጆሮዬ መስማቱን ያቆመ ነው የመሰለኝ ። ወዲያው ትዝ አለኝ ። ነፋሱ ፀጥ ብሏል ። ላለፉት አሥራ ሁለት ሰዐታት ያለማቋረጥ ነው የነፈሰው ። የዘንባባ ዛፎቹን እየገጨ ሲያልፍ ድምፀ ጆሮ ያነደቁር ነበር ። ተነስቼ ወደ መስኮቱ ሄጄ የፀሐይ መከላከያውን ከፈትኩት ።

እውጪ ሁሉም ነገር እንደራሰ ነው ። ነፋስ ግን አልነበረም ። የፀሐይዋም ሙቀት በበርትቷል ።

ምናልባት አውሎ ነፋሱ አቅሙን ጨርሶ ይሆናል ።

ሮዳ በጠዋት ተነስታ እየታጠበች የምትዘፍነውን ዘፈን ባለመስማቴና ብቻዬን በመሆኔ አፓርተማው አዲስ ሆነብኝ ። ብቸኝነት አስገራሚ ነገር ነው ። አጠገቤ ስትኖር ታናድደኝ ነበር ። አሁን ሳጣት ግን ቅር ቅር አለኝ ።

የቡናውን ጀበና ጥጄ ልብሴን ለበስኩ ። አንድ ሰዐት ከሩብ ላይ ወደ መኪና ማቆሚያው ወረድኩ ። ጥቁሩ ዘበኛ ሀንክ መኪና እየወለወለ ነበር ። ሀንክ ረጅም ሆኖ በአጥንቱ ላይ ስጋ ያለበት አይመስልም። አፓርተማው ውስጥ የምንኖረውን ሁሉ በስማችን ያውቀናል ።

ገና ሲያየኝ ፈገግ ብሎ "እንደምን አደሩ ሚስተር በርደን" አለኝ ። "ጠዋት ነው የተነሱት ። እህ ገባኝ የሚስስ በርደን መኪናም እዚህ የለች ።"

"አውሎ ነፋሱ እስከሚያቆም እሆቴል ትቆያለች ። እኔም እሚስተር ቪዳል ቤት ነው እምሰነብተው ። ሀንክ ደብዳቤ ከመጣ አንተ ጋ አቆይልኝ ።"

"እቆያለሁ ሚስተር በርደን አውሎ ነፋሱ በጣም አስቸጋሪ ነው እሚሆነው ።"

"ግን አቅሙን የጨረሰ ነው እሚመስለው?" ስለው ፈገግ ብሎ ራሱን ነቀነቀ ።

"አይደለም ጌታዬ ያቺ ትንሽ አውሎ ነፋስ አቅሟን አልጨረሰችም ። ጉልበት እያጠራቀመች ነው ። መሸት ሲል ያዩዋታል ።"



መኪናዬን በባዶው መንገድ ላይ እያሽከረከርኩ ወደ ቪዳል ቤት አመራሁ ። ከተማይቱ የተወረረች ነው እምትመስለው ። የትልልቅ መደብሮቹና የሱቆች መስኮቶች በጣውላ ታሽገዋል ።

የመኪና ዘር አይታይም ። እሆቴሉ አጠገብ ስደርስ ሰዎች ዘንባቦዎቹን ሲመለምሉና እረጃጅም ቅርንጫፎቻቸውን ሲቆርጡ አየሁ ።

የይለፍ ወረቀት ሳሳየው የጥበቃ ጓዱ ግባ በሚል እራሱን ነቀነቀ ። አውሎ ነፋሱ እስከቆመ ድረስ እዚሁ ነው እምቆየው ብዬ ነገርኩት ።

"እካባቢው ተጠራርጎ ካልሄደ እኔም እዚሁ ነኝ" አለኝ ።

"ሚስተር ቪዳል ተመልሷል እንዴ?"

"ከግማሽ ሰዐት በፊት ነው የገባው ።"

መኪናዬን አቁሜ እንደወረድኩ በቤቱ ላይ ለውጥ አየሁ ። መስኮቶቹ በሙሉ በጣውላ ታሽገዋል ። ሁለት ሰዎች የጭስ መውጫዎቹን ይደፍናሉ ። አንዱ ቻይናዊ አትክልተኛ ዕጊረዳ አበባዎችን ይከረከማል ። ሌላው በነፋሱ ሀይል ያጐነበሱ ዘንባባዎችን በእንጨት እያስደገፈ ያቃናል ።

እጨለማው ቢሮዬ ገብቼ መብራቱን አበራሁ ። እጠረጴዛዬ ላይ አንድ ፋኖስና አንድ የክብሪት ሣጥን ፡ አገኘሁ ። የታሸጉትን መስኮቶች ቀና ብዬ ተመለከትኩና መለስ ብዬ የጠረጴዛውን ሰዐት አየሁ ። ሁለት ሰዐት ሆኗል ።

የቪዳል የሂሣብ ሠራተኛ የተጓዙ ሰዎችን ስም ፡ ሥፍራውንና ዋጋውን የሚያሳይ የሂሣብ መግለጫ እንድሰጠው ጠይቆኝ ነበር ። ምንም የምሠራው ነገር ስለሌለና ከእስጨናቂው የሃሳብ ምጥም ለመላቀቅ መረጃዎቹን አውጥቼ እሪፖርቱን ማዘጋጀት ጀመርኩ ።

ሁለት ሰዐት ከአርባ አምስት ገደማ በሩ ተንኳኩቶ ዳየር ገባ ።

"ታዲያስ ጃል" ብሎ ትልቅ ባትሪ እጠረጴዛዬ ላይ አስቀመጠልኝ ።

"አውሎ ነፋሱ ከምሽቱ ወደ ሁለት ሰዐት ገደማ እንደሚደርስ ነው የተገመተው ። ኤሌክትሪክ ስለሚቋረጥ ይህን ባትሪ አጠገብህ አድርገው ። ያለአየር መቆጣጠሪያው ክፍሉ በጣም ነው እሚሞቀው" ብሎ እጠረጴዛዬ ላይ ተቀምጦ ሲጋራ ለኮሰ ።

"ቪዳል ከአንድ ሰዐት በፊት ነው የተመለሰው ። የተቆጣ ነው እሚመስል ። አሁን ከቫል ጋር ነው ያለው ።"

"እዚሁ እንቆያለን እለ እንዴ?" ስለው ዳየር ፈገግ አለ ።

"እንደምን አድርክ እንኳ አላለኝም ። አሁን የምሠራው ከዚህ ቢሮ በታች ባለው ክፍል ውስጥ ነው ። ድንገት የፈለገህ እንደሆን የሱም ቢሮ ከኔ ቢሮ በስተጀርባ ነው ያለው ። ብዙ ፖስታዎች እየመጡ ነው ። ምናልባት አውሎ ነፋሱ እስከሚያቆም የመጨረሻዎቹ ሊሆኑ ይችላሉ ።"

"እምሠራው ነገር ይኖራል?"

"አሁን ምንም የለ ። የውስጥ መገናኛ ቁጥሬ አራት ነው ። በኋላ እንገናኛለን" ብሎኝ ወጣ ።

ፀጥ ብዬ ተቀመጥኩ ። እቫል ክፍል ውስጥ ምን እየተፈፀመ ይሆን? እረግቼ መቀመጥ አልቻልኩም ። ሆዴም እየተሸበረ ነው ። በር ሳዬን ያስቀመጥኩበትን የጠረጴዛ መሳቢያ ከፈትኩ ። ሽጉጡ እውስጡ መኖሩን ባውቅም ልረጋጋ አልቻልኩም ።

መሳቢያውን ዘጋሁና የጀመርኩትን ሥራ ለመጨረስ ሞከርኩ ። ግን አእምሮዬ ወደ ቫል ክፍል እየገሰገሰ አላሠራ አለኝ ።

ልተኛባቸው ያመጣኋቸውን ነገሮች እመኪናዋ ውስጥ የረሳኋ ቸው መሆኑን ታወሰኝ ። ተነስቼ ወደ በሩ አመራሁ ። ከፊት አደረግሁና ቆም ብዬ አዳመጥኩ ። ምንም አይሰማ ። ቀስ ብዬ ወደ ቫል ክፍል ተራ መድኩ ። አሁንም ቆም ብዬ ሳዳምጥ ምንም አይሰማ ።

ቆይቶ የቪዳልን እምቧራቂ ሳቅ ስሰማ አንቀጠቀጠኝ ።

"ብትንሺ ይሻላል" ሲል ተሰማኝ "ተኝተሽ ስትገላበጭ መዋ ልሽ የባሰ ጉዳት ላይ ነው እሚጥልሽ ። ተነስተሽ አንድ ነገር ብት ሠሪ ይሻላል ።"

የበሩ እጀታ ሲንቀሳቀስ ስለአየሁ በፍጥነት ደረጃዎቹን ወረድኩ ። ቪዳል እደረጃው ላይ ሲደርስ እኔ አዳራሹ ውስጥ ገባሁ ።

"በርደን"

ድምፁ ልክ ከግርግዳ ጋር የተጋጨሁ ያህል ቀጥ አደረገኝ ። ዞር ብዬ ተመለከትኩት ። ግራጫ ሙሉ ልብስና ከሀር የተሠራ ነጭ ሸሚዝ

የዞን 4 ሕዝብ ቤተ መጻሕፍት
Zone 4 Public Library



ለብሷል ። ቀይ ክራባትም አሥሯል ። ደረጃዎቹን በፍጥነት ወርዶ ባጠገቤ እያለፈ ።

"ላነጋግርህ እፈልጋለሁ ።" አለኝ ። ግንባሩ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ተጨማዷል ። እረፍት የነሳው ነገር ያለ ይመስላል ። አንዳንዴ ያጨበ ጭባል ።

ከኋላው እየተከተልኩ ስሄድ የትከሻው ስፋትና ጥንካሬ ታየኝ ። አንድ በር ከፈተና ወደ ውስጥ ተምዘገዘገ ። ክፍሉ ሰፊ ሆኖ እመሀሉ ላይ አንድ ትልቅ ጠረጴዛ አለበት ። ምቾቱ በአይን ያስታውቃል ። በውስጡ ያሉት እቃዎች በሙሉ ምርጥ ናቸው ። ወደ ወንበሩ ሄዶና ተቀመጠ ።

"እዚህ በመቆየትህ በጣም ነው ደስ ያለኝ በርደን ። ማንያውቃል? የምትረዳን ነገር ይኖራል ። እኔም እዚሁ መቆየት አለብኝ ። የምጠብ ቀው አስፈላጊ የስልክ ጥሪ አለኝ ። ሚስስ ቪዳልም ከኔ ጋር መቆየቱን መርጣለች ። ለምን መቆየቱን እንደመረጠች እግዜር ይወቀው" አለ ትከሻውን እየነቀነቀ "ከሚስስ ክሌመንስ ጋር ብትሄድ ጥሩ ነበር ፣ ግን ጉዞውን አልፈለገውም ነው እምትለው" ብሎ ወደወንበሩ ተመ ለከተና "ቁጭ በል" አለኝ ።

ስቀመጥ በሩ ተንኳኩቶ አንድ ወንድ የቤት ሠራተኛ ቡና ይዞ መጣና እጠረጴዛው ላይ አደረገ ።

"ቡና ትጠጣለህ?" ብሎ ጠየቀኝ ቪዳል ።

"አልጠጣም አመሰግናለሁ" ቡናውን ከጠጣሁ እጉል ያደፋፍ ረኝ ይሆናል ብዬ ፈራሁ ። "ቅድም ጠጥቻለሁ "

"መልካም" አለና ለሠራተኛው እንዲወጣ ምልክት ሰጠው ። "ሀሪስ ወደ ቤትህ ብትሄድ ይሻላል ፣ ለኔ ጌስቲ ይሰራልኛል ።"

"በጣም ጥሩ ነው ጌታዬ" ብሎ ወጣ ።

"ሁሉም ተደናግጠዋል ። ድንጉጦችን ማየት እንዴት ያስጠላኝ መሰለህ ።" ብሎ ዝም አለና ቀጠለ ።

"ሥራህ በጣም ነው ያረካኝ በርደን ። ሚስስ ቪዳል ተኝታ ብቻ ህን መሥራቱ ቀላል እንዳልሆን ይሰማኛል ። ፀሐፊ አገኘህ እንዴ ?"

"አዎ አሁን ግን አውሎ ነፋሱ እስከሚያልፍ ድረስ እንዳትመጣ ነግሬያታለሁ ።"

"እንደጠበቅሁት ሚስስ ቪዳል ካንተ ጋር የጀመረችውን ሥራ መቀጠል አትፈልግም ። ከባድ ሆኖ ነው ያገኘችው ። ስለዚህ ከተስማማችህ ያገኘህትን ልጅ በቋሚነት እንድትሠራልህ አድርግ ። ስንት ነው እምትከፍላት?"

"ነገርኩት ።"

"ጥሩ ነዋ ። አንድ ሥራ እሰጥሀለሁ ። አሁኑኑ ጀምረው ። አውሎ ነፋሱ ይሆናል ፤ እንደሚሉት ከባድ ከሆነ ስልኩም መቋረጡ ነው ። መስመሮቹ በሙሉ ይበጣጠሳሉ ። ስለዚህ የአየሩ ሁኔታ እንደተሻሻለ የምንቀሳቀስበት አንድ የአየር ታክሲ ትይዝልኛለህ ።

"ለሶስት ሰዎች ከነጓዛቸው የሚሆን ቦታ ነው እምትይዘው ። ወደ ላንሳልቫዶር ነው የሚሄዱት ። ስማቸውን በኋላ እሰጥሀለሁ ። ብቻ አንተ አውሮፕላኑን ያዝ" ብሎ በምፀት ፈገግ አለና "ለዚያ ለማይ ረባ እጅ በእጅ የምከፍል መሆኑን ንገሩው" አለኝ ።

"እሺ ሚስተር ቪዳል ብዬ ተነሳሁ ።"

"እንደ ቆየኝ ። ሥራውን እንደጨረስክ እባክህ አንድ ውለታ ዋልልኝ" ይሄ ያልጠበቅሁበት ነበር ። ትኩር ብዬ ተመለከትኩት ።
"ምን ገዶኝ ሚስተር ቪዳል" አልኩት ።

"ዛሬ ከሰዐት በኋላ ሚስስ ቢዳልን እያጫወትካት እንድትውል እፈልጋለሁ ። ካንተ ጋር ትስማማላችሁ ። የሆነ ነገር እየፈጠርክ አዝናናት ። ዝም ብላ ትጨነቃለች ። እኔ አብሬያት እንዳልሆን ብዙ ሥራ አለብኝ"

የምሰማውን ማመን አቃተኝ ።

"በጣም ነው ደስ የሚለኝ" አልኩት በችኮላ ።

"ጐሽ" ብሎ እፊቱ ያለውን መዝገብ ማገላበጥ ጀመረ ። ውጣ ማለቱ ነው ።

ልቤ በደስታ እየዘለለ ከቢሮ ወጥቼ አዳራሹ ውስጥ ገባሁ ። ሚስስ ክሌመንስ ሀሪስና ወፍራሙ የወጥ ቤት ሀላፊ በደረጃው ቁል ቁል ሲወርዱ ተገናኘን ። ሁሉም ሻንጣ ተሸክመዋል ። ቆም ብዬ አሳለፍኳቸው ። ሚስስ ክሌሜንስ በአገጯ ሰላም አለችኝ ፤ ሀሪስ አንገቱን ደፋ ። የወጥ ቤት ሀላፊው ዘጋኝ ። ከቤቱ ወጥተው ሲሄዱ ወደዳየር ቢሮ ገባሁ ። በሁለት ጣቶቹ እየተየበ ነበር ። ሲያየኝ ፈገግ አለ ።



"ሁሉም ሄደዋል" አለኝ ።

"ወዴት ነው የሚሄዱት?"

"የመጨረሻውን አውሮፕላን ይዘው ወደዳላስ ሊበሩ ነው የተጣደፉት ። ሁሉም ሐርሚስን ፈርተውታል ። ቪዳል እንዲሄዱ ፈቅዶላቸዋል ። አሁን ጌስቲ ብቻ ነው ከኛ ጋር የቀረው ። ምግብ መሥራት እችላለሁ እያለ ይምላል ። እንደሚችል ተስፋ አለኝ ። የራስህን አልጋ ማንጠፍ ይኖርብሀል ፤ መተየብ ትችላለህ?"

"በመጠኑ"

"ትረዳኛለህ" ብሎ ከጠረጴዛው ላይ ሁለት ወረቀቶች አንስቶ ሰጠኝ ።
"እነዚህን በሁለት በሁለት ኮፒ ብትሠራልኝ በጣም ነው እማመሰግንህ"

"እሠራልሀለሁ" ብዬ ወረቀቶቹን ይዤ ወደ ቢሮዬ ተመልሼ እጠረጴዛዬ ላይ አኖርኳቸው ። ጥቂት አመነታሁና ከቢሮዬ ወጥቼ ወደ ቫል ክፍል አመራሁ ። ሶስት እርምጃዎች እንኳ አልተራመድኩም። ባለሁበት ቦታ ድርቅ ብዬ ቀረሁ ።

ጌስቲ እንደ ጣረ ሞት እየተራመደ በደረጃዎቹ ወደ ላይ ይመጣል ። ተያየን ፤ ከነጭ ባርኔጣው ሥር የእባብ አይኖቹ አቁለጨለጩብኝ ። ሳየው ተቁነጠነጥኩ ።

"የምትፈልገው ነገር አለ?" ብሎ ጠየቀኝ ። በፍጥነት ደረጃዎቹን እየወጣ ።

ወደ ኋላዬ አፈገፈግሁ ። እንደ ኮብራ መርዛምና አደገኛ መስሎ ታየኝ ። ፍርሀት አንቆ ያዘኝ ፤ ወደ ቢሮዬ ተመልሼ በፍጥነት በሩን ዘጋሁት ።

ወዳጆች መሆናችንን ቪዳል ቢያውቅ ሊገለን የሚችለው ይሄ ሰው መሆኑን ቫል ነግራኛለች ። በሥራ አካሌ ፍርሀት ለቀቀብኝ ። የፈራሁት መሆኔን በግልጽ ስላሳየሁት በራሴ ተናደድኩ ። አደገኛነቱ በግልጽ ስለሚታይ የማይፈራው ሰው አይኖርም ። ፍርሀቴን በፍፁም ልቆጣጠረው አልቻልኩም ።

በላብ የተጠመቁ እጆቼን በመሀረቤ እየጠረግሁ ተቀመጥኩ ። ኮቴውን አዳመጥኩ ። ምንም አይሰማ ። እደጅ ቆሞ ይሆናል አልኩ

ለራሴ ። ተነስቼ በሩን ለመቆለፍ ቃጥቶኝ ነበር ። ጥርሴን ነክሼ ተው
ኩት ።

ለመረጋጋት ከአስር ደቂቃ በላይ ወሰደብኝ ። ግን ከቢሮዬ ወጥቼ
ለመሄድ ወኔው አልነበረኝም ። ጌስቲ እደጅ ቆሞ ይጠብቀኝ አይጠብ
ቀኝ ስላላወቅሁ የመውጣት ፍላጎቴን ገትቼ ወደ ፍሎሪዳ የአየር
ታክስ አገልግሎት ደወልኩ ።

"ሄሎ በርደን" አለኝ ኤቨርት ። አሁንስ ምን ላድርግልህ? ያ
ያንተ ድንክ ባለፈው ጊዜ ቀጥ ብሎ ከፈለ አይደል ።

አውሎ ነፋሱ እንዳቆመ ሶስት ሰዎች የሚሄዱበት የአየር
ታክሲ ተዘጋጅቶ እንዲጠበቀው ይፈልጋል ።"

"ይቻላል ። ያው እንደበፊቱ ነው ።"

"ያው እንደበፊቱ ።"

"እሺ ። ሁሉም ነገር ተዘጋጅቶ እንደሚጠብቀው ንገረው ።"

"የአየር ጠባይ ተቆጣጣሪዎቹስ ምን ይላሉ?"

"አውሎ ነፋሱ በሶስት ወይም በአራት ቀናት ውስጥ እንደሚ
ያቆም ነው እሚናገሩት ። ግን በጣም ከባድ ይሆናል ነው እሚሉት ።
እስቲ ቆይ ዛሬ ማክሰኞ አይደል ። ቅዳሜ መብረር ይችል ይሆናል ።"

"እሽ እነግረዋለሁ ።"

አሁንም ቫልን ለማየት ፍላጎት አልነበረኝም ። ጌስቲ አንድ ባሊ
ሙሉ ቀዝቃዛ ውሀ የተረጨብኝን ያህል ነው ያቀዘቀዘኝ ። ስለዚህ
ዳየር የሰጠኝን ጽሑፍ መተየብ ጀመርኩ ።

እየተየብኩ ሳለሁ የነፋሱ ሀይል እየጨመረ መሄዱ ተሰማኝ ።
የዘንባባ ዛፎቹ ማፏጨት ጀመሩ ፤ በሩቁ ነጎድጓዱ ሲያስገመግም
ይሰማል ።

በምሣ ሰዐት ብዙም ብርሃን ወደ እሌለበት የምግብ ቤት ወረድኩ ።
እጠረጴዛው ላይ በሣህን የተደረጉ ሣንዲዎቹችና ቢራዎች አገኘሁ ።
ሁለቱን ሳንዲዊቾችና አንድ ጠርሙር ቢራ ይዤ ወደ ቢሮዬ ተመለ
ስኩ ። በልቼ ሳበቃ ዳየር የሰጠኝን ሥራ ተይቤ ጨረስኩ ።

ነፋሱ እያፏጨ በዛፎቹ መካከል ያልፋል ። በጣውላ ከታሸጉት



መስኮቶች ጋርም ይጋጫል ፤ የነጎድጓዱም ድምፅ እየቀረበ መጣ ።
ቆይቶ ዳየር በውስጥ መገናኛው ጠራኝ ።

"ንግግሮቹን ተይበህ ጨረስክ"

"አዎ እመጣልሀለሁ ።"

"ቪዳል ጠይቆኝ ነበር ። እባክህ ውሰድለት?"

ቪዳልን እወንበሩ ላይ ተቀምጦ አገኘሁት ። አንድ ብርጭቆ
ወተትና ሳንድዊቾች እፊቱ አሉ ። ማንበቡን አቁሞ ቀና ብሎ ተመለከ
ተኝ ።

"እንዲጻፍልህ የፈለግሀቸው ንግግሮች ናቸው" ብዬ ወረቀቶችን
እጠረጴዛው ላይ አስቀመጥኩለት ።

"አመሰግናለሁ ።" ደገፍ ብሎ ተቀምጦ አንድ ሣንዲዊች አነሳ ።

"የአየር ታክሲውን ጉዳይ ጨረስክ ?"

"አዎ ። ኤቨርት ቅዳሜ ለመብረር ይችሉ ይሆናል ብሎኛል ።"

"እንዳለው ቢሆን ጥሩ ነበር ። አሁን ሂድና ሚስስ ቪዳልን አጫ
ውታት ። ከ እሷ ጋ ነው የመጣሁት ። ብቻየን ተዋችሁኝ እያለች ታማ
ርራለች ።" ብሎ ተመለከተኝ ።

"እና አዳምጠኝ በርደን ። ብዙ አትዘንላት ፤ የሀሊና መታወክ
ደርሶብኛል ነው እምትለው ። ዝም ብላ ነው የምታወራው ፤ ስልችቷት
ነው ። ሴቶች ሁሌም አንድ ነገር ፈጥረው ሰው ሁሉ በነሱ ላይ እንዲ
ያተኩር ያደርጋሉ ። ስለዚህ የምትልህን ሁሉ አትቀበላት ። ገባህ?"
ሲለኝ አመነታሁ ። ከዚያ ራሴን አበረታታሁና ትክ ብዬ ተመለከ
ትኩት ።

"ግን ሚስተር ቪዳል ይቅርታ አድርግልኝና በምትለው አልስማ
ማም ።" ስለው ሊያነሳው የነበረውን ብዕር ለቀቀና ቀና ብሎ ተመለ
ከተኝ" "ምን አልክ?"

"እራሷን ስታ ስትወድቅ ከሚስስ ቪዳል ጋር ነበርኩ ። ተጐድ
ታለች ። ዶክተር ፎንቴን በቀን ሁለቴ ነበር እየመጣ የሚጐበኛት ።
በተጨማሪም አንድ ባለሙያ አምጥቶ አስመርምሯታል ። እና ይሄ
ሁሉ ሰዎችን ወደሷ ለመሳብ ሆን ብላ ያደረገች ነው ብሎ ሀሊናዬ

ሊቀበልልኝ አይችልም ።'' ስለው በትናንሽ አይኖቹ ትክ ብሎ እየተመለከተኝ ደገፍ ብሎ ተቀመጠ ።

''ግሩም ነው ፣ የአእምሮ መታወክ የደረሰባት ይመስልሀል ሚስተር በርደን?

''እኔ እንጃ ሙቼም ሆን ብለህ በቀልድ ወድቀህ ራስህን አትጎዳም።'' ስለው ከት ብሎ ሳቀ ።

''አባባልህ ስለሴቶች ምን ያህል እንደምታውቅ ነው ያሳየኝ ። ሰው ሁሉ የተዋቸው መስሎ ከተሰማቸው ። አትጠራጠር ወድቀው ራሳቸውን ከመጉዳት ፣ እጃቸውን በስለት ከመቁረጥ ፣ ወይም ከአቅማቸው በላይ የእንቅልፍ ኪኒን ከመዋጥ ወደ ኋላ አይሉም ። ሴቶች የተለዩ ፍጡሮች ናቸው ። ግን እኔ በደንብ ነው እማውቃቸው ስለሚስስ ቪዳል አትጨነቅ ። ሂድና አጫውታት ። ከውስጧ እንድትወጣ የሆነውን ነገር ፈጥረህ አስደስታት'' ብሎ ብዕሩን አንስቶ ስገባ ያነበው እነበረው ወረቀት ላይ ፈረመ ።

''እሺ በርደን አሁን ሂድ ። ብዙ ሥራ አለኝ''

''ሚስተር ቪዳል ልታስብበት የሚገባ ጉዳይ ይመስለኛል'' የሚሰማኝን ልነግረው ቆርጫለሁ ።

''ሚስስ ቪዳል በርግጥ ደህና አትመስለኝም'' ስለው ቀና ብሎ ተቀመጠ ።

''ደህና አይደለችም! ምን ማለትህ ነው?''

''አንድ አንዴ አእምሮዋ በተዕዕኖ ሥር የዋለ መስላ የምትታይበት ጊዜ አለ ።''

ቅንድቡ ብድግ ብድግ አለ ።

''አእምሮዋ በተፅዕኖ ሥር? ምን እያልክ ነው? ማነው እንዲዚያ የሚያደርጋት'' አለና ከት ብሎ ሳቀ ።

''ፋይዳ ቢስ ወሬ ነው'' ሲለኝ ተናደድኩና የምለውን ሳላውቅ ''ለዚህ ተጠያቂው አንተ ትመስለኛለህ ። አእምሮዋን በተፅዕኖ ስር ያዋልከው አንተ ነህ! '' ስለው ትክ ብሎ ተመለከተኝ ትናንሽ አይኖቹ ይንቀለቀላሉ ፣ በእንዲህ እንዳለን ስልኩ አንቃጨለ ። እንድወጣ በእጁ ምልክት ሰጠኝ ።



''በርደን ይህንን ካመንክ ማንኛውንም ነገር ታምናለህ ። አሁን ውጣልኝ!'' ብሎ መነጋገሪያውን አነሳ ፣ በሩን ዘግቼ ስወጣ ''ቪዳል ነኝ። ምን አይነት ሥራ ነው? በጣም ዘግይተሀል? '' ሲል ሰማሁት ።

ደረጃውን እየወጣሁ የሚሰማኝን ነግሬዋለሁ ብዬ አሰብኩ ። የደረስኩበት መሆኑን ያውቃል ። ይሄ በይበልጥ እንዲጠነቀቅ ያደርገው ይሆን? ለቫልስ ችግሯን ቀለል ያደርግላት ይሆን? የዷ ችግር እንዲቃለል ነበር ፍላጎቴ ።

እደረጃው አናት ላይ ስደርስ በኮሪዶሩ ውስጥ በፍጥነት ተራምጄ የቫልን ክፍል በር አንኳኳሁ ።

''ማነው?'' አለችኝ ባልተረጋጋ ድምፅ ።

''በርደን ነኝ'' አልኩኝ ወደ በሩ ጠጋ ብዬ ።

የቁልፍ ድምፅ ሰማሁና በሩ ተከፈተ ። ቫል ከበሩ ላይ ገለል ብላ አስገባችኝ ። ተያየን ። ሰማያዊ ካፖርት ቢጤ ጣል አድርጋለች ። ፀጉሯ እትከሻዋ ላይ ተከፍሷል ። በአይኖቿ ዙሪያ ያለው ቆዳም ተሸብሽቦና ገርጥታ ሳያት ልገልፀው የማልችለው ስሜት ተሰማኝ ።

''ፍቅርዬ አሁን እንዴት ነሽ?'' በእቅፌ ውስጥ ባውላት ምንኛ ደስ ባለኝ ።

''እንዴት ነሽ !?'' አለችና በዝግታ ተራምዳ እወንበሩ ላይ ተቀመጠች ።

''ተወጥሬያለሁ ፣ በርደን ። ምን እንደማደርግ አላውቅም ። ምንም የምፈልገው ነገር የለ ። እራሴን ማጥፋት ብቻ ነው እምፈልገው ።'' ብላ አይኖቿን ስትጨፍን ፊቷ ተጨማደደ ።

''በራሴ ላይ ለመፍረድ እንኳ አልቻልኩም'' በድንገት የጮኸው ንዑድጓድ አስበረገገኝ ። ነፋሱ በከፍተኛ ሀይል ይነፍሳል ።

''ራስሽን ማጥፋት?'' በፍርሀት ቀዘቀዝኩ ። ምን ሆንሽ ቫል? አስቸገረሽ እንዴ?''

''እሱም አለ?'' ብላ በእጇ አይኖቿን ሸፈነች ። ''እሱ እያስጨንቀኝም የሁለታችን ነገር እያበቃለት ነው ። አገሩን ለቆ ለመውጣት እየተዘጋጀ ነው ፤ እኔም አብሬው ነው እምሄደው ። ''

''ወዴት ነው እሚሄደው?''

‘‘ሊማ ውስጥ ለመኖር ወስኗል ።. . .ከዚያ አስይዘው ሊያስመጡት አይችሉም ።’’

ወንበር ሳብኩና እጠገቧ ተቀመጥኩ ።

‘‘አስይዘው ሊያስመጡት? ቫል የኔ ፍቅር በእንቆቅልሽ አትናገሪ። ችግር ገጥሞታል እንዴ?’’ ስላት በራሷ አዎንታዋን ገለፀችልኝ ።

‘‘ከዚህ በፊት የጠየቅሽኝ ልክ ነበር በርደን ። የገነባው ሁሉ እየፈረሰ ነው ። በሚሊዮን የሚቆጠር እዳ አለበት ። የአገር ውስጥ ገቢ ሰዎችም የታክስ እዳውን እየመረመሩ ነው ። እሱን ግን ይሄ ሁሉ ያሳሰበው አይመስልም ። እንደቀልድ ነው እሚመለከተው ። አውሎ ነፋሱ እንዳቆመ እሱ ፣ እኔና ጌሰቲ ወደ ሳንሳልቫዶር እንሄዳለን ። እዚያ ደብቆ ያስቀመጠው ገንዘብ አለው ። ከዚያ ወደ ሊማ እንሄዳለን ። እንደገና መቋቋም እችላለሁ ባይ ነው ። በዚህ አይነት ከወጣ ወደ አሜሪካ እንደገና መመለስ አይችልም ማለት ነው ። እኔም ከሱ ጋር ከሄድኩ ወደዚህ ልመለስ አልችልም ።

‘‘እንደገና መለያየታችን ነው ፤ አሁን ግን ተመልሰን የምንገናኝ አይመስለኝም ።’’

ላምናት አልቻልኩም ። እጅዋን ጨበጥ አድርጌ ያዝኩ ።

‘‘ይዞሽ ሲሄድ ዝም ብዬ አላይም ቫል ። እንደምረዳሽ ቃል ገብቻለሁ ። ስለዚህ የተቻለኝን ሁሉ አደርጋለሁ ። የታክሱን ጉዳይ ለሚከታተሉት ሠራተኞች ለመሸሽ እየተዘጋጀ መሆኑን እነግራቸዋለሁ ። ይህንን ካወቁ ያስይዙታል’’ ስላት እራሷን ነቀነቀች ።

‘‘ያን አሁን ማድረግ አይቻልም ። ጠበቆቹ አሉ ። የእሥራት ትእዛዝ እስከሚያስወጡ ድረስ አገሩን ለቆ ይወጣል ። ያ አያዋጣም በርደን ። እሱን በዚያ መንገድ ማቆም አይቻልም’’ አለችኝ በድንገት ተነስታ እክፍሉ ውስጥ እየተንጐራደደች ።

‘‘ምንም መንገድ የለ. . .’’

ሀይለኛው ነፋስ ከቤቱ ጋር እየተላተመ ሲያልፍ ነጐድጓዱም አስገመገመ ። ዝቡና እጣራው ላይ ሲያርፍ ድምፁ ይሰማል ።

እመሳቢያው ውስጥ ያለው ሽጉጥ ትዝ አለኝ ።

‘‘ቫል ሽጉጥ አለኝ’’ ቆም ብላ በአፈጠጡ አይኖቻ ተመለከተችኝ ።



‘‘ሽጉጥ’’

‘‘ሲሞት ነፃ ትወጪያለሽ’’ ስላት እንገቷን እንቃ ያዘች ።

‘‘ቢሞትም እንኳ ነፃ አልወጣም’’ አይኖቿ ተጉረጠረጡ ።

‘‘እኔን ግደለኝ’’ ብላ ጮኸች ። መፍትሄው ይሄ ብቻ ነው ። ምን ያህል እንደደከመኝ ብታውቅ? ከሱ ጋር በግድ እንዲህ አይነት ኑሮ መኖሩ ሰልችቶኛል! ህይወቴ አስጠልቶኛል ! በራሴ ፈቃድ ሳደርገው የምችል ብሆን ሽጉጡን እንድትሰጠኝ እለምንህ ነበር ።’’ ወደ እኔ መጣችና ክንዴን ያዝ አደረገች

‘‘አንተ ልታደርገው ትችላለህ በርደን ። ጭንቅላቴን በልና ጣለኝ፤ ራሴን የገደልኩ ነው እሚመስላቸው ። አንተን የሚወነጅልህ አይኖርም ፣ ፍቅርዬ ፣ በዚህ መንገድ ነፃ እንደምታወጣኝ አይታይህም? እባክህ እሺ በለኝ ።’’ ስትለኝ በፍርሀት ተመለከትኳት ። ሰውየው እሳብዷታል። ጣቶቿ ክንዴን እጥብቀው ያዙ ‘‘የሽጉጡ ድምፅ በማዕበሉ ስለሚዋጥ ማንም ሊሰማው አይችልም ። ሀኪሞቹም የአእምሮ ቀውስ እንደደረሰብኝ ያውቃሉ ። ፍቅርዬ ምንም ችግር አይደርስብህም ። ማንም አይጠረጥርህ ፤ ሽጉጡን አውጣና አሁኑኑ ግደለኝ ። እባክህ ማንም አይጠረጥርህ ’’

‘‘ቫል እባክሽ ስለ እግዚአብሔር ብለሽ ጠንክር በይ?’’ ማዕበሉ ከፍተኛ ድምፅ ስለሚያሰማ ጮክ ማለት ነበረብኝ ።

‘‘አላደርገውም በቃ! እቁሚ! እባክሽ በርቺ! አንድ መሽሎኪያ ቀዳዳ እናጣም ።’’ ክንዴን ለቃ ወደ ኋላዋ ተራመደች ። አይኗ ውስጥ ያለው ጭንቀት አንጀቴን አላወሰው ።

‘‘የምትወደኝ መስሎኝ ነበር ። ከወደድከኝ ለእንዲህ አይነቱ ሥቃይ እንዴት ትዳርገኛለህ?. . .በቃኝ! ውጣልኝ!’’ ብላ ወደ አልጋው ሮጠችና በደረቷ ተደፋች ።

ሀይለኛ ድምፅ ቤቱን አናጋው ፣ አንድ ዛፍ ተገርስሶ የወደቀበት ነው እሚመስለው ። ቀስ ብዬ ሄድኩና እጆቼን እትከሻዋ ላይ ጣል አደረግሁ ።

‘‘ፍቅርዬ እባክሽ ተይው እረዳሻለሁ ብያለሁ እረዳሻለሁ ። ታገሽኝ እባክሽ’’ ስላት ገልበጥ ብላ ተመለከተቺኝ ። ፊቷ በፍርሀትና በቁጣ ተኮማትሯል ።

"ውጣልኝ! ጠልቼሀለሁ! ተወኝ ሂድልኝ!" ብላ ጮኸች ። ጩኸቷ ማዕበሉን አልፎ የሚሰማ ስለመሰለኝ ትቻት ወጣሁ ።

ቆም ብዬ ሳዳምጥ ስታለቅስ የሰማኋት መሰለኝ ። ተንደርድሬ ወደ ቢሮዬ ገባሁ ።

የማዕበሉ ድምፅ ጭንቅላቴን በጠበጠው ። ጀሮዬን በእጆቼ ደፍኜ ተቀመጥኩ ። እማብድ መስሎኝ ተሰማኝ ።

አንድ ነገር ማድረግ አለብኝ ። አሁን ሌላ ምርጫ የለኝም ። እንዳ ንለያይ ከፈለግሁ ቪዳልን መግደል አለብኝ ።

የሆነ ድምፅ ሰምቼ ነቃሁ ። ሳዳምጥ ከታች እንጨት ቢጤ ሲሰ ነጠቅ ተሰማኝ ። ወዲያው የቢሮዬ በር በሀይል ተበረገደና ሀይለኛ ነፋስ ገብቶ እጠረጴዛዬ ላይ ያሉትን ወረቀቶችና ሁለት ስልኮች ጣላቸው ።

"በርደን" ቪዳል ከታች ጮሆ ተጣራ ። ዘልዬ ወደ ኮሪደሩ ስወጣ ሀይለኛ ነፋስ ተቀበለኝ ፤ ብረቱን ይዤ ከነፋሱ ጋር እየታገልኩ በደረጃው ወረድኩ ። በተከፈተው በር እያፏጨ የሚገባው ነፋስ ሀይል አስደነገጠኝ ። ቪዳልና ዳየር በሩን ለመዝጋት ሲታገሉ ይታያሉ ።

ትላልቅ የዘይት ቅብ ስዕሎችና የጥንት መሣሪያዎች ያሉበት አዳ ራሽ ምስቅልቅሉ ወጥቷል ። አራቱ ትላልቅ ሥዕሎች እመሬት ወርደው ተከስክሰዋል ። ሁለቱ መድፎች ውልቅልቃቸው ወጥቷል ።

እወለሉ ላይ ጌስቲ ፊቱ በደም ተጨማልቆ ወድቋል ። ትልቅ ፍሬም ያለው ስዕል ወድቆበት ተጭኖታል ።

እሱን አልፌ ከውሽንፍሩ ጋር እየታገልኩ በሩን ለመዝጋት እሚፍጨረጨሩት ሰዎች ጋ ደረስኩ ። ለሶስት እንደምንም ብለን ዘጋነው ።

"በእንጨቱ ዝጋው!" ብሎ ጮኸ ቪዳል "በዶማው እጀታ ተጠ ቀም!" ዳየር በሩን ለቆ እንጨቱን ሊያመጣ ሮጠ ። የሱ ድጋፍ ሲቀ ንስ በሩ እንደገና ተከፈተ ። ውሽንፍሩ እኔና ቪዳልን አሽቀንጥሮ ወረ ወረን ። በሩን ለመዝጋት እንደገና ትግል ገጠምን ። ዝናብ የቀላቀለው ነፋስ ፊታችንን እየገረፈ አስቸገረን ። በመጨረሻው ለሶስት እንደምንም ብለን ዘጋነውና በእንጨቱ ቀረቀርነው ። ሁላታችንም ብስብስ ብለናል ።

ጌስቲ እያቃሰተ ለመቀመጥ ሞከረ ። ዳየር አጠገቡ በርከክ አለና



ደገፈው ። እኔ ፈራሁ ት ፤ ከቪዳል ጋር ተጋግዘው አነሱት ! ደሙን እያንጠባጠበ ቀጥ ብሎ ቆመ ።

"ደህና ነኝ" አለ ሰውነቱን እዳየር ላይ ጥሎ

"እሱን ለኔ ተውና እናንተ የተበታተነውን እቃ ሰብስቡ" አለ ቪዳል ። ዳየር ጌስቲን ከኮሪደሩ በስተጀርባ ወደአለው ክፍል ውሰደው ።"

"ፒው!" አለ ዳየር እፊቱ ላይ ያለውን ውሀ እየጠረገ ። ትርፍ ልብስ አምጥተሀል?"

"አዎ"

"መልካም ። ልብሶቻችንን ለውጠን እንሠራለን ። እንዲህ አይነት አውሎ ነፋስ አጋጥሞኝ አያውቅም ። በዚህ አይነት ቢያንስ ቢያንስ አራት ቀን ልናሳልፍ ነው ማለት ነው ።" ደረጃውን ወጣንና ወደ የክፍላችን ገባን ። ልብሴን ለመለወጥ ብዙም ጊዜ አልወሰደብኝ ። ወደ አዳራሹ ወርጄ ስዕሎቹን እግርግዳው ላይ እያስደገፍኩ ሳቆም ዳየር ልብሱን ለውጦ መጣ ።

"ስልኩም ተበጥሷል ።" አለኝ የተበታተነውን የመሣሪያ እቃ ሰብስበን አንድ ክፍል ውስጥ ስናስገባ ።

"መብራቱም አሁን ሊጠፋ ይችላል ። ዳየር ትልቅ ባትሪ እቀ በቶው ውስጥ ሻጥ አድርጓል ። ቪዳል የራሱ ልብሱን እንደለበሰ መጣ ። ደረጃውን ሲወጣ ዳየር ጌስቲ እንዴት ነው?" ብሎ ሲጠይቀው ቆም ሳቁን ለቀቀና ፣

"በርደን እየተዝናናህ ነው እይደል? ከቦስተኑ ሥራህ ለውጥ ያገኘህ ይመስለኛል እ.ሀ.ሀ.ሀ. . ." አለ ። በጥላቻ ፀጥ ብዬ ተመለከ ትኩት ።

ከዚያ ወደ ዳየር ዞር ብሎ ፣

"ተኝቶ እንዲቆይ ነግሬዋለሁ ። አታስነሱት ። መድሐኒት ሰጥቼ ዋለሁ ፤ ነገ ይሻለው ይሆናል ። እራታችንን አንተ አዘጋጅ ። በርደን አንተም እርዳው" ሁለቱን ደረጃ ባንድ እየተራመደ በኮሪደሩ ውስጥ ተወረወረ ፣

ሰዐቱን ተመለከትኩ ። አስር ከሃምሣ ሆኗል ። ከሰዐት በኋላው ላይመለስ የሚፈረጥጥ ይመስላል ።

"የጀመርነውን እንጨርስና ማድቤቱን እናየዋለና" አለኝ ዳየር ።

"የሚጠጣ ነገር ባገኝ ደስ ይለኛል ። አንተስ?" በተወሰኑ ደቂቃዎች የጀመርነውን ሥራ አከናወንንና ወደ ማድቤቱ ገባን ። ዳየር ማቀዝቀዣውን ከፍቶ ተመለከተ ።

"በቂ ምግብ አለን ። ሌላው ቢቀር አንራብም"

የቁም ሣጥኑን ስከፍት መጠጦች አገኘሁ ።

"ዊስኪ ይሻላል?"

"ይመስለኛል"

ውስኪውን በሁለት ብርጭቆዎች ሞልቶ በረዶ ጨመረበትና ተመለከተኝ ። ይሄ ሁሉ ሲሆን ውሽንፍር የቀላቀለው ነፋስ ከቤቱ ጋር እየተላተመ ያልፋል ። ድምፁ አስጨናቂ ነው ።

መጠጡን ስቀምስ ተረጋጋሁ ። አእምሮዬም ወደ ቫል ገሰገሰ ። ዳየር መጠጡን ሲጨርስ ፣

"መብራቱ እያለ በሮቹንና መስኮቶቹን ብንመለከት አይሻልም፣ እንደቅድሙ መሆን አንፈልግም አይደል!" አለኝ ።

ወደ አትክልቱ ሥፍራ የሚያስወጣው በር ተዳክሞ ስላገኘነው ዳየር እንጨትና ምስማር አመጣና አጠናከርነው ። በርና መስኮቶችን ጠግነን ስንጨርስ ሰዐቱ ወደ አስራ ሁለት ተጠጋ ።

"እርቦኛል አለ ዳየር መብላት ትፈልጋለህ?" "አልበላም. . . ብጠጣ ግን አልጠላም ።"

እኔ መጠጡን ስቀዳው ዳየር ለራሱ ሳንዱዊች አዘጋጀ ።

"ሚስስ ቪዳልስ እንዴት ትሆን?" ብሎ ጠየቀኝ ። ዳቦውን እያላመጠ ፣ "የምትፈልገው ነገር ይኖር ይሆናል ።"

"አንተ ብላ እኔ ሄጄ እጠይቃታለሁ" ውስኪውን በመጠጣቱ ቀለል ብሎኛል ። ደረጃውን ወጥቼ እኮሪደሩ ውስጥ ስገባ ቪዳል ከክፍሉ ሲወጣ አየሁና ቆም አልኩ ። ልብሱን ለውጧል ። ዜማ ብጤ እያሰማ በሩን ዘግቶ ቁልፉን እበሩ ላይ ትቶ ዞር ብሎ ተተመለከተኝ ።

"እሺ በርደን"



"ሚ—ሚስስ ቪዳል ምናምን ትፈልግ እንደሁ ለመጠየቅ ነበር" እልኩት ።

"ማስታወስህ መልካም ነው . . . የምትፈልገው ነገር ያለ አይመስለኝም ። ለተወሰነ ጊዜ ለብቻዋ እንተዋታለን ።

"ግን የማይገባ ነገር እየፈጸመች ነው" ብሎ ሳቀ ። "ሴቶች ሲያስቸግሩ ብቻቸውን መተው ጥሩ ሆኖ ነው ያገኘሁት ። ገሸሽ ሲታደርጋቸው አይወዱም" ብሎ ክንዴን እንደብረት በጠነከሩት ጣቶቹ ጨበጥ አደረገው ።

"እማያስቸግርህ ከሆነ ለኔ ምናምን ብታመጣልኝ ። በርደን? ሳንድዊችና ብዙ ቡና አምጣልኝ" ብሎ እየገፋተተ ወደ ደረጃው ወሰደኝ ።

"እቢሮዬ አድርግልኝ እሺ?"

ከብረት ጣቶቹ ክንዶቼን አስለቀቅሁ ። ቆማጣ የያዘኝን ያህል ነው የቀፈፈኝ ።

"ስለሚስስ ቪዳል አታስብ በርደን አሁን ጊዜው ስላለኝ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እኔ አስብለታለሁ ።" ብሎ ፈገግ አለ ።

በጥላቻ ትኩር ብሎ ተመለከተኝ ። ከዚያ ወደ መኝታ ክፍሉ ገባና በሩን በዝግታ እፊቴ ላይ ዘጋው ።

"ሂ በርደን' ዳየር በጭንቅላቱ ጠቅሶ ጠራኝ ።

"ምንድነው?" አልኩት አብሮኝ እንዲሆን አልፈለግሁም ።

"ወደዚህ ና" ሰበብ ስላጣሁ እያመነታሁ ደረጃዎቹን ስወርድ ተመልሶ ወደ ማድቤቱ ገባ ። ተከትዬው ስገባ "ቫል የምትፈልገው ነገር አለ?" ብሎ ጠየቀኝ ።

"ቪዳል ምንም አትፈልግም ነው እሚለው ።" የተሰማኝን መራራ ስሜት ልደብቀው አልቻልኩም ።

"በሩን ቆልፎባታል ።"

"እንደ አሻንጉሊት ነው እሚጫወትባት" አለና ዳየር አያገባኝም በሚል አይነት ትከሻውን ነቀነቀ ።

"ስለሷ አታስብ በርደን ። እኔና አንተ ሌሎች ችግሮች አሉብን ። በሩን ዝጋና ድምፅህን ዝቅ አድርገህ ተናገር ።"

ትክ ብዬ ተመለከትኩት ። እፊቱ ላይ ጥርጣሬና ጭንቀት ይታይ ቢታል ። በሩን ስዘጋ ውስኪውን መቅዳት ጀመረ ።

"ቪዳል የሚቀምሰው ይፈልጋል ።"

"ተዘጋጅቶለታል ። አንተስ ምንም እንደማትፈልግ እርግጠኛ ነህ? ።"

"ምንም አልፈልግ ። የኔና ያንተ ችግር ደግሞ ምንድ ነው?" ስለው እጁን ዝም በል በሚል አነሳ ።

"ወደ ቢሮው እየወረደ ነው ፣ ራቱን ወስጄለት ስመለስ እንነጋገራለን ።"

እትሪው ላይ ያደረገውን ሳንድዊችና ቡና አንስቶ ከማድቤቱ ወጣ ። እስኪመለስ ውስኪየን በጄ ይዤ በተመሰቃቀለ ሀሣብ ተወጥሬ እማድቤቱ ውስጥ ተንጐራደድኩ ።

ሲመለስ በሩን ዘጋና

"ከእንግዲህ ሥራ የለብንም" አለኝ "እንዳትረብሹኝ የሚል ትዕዛዝ ተሰጥቶኛል"

ተጠጋኝና ድምፁን ዝቅ አድርጎ ፣

"ይህን ሥራ ስታጣ ምን ታደርጋለህ?" ብሎ ጠየቀኝ ፣ ዝም ብዬ ተመለከትኩት ።

"ወደድሮው ሥራዬ እመለሳለሁ ። ግን ይኸኛውን እማጣው ይመስልሀል?"

"እንደዚያ ነው የሚመስለው ። እኔም የማጣው ነው እሚመስለኝ። ክፍት ሆኖ የሚጠብቀኝ ሥራ እንኳ የለኝም ።"

"ምንድነው እንደዚህ እንድታስብ ያደረገህ?"

"በመሀከላችን ይቅርና ቪዳል ከፍተኛ ችግር ላይ ነው ያለው ። እሱ እቫል ጋ እንደሄደ ፈልግልኝ ብሎኝ የነበረውን ወረቀት ይዤ ለት እቢሮው ገባሁ ። እጠረጴዛው ላይ ከነገረፈጁ ከጀሰን ሻከርማን የተጻፈ ደብዳቤ አየሁ ። ያገር ውስጥ ገቢ ሰዎች ቀረጥ ባለመከፈል ማታለል በሚል ወንጀል ከሰው ሊያሳስሩት እየሞከሩ ነው ። ጉዳዩ ተስፋ ስየሌለው በቶሎ አገሩን ለቆ እንዲወጣ ነው ሻከርማን የጻፈ



ለት ። እሊማ ውስጥ የሚሸሸግበት ሥፍራ አለው ። እዚያ ሊያገኙት አይችሉም ። ግን እሊማ ውስጥ ማን መኖር ይፈልጋል?

"ወደ ሣንሳልባዶር ለመሄድ የአየር ታክሲ ይዟል" ስለው ዳየር ደንገጥ ብሎ ።

"ሥራዬ ደህና ሰንብት ። ብዙ ገንዘብ የለውም. . ."

"ግን በሚሊዮን የሚቆጠር ብር ነው ያለው" ብዬ አቋረጥኩት ። ዳየር በእሉታ እራሱን ነቀነቀ ።

"በሚሊዮን የሚቆጠር ብር ነበረው ። አሁን ግን የለውም ። ሲያብድ ከአንድ አገር መንግሥት ጋር ብዙ ብር የሚያወጣ ሥራ ጀምሮ ነው የከሠረው ።" ብሎ የማድቤቱን በር በጥርጣሬ ተመለከተ ።

"ይህ ጉዳይ በጣም ሚስጥር ነው ፣ ልነግርህም አይገባኝ ነበር ። ያልተከፈለ ከፍተኛ የባንክ እዳም አለበት ። በርግጥ እችግር ውስጥ ነው ያለው ። ምን እንደማስብ ታውቃለህ? በእንደዚህ አይነት ሲኖር ቆይቶ (አኗኗሩን ያየኸው ነው) ሊማ መቀበሪያው ነው እምትሆነው ።

"ምን ማለትህ ነው?" አሁን በጉጉት እያዳመጥኩት ነው ።

"እራሱን ገደለ ቢሉኝ አያስደንቀኝም ። ቪዳል እንደምታየው ሙሉ በሙሉ ጠንካራ እንዳይመስልህ ። ኑሮ እስከተስተካከለለት ድረስ ብቻ ነው ደህና መስሎ የሚታየው ። ግን አንድ ችግር ሲያጋጥመው ወዲያው ነው ፍርስርስ የሚል ። ልሳሳት እችላለሁ ። ግን እንደዚያ ሆኖ ነው እሚታየኝ ።"

ያለኝን እሰብኩበትና እራሴን ነቀነቅሁ ።

"ራሱን ያጠፋል ብዬ አስቤውም አላውቅ ፣ በጭራሽ . . . ቪዳል አያረገውም" ስለው ዳየር ትከሻውን ነቀነቀ ።

"እኔ የማውቀውን ያህል አታውቀውም ፣ ግን እኔ ሲቀውስ እንኳ ባየው አይገርመኝም" ብሎ ውስኪውን ጨለጠው "የሰማሁትን ልንገርህ ብዬ ነው ። ይህን ሁሉ ያጫወትኩህ ። ከሱ ጋር መሥራቱ ዘለቄታ እንደሌለው ሁሌም ይሰማኝ ነበር ። ስለዚህ ብዙም ባይሆን ከረምቱን የምወጣበት ጥቂት ገንዘብ አጠራቅሜያለሁ ።"

የሚለውን በከፊል ነበር እማዳምጠው ። አንድ ሀሣብ በአእምሮዬ ውስጥ ቅርፅ እየያዘ ነበር ።

"በል እንግዲህ ወደ ቢሮዬ ልውጣ ። የምሠራው ነገር አለኝ" ብሎ ወደ በሩ አመራ ። "ዛሬ ማታ በሰላም የምናድር ይመስለኛል ። የሚያስፈራ ነገር ከሰማህ በሩጫ ድረስ ። ደህና እደር ።"

ከፍተኛ ድምፅ እያሰማ ከቤቱ ጋር የሚጋጨውን ማዕበል እያዳመጥኩ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ቆምኩ ። ከዚያ የውስኪውን ጠርሙስና ብርጭቆየን ይዤ ወደ ቢሮዬ ሄድኩ ። የያዝኩትን እጠረጴዛዬ ላይ ሳስቀምጥ መብራቱ ድርግም አለ ።

"ዳየር ያመጣልኝ ባትሪ እጠረጴዛው ላይ ስለነበር በዳበሳ ፈልጌ አገኘሁትና አበራሁት ። ባትሪውን ይዤ በፍጥነት ወደ ኮሪደሩ ስወጣ ቪዳል ሁለቱን ደረጃ ባንዴ እየተራመደ መጣ ። ባትሪ ይዟል ።

"እሺ በርደን ሚስስ ቪዳልን እኔ እጠብቃታለሁ ። አንተ ራስህን ጠብቅ" አለኝ ።

ወዲያው ዳየር የከፍሉን በር ከፍቶ ብቅ አለ ። ለአውሎ ነፋስ የሚያገለግል ፋኖስ ይዟል ።

"እሱን ለኔ ስጠኝ" አለ ቪዳል ፋኖሱን ከዳየር እየተቀበለ ፣ "እታች ውረድና የኔን ፋኖስ ለኩስልኝ" ብሎ ወደ ቫል ክፍል ሄደና በቁልፍ ከፍቶ በሩን ገርበብ አድርጎ ገባ ። ዳየር "መብራቱ ከዚህ በፊት አለመጥፋቱን የሚያስገርም ነው" ብሎ ባትሪውን እያበራ ወደ ቪዳል ቢሮ ወረደ ።

ቆሜ የቫልን ክፍል በር ተመለከትኩ ። እኔ ሳልሆን ቪዳል እክፍሏ በመግባቱ ተበሳጭቻለሁ ።

"ቫለሪ ምንም የሚያስፈራሽ ነገር የለም ።" ሲል ሰማሁት ። ቪዳልን ። "መብራት አምጥቼልሻለሁ ፣ እዚያ ቁጭ ከምትይ ብትተኚ የሚሻል ይመስለኛል ። እንደቅድሙ ባታስቸግሪኝ ጥሩ ነው ።"

ቫልን ሲቃ ሲተናነቃት ሰማሁ ። ድምጿን ስሰማ በጨቤ የተወጋሁ ያህል ቆሰልኩ ።

"እባክሽ አትነፋረቂ" አለ ቪዳል ትግስቱ እያለቀ ፣ "ምግብ ትፈልጊያለሽ?"

"ውጣልኝ" አለች ዝቅ ባለ ድምፅ ።

"ደስ እንዳለሽ" ብሎ ከክፍሉ ወጣ ። በፍጥነት ወደ ቢሮዬ



ገብቼ ደረጃዎቹን እስኪወርድ ድረስ ተደበቅሁ ። ከዚያ ዳየር ሲመጣ ወደ ኮሪደሩ ወጣሁ ።

"መግባቴ ነው ።" አለኝ ። "ማዕበሉ እንደዚህ እየጮኸ እንዴት እንደምንተኛ እንጃ ፣

"ጌስቲን አየኸው እንዴ?" ብዬ ጠየቅሁት ።

"አላየሁትም ። ረስቼዋለሁ ። አሁን ሄጄ ባየው የሚሻል ይመስለኛል ።"

"እኔ አየዋለሁ ። ክፍሉ የትኛው ነው?"

"እታችኛው ኮሪዶር ውስጥ አራተኛው በር ነው" ቆሜ አዳመጥኩ ። ከሚጮኸው የነፋስና የዝናብ ድምፅ ሌላ ምንም ነገር አይሰማም ። እራሴን አደፋፈርኩና ደረጃዎቹን ወርጄ በቪዳል በር አጠገብ አልፌ ወደ ጌስቲ ክፍል አመራለሁ" እበሩ ላይ ቆም ብዬ አዳመጥኩ ። ጌስቲ ያንኮራፋል ። ኩርፊያው ከሰው ሳይሆን ከአሳማ የሚወጣ ነው እሚመስል ። እኮሪዶሩ ውስጥ ወደ ላይና ወደ ታች ተመለከትኩ ። በሩን ከፊት አደረግሁና ባትሪውን አልጋው ላይ አበራሁ ።

ጌስቲ በጀርባው ተንጋሎ ተኝቷል ። እግንባሩ ላይ ሠፊ ፕላስተር ተለጥፎበታል ። አፉን ከፍቶ ነው የተኛው ። ሲያንኮራፋ ድምፁ ክፍሉን ያርገበግበዋል ።

በሱ በኩል እሚያስፈራኝ ነገር አለመኖሩን ካረጋገጋሁ በኋላ በሩን ዘግቼ ወደ ቢሮዬ ተመለስኩ ። ፋኖሱን ለኮስኩና ተቀመጥኩ ።

ቪዳልን ያለምንም ችግር ለመግደል የምችልበት እቅድ አልመጣልህ ብሎ ቀይቶ አሁን ቁልጭ ብሎ ታየኝ ። ቫልና ዳየር ሳያውቁት መንገዱን አሳዩኝ ። ከእነሱ ባልሰማው ኖሮ አይገለጽልኝም ነበር ። እንዴት ቀላል ነው ።

ቪዳል ወድቋል ፤ መታሠሩ የማይቀር ነው ። በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ከሥሮ በስደት ወደ ሊማ ሊሄድ ነው ። እነዚህ ሁሉ ለፖሊስ ምርመራ በማስረዳጃነት ሊቀርቡ የሚችሉ እውነተኛ ነገሮች ናቸው ።

በተጨማሪም የአውሎ ነፋሱ ድምፅ የሚፈጥርበት ጭንቀት ፣ ለወደፊቱ ያለው ተስፋ መመንመን ፤ ለመታሠር ያለው ፍርሀት ሁሉ እራሱን እንዲያጠፋ ሊያነሳሱ የሚችሉ በቂ ምኽንያቶች ናቸው ። ይህን ጉዳይ ዝግ ብዬ አሰብኩበት ።

ዳየር ጥሩ ምስክር ይሆናል ። ለፖሊሶቹ የቪዳልን የገንዘብ ሁኔታ ሊያስረዳቸው ይችላል ። ቪዳል ካለበት ችግር በቀላሉ የሚገላገልበትን መንገድ ቢመርጥ ዳየርን አያስገርመውም ። እኔን መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ የሚያገኙት አይመስለኝም ። አዲስ ሠራተኛ ስለሆንኩ ስለቪዳል ያውቃል ብሎ የሚገምት አይኖርም ። ጥርጣሬው ወደ እኔ እንዳይመጣ እቅዴ ምንም አይነት ጉድለት እንዳይኖረው ማድረግ አለብኝ ።

ውስኪ ቀድቼ አንድ ሁለቴ ተጐነጨሁ ። ልቤ ይዘላል ፤ ፊቴ በላብ ተጠምቋል ፤ የአየር መቆጣጠሪያው ስለማይሰራ ክፍሉ መወበቅ ጀምሯል ። የማዕበሉ ድምፅ እብድ እሚመታው ከበሮ ውስጥ የተቀመጥኩ ያህል አስጨነቀኝ ።

የምፈራው አንድ ሰው በከባድ እንቅልፍ ውስጥ ነው ያለው ። ጌስቲ በመተኛት ፈንታ እቤቱ ውስጥ ከወዲያ ወዲህ የሚል ቢሆን ኖሮ ወኔውን አግኝቼ እቅዴን ተግባራዊ ለማድረግ አልሞክረውም ነበር ።

ቪዳል እቢሮው ውስጥ ብቻውን ነው ያለው ።

ቫል በሽጉጥ እንድገላት ስትማጸነኝ ።

"በማዕበሉ ውስጥ ድምፁን የሚሰማው አይኖርም ። ፍቅርዬ ምንም ችግር አያጋጥምህ ፤ ማንም አይጠረጥርህ" ነው ያለችኝ ።

ልክ ነው ። ማንም አይጠረጥረኝ ። ድምጼን አጥፍቼ እወርድና እቢሮው ውስጥ እገባለሁ ፤ ክፍሉ በከፊል ጨለማ ነው እሚሆነው ። ሽጉጤን እንዳያየው አድርጌ በእጄ እይዘዋለሁ ። ስለቫል ላነጋግርህ እፈልጋለሁ ። እለዋለሁ ። ተቆጥቶ ውጣ ይለኛል ። እንዲያዳምጠኝ እያግባባሁ እጠጋና ሽጉጡን እደግንበታለሁ ። ከዚያ ጭንቅላቱን ብዬ እጥለዋለሁ ።

ላደርገው እችላለሁ ። ማድረግ አለብኝ ።

ማንም አይጠረጥረኝም ። በዕዳ ከመታሠር ብሎ እራሱ የፈፀመው ነው እሚመስል ።

ምን እጠብቃለሁ?

ዳየር ተኝቷል ። ጌስቲም እንቅልፍ ውስጥ ነው ። ከዚህ የተሻለ አጋጣሚ አይኖርም ። የማዕበሉና የዛፎቹ ድምፅ የሽጉጡን ጩኸት ውጠው ያስቀሩታል ።



ቫል ብቻዋን ተዘግቶባት ስታለቅስ ታየችኝ ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሁሉም ነገር አብቅቶ ነፃ ትወጣለች ። የፖሊስ ምርመራው ሲያበቃ ከስድስት ዓመት ጥበቃ በኋላ እንደገና አብረን እንሆናለን ።

ተነስቼ ወደወንበሩ አመራሁና ቆምኩ ። ሽጉጡስ? ቀስ ብዬ ወደ ጠረጴዛው ተራመድኩ ። መሳቢያውን ከፍቼ ቦርሳውን አወጣሁ ። በድንጋጤ የሠራ አካሌ ቀዘቀዘ ። ቦርሳው ባዶ ነው ። በሚንቀጠቀጡት እጆቼ መሳቢያውን አራግፌ ፈተሽኩ ። ሀይለኛ ነጐድጓድ ቤቱን አናወጠው ።

ሽጉጡ የለም ።

# ዘጠኝ

ሽጉጡ እቦርሳው ውስጥ ነበር። አሁን የለም። ማ ወሰደው? ቪዳል ይሆን ወይስ ጌሰቲ? ግን ሁለቱም ሽጉጥ እንዳለኝ አያውቁም።

ቪዳልን ለመግደል ከወሰንኩ በኋላ ሽጉጡን ሳጣው መሀል እናቴን የተመታሁ ያህል ነው ያስደነገጠኝ። በሚንቀጠቀጡት እጆቼ ፊቴን ሸፍኜ እወንበሩ ላይ እንዘፍ ብዬ ተቀመጥኩ።

የማዕበሉ ድምፅ ያለማቋረጥ ይሰማል፤ የነፋሱ ፉጨት እጭንቅላቴ ውስጥ ያስተጋባል። ታዲያ ሽጉጡን ማነው የወሰደው? ሽጉጥ እንዳለኝ የምታውቀው ቫል ብቻ ነች።

ቫል!

እንድገላት ተማፅናኝ ነበር። እኔና ዳየር የበሮቹንና የመስኮቶቹን ደህንነት ለማየት እንደወጣን ወፈፍ አድርጓት እቢሮየ ገብታ ትስፈትሽ አግኝታ ወስዳው ይሆን? በፍጥነት ተነሳሁ። ጉዴ! እራሷን ገላ ይሆን?

ማዕበሉ እንደዚያ እየጮኸ የሽጉጡን ድምፅ ልሰማው አልችልም። በጭንቀት ተወጥሬ ዘለግ ላለ ጊዜ ቆምኩ። ለዘላለም የማጣት መሆኑ ሲሰማኝ ነው ምን ያህል እንደምወዳትና በህልሜ ብቻ እያገኘኋት ያሳለፍኳቸውን ስድስት ባዶ አመታት ለመርሳት እርሷ እንደምታስፈልገኝ የተገነዘብኩት።

ወደ ኮሪደሩ ወጣሁ። ሞታ ይሆን? ልቤ እየተሸበረ በዝግታ እርምጃ ወደ በሯ ተጠጋሁ። እበሩ ላይ ተለጥፌ ለማዳመጥ ሞከርኩ፤ ግን የማዕበሉ ድምፅ ምንም አያሰማ። እራሴን አደፋፍሬ በሩን ከፈትኩ። አልጋው ላይ ተዘርግታ ለዘላለሙ ተለይታኝ አገኛት ይሆን? ወይስ ጭንቅላቷ ቆስሎ በደም ተነክራ አገኛት ይሆን?

"ማነው?"

የሷ ድምጽ። ነው በህይወት አለች!

በፍጥነት ወደ ውስጥ ገብቼ ፣ በሩን ዘጋሁ ። እፋኖሱ አጠገብ እወንበሩ ላይ እንደ ተቀመጠች ቆም ብዬ ተመለከትኳት ። እጆቿን እጭኗ ላይ ጣል አድርጋለች ። የፋኖሱ ብርሃን እፊቷ ላይ ሲያርፍ ሀውልት አስመስሏታል ።

"እ ቫል!"

እየተንገዳገድኩ ሄጄ እፊቷ ተንበረከክሁ ። ጭንቅላቴን እጭኖቿ መሀከል ቀብሬ እወገቧ ላይ ተጠመጠምኩ ። ፀጉሬን በጣቶቿ አሸት አሸት አደረገች ።

"ንገረኝ!" አለችኝ እየተንቀጠቀጠች "እትፍራ ነፃ ወጥተሻል በለኝ!"

አልተንቀሳቀስኩም ። ምንድነው ያለችው፣ የነጐድጓድ ድምፅ መስኮቱን አናጋው ።

"በርደን የኔ ፍቅር . . .ነፃ ወጥተሻል በለኝ!"

በህይወት ሳገኛት የተሰማኝ ስሜት እንዳደነዘዘኝ ነው ።

"በርደን" ድምጿ ከፍ አለ ። ትከሻየን ጨብጥ አድርጋ ቀና ስታ ደርገኝ አይን ለአይን ተያየን ።

ለምንድነው ፊቷ ከእብነበረድ ተቀርጾ የወጣ የሚመስለኝ፣ ከፍ ዝቅ የሚለው መብራት ይሆን፣

"ሸጉጤን መልሺልኝ!" አልኳት ።

"ሽጉጥ፣ ምን ማለትህ ነው?" ቀስ ብዬ ተነስቼ ቆምኩ ።

"ልታታልይኝ አትሞክሪ ቫል ሽጉጡን መልሺልኝ"

"ሽጉጥ !? በርደን ረጋ በል እስቲ ሽጉጥ አለኝ ብለህ ነው የነገርከኝ ።" ብላ በሰለለ ድምፅ ጮኸች ።

"ጠፍቷል ። በእግዜር ብለሽ ቫል ፣ እንደዚህ አታሠቃይኝ! ወስደሺዋል አይደል?"

"እኔ!" ብላ ጉንበስ አለች ። ፊቷ ሳንባ መሰለ ። አይኖቿ ደም ለበሱ ።



"እኔ አልወሰድኩም! ምንድነው እምትለው፣ አልሞተም እንዴ?"

"አልሞተም ። ልገለው ነበር" ብዬ አይኖቿን ማየት ስላቃተኝ ፊቴን አዞርኩ ።

"በደንብ አቅጄው ነበር ፤ ቀላል ነበር ፤ ራሱን ያጠፋ ነበር እሚ መስለው ፤ ምክንያቶችም ነበሩ ። መርማሪዎቹ ሁሉ በመጀመሪያ መነሻውን ነው እሚጠይቁት ። የመታሠር ወይም ከአገር የመሰደድ ፍርሀት ነበረበት ፣ ገንዘቡን በሙሉ ከስሯል ፤ እኔ ማድረግ የነበረብኝ ዝም ብዬ ገብቼ በሽጉጥ ጭንቅላቱን ማለት ብቻ ነበር" እያልኩ እራ ቅኋት ።

"ግን ሽጉጡ ጠፋ"

ለጥቂት ጊዜ ፀጥ አልን ። ከዚያ በደንብ በማይሰማ ድምፅ ተናገ ረች ።

"ማ ወሰደው?"

"አንቺ ! እራስሽ ነሽ የወሰድሺው!"

"በጭራሽ ስትለኝ ተስፋ በመቁረጥ እጆቼን አወናጨፍኩ ።

"አሁን ምንድ ነው እማደርግ ? መሣሪያ የለኝም ። በባዶ እጄ ልቋቋመው አልችልም ። በጣም ጠንካራ ነው ።" ስላት ዝግ ብላ በረ ጅሙ ተነፈሰች ።

"ምንም ማድረግ አይቻልም ። የሚጠብቀው ሀይል አለ ። ሠይጣ ኖችን የሚጠብቃቸው ሀይል አለ ። እባክህ ሂድ ! እዚህ ያገኙህ እን ደሁ! . . ."

"ልረዳሽ ቃል ገብቻለሁ ። አሁንም ቃል እገባለሁ !"

"እባክህ ሂድልኝ!" ብላ አይኖቿን በእጆቿ ሸፍና ማልቀስ ጀመ ረች ።

"ነፃ አወጣሻለሁ ቫል!" አልኩ እየተንቀጠቀጥኩ ።

"ከዛሬ ወዲህ አጠገብሽ አይደርስም ።"

"እ ! እባክህ ውጣ! ባዶ ቃልህን አትስጠኝ! ምንም መፍትሄ እንደሌለው ነግሬሀለሁ ። በእግዜር ብለህ ውጣልኝ !"

ትቻት ወደ ቢሮዬ ተመለስኩ ። ባትሪውን እጠረጴዛው ላይ አኑሬ መስኮቶቹ የታሸጉባቸው ጣውላዎች ማዕበሉ ሲመታቸው የሚያሰሙትን የመሠነጣጠቅ ድምፅ ቆም ብዬ አዳመጥኩ ።

"ባዶ ቃሎችህ!" እንዲህ ስትለኝ በጣም ነው የቆሰልኩት ። ወንበሬን ስቤ ተቀመጥኩ ። ብልጭ ድርግም የሚለው የፋኖስ መብራት ጣዕረሞት የመሠለ ጥላ ይፈጥራል ።

ቫል ካልወሰደችው ማ ሊወስደው ይችላል? ። ሽጉጡን ለመጨረሻ ጊዜ መቼ እንዳየሁት ለማስታወስ ሞከርኩ ።ዛሬ ጠዋት መሳቢያውን ከፍቼ መኖሩን አረጋግጬ ነበር ። ከዚያ ወዲህ አላየሁትም ። ስለዚህ ቪዳል ፣ ዳየር ወይም ጌስቲ አግኝተው ሊወስዱት ይችላሉ ።

ቪዳልን ከጥርጣሬዬ ውስጥ ወዲየው አስወጣሁት ። ምክንያቱም እሱ ቢያገኘው ኖሮ ለምን እንደያዝኩት ይጠይቀኝ ነበር ። ዳየርም ቢያገኘው አይነካውም ዳየር ለማንሳት እንኳ የሚፈራ ነው እሚመስለኝ ።

ስለዚህ ጌስቲ መሆን አለበት ።

የውስኪውን ጠርሙስ አነሳሁና በዛ አድርጌ ቀድቼ ጨለጥኩት ። አልኮሉ በመጠኑም ቢሆን አረጋጋኝ ። ባትሪዬን አንስቼ ወደ በሩ ተራምጄ በጨለማ የተዋጠውን ኮሪደር ተመለከትኩ ። ከዚያ በደረጃዎቹ በፍጥነት ወረድኩና እጌስቲ ክፍል በር ላይ ደረስኩ ። ቆም ብዬ ሳዳምጥ አሁንም እያንኮራፋ ነው ።

ረዘም ላለ ጊዜ እያመነታሁ ከቆምኩ በኋላ በሩን ከፈትኩና ገርበብ አድርጌ ትቼው ወደ ውስጥ ገባሁ ።

የሲጋራ የላብና የፀጉር ቅባት ሽታ ክፍሉን አውዶታል ። ልቤ የደረቴን አጥንት ይረግጣል ። እፎ ደርቋል ፤ ውስኪው ባያደፋፍረኝ ኖሮ ከፍሉን በሩጫ ለቅቄ እወጣ ነበር ።

ጌስቲ በድንገት በሀይል ሲያንኮራፋ ፀጉሬ ቆመ ። ወዲያው ማንኮራፋቱን አቆመ ።

ነቃ እንዴ ?

ፀጥ ብዬ ቆምኩ ላቤ በግንባሬ ላይ ተንጠባጠበ ። ሲገላበጥ ተሰማኝ ። ትንሽ ቆይቶ ማንኮራፋቱን ቀጠለ ።



ረዘም ላለ ጊዜ ፀጥ ብዬ ቆምኩ ። እንቅልፍ እንደያዘው ሳረጋግጥ ባትሪዬን አበራሁ ። ብርሀኑ ወደ አልጋው እንዳይደርስ ከልዬ ትንሿን ክፍል አዳረስኩ ፣ እጠገቤ ግርግዳውን ተደግፎ የቆመ ኮመዲኖ አለ ። ሽጉጡን እዚህ ውስጥ መሆን አለበት ፣ የሚያስቀምጠው ። በዝግታ አንዱን መሣቢያ ከፈትኩት ፣ በሸሚዞች ተሞልቷል ። ሽጉጤ ግን የለም ። ሌላውን መሳቢያ ለመክፈት ስሞክር ሲጢጥ ብሎ በድንጋጤ አደነዘዘኝ ። ማንኮራፋቱን አቆመ ። ባትሪውን አጠፋሁ ። ከዚያ መሳቢያውን በዝግታ መዝጋት ጀመርኩ ። በጭለማው ውስጥ ጌስቲ"

"ማነህ አንተ" ብሎ ጮኸ ።

መሳቢያውን ዘግቼ ከኮሞዲኖው ራቅ ብዬ ቆምኩ

"እኔ ነኝ አይዞህ" አልኩና ባትሪወን አበራሁ ። ድምጼ በግድ ነው የሚወጣው ጌስቲ አልጋው ላይ ቁጭ ብሏል እባብ አይኑ ብርሃኑ ሲያርፍበት ተንቀለቀለ ። ዘልሎ የሚያንቀኝ መሰለኝ ።

"ምን ትፈልጋለህ !?" ብሎ አፈጠጠብኝ ።

እንዴት እንደሆንክ ለማየት ነው የመጣሁት" ብዬ ወደ በሩ አፈገፈግሁ ። ጥቁሩን ጉርድ ሸሚዙን ለብሷል ። ሰፊው አገጩ ባቆጠቆጠ ጺም ተሸፍኗል ።

"እራሴን በጣም አሞኛል ። መተኛት እፈልጋሪሁ ፣ብዬ ተናግሬ ያለሁ ። የሚሰማኝ ይሄ ነው ፡፡አሁን ሹልክ ብለህ ውጣ ። ተመልሰህ ብትመጣ ልብ አድርግ !" ብሎ ጮኸብኝ ፣

በጨለማ ወደ ተዋጠው ኮሪደር ወጥቼ በሩን ዘጋሁ ። ከድንጋጤዬ የተነሳ የምወድቅ መስሎኝ ነበር ።

በኮሪደሩ ውስጥ ስራመድ ከደረጃው በኩል ብርሃን አየሁ ። ከዚያ ኮቴ ሰማሁ ። አንድ ሰው ደረጃዎቹን እየወረደ ነበር ። ግርግዳውን ተደግፌ ቆም አልኩ ። የባትሪው ብርሃን እደረጃዎቹ ላይ አበራ ።

ዝም ብዬ ስመለከተው በቀጥታ ወደ ቪዳል በር አመራ ። እንኳኩቶ ከፈተና እበሩ ላይ ቆመ ።

"እንዳትረብሹኝ ብየህ አልነበረም" ብሎ ቪዳል ሲጮህ ተሰማኝ ።

“ይቅርታ ጌታዬ ሚስስ ቪዳል. . .” የዳየር ድምፅ ተዋጠ ።

“እሺ ስለሚስስ ቪዳል ምን አድርግ ነው የምትለኝ ።”

“ደህና አትመስለኝም ። እያለቀሰች ስታቃስት ሰምቻታለሁ ። ብታውቀው ይሻላል ብዬ ነው ።”

“በጣም ጥሩ አስበህላታል ዳየር” ድምፁ በቁጣና በምፀት የተመላ ነበር ።

“ለሚስስ ቪዳል በማሰብ እንደበርደን ልታስቸግረኝ ነው!”

“ልታያት የሚገባ ይመስለኛል ጌታዬ አንድ ነገር የሆነች ነው እሚመስለው ።” ብሎ ዳየር ወደኮሪደሩ ወጣ ።

“ምን ጣጣ ነው!” ቪዳል በቁጣ ገነፈለ ።

ወንበሩን ሲስብ ተሰማኝ ። ወዲያው የቢሮውን በር በሀይል ዘግቶ ወጣ ።

“የሚስስ ቪዳል እብደት እያሰለቸኝና እያዳከመኝ ነው” ብሎ ዳየርን ወደ ጐን ገፋ አድርጎ ደረጃዎቹን በፍጥነት ወጣ ። ዳየር ጥቂት አመነታና ተከተለው ።

ወደፊት ተራምጄ እደረጃው ጋ ስደርስ ዳየርን እላይ ቆሞ ስላየሁት ቆም አልኩ ።

ከማዕበሉ ድምፅ አልፎ ቪዳል በጩኸት ሲናገር ይሰማኛል ። ዳየር ወዲያው ተንቀሳቀሰ ። ደረጃውን በፍጥነት ወጣና ባትሪውን በረጅሙ አበራ ። ቫል አይኖቿ እየተጕረጠረጡ እጆቿን እያወናጨፈች ከክፍሉ ውስጥ ተንደራድራ ወጣች ።

ከውስጥ ቪዳል “ተመለሺ! ትሰሚኛለሽ ተመለሺ !” እያለ ሲጮኽ ተሰማኝ ።

ቆም ብላ ወደ ውስጥ ተመለከተችና ቢጠባቡ ደረጃ እጣራው ላይ ወዳለችው ትንሽ ክፍል ተንደረደረች ።

ቪዳል በበሩ ብቅ አለ ። ፊቱ በቁጣ ተጨማዷል ።

“ቫለሪ ተመለሽ !”

ከዚያ ሃይለኛ ነፋስ ወደ ውስጥ ገባና እንገደገደው ። ዳየርን ገፍቼ



አልፌ ወደ ቪዳል ሮጥኩ ። ሀይለኛው ነፋስ ከግርግዳው ጋር ለተመኝ ።

“ይቺ እብድ ወደ ቤቱ ጣራ እየወጣች ነው”

አለና የደረጃውን መደገፊያ ብረት ይዞ ወደ ላይ ለመውጣት ሞከረ ። ነፋሱ እየታገለኝ እኔም ተከትዬው ወጣሁ ።

ከፊት ለፊታችን በተከፈተው በር ውሽንፍሩ በከፍተኛ ሀይል ወደ ውስጥ ይነፍሳል ። መዝጊያው ከግርግዳው ጋር ተለጥፎ አይታይም ።

“እልቆላታል” አለ ቪዳል ። ማንም እዚያ ወጥቶ በህይወት ሊኖር አይችልም ።”

ወደ ተከፈተው በር እየታገለ ሄዶ መቃኑን ያዘና ውሽንፍሩ እየገፋው ወደ ውጪ ተመለከተ ። ወዲያው አይን የሚያጥበረብር መብረቅ ሰማዩን አበራው ። ነጐድጓዱም ጆሮ የሚያደነቁር ድምፅ አሰማ ። ወደሱ ልሂድ ስሞክር ነፋሱ ጨልፎ ጣለኝ ። ቪዳል ባለው አስደናቂ ጉልበት ማዕበሉን ተቋቋሞ እበሩ ላይ እንደቆመ ነው ።

ከዚያ ዳየርን አየሁት ።

እየተፍጨረጨረ ደረጃውን ወጣ ። አይኖቹ ፈጥጠዋል ፤ አፉ ተከፍቷል ፤ እኔን አልፎ እየተ ንደረደረ ወደ ቪዳል ሄደና በሁለት እጆቹ እጀርባው ላይ አረፈ ። ቪዳል ተንገዳገደና መቆም ሲያቅተው ወደፊት ተንደርድሮ እውሽንፍሩ ውስጥ ገባ ። ነፋሱ ጠልፎ ሲወስደው አስፈሪ ለሆነች ቅፅበት አየሁት ። ከዚያ የያዝኩት ባትሪ ከጄ አመለጠና በደረጃው ቁልቁል ተንከባለለ ። ሁሉም ነገር በጭለማ ተዋጠ ። ዳየር በጥርሶቹ መካከል እየተነፈሰ ከነፋሱ ጋር ታግሎ በሩን ሲቀረቅረው ተሰማኝ ።

ቫልና ቪዳል እጣራው ላይ ናቸው ። ማዕበሉ ሊጠርጋቸው ይችላል ። ዳየር አብዷል እንዴ? በሩን ዘግቶ ስምንድነው ለሞት የዳረጋቸው?

* * *

ዳየር ድንገት ባትሪውን ሲያበራ ብርሀኑ አይኖቼን ወጋቸው ። በሩን በጀርባው ተደግፎ ነው የቆመው ። ፊቱ ሞራ መስሏል ፤ ከንፈሮቹ ይንቀጠቀጣሉ ።

"ዳየር እውጪ ነው እኮ ያለችው" ብዬ ጮሁበት "በሩን ልቀቀው። ማዕበሉ ይገድላታል። ወጥቼ አያታለሁ"

"በርደን!"

ድምጿን ስሰማ ድርቅ ብዬ ቀረሁ። ሰውነቴ አልታዘዝ ብሎ አይኖቼ ብቻ በዝግታ ወደ እሷ ዞሩ።

ቫል በቀኝ በኩል ከአለቸው ትንሽ ክፍል በር ላይ ቆማለች፣

"ምንም አልሆንኩ በርደን" አለችኝ። አስፈሪ ፈገግታ በከንፈሮቿ ዙሪያ ይታያል።

"ያለው ምርጫ ይሄ ብቻ ነበር።አንተ ልታደርገው ስላልቻልክ እኛ አደርግነው።"

"እንዴ እሷን፣ እንዴ ዳየርን ተመለከትኩ። ዳየር ከግንባሩ ላይ የሚንቀገርቀውን ላብ በሸሚዙ እየጠረገ ነበር። ቆይቼ ወደ እሷ ዞር አልኩ።

"በመጨረሻው ነፃ ወጣሁ በርደን!.." አለች ቫል በሚንቀጠቀጠው ድምጿ" ለዘላለሙ ተሰናበቷል።"

የምትለው ሊገባኝ አልቻለም። በጣም ስለተረበሽኩ ራሴን የምስት መሥሎ ስለ ታየኝ የደረጃውን መደገፊያ በሁለት እጆቼ ይገፎምኩ።

"አንቺና ዳየር። ምን ምን እያልሽ ነው?" አልኳት እየተናነቀ አልወጣ በሚል ድምፅ

"አንተ ልትረዳኝ አልቻልክም በርደን። ስለዚህ ዳየር ነፃ አወጣኝ፣"

ቅናትና ንዴት ሠፈሩብኝ። ዳየርን ዞር ብዬ ተመለከትኩት።

"ምንህ ነችና ነው እንደዚህ ያደረግህላት ? ገደልከው እኮ!"

"ዝም በል!" አለኝ እየተንቀጠቀጠ።

"እንዴ ሆኗል!"

ጥቂት ቆይቶ የአውሎ ነፋሱን ድምፅ አልፎ በሩ በሃይል ሲንኳኳ ተሰማኝ። በሩ ጀርባውን ያቃጠለው፣ይመስል ዳየር ወደፊት



ዘለለ። ፊቱ በፍርሀት ተዋጠ። በድንጋጤ ቫልን ተመለከታት። እሷም ኩምሽሽ አለች። ገፅታዋ እንደ አሮጊት ፊት ተጨማደደ።

"በርደን!" የቪዳል ድምፅ በሩን አልፎ ገባ፣

"በህይወት አለ!" ብዬ ወደ በሩ ስራመድ ዳየር መንገዱን ዘጋብኝ።

"እንዲሞት ትፈልጋለህ። አይደል!" ተንቀጠቀጠ፣ "ተወው፣ ማዕበሉ ጠርጐ፣ ይወስደዋል። ቫል ነፃ እንድትወጣ አትፈልግም እንዴ ?" ሲለኝ አመንታሁ።

"በርደን በሩን ክፈትልኝ!" አለኝ ቪዳል ደከም ባለ ድምፅ።

"በርደን!"

"እየጠራኝ ነው!"

"ተወው ይጣራ!" አለኝ ዳየር አስፈሪ በሆነ ድምፅ።

"አንተ ከዚህ ሂድ። ለኔ ተውልኝ። በዚህ አይነት ብዙ ሊቆይ አይችልም"፣

"አልሄድም!"

አባቴ እጁ በደም ተነክሮ የገደላትን ጥንቸል ሲገፍ ታየኝ። በውስጤ የነበረው እንድንነገር በሃል የመግደል ፍርሀት ተቀሰቀሰ።አመቺ ሁኔታ ቢያጋጥመኝም፣ ጨክኜ ቪዳልን ልገለው እንደማልችል ተገነዘብኩ። አሁንም ቢሆን ሲሞት ዝም ብዬ ፣ ማየት አልችልም። ላድነው ይገባል። እንዳድነው እየተማፀነኝ ዝም ብዬ ቆሜ መመልከት አልችልም። በድንገት ማንኳኳቱን አቆመ።

"አበቃለት፣" አለ ዳየር ቫል ፊቷን በእጅዋ ሸፈነች።

ወደ በሩ ስራመድ ዳየር ክንዴን ያዝ አድርጐ፣

"ተመለስ" አለኝ።

ገፍትሬው መቀርቀሪያውን ለመክፈት ስታገል አንድ ነገር ጆሮ ግንዴን አቀመሠኝ። እየተተንገዳገድኩ ዞር ስል ዳየር እቀኝ አይኔ ላይ በቡጢ ደረገመብኝ። ብልጭ አለብኝና በደንብ ሜየት ተሳነኝ።

ሁለመናዬ በንዴት ጋለ። እጄን ስሰድ የዳየርን አንገት አገኘሁ። ጣቶቼ እጉሮሮው ውስጥ ጠለቁ። የያዘውን ባትሪ ጣለና ጣቶቼን

ከአንገቱ ለማላቀቅ ታገለ ። ግን እኔ ከሱ እጠነክር ስለነበረ አልቻለም ።

እግሮቹ ሽምድምድ አሉ ፤ ተንበረከከ ፤ ከበፊቱ በበለጠ ሀይል አነቅሁት ። ቫል ስትጠራኝ በደንብ አልተሰማኝም ፡”

“በቃ! በቃ! በቃ!” ብላ እጅሮዬ ላይ ስትጮኽብኝ ነቃሁ ፡ ዳየርን አሽቀንጥሬ ጥዬ ቫልን ገፍትሬ ወደ በሩ ሄድኩና መቀርቀሪያውን ሳብኩት ።

በሩ ቢኃል ሲከፈት ነፋሱ ወደ ውስጥ ተወረወረ ። ተንበረከኩ። በጭለማው ወደውጪ ተመለከትኩ ።

“ቪዳል!”

ወዲያው መብረቁ ብልጭ ብሎ እጣራው ላይ አበራ ።አየሁት ፤ በደረቱ ተደፍቷል ። ነፋሱ ይጐትተዋል ። እረጠበው ጣራ ላይ አንድ ነገር ለመያዝ ይሞክራል ። እጫፉ ላይ ከደረሰ መመለሺያ የለውም ።

ከኋላዬ በሩ በሀይል ተዘግቶ ሲቀረቀር ሰማሁ ።ዳየር ነው የዘጋብኝ ። ሆኖም ግድ አልነበረብኝም ። ቪዳልን እንዳድነው ከውስጤ የሚገፋፋኝ ሀይል አለ ። አድነዋለሁ ።እጣራው ላይ በደረቴ ተኝቼ ውሽንፍሩ እየገፋኝ እሱ ወዳለበት መንሸራተት ጀመርኩ ።

“ቪዳል!” ጮክ ብዬ ጠራሁት ።

ዞር ሲል በመብረቁ ብርሃን አየኝ ።

ንፋሱ ሳላስበው በድንገት ወደሱ ወረወረኝ ።ስንከባለል አንድ አጭር ግንብ አገኘሁና ተንጠለጠልኩበት ። ነፋሱ ቪዳልን ወደ ጣራው መጨረሻ ፡ሲገፋው አየሁ ። በመሀከላችን የአስር ጫማ ርቀት ነው ያለው ። የያዝኩትን ለቀቅ ሳደርግ ነፋስ እሱ ወዳለበት ገፋኝ ። ግንቡን ያዝኩና እግሬን ዘርግቼ ሰደድኩለት ። እንደምንም ተንጠራርቶ እቁርጭምጭሚቴ ላይ ያዘኝ ።

ነፋሱ ባለው ሀይል ይገርፈናል ፤ የቪዳል እጆች ወደ ጉልበቴ ከፍ አሉ ።እጆቼ መያዝ አቃታቸው ፡ክንዴ ከትከሻዬ ላይ ተነቅሎ የወጣ መሰለኝ ፤ ቪዳል እላዬ ላይ ወጣብኝ ፡ እጆቼ ዝለው የያዙትን ሲለቁ ቪዳል በኔ ላይ አልፎ ግርግዳውን ያዘ ። እየተንሸራተትኩ ስወርድ እጆቼ ጃኬቱን አገኙ ።



በውሀ ተነከርን ። ነፋሱ እየገረፈን ለጥቂት ጊዜ ትንፋሽ እስክምናገኝ እጣራው ላይ ተጋደምን ቆየን ። ከዚያ ቪዳል በሚያስደንቅ ሀይል እኔን እየጐተተ ግርግዳውን ይዞ ወደ ላይ ተሰባ ። እጭስ መውጫውጋ እስከምንደርስ ድረስ ይዞኝ ወጣ ። አሁን ነፋሱ ባያቋርጥም እንደበፊቱ ሊገፈትረን አልቻለም ።

ቪዳል ጐንበስ ብሎ ወደጆሮዬ ተጠጋ ።

“ከዚህ ራቅ ብሎ ሌላ መግቢያ አለ” አለኝ ጮክ ብሎ ፡ “እሱ ዝግ ከሆነ አበቃልን ማለት ነው ።”

የመብረቁ ብርሃንፊቱን አሳየኝ ።ፍርሀት አይታይበትም ። እንዲያውም ረጋ ብሎ በራሱ የተማመነ ነው እሚመስል ።

“አንተ እዚህ ቆይ እኔ ወደ በሩ ለመድረስ እሞክራለሁ ።”

“አትችልም!” ብዬ ጮሁጮ ፡

ምንም ሳይለኝ ጐንበስ ብሎ ከተጠለልንበት ቦታ ወጣ ። ነፋሱ ወዲያው ጠለፈው ፤ ፈጠን ብዬ ክንዱን ባልይዘው ኖሮ ነፋሱ ከጣራው አውርዶ ወደ መሬት ይወረውረው ነበር ። ወደ መጠለያው ጐትቼ መለስኩት ።

“እዚህ መቆየት አለብን ማለት ነው” አለ ። ዝናቡ እየወረደብን ነፋሱ እየገረፈን ፤ አለንበት ቆየን ። ሌላው ቢቀር እዚህ የሚያሠጋ አደጋ ውስጥ አይደለንም ።

ጊዜው አያልፍም ። በህይወቴ አጋጥሞኝ የማያውቅ አስጨናቂ ጊዜ ነበር ። ውሽንፍሩ ጥቂት እንኳ ጋብ አላለም ። ለመተንፈስ እንኳ ፊታችንን ከልለን ማጐንበስ ነበረብን የማያቋርጠው የነጐድጓድ ድምፅ ጆሮዬን ደፈነው ። እራሴ ተበጠበጠ ። እንደዚህ ሆነን ለምን ያህል ጊዜ እንደምንቆይ እንኳ መገመት አልቻልኩም ።

ቪዳል ድንገት ሳላስበው ክንዴን ያዝ አደረገ ።

“ተመልከት !”

በጣቱ ወደ አመለከተኝ ቦታ ዞር አልኩ ። ከፊቱ ለፊታችን ራቅ ብሎ የባትሪ ብርሃን አየን ። ብርሃኑ በጣራው ላይ ተዘዋውሮ አለፈ ንና ወደ ሌላ ቦታ አበራ ። ከዚያ ሲመለስ እኛ ላይ አረፈ ። ለተወሰነ ሴኮንዶች ቆይቶ ጠፋ ።

በሽጉጥ ልገለው እንደነበረ በምን አወቀ ?'' ግራ መጋባቴን ሲያይ ከት ብሎ ሣቀ ። ባለቤቴ ልታሳምንህ ብትሞክርም ከሰው የተለየ መለኮታዊ ሀይል የለኝም በርደን ። በመጀመሪያ ከሷ ጋር . . .ያላችሁን ግንኙነት አላውቅም ነበር ። አደገኛ መሆኗን ካወቅሁ በኋላ ግን እዚህ ቤት ውስጥ ባሉት ክፍሎች ሁሉ ስውር ማዳመጫ አስገባሁ እሳንሳልባዶርም በአንተና በሚስቴ የሆቴል ክፍል ውስጥ ማዳመጫ አስገብቼ ነበር ። ላለፉት ሳምንታት እኔን ለማጥፋት ታቅድ የነበረውን ሁሉ በአድናቆትም ባይሆን በጉጉት አዳምጥ ነበር ።''

''ምንድነው የምትለው ? ቫል አደገኛ ነች ማለትህ ነው !?'' አልኩና ጠጋ ብዬ አፈጠጥኩበት ።

''አንተ ነህ አደገኛው! ማወቅህ ካልቀረ የባል ፍቅር ለስድስት አመታት በልቤ ውስጥ እንደቆየና አሁንም የምወዳት መሆኑን ልገልፅልህ እፈልጋለሁ ።''

''አውቄያለሁ ። በጣም ነው እማዝንልህ በርደን ። ከዚህ ሁሉ በኋላ እንኳ መሳሪያ አድርጋ ስትጠቀምብህ እንደቆየች አይታይህም ?''

''እትስማው'' አልኩት እራሴን ። ቫል አስጠንቅቃሀለች ። ይሄ ሰው እርኩስ መንፈስ ነው ! እንድትጠላት ሊያደርግህ ነው እሚሞክረው ።''

''ምስኪኑ በርደን'' አለ ፀጥ ብሎ ከተቀመጠ በኋላ ።

''የሚያስደነግጥ ነገር ልትሰማ ነው ። ቫል ማንንም ማፍቀር የምትችል ሴት አይደለችም ።

''ባንተና በዳየር ላይ እንዳደረገችው በሰዎች መጠቀም ነው እምትፈልገው ። ባይሳካለትም በኔም ለመጠቀም ሞክራለች ።''

''ስለሷ እጥላልተህ የምትነግረኝን ሁሉ አላምንም !'' ብየ ጮህኩበት ። ''ሰይጣን እንደሆንክና በማንም ላይ ክፉ ነገር ከመፈጸም ወደ ኋላ እንደማትል ደጋግማ በመንገር አስጠንቅቃኛለች ። አእምሮዋን በቁጥጥርህ ስር እያደረግህ ሳታውቀው ስትገናኛት ቆይተሀል ። ከዚህ የበለጠ ምን ሰይጣናዊ ድርጊት ይኖራል ?''

''ያም ሆኖ አዳንከኝ!'' አለና ቀና ብሎ ተመለከተኝ ።

''ለምንድነው እንደዚያ ያደረግኸው በርደን ?''



''ለምን አደረግሁት !? ሀሊና አለኝ ። በአንተ ሞት ዘላለም ስፀፀት ከምኖር ሞቴን እመርጣለሁ ።''

''በጣም የሚደንቅ ነው ።ያም ሆኖ ልትገለኝ ተነሳስተህ ነበር ። አሳምናህ ነበር ። አይደል ?''

''ስለሷ ካንተ ጋር መነጋገር አልፈልግም ።''

''አእምሮዋን በተፅዕኖ ሥር እውሎታል ብለህ በርግጥ ታምናለህ ?'' ብሎ ጠየቀኝ ልታሣምንህ ስትሞክር የተቀዳውን ክር ሣዳምጥ ምን ያህል የማሣመን ችሎታ እንዳላት አውቄያለሁ ። ግን እውነት እልሀለሁ የሰውን አእምሮ በተፅዕኖ ሥር የማዋል ችሎታ የለኝም ።

''ካንተ ይልቅ እሷን ባምን ይሸለኛል ።''

በምንነጋገርበት ወቅት ማዕበሉ እንዴም ጋብ አላለ ። ነጐድጓዱ ያለማቋረጥ ያስገመግማል ። ውሽንፍሩ እያፏጨ በጣውላ ከታሸጉት መስኮቶች ጋር እየተላተመ ያልፍል ።

ቪዳል ብድግ ብሎ

''እስካሁን የቢሮየን በር ሰብረው ገብተው ይሆናል በርደን ። ተከተለኝ ። በአይንህ ተመልከት'' ብሎ በሩን ከፍቶ ቆመ ።

እተቀመጥሁበት ሆኜ እመነታሁ ። ዳየር ቪዳልን ገፍትሮ ሲወረውረው የነበረው ሁኔታና በቫል ከንፈር ላይ ያየሁት የጥላቻ ፈገግታ በአይኔ ህሊናዬ ታየኝ ። የተናገረችውንም ቃል በቃል አስታወስኩ።

''ሌላ አማራጭ አልነበረም ። አንተ ልታደርገው ስላልቻልክ እኛ አደረግነው ።''

''አይተህት ማረጋገጡን ፈራህ እንዴ በርደን ? አንተ እንደምታስበው መልአክ አለመሆኗን ማየቱ አስፈራህ እንዴ ?'' በድምፁ ውስጥ የሰማሁት ጥላቻ እንደጅራፍ ሞሸለቀኝ ።

ተነስቼ ተከተልኩት ። በኮሪደሩ ወርደን እደረጃው እናት አጠገብ ያለውን አንድ በር ሲከፍት ቢሮዩ ፊት ለፊት ታየኝ ።

ቪዳል ቆየኝ አለና በፍጥነት ወደ ክፍሉ ገባ ። እጨለማው ውስጥ እንደቆምኩ አውሎ ነፋሱ ከቤቱ ጋር ሲጋጭ ይሰማኛል ።

ሶስት ደቂቃ ያህል እንኳ ሳይቆይ ተመለሰ ። በባትሪው ብርሃን ሽሚዝና ሱሪ መልበሱን አየሁ ።

“ጌሰቲ!’ ብሎ ጮኸ ቪዳል ። ትንሽ ተስፋ እንዳለ ተሰማኝ ።

ብርሀኑ እንደገና ታየ ፤ ከዚያ ጌሰቲ ወደ እኛ ሲመጣ በመብረቁ ብርሃን አየሁት ። ነፋሱ እጣራው ላይ ጣለው ። ቁልቁል ሲያንከባልለው ሳይ ከጣራው ላይ አውርዶ የወረወረው መስሎኝ ነበር ። ግን እንደገና ብልጭ ሲል ወገቡ በገመድ መታሠሩን አየሁ ። የገመዱ ጫፍ እሱ ከወጣበት ቦታ የሆነ ነገር ላይ ታስሯል ።

ቀስ እያለ ወደ እኛ ተጠጋ ። ነፋሱ መልሶ እንከባለለው ። ገመዱ ባይኖር ኖሮ ጠራርጎ ይወስደው ነበር ።

“ያዘኝ ብሎ ጮኸ ቪዳል”

ጃኬቱን ጥርቅም አድርጌ ስይዝ ከተጠለልንበት ቦታ እየጐተተኝ ወጣን ። ወዲያው ነፋሱ ጌሰቲ ወዳለበት እየገፋ ወሰደን ። እጠገቡ ስን ደርስ ጌሰቲ የቪዳልን እጅ ያዘ ።

ወደተከፈተው በር ለመድረስ ረጅሙና አስቸጋሪው ትግል ተጀመረ ። ጌሰቲ ገመዱን ይዞ ሁለታችንን እየጐተተ በጣራው ላይ ተሳበ ። ከብዙ ትግል በኋላ እበሩ ላይ ደረሰንና ካዝናቡና ከነፋሱ አምልጠን ወደ ውስጥ ገባን ። ጉልበቴ ተብረክርኮ ሙቆም አቃተኝ ። እግርግዳው ላይ ስደገፍ ቪዳልና ጌሰቲ ተጋግዘው በሩን ዘጉት ።

“በፍጥነት አልደረስክልንም !” አለ ቪዳል በቁጣ ምን ስታደርግ ነበር !?” ጌሰቲ አጉረመረመ ።

“ገመዱን ስፈልግ ነዋ! በቀላሉ ያገኘሁት መሠለህ ?”

“እነሱስ የት ናቸው ?”

“ያንተን ቢሮ ሰብረው ለመግባት እየሞከሩ ነው”

“ያ ብዙ ጊዜ ይወስድባቸዋል አንተንስ የት ይሆናል ብለው ይሆን የሚያስቡት ?” ብሎ ሲጠይቀው ጌሰቲ ባፍንጫው የፌዝ ሳቅ ሳቀ ።

“ዳየር ከተኛሁበት እስነስቶ የደነገጠ በመምሰል እየጮኸ አንተ ወደ አትክልት ቦታው ሄደህ ችግር የገጠመህ መሆኑን ሲነግረኝ አመንኩት ። ከፍቼ ስወጣ ያ የውሻ ልጅ ከጀርባዬ በሩን ቀረቀረብኝ ። ከዚያ እናንተን እጣራው ላይ አየኋችሁና ገመድ ይዤ የጓሮውን በር ከፍቼ ደረስኩላችሁ ።”



“የጀመሩት ሥራ ከአንድ ሰዐት በላይ ይወስድባቸዋል እስከ ዚያ እኛ እንታጠብ ። ልብሳችንን መለወጥ እንችላለን አለ ቪዳል ።” “ጌሰቲ ለበርደን የሚለብሰው ፈልግለት ። እኔ እህሪስ ክፍል እርፋለሁ” ብሎ ትንሽ ባትሪ ከኪሱ አወጣና እኮሪደሩ ፣ መጨረሻ ላይ ወደሚገኘው ክፍል አመራ ።

ጌሰቲ ወደ ሌላ ክፍል ይዞኝ ሄዶ ፤ ፋኖስ ለኮሰና በጥላቻ በተመሉ እባብ አይኖቹ ተመለከተኝ ።

“እሺ እጅሬ ራስህን እርዳ” ብሎ ትቶኝ ሄደ ።

እየተጠራጠርኩ ወደ መታጠቢያው ክፍል ገብቼ ልብሴን እውልቄ ከታጠብኩ በኋላ ወደ ክፍሉ ተመለስኩ ። ቁም ሣጥኑን ከፍቼ ስመለከት ልክ የሚሆነኝ ሸሚዝና ሱሪ አገኘሁና ለበስኩ ።

በደመነፍስ ነበር የምንቀሳቀሰው ። ጭንቅላቴ ሙሉ በሙሉ ባዶ ሆኗል ። በቅዠት ውስጥ ያለሁ ነው የመሰለኝ ። ግን በይበልጥ ያስፈራኝ ያለሁበት ቅዠት ሳይሆን ስነቃ የሚያጋጥመኝ እውነታ ነበር ። ቪዳል በሩን በርግዶ ገባ ። እቁርጭሚጪምቱ ድረስ የሚደርስ ካፖርት ለብሷል ።

“በርደን ተከተለኝ ። የምትጠጣው ነገር ያስፈልገሀል ።” ብሎ በኮሪደሩ ውስጥ እየመራ እህሪስ ክፍል ውስጥ አስገባኝ ። ጌሰቲ እትከሻው ላይ ፎጣ ጣል አድርጎ ውስኪ ይቀዳል ። “ለበርደን የሚጠጣ ስጠውና ውጣ” አለው ቪዳል ፡

“እሺ ጌታዬ” ጌሰቲ በውስኪና በበረዶ የተመላ ብርጭቆ ሰጥቶኝ ወጣ ።

“ቁጭ በል በርደን” አለ ቪዳል “ከፈለግህ አጭስ እዚያ ፓኮ ውስጥ ሲጋራዎች አሉልህ”

ውስኪውን ተጐንጭቼ ብርጭቆውን አጠገቤ አለው ጠረጴዛዋ ላይ አኑሬ ተቀመጥኩ ።

“በጣም ነው ያስደነቀኝ” አለኝ ቪዳል ። ትክ ብሎ እየተመለከተኝ ። “አዳንከኝ” ብሎ እግሮቹን አነባበረ ።” ለምን እንደዚያ እንዳደረግህ ለማወቅ በጣም ነው የጓጓሁት ። ከአንድ ሰዐት በፊት በሽጉጥ ልትገለኝ ተነስተህ ነበር” ሲለኝ ተሸማቀቅሁ ።

“ንገረኝ በርደን ለምንድ ነው ያዳንከኝ ?”

"አሁን ወደታች እንውረድ" አለኝ ደረጃውን ወርደን ስንጨርስ የቢሮው በር ተከፍቶ ከውስጡ ብርሀን ጭልጭል ሲል አየሁ ። ጌስቲም እበሩ ጥግ ቆሟል ። ሲያየን ወደ እኛ መጣ ።

"ካዝናውን ለመክፈት እየሞከረ ነው" አለ ።

"የሚችለው አይመስለኝም" አለ ቪዳል በተረጋጋ ድምፅ ። የእውሎ ነፋሱ ድምፅ ዝቅ አለ ። ቪዳል እጄን ይዞ ወደበሩ እየጐተተ "አዳምጥ አለኝ ። አለህበት ሆነህ አዳምጥ ።"

እቆምኩበት ሆኜ ወደ ክፍሉ ውስጥ ማየት አልቻልኩም ። የሚሰማኝም የውሽንፍሩ ድምፅ ብቻ ነበር ።

ቆይቶ የቫልን ድምፅ ሰማሁ ።

"ምን እያደረግህ ነው ? ልከፍተው እችላለሁ ብለህ ከፈተው!" በቁጣና በጥላቻ የሰለለ ድምጿን ልለየው አልቻልኩም ።

"ቁጥሮቹን ለውጧቸዋል" ብሎ ጮኸ ዳየር ። እየተርበተበተ "አይከፈትም"

"ብትከፍተው ይሻልሀል አንተ ደደብ የውሻ ልጅ !" ብላ ጮኸች ቫል "ያን ሁሉ ነገር በከንቱ የፈፀምኩ ይመስለሀል !?"

የምትናገረው እያንዳዱ ቃል ያሸማቅቀኛል ። ቪዳል ክንዴን እንደያዘ ነው ፣

"እንግባ በርደን" አለኝ "እናስደንግጣቸው !" ልቋቋመው ከመሞከሬ በፊት እየገፋ ይዞኝ ገባና ሁለታችንም እክፍሉ ውስጥ ዝም ብለን ቆምን ።

የቫል ጩኸት ከማዕበሉ አልፎ ተሰማ ። ዳየር ከግርግዳው ጋር እተሠራው ካዝና አጠገብ ቆሟል ። የሶስት ፋኖሶች ብርሃን ሁሉንም ነገር ወለል አድርጎ ያሣያል ። ቫልም አይኖቿ ፈጥጠው ድንጋይ መስላ አጠገቡ ቆማለች ።

"እድል የላችሁም!" አለ ቪዳል ወደ ክፍሉ መሀል እየተራመደ "ልክ ነህ ለጥንቃቄ ብዬ ቁጥሩን ለውጬዋለሁ. . . " አለና ከት ብሎ ሣቀ ።

"ይሄውልሽ ቫለሪ ሚስኪኑ በርደን አሁንም መልአክ ነሽ ብሎ ነው እሚያምነው ።" ፍርሀት ሌላ ሰው አስመስሏታል ።



በዚህ ጊዜ ጌስቲ ገባ ። ቫል ገና ስታየው ጮኸች ። ፍዝዝ ብሎ የቆመው ዳየር ተዝለፈለፈ ። ፊቱ አመድ ለብሰ ።—

ቪዳል ወደ ጠረጴዛው ሄዶ ወንበር ስቦ ተቀመጠ ፣

"አሁን ለበርደን ሁኔታውን እናሳየው" ያዳነኝ በመሆኑ ይሄ የሚበዛበት አይመስለኝም ።" አጠገቡ ወዳለው ወንበር እያመለከተኝ ።

"ቁጭ በል በርደን እናንተም ተቀመጡ" አለ ።

ረዘም ላለ ጊዜ ሁላችንም ፀጥ አልን ። ከዚያ ቫል ተቀመጠች ። ዳየር ጌስተን በፍርሀት ተመለከተና ከቫል ራቅ ብሎ ተቀመጠ ። እኔም ቪዳል እንድቀመጥበት አመለከተኝ ወንበር ላይ ተቀመጥኩ ።

"መልካም" አለ ቪዳል በቀጥታ ወደ እኔ እየተመለከተ ።

"እነዚህ ሁለቱ ለምን አግባብተው የግድያ ወንጀል ሊያስፈጽሙህ እንደነበር አስረዳለሁ ። ዳየር ሊከፍተው እየሞከረ እነበረው ካዝና ውስጥ ስምንት ሚሊዮን ዶላር የሚያወጡ ከአንድ ሀገር መንግሥት ጋር የተዋዋልኩባቸው ሰነዶች አሉበት ። ገንዘቡ ሰነዶቹን ይዞ ለቀረበ ወዲያው ይከፈላል ። ከዚህ ገንዘብ እኔ የማገኘው ኮሚሽኑን ሲሆን ቀሪው የኤልሳልቫዶር መንግሥት ነው ። ዳየር ውሉ ታው ሲፈጸም አብሮኝ ነበር የጽሑፉን ሥራ የሠራው እሱ ነው ። ስለዚህ ሰነዶቹ እካዝናው ውስጥ መኖራቸውን ያውቃል ። ከጥቂት ሳምንታት በፊት ባለቤቴና እሱ ወዳጆች መሆናቸውን ደረስኩበት ። በοι መተማመን ካቆምኩ ቆየት ብዬ ስለነበር ድርጊታቸውን ስደርስበት አላስ ቸገረኝም ። ከሱ በፊት ሌሎች ወዳጆችም ነበሯት ። እንግዶቹን በደንብ ስለምታስተናግድልኝ ለኔ ታማኝ አለመሆኗ አላሳሰበኝም ነበር ። ነገር ግን የቅርብ እረዳቴ ታማኝ አለመሆኑ በጣም አሳሰበኝ ። ስለዚህ በቤታችን ክፍሎች ውስጥ ማዳመጪያ እንዲገባ አደረግሁ ። ሊገሉኝ ማቀዳቸውንም ስደርስበት እንደዚህ ማድረጌ ትክክል ሆኖ ነው ያገኘሁት ። ሲያሴሩብኝ የነበሩት ሁሉ በቴፕ ተቀድቷል ። ዳየር ስለሰነዶቹ ለቫል ከነገራት በኋላ ካዝናውን ሊከፍተው እንደሚችል ያረጋግጥላታል ። ለተወሰነ ጊዜ ቫል እኔን የምታስወግድበትን መንገድ ስትፈልግ ቆየች ። እኔ ከሞትኩ የሟች ሚስት ፣ በመሆኗ ሀብቴን ወርሳ በቀላሉ ሀብታም እንደምትሆን ታይቷት ነበር ። በዚህ ላይ እኔን ከማስወገድ አልፋ ሌላ ስምንት ሚሊዮን ዶላር ልታገኝ መቻ ሏን ስትሰማ እቅዷን ከመፈፀም ወደ ኋላ ልትል አልቻለችም ። ዳየ

ርን እንዲገለኝ ስታግባባው የተቀዳ እስደናቂ ክር አለ ። ዳየር ግን የተባለውን ለመፈጸም ወኔ አጣ ። በዚህ ክር ላይ ቫል እራሷ ልትገለኝ የምትችልበትን ሁኔታ ሁሉ ስትናገር ይሰማል ። ግን የፖሊስ ምርመራውን ስለፈራች ያሰበችውን ለመፈጸም አልሞከረችም ።

ከዚያ አንተ ምስኪን በርደን ወደ ፓራዳይዝ ከተማ መጣህ ። ሳንሳልቫዶርን እሱ ካላስጐበኘኝ ብላ ሙዝዝ ስትል ገርሞኝ ነበር ። ልታጻምጠው ከፈለግህ እሷና ዳየር ባንተ ለመጠቀም እቅድ ሲያወጡ የተቀዳ ክር አለልህ ። ያለችውን ቃል በቃል ባላስታውስም በቀላሉ የምትታለል መሆንክን እንደምታውቅና ካንተ ጋር ፍቅር በመለዋወጥ ለሷ የነበረህን ስሜት እንደገና በመቀስቀስ እሷ ሙሉ በሙሉ በኔ ተፅዕኖ ሥር መዋሏንና ነፃ የምትወጣው ከሁለት እንዳችን ስንሞት መሆኑን ልታሳምን እንደምትችል ስትናገር ትሰማለች። በርደን ቀደም ብዬ አስጠንቅቄሀለሁ ። እሷ ያለችህ ሁሉ ትርጉም የሌለው ከንቱ ወሬ ነው ። ይህንን ካመንክ ማንኛውንም ነገር ታምናለህ ። እሳንሳልቫዶር እኮንቴታል ሆቴል ስናርፍም አንተና እሷ ክፍል ውስጥ ማዳመጫ እንዲገባ አስደረግሁ ።

ካንተ ጋር ስትወያይ የተቀዳው ክር የሚያስደስት ባይሆንም አስደናቂ ነው ። ትሪልባይና እስፔንጋሊ ! ምስኪኑ በርደን እንዴት እንደተሞኘህ ይታይሀል ? ስለሰይጣንና እኔ በተፅዕኖዬ ሥር እንዴት እንዳዋልኳት ያወራችልህን ሁሉ ማመንህ የሚገርም ነው ። እርግጥ ዳየር እሷ ያወራችልህን ለማስተማመን ብዙ ጥሯል ። ሌላው ቀርቶ ሽማግሌው ዶክተር የተወራልህን እንዲያረጋግጥልህ ያደረገው እሱ ነው ። ያ ሽማግሌ ያወራልህ እውነተኛ ነው ብለህ ገምተህ ነበር ? የሱንም ማንነት አስጠንቻለሁ ። ገንዘብ ከሰጠኸው እናቱን ለመሸጥ የሚመለስ አይደለም ። የሆነው ሆኖ ቫልና ዳየር እሷ ከኔ ሰይጣናዊ ተፅዕኖ ልትላቀቅ የምትችለው እኔን ስትገለኝ ብቻ መሆኑን ሊያሣምኑህ ችለዋል ። ሀሳቡን በአእምሮህ ውስጥ በደንብ ከቀረፁ በኋላ እኔን በመግደልህ ምንም ችግር የማይደርስብህ መሆኑን እንድታምን እኔ ራሴን ያጠፋሁ መሆኑን ሊያሳምኑ የሚችሉ ምክንያቶች አቀረቡልህ "አለና ከት ብሎ ሣቀ" "የከሠርኩ መሆኔ ! ብዙ የታክስ እዳ ያለብኝ መሆኑን በዚህም ምክንያት ወደ ሊማ ይዞኝ ሊኮበልል ነው ብላ ካወራችልህ ታሪክ አንድም እውነት የለበት ። ግን አንተ ታሪኩን ስትሰማ በጣም በመደነቅህና በማመንህ ለጥንቃቄው ብዬ ሽጉጥህን ወሰድኩብህ ። ጣትህን ስታጮህ ፍዝዝ ብላ በመነሁለሏና በመውደቋ አንተን ብቻ ሳይሆን ዶክተሮቹንም አቂላቸዋለች ። ያ ድር



ጊት የእውነት አልበረም ። ጐበዝ ፀሐፊ ከመሆኗ በፊት እየተዘዋወረ ትርኢቶችን ከሚያሳይ ቡድን ጋር ስትሠራ በነበረችበት ጊዜ የተማረችውን የማስመሠል ጥበብ ነው ፡በእናንተ ላይ የተጠቀመችው ። በርደን ፡ የምልህን ሁሉ እንድታምን አልጠይቅህም ። ክሮቹን አዳምጥ ። እነሱ በደንብ ያሣምኑሀል ።" ብሎ ድርቅ ብላ መሬት መሬት እየተመለከተች ወደ ተቀመጠችው ቫል ዞር አለ ።

"ይህን ሁሉ ጥንቃቄ አድርጌም እንኳ አታላኝ ነበር ። እርግጥ ንቄያታለሁ ። ቅድም ወደ ጣራው ላዉ የወጣች መስሎኝ ነበር ። የዳየርንም ችሎታ በንቀት ተመልክቼዋለሁ ። እንደዚያ ለማድረግ ወኔው ይኖረዋል ብዬ አላመንኩም ። ሰነዶቹን በእጃቸው የማስገባት ተስፋ ባይኖራቸውም እኔን መግደሉ ከሞላ ጐደል ተሳክቶላቸው ነበር ።" ብሎ ተነሳ ።

"ለዛሬ ማታ ይሄ የሚበቃ ይመስለኛል ። ነገ ክሮቹን ማዳመጥ ትችላለህ ። አስደናቂ ከመሆኑም በላይ አውሎ ነፋሱ እስከሚያቆም ጊዜ ያሳልፍልሀል ። አሰልቺ ቢሆንም ለሁለት ወይም ለሶስት ቀናት እዚህ መቆየታችን ግዴታ ነው ።ሁላችሁም በየክፍላችሁ ብትቆዩ መልካም ይሆናል ። በምግብ በኩል ጌስቲ አለ ። እንዳችሁም መጨነቅ የለባችሁም ። የፍቺውን ጉዳይ እኔ ራሴ አስፈጽማለሁ ። ዳየር ሌላ ሥራ መፈለግ ይኖርበታል በርደን ላንተ ግን ቤኔ ድርጅት ውስጥ አንድ ቦታ አላጣልህም ። እንዴት እንደሚሆን ነገ እንነጋገራለን ።" ብሎ ወደ በሩ ተራመደ ።

"ደህና እደሩ" ጌስተን አስከትሎ ከክፍሉ ወጣ ።

አቀርቅራ መሬት መሬቱን እያየች ወደ ተቀመጠችው ቫል ተመለከትኩና ወደ ዳየር ዞር አልኩ ። አይኖቼን እየሸሸ ተነስቶ እያጉተመተመ ድርቅ እንዳለ ወጥቶ ሄደ ።

ፀጥ ብዬ ተቀመጥኩ ። አውሎ ነፋሱ ከቤቱ ጋር እየተላተመ ማለቱን እንደ ቀጠለ ነው ።

"ቫል !" ስላት ቀና አላለችም ።

"እምንሻለህ ፤ እየዋሸ መሆኑን ንገሪኝ !" አልኳት የወንበሩን ጉንና ጉን መደገፊያ ጭብጥ አድርጌ ይዤ ። አልተንቀሳቀሰችም። ቀናም ብላ አላየችኝም ፡

"ቫል እየዋሸ መሆን አለበት ! በኔ ላይ እንዲህ አይነቱን ነገር

አትፈፅሚም ። ከተለያየን ጀምሮ ለስድስት አመታት ከልቤ ውስጥ ለአንድ ደቂቃ እንኳ ወጥተሽ አታውቂም ። አሁንም እወስድሻለሁ ፣ ቫል እባክሽ እየዋሽ መሆኑን ንገሪኝ !?"

እሁንም ምንም አላለች ።

"ስለ ፈጣሪ ብለሽ ቫል!"

ድንገት እራሷን ነቀነቀችና ዝግ ባለ ደረቅ ድምፅ

"እየዋሽ አልነበረም" ። አለችኝ ፣

ተናገረችው ፤ በረጂሙ ተነፈስኩ ።

"ቫል የኔ ፍቅር እባክሽ አድሚጪኝ ። ሊፈታሽ ነው ፤ ሌላው ቢቀር ከሱ ነፃ ትወጫለሽ ። አብረን የትም መሄድ እንችላለን ። በሮጻ ምክንያት መጋባት ባንችልም ፡ አብረን የምንሠራው ሥራ ማግኘት እንችላለን ። ፍቅርዬ ላደረግሺው ሁሉ ግድ የለኝም ። ስለዳየርም ግድ የለኝ ፤ እወድሻለሁ ። አብረን አዲስ ህይወት ልንመሠረት እችንላለን" ስላት ቀና ብላ ተመለከተችኝ ። በአይኖቿ ውስጥ ያየሁት መራራ ንቀት አኮማተረኝ ።

"ካንተ ጋር አዲስ ህይወት ?!" ብድግ አለች ።

"ካንተ ጋር?! አንተ ደካማ ወኔ ቢስ ! እኔ አፍቅሬህም አላውቅ ! ሁሌም አንተ ለኔ የጅል ቀልድ ነበርክ ፤" ብላ ጮኸችብኝ ። ፊቷ በጥላቻና በንዴት ተጨማደደ ።

"ያንተን ወኔ ቢስ ፍቅር ማን ይፈልገዋል ? ከዛሬ ጀምሮ በአ ይኔ እንደማላይህ ተስፋ አለኝ!" እራሴን በእጆቼ ደግፌ ወደ እውነትነት እተለወጠው ቅዠት ውስጥ እንደተቀመጥኩ ጥላኝ ወጣች ።

* * *

አውሎ ነፋሱ መስኮቶቹ ከታሸጉበት ጣውላ ጋር እየተላተመ ሲያልፍ ነጐድጓዱ ቤቱን እናወጠው ። ክፍሉን ለቅቄ ከመውጣቴ በፊት ወድ የሆነውን ምንጣፍ አቀርቅሬ እየተመለከትኩ ፣ የጭካኔ አነገሯን አስታወስኩ ።

"አፍቅሬህ አላውቅም !"



ለብዙ አመታት ሲያመልኩባት የኖሩትን ሴት በእውን ሳይ ሆን በምናብ ውስጥ የነበረች መሆኗን ማወቁ ምንኛ እጥንት ይሰ ብራል ? የህይወቴ መጨረሻ እንደ ሆነ ሁሉ አውሎ ነፋሱን እያዳመ ጥኩ ተቀምጬ ቀሩሁ ።

"ሄይ አጅሬ ተነስ!!"

የጌስቲ ጐርናና ድምፅ ቀና ብዬ እንድመለከት አስገደደኝ ። አፉ በሽሙጥ ተጣሞ አጠገቤ ቆሟል ። ወደ ኋላ አፈገፈግሁ ።

"ካጠገቤ ዞር በል ።!"

"ብድግ በል! በፈለግሁ ጊዜ ላገኝህ እምችልበት ቦታ እንድት ሆን እፈልጋለሁ ። ተንቀሳቀስ ! ።"

ዛቻው ከመቀመጫዬ አስነሳኝ ። እንዲነካኝ አልፈልግም ፤ ግን ነካኝ ። ክንዴን ፡ እንደብረት በጠነከሩ ጣቶቹ አንቆ ያዘና ከክፍሉ አው ጥቶ እየጐተተ በአዳራሹ ፡ ውስጥ አልፎ እደረጃዎቹ አጠገብ አደረ ሰኝ ። ዝምብዬ ተነዳሁለት ። እላይ ስንደርስ ፡ ቪዳልን እክፍሉ በር ላይ ቆሞ አየሁት በእጁ የያዘው ባትሪ እወለሉ ላይ ያበራል ።! በብር ሀን ውጋጋን የተቆጣ ፊቱን እየሁ ።

ቆም ብዬ ተመለከትኩት ፤ ወደ ክፍሉ ገብቶ በሩን ሲዘጋ ነጓድ ጓዱ ቤቱን አነቃነቀው ። በሚንቀለቀሉ አይኖቹ ውስጥ አንድ ነገር አለ ። ፍርሀት የለቀቀብኝ አንድ ከፉ ነገር አለ ።

"ሂድ እንጂ !" አለ ጌስቲ እየጐነተለኝ ። አደጋ መኖሩ ተሰማኝ ። እኔ ክፍል አጠገብ ስንደርስ ጌስቲ በሩን ከፈተው ። አንድ አሰቃቂ ነገር የሚፈፀም መሆኑ ስለታወቀኝ አለሁበት ቦታ ድርቅ ብዬ ቆምኩ ።

እዚህ ቤት ውስጥ ለአንድ ደቂቃ እንኳ ከመቆየት ደረጃውን በሩጫ ወርደህ በሩን ከፈትህ ማዕበሉን ብትጋፈጠው ይሻላል የሚል ስሜት ተሰማኝ ።

ከብረት የተሰሩ ጣቶቹ ክንዴን ጨብጠው ይዘው እንደ ሲሚንቶ ግርግዳ የጠነከረው ትከሻው እደረቴ ላይ ሲያርፍ ወደ ኋላዬ ተንገዳ ግጄ እጭለማው ክፍል ውስጥ ገባሁ ። በሩ በሀይል ተዘጋ ።

የአልጋውን እግር እስከምንካው ድረስ በጭለማው ውስጥ ተደ ናበርኩ ። ጭለማው አይን ቢወጋ እያሳይም ። አልጋው ላይ ስቀመጥ የአ ውሎ ነፋሱ ድምፅ እኔ ላይ እያረፈ የሚጮኽ ያህል ተሰማኝ ።

ያንቀጠቅጠኝ ጀመር ፤ ላቆመው የማልችል አንድ ክፉ ነገር ሊፈጸም ነው ። ጣቶቼ ፍራሹን በስተው ገቡ ። ልቤ ደረቴን እረገጠ ። ፀጥ ብዬ እተቀመጥኩበት ቀረሁ ።

ቆየት ብሎ በሩቁ ጩኸት ተሰማኝና ወዲያው በእውሎ ነፋስ ድምፅ ተዋጠ ። ግን የሰው ጩኸት እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ ።

እየተርበተበትኩ ። ተነሳሁና ወደ በሩ ሄጄ በዳበሳ መክፈቻውን አገኘሁት ። ልከፍተው ግን አልቻልኩም ። ተቆልፏል ።

ጩኸቱን እንደገና ሰማሁ ። አሁን አልተጠራጠርኩም ፡ ቫል እየ ጮኸች ነበር ።

በሩን በትከሻዬ ደጋግሜ ገጨሁት ። ፍንክችም አላለ ። ሙከራዬ ከጡብ የተሠራ ግርግዳ የመግጨት ያህል ነበር ። መክፈቻውን ታገ ልኩ ። ደጋግሜ ብደበድበውም ድምፁ በማዕበሉ ከመዋጥ አልፎ ምንም አላስገኘልኝ ።

ቆይቶ ሀይለኛ ነፋስ ወደ ቤቱ ውስጥ ሲገባ በሩ ተንገጫገጨ ። ወደ ጣራው ላይ የሚያስወጣ በር ተከፍቷል ።

"ቫል!"

ባለኝ አቅም ሁሉ ከበሩ ጋር ታገልኩ ። ካለበት ቦታ ፈቅ ላደር ገው ግን አልቻልኩም ። ወደ ጣራው ላይ የሚያስወጣው በር ሲዘጋ ነፋሱ ፀጥ አለ ።

እበሩ ላይ ተደግፌ ሳዳምጥ እቤቱ ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ ፀጥታ ሠፈነ እውጪ እያስገመገመ የሚያልፈው የማዕበል ድምፅ ብቻ ነበር የሚሠማው እውስጤ አንድ ነገር ሲሞት ተሰማኝ ። የሠራ አካሌ ተብረከረከ ።

"በጭለማው ውስጥ እያዘገምኩ ወደ አልጋው ሄጄ ተቀመጥኩ ። ቫል መሞቷ ታወቀኝ ። ጌሰቲ ቫልን አስገድዶ እጣራው ላይ እንድት ወጣ በማድረግ ለማዕበሉ አሳልፎ ሰጥቷታል ። ከሩቅ የሰማሁት ጩኸት አሁንም በውስጤ ያስተጋባል ።

በሩ በድንገት ተከፈተና ቪዳል ፋኖስ ይዞ ገባ ።

"የሚያሳዝን አደጋ ደረሰ በርደን" አለኝ ፋኖሱን እጠረጴዛው ላይ እያስቀመጠ ። "ቫል በማዕበሉ ተወሰደች ፡" ብሎ ባገኙት እርካታ ደስ ባላቸው አይኖቹ ተመለከተኝ ።

700/93



"ይገባሀል? በአእምሮ መታወክ ትሠቃይ እንደነበረ ዶክተሮቹ ያውቃሉ ።እውሎ ነፋሱ በጣም ስለረበሻት ራሷን መቆጣጠር አቅ ቷት እኔ ከመድረሴ በፊት እጣሪው ላይ ወጣችና ማዕበሉ ወሰዳት ።" በሚናገርበት ጊዜ ሁሉ አይኖቹ ከኔ ላይ አልተነቀሉም ።

"ገባህ?"

"አንተ ነህ የገደልካት!"

"ደደብ አትሁን በርደን ። አደጋ ነው ያጋጠማት ። ዳየርም... " አለና ከት ብሎ ሣቀ "ጀግንነቱን ሊያሣይ የፈለገ ይመስላል ። እኔና ጌሰቲ ልንይዘው ስንሞክር አምልጦን ተከትሏት እጣራው ላይ ወጣ ። ማዕበሉ እሱንም ጠለፈው ። ገባህ !?"

"ሁለቱንም አንተ ነህ የገደልካቸው"

"ገንዘቤንም ሆነ ይህወቴን አለአግባብ ለመውሰድ የሚሞክር ሁሉ ቅጣቱን ሳያገኝ አይቀርም!" አለኝ ። ቆጣ ብሎ ። "አንተ እዚህ ውስጥ መግባት የለብህም ። በርደን ። ተኝተህ ስለነበር ምንም አልሠ ማህም ። ፖሊስም የሚጠይቅህ አይመስለኝም ። ቢጠይቅህም ምን እንደ ምትል ታውቃለህ ። ይህን እድል የምሠጥህ ስለአዳንከኝ ነው ።"

ጌሰቲ በበሩ ብቅ ብሎ በሚያስፈራ ሁኔታ ተመለከተኝ ። ገና ሳየው ፍርሀት ለቀቀብኝ ፤ ሽባ የሚያደርግ ፍርሀት ።

"አደጋ ነው የደረሰው" አልኩኝ በችኮላ ።

"ልክ ነህ" አለ ቪዳል "እንደነሱ አይነት ሰዎች በህይወት ሊኖሩ አይገባም" ብሎ ትቶኝ ወጣ ። ጌሰቲም ትክ ብሎ ሲመለከተኝ ቆየና ተከትሎት ወጣ ።

ከፍ ዝቅ የሚለውን የፋኖስ ብርሀን እየተመለከትኩ ፡ ቁጭ አልኩ ። ስለቫል ከአላለምኩ ህይወቴ ባዶ ነው እሚሆነው ። ከእንግ ዲህ ማንም የለኝ ብዬ ሳስብ ሮዳ ትዝ አለችኝ ። ከነግድ የለሽነቷ ከም ንም እሷ ትሻላለች ።

ሮዳ ከምንም የምትሻል መሆኗን ለማመን እየሞከርኩና የእ ውሎ ነፋሱን ድምፅ እያዳመጥኩ ቁጭ ብዬ ቀረሁ ። ያሰብኩት የማ ይረባ ነገር ቢሆንም ከፊቴ የተዘረጋውን እረጂም ጊዜ እንዳሳልፍ አግዞኛል ።

ተ ፈ ጸ መ

# ትንግርት

በሕይወት ውስጥ ይሆናሉ የተባሉ ነገሮች ሣይሆኑ ፤ አይሆኑም የተባሉት ደግሞ ሲሆኑ የሚታይበት አጋጣሚ አለ ።

በእውን የማይታሰቡ አስደናቂ ነገሮች ይፈፀሙና ያስገርሙናል ፣ጉድ ያሰኙናል ።እንዲህም ይሆናል እንዴ? እንድንል ያስገድዱናል ።

በትንግርት ውስጥ ዘልቀን ስንገባ የሚያጋጥመን እንዲህ አይነት የሕይወት አይታመኔ ድንቅና እውን ሁኔታ ነው ።

ዋጋው ብር 5.50